በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ-ምረቃ ት/ቤት

# የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓቶችና ዝርውቃል ተረኮቻቸው

በ
ምንዳ ገብሬ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሰኔ 2000 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
የድኅረምረቃ መርሐግብር

# የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው

በሥነጽሑፍና ፎክሎር የኤም.ኤ.ዲግሪ
ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

ምንዳ ገብሬ

አማካሪ
ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ

ሰኔ፣ 2000 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓቶችና ዝርውቃል ተረኮቻቸው

በ

ምንዳ ገብሬ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለትምህርት
የድኅረምረቃ መርሐግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |

## ማረጋገጫ

ይህ ቴሲስ የእኔ መሆኑንና ፣ በውስጡም የተገለገልኩባቸውን ምንጮች (ማቴሪያሎች) በሙሉ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ስም ምንዳ ገብሬ

ፊርማ [signature]

የማስረከቢያ ጊዜ ሰኔ 2000 ዓ.ም

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ምስጋና

ይህ ጥናት ከዳር እንዲርስ ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው በማረምና በተቻለ መጠን ተስተካክሎ እንዲቀርብ በተለያዩ ጊዜያት ገንቢ አስተያየታቸውንና ምክራቸውን ላካፈሉኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ።

ለሥራው ከሚያስፈልጉ ግብአቶች መካከል ዋነኞቹ መረጃዎች ናቸው። በመሆኑም ከጅምር አንስቶ አስፈላጊ በሆኑባቸው ጊዜያት ሁሉ፣ የቃልም ሆነ የጽሁፍ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ ግለሰቦች፣ እንዲሁም ለጌዴኦ ዞን መስተዳድር፣ ለዞኑ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ሁሉም በያሉበት ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

ጥናቱን በማካሂድበት ወቅት፣ መረጃዎች የሚገኙባቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት፣ እንዳዴም በመኖሪያ ቤታቸው እያረፍኩ ፣ ሥራዬን እንዳካሂድ በመርዳት፣ ከአካባቢው ሰዎች በማስተዋወቅ፣ ላደረጉልኝ ከፍተኛ እገዛ አቶ ውብሸት ጌታቸውና ቤተሰቦቹ ባለውለታዬ ናቸው።

ይህን ስራ ገና ከጅምሩ አንስቶ፣ የሞራልና የሀሳብ ድጋፍ በማድረግ እስከመጨረሻው ድረስ ከጎኔ ላልተለየችኝ ባለቤቴ ወ/ሮ ጽጌ ታፈሰና ለልጆቻችን ከምስጋና በላይ የምለው ቢኖር ደስ ይለኛል። እንዲሁም ጽሑፉን ሲዘጋጅም ሆነ ሲታረም ደጋግሞ በመተየብ ላበረከቱት አስተዋፅኦ ለወ/ት ሲና እንዲሁም ለሜሮን ፋንታዬ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

በመጨረሻም መስሪያ ቤቴ፣ መደበኛ የሥራ ጊዜዬን በማስተካከል ላደረገልኝ ቀና ትብብር፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለጥናቱ ማካሄጃ የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ወጪዎች መሸፈኛ እንዲሆን ላደረገልኝ የገንዘብ ድጋፍ ለሁሉም ምስጋና ይግባቸው።

## ሙዳየ ቃላት

| | | |
|---|---|---|
| Abagada - | አባገዳ - | በጌዴኦ ባህላዊ አስተዳደር የሥርዓቱ ዋና መሪ ነው:: |
| Abokie - | አቦኬ - | አባቴ |
| Angaffa - | አንጋፋ - | የመጀመሪያ ልጅ |
| Araraa - | አራራ - | እርቅ ማለት ሲሆን፣ ማንኛውም የጌዴኦ ህብረተሰብ አባል ይቅር ብሎ እርቅ መፈፀም አለበት ተብሎ ይታመናል :: |
| Ayokie - | አዮኪ - | እናቴ |
| Ballee - | ባሌ - | የጌዴኦ ጥንታዊና ባህላዊ መተዳደሪያ ሥርዐት |
| Bedecha - | በደቻ - | ትልቅ ዋረካ መሰል ዛፍ ሲሆን ፣ ቀደም ሲል አሁን በዲላ ከተማ መሐል የዲላ ሶንን ከተሰራበት ቦታ ላይ እንደነበረ ይነገራል :: |
| Bilbanna Baalle - | ቢልባና ባሌ - | ጥንታዊው የጌዴኦ ባህላዊ አስተዳደር ገና ሲጀመር የመጀመሪያውን የገዳ ሥርዓት የመራ የጌዴኦ ጎሳ ነው :: |
| Bobbassa - | ቦባሳ - | ህዝባዊ ጦሩን የሚመራ (ዋና አዛዥ) |
| Boota - | ቡታ - | ከቤተሰብ ዕውቅና ውጪ በስውር የሚደረግ የጠለፋ ጋብቻ |
| Bulbulo - | ቡልቡሎ - | የማር ብጥብጥ |
| Bunno - | ቡኖ - | ቡና |
| Bussedie - | ቡሰዴ - | ባል የሞተባት ሴት ወይም ሚስቱ የሞተችበት ወንድ የሚጠሩበት ቅፅል ስም |
| Dala - | ዳላ - | የባል ወንድም የሟችን ሚስት ከነንብረቱና ልጆቹ ጭምር በመውረስ ማግባት |
| Dallenna Baalle - | ዳለና ባሌ - | በጥንታዊ የጌዴኦ ሥርዓት ባህላዊ አስተዳደር ስምንት ዓመት ቆይታውን ሲጨርስ የተረከበው ሁለተኛው የገዳ ሥርዓት |
| Dano - | ዳኖ - | በድንገት ሳይታሰብ የተከሰተ አደጋ ወይም አጋጣሚ:: |
| Ejja - | ኤጃ - | ባለ አራት ፈርጅ ትልቅ ባህለዊ ቡሉኮ |
| Facie - | ፋጪ - | በህዝብ ፊት ጥፋትን አምኖ መናዘዝ (ንስሃ መግባት) ማለት ነው:: |
| Faroo - | ፋሮ - | መልካም/ጥሩ/ ዕድል |
| Fixxassa - | ፊጣሳ - | ድምፅ ሳያሰሙ በለሆሳስ የሚደረግ ለቅሶ |

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

| | | |
|---|---|---|
| Gaafie - | ጋፌ - | አንድ ነገር ለማውጣጣትና ዳኝነት ለመስጠት የሚደረጉ ጥያቄዎች |
| Gada - | ገዳ - | ከጎሳሎ የጀመረ የጌዴኦ ባህላዊ አስተዳደር ሥርዓት |
| Gateekin gaafi | ጋቴኬ ጋፊ | “ በእኔ ጆሮ ይብቀል ፤ በሌላው ቀንድ ይብቀል” በማለት |
| gawwi - | ገው - | ጢንጎ ተረኮችን የመዝጊያ ቀመር ነው ። |
| Gedeuffa - | ጌዴኡፋ - | የጌዴኦኛ ቋንቋ |
| Gondoroo - | ጎንዶሮ - | ዳግመኛ በማይመለስና በማያገረሽ ሁኔታ እርቅ መፈፀም |
| Hawadie - | ሐዋዴ - | በጎረቤት ወይም በአካባቢ ሰዎች አማካይነት በማስኮብለል የሚፈፀም የጋብቻ ዓይነት |
| Hayyichcha - | ሐይቻ - | በጌዴኦ ባህላዊ አስተዳደር የአንድ አካባቢ ሶንጎ መሪ ሆኖ በአባገዳ የሚሾም ሰው ነው ። |
| Jalaaba - | ጀላባ - | የአባገዳ ምክትል(ረዳት) የሆነ ሰው ማለት ነው ። |
| Jalqaba - | ጃልቀባ- | የሮጋ ረዳት ነው። በሮጋ አመራር ሰጪነት ለበታች ይሰጣል። |
| Kadha - | ከዳ - | በተጋቢዎች ቤተሰቦች ፍቃድ ላይ የተመሰረተ ጋብቻ |
| Karragungo - | ከረሳንጆ - | ማንኛውም ወደ ሶንጎ የሚመጣ ሰው የያዘውን ብትር የሚያስቀምጥበት ባላ ያለው እንጨት |
| Kelffata - | ኬልፋታ - | አእምሮአዊ ንፅህና ( cleansing ) የማግኘት ሥርዓት |
| Kinticho - | ኪንቲቾ - | ሚስቱ የሞተችበት፣ከሚቿ ታናሽ እህቶች አንዷን ሲያገባ |
| Lafe - | ላፌ - | አጥንት ማለት ነው ፤ ጎንዶሮ ሲደረግ በሚታረቁ ሰዎች መካከል ግራና ቀኝ ተይዞ ላፌ ይሰበራል |
| Mageno - | ማገኖ - | የሰማይ አምላክ ( ፈጣሪ) |
| Mammasa- | መማሳ- | በጌዴኦ ህብረተሰብ ሚታዊና ፤ አፈታሪካዊ ይዘት ያላቸው ዝርው ቃል ተረኮች |
| Motie - | ሞቴ - | ከእንጨት የሚሰራ ባለሦስት እግር መቀመጫ ሲሆን፣ ለሽማግሌዎችና ለትልልቅ ሰዎች የሚያገለግል ነው ። |
| Murra - | ሙራ - | ከባህላዊ አመራሩ የሚሰጡ ትዕዛዛትንና መመሪያዎችን ለህዝብ ጆሮ የሚያደርስ ተላላኪ ማለት ነው ። |
| Qeexala - | ቄጣላ - | ጦርነት፣ ድርቅ፣ ረሃብ፣ በሽታ፣ ሲከሰት ማገኖን (ፈጣሪን) የመማፀኛ ህብረ ዝማሬ ነው ። |
| Qiid - | ቂድ - | ይጥፋ፣ ይወገድ፣ ይቀዝቅዝ ማለት ነው። |

| | | |
|---|---|---|
| Raaba - | ራባ - | ሥልጣኑን ከለባው (ዕጩ) ላይ ለመረከብ ተዘጋጅቶ የሚገኝ ተተኪ በድን ማለት ነው:: |
| Roga - | ሮጋ - | ክልል ማለት ነው ፤ የጌዴኦ ዞን በገዳ ሥርዓት መሠረት በሦስት ክልሎች የተዋቀረ ሲሆን እያንዳንዱ ክልልም ሮጋ ይባላል :: |
| Suppottee Roga - <br> Dhiibeta Roga- <br> Rhiikaata Roga - | ሱፓቴ ሮጋ - <br> ዲፐቲ ሮጋ - <br> ሪቀታ ሮጋ - | የጌዴኦ ዞን በባህላዊ አስተዳደሩ ሥርዐት መሠረት በሦስት ክልሎች ተከፍሎ የእያንዳንዱ ክልል ሀላፊ ወይም ሹም መጠሪያ ሲሆን ፣ ተጠሪነታቸውም ለአባ ገዳ ነው:: |
| Senecha - | ሰነቻ - | ከህዝብ መካከል የሚመረጥ(ህዝባዊ ጦር) ማለት ሲሆን፣ ግልጋሎቱም ጠላት ለማጥቃት ሲመጣ የሚከላከል ነው:: |
| Shole Baxxie - | ሾሌ ባጤ - | ከሁለተኛዋ ሚስታቸው የተወለዱ የደራሶ ሦስት ልጆች |
| Songo - | ሶንጎ - | በጌዴኦ ህብረተሰብ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ አምልኮታዊ ክንውኖች የሚካሄዱበትና በየአካባቢው የሚገኝ አማካይ የሆነ ሥፍራ ነው :: |
| Wabeeko - | ዋቢኮ - | ነቢያት ማለት ሲሆን ፣ በፈጣሪና በሰዎች መካከል እንደ ድልድይ በመሆን ወደፊት የሚሆነውን ሁሉ የሚተነብዩ ሰዎች ማለት ነው:: |
| Warraye - | ዋራየ - | ሶረኒ (ብርቅዬ) ወፍ |
| Wassa - | ዋሳ - | ቆጮ |
| Wayyo - | ዎዩ - | ከሰባቱ የጌዴኦ ጐሣዎች መካከል ለማገኖ 'Mageno' መስዋዕት የሚያቀርቡና ማንኛውንም አምልኮታዊ ሥርዓት በበላይነት የሚመሩ የተከበሩ ሰዎች ናቸው |
| Weyee - | ወዬ - | ተከልሎና ተከብሮ የሚቀመጥ የመስዋዕት ማቅረቢያ ስፍራ ነው :: |
| Xingo - | ጢንጎ - | ለማስተማሪያ፣ ለማዝናኛ፣ለመገሰጫ ወዘተ. የሚነገሩ የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች :: |
| Xingo-Xingaani - | ጢንጎ ጢንጋኒ- | በጌዴኦ "ተረት ተረት" ማለት ሲሆን፣ ተረት ለመናገር በሚፈልግ ሰው የሚነገር የመክፈቻ ቀመር ነው |

*** M = Mammassa – (መማሳ)**

*** X = Xingo – (ጢንጎ)**

# አጠቃሎ

የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው በሚል ርዕስ የቀረበው ይህ ቴሲስ፣ ያተኮረባቸውና በሂደቱ መጨረሻ የደረሰባቸው ዋና ዋና ነጥቦች ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው፡፡ ጌዴኦ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ሥር ከሚገኙ አስራ ሦስት ዞኖች መካከል አንዱ ነው፡፡ ቋንቋቸው ጌዴኦኛ (Gdeeuffa) ሲሆን፣ ባህላዊና ማህበራዊ ተመሳስሎ ካላቸው ከቡርጂ፣ሐዲያ፣ሲዳማ እና ከምባታ ህዝቦች ቋንቋዎች ጋር እንደሚዛመድ McClellan (1988:28) ይገልፃል፡፡

በዚህ ጥናት ለአብነት የተጠቀሱትን የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓቶችን (ቄጠላ፣ ፋጨ ፣ ጎንደሮ፣ የጋብቻና ጥንታዊ የሃዘን ሥርዓት) ክዋኔዎችን እየዳሰሰ፣ የዝርው ቃል ተረኮቻቸውንም ጎሳዊ ምደባ/ethnic categories/፣ ካባቢያዊ ስያሜ፣ (መጠሪያ) እንዲሁም ማህበራዊ ግልጋሎታቸውን ወዘተ. በመመርመር ምንነታቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

ጥናቱ፣ በተሳትፎ ምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅና (በፅሁፍና በድምፅ) በቡድን ወይይት፣ በመሳሰሉ የምርምር መሳሪያዎች ከመስክ፣ እንዲሁም ቀጥታ ግኙነት ካላቸው ከተለያዩ ፅሑፎችና ጥናታዊ ሥራዎች፣ በንባብ የተገኙ ግንዛቤዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን አካቶ በገላጭ ዘዴ (descriptive method) የተካሄደ ሥራ ነው፡፡ የህብረተሰቡን ባህል ያውቃሉ ተብለው በአካባቢው ነዋሪዎች ከሚጠቆሙ ሰዎች መረጃዎችን፣ በሰው ሰራሽ ዘዴ (Artificial Setting) በመገልገል ተሰባስበዋል፡፡ በመገኛ ቋንቋ የተሰባሰቡ መረጃዎችም እንዲሁ፣ አማርኛና ጌዴኦኛ ቋንቋዎችን በሚገባ በሚያውቁ ሰዎች ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉመው የመረጃ ሰነዶች ሆነዋል፡፡

በተገኙት መረጃዎች መሠረት፣
የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች የልማዳዊ ሥርዓቶቹ መግለጫ፣ ማጠናከሪያና ቀጣይነታቸው እንዲጠበቅ መልሰውም መትከያዎቻቸው እንደሆኑና እንደሚሆኑም በጥናቱ ተደርሶባቸዋል፡፡ ዝርው ቃል ተረኮቻቸው በሁለት ጎሳዊ ምድቦች እንደሚከፈሉ ማወቅ ተችሏል፡፡ በአካባቢያዊ ስያሜዎቻቸው/መጠሪያዎቻቸው መማሳ 'Mammassa' እና ጢንጎ 'xingo' ይባላሉ፡፡ እያንዳንዳቸው በአወቃቀር፣ በአቀራረብ፣ በታዳሚዎች ዕድሜና ፣በመቼት ወዘተ. ይለያያሉ፡፡ ዝርው ቃል ተረኮች የሚያበረክቱት ማህበራዊ አገልግሎት በተለይ ወጣቱን ትውልድ እነሱ



ILS LIBRARY UNIVERSITY

(ህብረተሰቡ) ሠናይ በሚሏቸው ሥራተ-አምልኮታዊ (ritual) ሥነ-ምግባራዊ (ethical) እና ግብረ-ገባዊ (moral) ይዘቶች ባሏቸው እሴቶች ለማነፅ፣ እንቢተኞችንና አሻፈረኝ ባዮችን ደግሞ ለመገሰፅ እንደሚገለገሉባቸው ጥናቱ ያመለክታል።

የዚህ ጥናት ይሁን፣ አሁን አሁን እየተተውና እየተረሱ በመሄድ ላይ ያሉት ዝርው ቃል ተረኮችና ልማዳዊ ሥርዓቶቻቸው ጭራሽኑ ደብዛቸው ከመጥፋቱ በፊት፣ የሚገኙትን ቶሎ ቶሎ በመሰብሰብ፣ ቀደም ላሉትና ላሁኖቹ እንደትዝታ፣ ለነገዎቹና ለመጪዎቹ ደግሞ እንደማስታወሻ እንዲሆኑ በቅርስነት ለማኖር፣ ያገለግላል።

በጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓቶች ውስጥ ህብረተሰቡ አጥብቆ ሊይዛቸውና ሊከተላቸው የሚገቡ፣ ሰላም፣ ፍትህ፣ እውነትና ሐቅ እንጂ፣ ግጭት አድሎአዊነት፣ ሐሰትና ክህደት የእርሱ አለመሆናቸውን እንዲገነዘብ ማድረጊያ ጠቃሚ እሴቶች እንዳሏቸው መረጃዎች ያመለክታሉ። ስለሆነም፣ እነዚህን አውቆ በማሳወቅ ረገድ ጥናቱ የራሱ ድርሻ ይኖረዋል። በዚህ ሳቢያም ለሌሎች የሥነ-ቃል ጥናቶች መነሻ በመሆን ሊያገለግል እንደሚችል የጥናቱ አቅራቢ ይገምታል።



UNIVERSITY ... IES LIBRARY

# ማውጫ


ገጽ

ምስጋና ........................................................................................................ I

ሙዳየ ቃላት .................................................................................................. II

አጠቃሎ ........................................................................................................ V

1.0 መግቢያ ................................................................................................... 1

1.1.የጥናቱ መሠረተ ሃሳብ ........................................................................... 2

1.2.የጥናቱ ቀስቃሽ ምክንያ ........................................................................ 4

1.3.የጥናቱ ዓላማ ...................................................................................... 5

1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ .................................................................................. 5

1.5.የጥናቱ ወሰን ....................................................................................... 7

1.6.ያጠናን ዘዴ ........................................................................................... 8

1.7.ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ................................................ 10

2.0 የጌዴኦ ዞን አካባቢያዊና አስተዳደራዊ ገፅታ ............................................. 12

2.1የህዝብ ስርጭትና አሰፋፈር ....................................................................... 13

2.2መልክዓ ምድርና አየር ንብረት .................................................................. 14

2.3የዞኑ ምጣኔ ሀብት ................................................................................... 14

2.4የቱሪዝም ሀብት ....................................................................................... 16

2.4.1 ቱቱፈላ ትክል ድንጋዮች(Tuuttofala Stalae) ......................................... 16

2.4.2 ቱቲቲ ትክል ድንጋዮች(Tuutiti Stalae) ................................................ 17

2.5ባህላዊ አስተዳደር ...................................................................................... 17

2.5.1 የአባገዳ ምርጫ መስፈርቶች ................................................................... 19

2.5.2 የአባገዳ ዋና ዋና ተግባራት .................................................................... 21

3.0 ክለሳ ድርሳን .......................................................................................... 23

3.1የዝርው ቃል ተረኮች ገለፃ ........................................................................ 23

3.2የተረክ ዓይነቶች ...................................................................................... 25

3.3የተረክ መዋቅር ........................................................................................ 28

3.4የተረክ ግልጋሎት ...................................................................................... 30

3.5የተረክ ታዳሚ ....................................................................................31

3.6የተረክ መቼት ....................................................................................32

3.7የዝርው ቃል ተረኮች ጥናት በሀገራችን.................................................33

4.0 የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓት........................................................................38

4.1የሶንጎ ማህበራዊ ግልጋሎት......................................................................39

4.2ቄጠላ (Qeexla) (አምልኮታዊ ጭፈራ) ........................................................41

4.3ፋጩ፡ (Facie) ....................................................................................42

4.4ጎንዶሮ (Gondoroo) ............................................................................43

4.5የጌዴኦ ባህላዊ ጋብቻ..............................................................................47

4.6ባህላዊ የሀዘን ሥርዓት............................................................................51

5.0 የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች በመረጃ አቀባዮች ግንዛቤ........................................54

5.1የጌዴኦ ቃል ተረኮች ክዋኔና መቼት.............................................................59

5.2 የጌዴኦ ቃል ተረኮች ማህበራዊ ግለጋሎት ....................................................64

6.0 በጥናቱ የተደረሰባቸው ግንዛቤዎች................................................................65

6.1ጎሳዊ ምደባዎች ....................................................................................66

6.1.1 መማሳ (Mammassa) ........................................................................66

6.1.1.1 መማሳ ተረክ አንድ .....................................................................67

6.1.1.2 መማሳ ተረክ ሁለት .....................................................................67

6.1.2 ጢንጎ (Xingo)...................................................................................68

6.1.2.1 ጢንጎ (Xingo) ተረክ አንድ..........................................................70

6.1.2.2 ጢንጎ (Xingo) ተረክ ሁለት..........................................................71

6.1.3 የጢንጎ እና መማሳ ቃል ተረኮች ልዩነት እና ተመሳስሎ ..............................72

6.2የጌዴኦ ተረኮች መዋቅር ..........................................................................72

ማጠቃለያና ይሁንታ ...................................................................................77

መዘርዝር (Bibliography).............................................................................81

የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ..............................................................................84

የተረኮች ስብስብ

## 1.0 መግቢያ

ጌዴኦዎች በደቡብ ብሔር-ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች ሲሆኑ፣ ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ ባህላቸውን፣ እምነታቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ ታሪካቸውን፣ ልምዶቻቸውንና ባጠቃላይ ዕድሜ ጠገብ የሆኑ እሴቶቻቸውን በዝርው ቃል ተረኮቻቸው አማካይነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፉ እንደቆዩ Tadesse(2000:22) ይገልፃሉ፡፡ ይህ ጥናት፣ ስለ ህብረተሰቡ አስተዳደራዊ፣ ኤኮኖሚያዊ ፣አምልኮታዊና ማህበራዊ ህይወቱ መጠነኛ ግንዛቤ ይሰጣል ተብሎ ይገመታል፡፡ የቀድሞው ደራሳ የዛሬው ጌዴኦ ዞን የደርግ አስተዳደር ሥርዓት ማክተሚያ እስከተቃረበበት ጊዜ ድረስ "ደራሳ አውራጃ " ተብሎ በሲዳማ ክ/ሀገር ስር ይተዳደር ነበር፡፡ ነገር ግን፣በ1979 ዓ.ም የደራሳ አውራጃ ገበሬዎች ዲላ ከተማ ላይ ተሰባስበው ደራሳ የሚለው መጠሪያ ክብረ-ነክ የሆነ ፍካሬያዊ ፍቺ ያዘለ በመሆኑ እንዲቀየር በጠየቁት መሠረት ጌዴኦ በሚለው ስያሜ እንደተተካ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

*"እኔ ራሴ ደራሳ ለሚለው ስያሜ መለወጥ እስከመጨረሻው ድረስ ታግያለሁ፡፡ ጥንት ደራሳ እየተባልን በማንፈልገው ስም ስንጠራ ቆይተን እነሆ ዛሬ መብታችን ተከብሮልን ጌዴኦ በሚለው በጥንቱና በመጀመሪያው ስማችን እንጠራለን" ሲሉ ሐይቻ ጂቢቻ ቦረሜ ይገልፃሉ፡፡*

በዚህ ጥናት ውስጥ የቃላት አጠቃቀምን በተመለከተ፣ "Oral-Prose Narrative" የሚለው የእንግሊዝኛ ሐረግ፣ በተቀባዩ የአማርኛ ቋንቋ "ዝርው-ቃል ተረክ" የሚለውን ፍቺ ይዟል፡፡ እንዲሁም "Folktales,Tales,Stories" የሚሉትን ቃላት እያንዳንዳቸውን በተናጠል ሳይሆን በጥቅል የእንግሊዝኛውን "Narratives" የሚለውን መጠሪያ በመውሰድ፣ በአማርኛ 'ተረኮች' በሚል ፍቺ እንዲያገለግል ተደርጓል ፡፡ ስለዚህ "ዝርው ቃል ተረኮች" የሚለው ሐረግ በዚህ ግንዛቤ ተወስዶ ግልጋሎት ላይ የዋለ መሆኑ ለታወቅ ይገባል፡፡

ጥናቱ በስድስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ነው፡፡ ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መሠረተ ሀሳቦች የሆኑት፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ ያጠናን ዘዴው፣ እንዲሁም ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች እንደየቅደም ተከተላቸው ተዘርዝረዋል፡፡ ምዕራፍ ሁለት የጌዴኦ አካባቢያዊና አስተዳደራዊ ገጽታ የተገለፀበት ነው፡፡ በዚህም የዞኑ ዋና ዋና የምጣኔ ሀብት መሠረት፣ እንዲሁም በህብረተሰቡ ማህበራዊና

ባህላዊ ህይወት አመራር ውስጥ አሁንም ድረስ ከፍተኛ ሥፍራ ይዞ ስለሚገኘው የገዳ (Gada) ሥርዓት አወቃቀርና ተግባራቱ ተጠቅሰዋል። በተጨማሪም ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጽሑፎች ተቃኝተዋል። ምዕራፍ ሶስት ክለሳ ድርሳን ሲሆን፣ በተለይ ስለ ዝርው ቃል-ተረኮች ምንነት፣ ስለሚቀርቡበት መቼት፣ የተረኮችን ዓይነት፣ ስለ ተረክ ታዳሚዎች፣ ወዘተ. በመስኩ ምሁራን የተሰጡ ገለፃዎችን የምንከልስበት ነው። ምዕራፍ አራት፣ የተወሰኑ የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓቶች የተዳሰሱበት ሲሆን፣ በተለይም ስለ 'Songo' ምንነትና ስለሚያበረክታቸው ግልጋሎቶች፣ቁጠላ 'Qeexla' (አምልኮታዊ ጭፈራ)፣ ፋጬ 'Facie' (በህዝብ ፊት ጥፋትን አምኖ መናዘዝ)፣ ጎንዶሮ 'Gondoroo' (ሥራተ-እርቅ) ስለ ባህላዊ ጋብቻቸው፣ጥንታዊው የሀዘን ሥርዓት፣ የመሳሰሉትን ብቻ የሚመለከት ነው። ምዕራፍ አምስት፣ የጌዴኦ መረጃ አቀባዮች ስለ ዝርውቃል ተረኮቻቸው ምንነት በራሳቸው አንደበት የሰጧቸውን የቃለ መጠይቅ ምላሾቻቸውንና ገለፃዎቻቸውን እንዲሁም ስለጌዴኦ ቃል ተረኮች ክዋኔና መቼት ማህበራዊ ግልጋሎት የምንመለከትበት ነው። ምዕራፍ ስድስት በጥናቱ የተደረሰባቸው ግኝቤዎች የተዘረዘሩበት ነው። በተለይ፣ የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች ጎሳዊ ምደባና ስያሜ፣ ስለተረኮቹ መዋቅር እንዲሁም ማህበራዊ ግልጋሎቶቻቸው ተገልፀዋል። ከየተረኮቹም ለአብነት ያህል ተጠቃቅሰዋል። ከነዚህ በተጨማሪ፣ የጥናቱ ማጠቃለያና ይሁንታም የቀረበው በዚሁ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ነው።

## 1.1. የጥናቱ መሠረተ-ሃሳብ

የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች ከልማዳዊ ሥርዓቶቻቸው ጋር በማስተያየት ያላቸውን ግንኙነትና ምንነታቸውን በስፋት የዳሰሰ ከዚህ ቀደም ሲል የተሠራ አካዳሚያዊ ጥናት ማግኘት አልተቻለም። ይሁን እንጂ፣ በዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ በሌሎች የሥነ-ቃሎች ዘርፎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ስለመኖራቸው ፍለጋም ተካሂዷል። ፊቃደ ባደረጉት የመጀመሪያ ደረጃ መዘርዝራዊ ቅኝት (Preliminary Review and Bibliography,1984) ውስጥ፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በጌዴኦ ቋንቋ ዜና ልሳን፣ ቅጽ1 ቁጥር. 2፣(1973፡18-21)፣ ጌዴኦኛ ተረትና ምሳሌ፣ ዜና ልሳን፣ ቅጽ 3፣ ቁጥር 1(1975፡42-45)፣ Wedekind, Klaus. "Gedeo Folklore" (1977) የሚሉ በመጽሔት ላይ የወጡ ሥራዎች እንዳሉ አሳይተዋል ። ይሁን እንጂ፣ እርሳቸውም ቢሆኑ፣ በቅኝታቸው ውስጥ የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች ከልማዳዊ ሥርዓቶቻቸው አንፃር በመመልከት ያላቸውን ተደጋጋፊነት የሚያሳይ አካዳሚያዊ ጥናት መኖሩን አላመለከቱም። ስለዚህም ይህ ዘርፍ መጠናት የሚኖርበት አንድ የሥነቃል ዘውግ መሆኑ ግልፅ ነበር። ይህ የእርሳቸው ቅኝትም፣ ይህን ጥናት ማካሄድ የሚያስችል ሌላ ተጨማሪ ፍንጭ ጠቋሚ መረጃ በመሆን አስተዋፅኦ አለው።

የህብረተ-ሰቡ ልማዳዊ ሕይወት ምን እንደሚመስል ወደ ኋላ ስንመለከት፣ ጥንት ጌዴኦ አንድና ብቸኛ በሆነው ማገኖ 'Mageno' (የሰማይ አምላክ) ያምን ነበር። በምድራዊው ሰውና በሰማይ አምላክ መካከል አማላጅ ሆነው የሚያገለግሉ ዋቤኮ "Wabeeko" [1] ( የምድር አዋቂዎች ) የሚባሉ ሰዎች አሉ። ማንም የህብረተ-ሰቡ አባል የፈጣሪው ተራዳኢነትና ርህራሄ እንዳይነፈገው ይፈልጋል። ለዚህም ምን መፈፀም እዳለበት ፣ አስቀድሞ የሚወያየው ከእነዚህ "አዋቂዎች" ጋር ነው Tadesse,(2000:27)።

በባህላዊ ሥርዓቱ መሠረት፣ በጋብቻ ላይ ጋብቻ አይከለከልም። አንድ ሰው ሀብት እስካለው ድረስ ብዙ ሚስቶች ማግባት ይችላል።በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርኳቸው ሰዎች የሚከተሉትን አስተያየቶች ሰጥተዋል። "እኔ ካገባኋቸው ዘጠኝ ህጋዊ ሚስቶቼ በድምሩ ሰማኒያ አምስት ልጆች ወልጃለሁ "የሚሉት የአንድ መቶ ዓመት ዕድሜ ባለፀጋው አቶ ቀቀቦ ሾታ የልጆቻቸውን ስም እንኳን በሙሉ አጥርተው አያውቁም። እንዲሁም ሐይቻ አለማይሁ ቦኮ "ከሁለት ህጋዊ ሚስቶቼ ከአሥር በላይ ልጆች ወልጃለሁ አሁንም ከእነርሱ ጋር አብሬ እኖራለሁ "ብለዋል።

ከዚህ ሌላ፣ ህብረተሰቡ ባህላዊ፣ አምልኮታዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮቹን የሚከውንባቸው አማካይ ቦታዎች በአካባቢው አጠራር ሶንጎዎች (Songo) በየጎጡ ይገኛሉ። በእነዚህ ቦታዎች ከላይ የተጠቀሱት የህብረተ-ሰቡ ማህበረ-ባህላዊ እንቅስቃሴዎች እስከ ዛሬ ድረስ እየተካሄዱ ናቸው። ሲሉ ሐይቻ ጂቢቾ ቦረሜ ይገልፃሉ።

ይህ ጥናት ከላይ የተጠቀሱትን መንደርደሪያ ሃሳቦች መሰረት አድርጎ ሲካሄድ፣ ልማዳዊ ሥርዓቶቹ ለቃል ተረኮቹ፣ ቃል ተረኮቹም እንዲሁ ለልማዳዊ ሥርዓቶቹ፣ ያላቸውን ግንኙነትና ተደጋጋፊነት እየዳሰሰ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የተረኮቹን የምደባ መስፈርት፣ የሚታወቁበትን አካባቢያዊ ስያሜ ወይም መጠሪያ ያፈላልጋል። እንዲሁም፣ ዝርው ቃል ተረኮች በህብረተ-ሰቡ ውስጥ ያላቸውን ማህበራዊ ግልጋሎትና አሁን የሚገኙበትን ሁኔታም ወዘተ. በመመርመር የደረሰባቸውን ግኝቶች ለማመልከት የተካሄደ ነው።

---

[1] በጌዴኦ አምልኮታዊ ሥርዓት ውስጥ ምድራዊውን ሰው ከሰማይ አምላክ ጋር የሚያማልዱ ናቸው።

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

## 1.2. የጥናቱ ቀስቃሽ ምክንያት

በሀገራችን በስፋት ካልተዳሰሱት የሥነ-ቃል ምርምር ዘርፎች መካከል፣ የዝርው ቃል ተረኮች ጥናት አንዱ መስክ ነው ፈቃደ (1991፣42)። በመሆኑም ይህ ሰፊ ህዝባዊ ሀብት፣ እየተካሄደ ባለው አካዳሚያዊ ምርምርና ሌላም አግባብነት ባላቸው መስመሮች አማካይነት በሚደረጉ ጥናቶች ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባው አያጠያይቅም። የጥናቱ አቅራቢ በሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፌን በዚህ ዙሪያ ለማድረግ ከፍተኛ ፍላጎት ነበረኝ። ሆኖም፣ በየትኛው ህብረተሰብ ላይ ብሰራ ይሻላል? እያልኩ የተለያዩ ርዕሶችን ሳማርጥ፣ በመካከሉ በጌዴኦ ዋና ከተማ ዲላ ውስጥ የሚኖር አንድ ወዳጄ "ኦዱ-ያኣ" ተብላ የተሰየመች የክልሉን ዓመታዊ መጽሔት ልኮልኝ የማንበብ አጋጣሚ አገኘሁ። ከፅሁፉ ባገኘሁት ግንዛቤ ስለ ተቀሰቀስኩ ወደ ህብረተሰቡ ዘለቅ ብዬ ለማጥናት ባሳደረብኝ፣ ጉጉት ወደ ሥራው መግባት ቻልኩ።

በመጽሔቱ መግቢያ ላይ ከሰፈረው ሐሳብ፣

> *የክልላችን የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ በተፈለገው ደረጃ ዕድገት ባለማሳየቱ የሕትመት ውጤቶችን እያዘጋጀን የብሔረሰቡን ባህል፣ ታሪክና ወግ ለማሳወቅ አጋጣሚውን ሳንጠቀም ቆይተን፣ ይህችን በዞናችን የመጀመሪያ የሆነችውን መጽሔት ለማሳተም በመቻሉ፣ የዞናችንን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ፣ የጌዴኦ ብሔረሰብ ማንነት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ለሌሎች ለማሳወቅ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮልናል። ኦዳያኣ (1997:5)*

የሚለው አስተያየት ይገኝበታል። ይህ አስተያየት በራሱ በህብረተሰቡ ባህልና ወግ ዙሪያ የሚጠና ነገር ስለ መኖሩ ሌላው ፍንጭ የሚሰጥ አጋጣሚ ነበር። በህብረተ-ሰቡ ማህበረ-ባህላዊ ህይወት ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች እንዳሉ ባደረግሁት ዳሰሳ፣ ከመረጥኩት ርዕስ ጉዳይ ጋር በሩቁ የሚገናኙ፣ የእነ ጥላሁን (1991 ዓ.ም)፣ Tadesse, (2002); Dagne, (1995); WedkindKlaus, (1977) ወ.ዘ.ተ. ሥራዎችን ማግኘት ችዬአለሁ። ከእነዚህ ሥራዎች ስለ ህብረተ-ሰቡ ባህል፣ ልማዳዊ ሥርዓትና ታሪክ የሚገልፁ ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ማግኘት ተችሎአል። ነገር ግን እንዴት ይጠና? በምን ስልትና፣ በምን አጋጣሚ ማጥናት እችላለሁ? የሚሉት ጥያቄዎች ባይዘነጉም፣ አስቀድመው ምላሽ ማግኘት የነበረባቸው ነበሩ። ስለሆነም ጥናቱን ለማካሄድ በአካባቢው ታዋቂ ሰዎችን ማፈላለግ፣ የዞኑን መስተዳድር ይሁንታ

ማረጋገጥና የባህል ቢሮውን ትብብር ማግኘት ቀዳሚ ተግባራት ሆኑ፡፡ ደረጃ በደረጃ በነዚህ ላይ የተደረጉ ጥረቶች ሁሉ የተሳኩ በመሆናቸው፣ ወደፊት ለመቀጠል የሚያበረታታ ሁኔታ ተፈጥሮ ጥናቱ ከዳር ሊደርስ ችሏል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

ማንኛውም በየዘርፉ የሚካሄድ ጥናት የራሱ ዓላማና የመጨረሻ የሚለው ግብም ይኖረዋል፡፡ በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ልማዳዊ ሥርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው መካከል ምን ግንኙነት አለ? ዝርው ቃል ተረኮቻቸውስ ክፍልፋዮች አሏቸው ወይስ የሏቸውም? ካሏቸው ምን ተብለው ይጠራሉ? የክፍልፋዮቹ መስፈርቶችስ ምንድናቸው? ህብረተሰቡ እነዚህን ተረኮች ለምን ዓላማና ግልጋሎት ያውላቸዋል? ወዘተ. ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ፍለጋ የተካሄደ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ የሚዘልቀው፣ ቀጥሎ በተመለከተው አካሄድ ነው፡፡

1. በህብረተሰቡ ልማዳዊ ሥርዓቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው ውስጥ ምን ግንኙነቶች እንዳሉ መርምሮ ለማመልከት፣ በተወሰኑት ላይ ዘርዘር ያለ ዳሰሳ ማካሄድ፣
2. የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች በሚያበረክቷቸው ማህበራዊ ግልጋሎቶች አንፃር ሲመረመሩ፣ ይዘቶቻቸው በምን በምን ላይ እንደሚያተኩሩ ለማሳየት፣
3. የተረኮቻቸውን ኅሳዊ ምደባና አካባቢያዊ ስያሜዎቻቸውን ለይቶ ለማውጣት፣
4. ስለዝርው ቃል ተረኮች ምንነት በመስኩ ምሁራን የተሰጡ ገለፃዎችን ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች ጋር በማስተያየት፣ ክዋኔያቸውን፣ አወቃቀራቸውን ተመሳስሎና ልዩነቶቻቸውን ለይቶ ማመልከት፣ የሚሉ ናቸው፡፡

በመጨረሻም በጥናቱ ሂደት የተደረሰባቸውን ግኝቶች መግለጽ የዚህ ጥናት ዓይነተኛ ዓላማ፣ ነው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ማንኛውም ጥናት እንደየርዕሰ ጉዳዩ ዓይነት፣ ዓላማና ግልጋሎት ላይ ተመስርቶ ይካሄዳል፡፡ በውጤቱም አንድ ተፈላጊ ነገርን ሊያስገኝ ይችላል፡፡ በዚህ አንፃር፣ በአንድ ህብረተሰብ ሥነ-ቃል ላይ የሚደረግ ጥናትም ቢሆን እንደዚሁ የዚያን ህብረተሰብ ማንነት፣ ፍላጎት፣ ሥነልቡናዊ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ዝንባሌና ማህበራዊ ህይወቱን ለማወቅ እንደሚረዳ እሙን ነው፡፡ የተጠቀሱትን ማህበራዊ ሁኔታዎች በወጉ ለመረዳት ከኋላ ጀምሮ ወደ ፊት መምጣት የግድ ነው፡፡ ይህን አስመልክተው ፈቃደ (1991፡91) "የዛሬው ትውልድ የቆመበትን መሠረት ለማወቅና የነገውንም መንገድ ለመቅደድ ስለሚበጅ የሥነ-ቃል ጥናት አንድን ህዝብ የማወቂያና የዚያንም ህዝብ አስተሳሰብ መለወጫ መንገድ መፈለጊያ መሳሪያ ሊሆን ይችላል፡፡" በማለት ይገልፃሉ፡፡ በዚህም መሠረት ስለ ዛሬ ጌዴኦ ለመናገር ስንፈልግ፣ ስለ ትናንቱ ጌዴኦ በመጠኑም ቢሆን ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል፡፡ የወደፊቱንም ቢሆን በዛሬው ላይ ተመርኩዘን እንዲህ ሊሆን ይችላል የምንልበት መንደርደሪያ ያስፈልገናል፡፡ ዛሬ ስለ ጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ልማዳዊ ሥርዓት፣ ስለ ዝርው ቃል ተረኮቻቸው ምንነትና ፋይዳ ላይ የተመሰረተው ይህ ጥናት፣ ያለፉትን ማህበረ-ባህላዊ ክንውኖችን ይዞ፣ ዛሬ ደግሞ ከመስክ የተገኙትን መረጃዎች አክሎ፣ በዚህ ዙሪያ ለወደፊት ለሚደረጉ ጥናቶች መረጃ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

በተጨማሪም፣ ያንድን ህብረተ-ሰብ ሥነ-ቃል በራሱ በህብረተሰቡ ውስጥ ተገኝቶ በሚገባ ማጥናትና መረዳት መቻል በአንድ መልኩ የህብረተሰቡ ፍላጎቶች ምን ምን እንደሆኑ በቅርበት ሆኖ ለመገምገም ያስችላል፡፡ በተለይም አካባቢን፣ ልምድን፣ ፍላጎትን ወዘተ. ተከትለው የተወጠኑ የጋራ የልማት ዕቅዶች ላይ ህብረተ-ሰቡ፣ የሚኖረውን ተሳትፎና የዕቅዱንም ውጤታማነት በቀላሉ ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን፣ የህብረተ-ሰቡን እሴቶች ወደ ጐን ተትተው ወይም ችላ ተብለው የሚሰሩ የልማት ዕቅዶች ጉዳት ያስከትላሉ፡፡ ይህን ጉዳት ከሥነ-ቃል ማህበራዊ ግልጋሎት (functions) አንፃር ሊጤን ይችላል፡፡ ቀጥሎ የቀረበው የመስክ መረጃ በተጨባጭ የሚያረጋግጥልን፣ ሥነቃል በህብረተሰቡ ውስጥ የሚጫወተውን ወሳኝ ሚና ሲሆን ይህም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

> *በአየርላንድ መንግሥት የሚደገፍ አንድ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት በአንድ ወቅት በጨሌ ወረዳ ውስጥ ለሚገኙ የገጠር ገበሬ ማህበር-አባላት በጤና ዘርፍ አንድ ጠቃሚ ሥራ ለመስራት የአሰሳ ጥናት ያካሄዳል፡፡ ያካባቢው ጤና ጣቢያ ደግሞ ህብረተሰቡ ከንፅህና ጉድለት የተነሳ በተላላፊ በሽታ አዘውትሮ እንደሚጠቃ መረጃውን አጠናቅሮ ለተባለው ድርጅት ያቀርባል፡፡ ድርጅቱ ያገኘውን መረጃ ተመርኩዞ "ለሶስት አባወራ አንድ" በሆነ ስሌት ዘመናዊ ደረቅ ሽንት ቤቶችን በግንብና በሲሚንቶ ሰርቶ ለማህበሩ አባላት ያስረክባል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ቆይቶ በሌላ ጊዜ ሽንት ቤቶቹን ያሰራው ድርጅት በጤና በኩል ምን ውጤት እንደተገኘ ለመገምገም ሲመጣ ያገኘው ነገር የተለየ ነበር፡፡ ሽንት ቤቶቹ መጀመሪያውኑ እንደተሰሩ፣ ምንም ንፅህናቸው ሳይጓደል ነገር ግን ውስጣቸው የመሬት ማዳበሪያ በያዙ ጆንያዎች ተሞልተውና በሮቻቸው ተቆልፈው ይገኛሉ፡፡ ለምን እንዲህ ሊሆን እንደቻለና ሰዎች እንዳልተጠቀሙባቸው ሲጠየቁ፣ የሰጡት መልስ "የወንድ ልጅ መማከሪያው እዳሪ ሲወጣ ነው፡፡" የሚልና በተጨማሪም "የልጅ ሚስትና የባልየው አባት በአንድ ጉድጓድ አብረው አይቀመጡም በባህላችን የተከለከለ ነው"[2] የሚል ነበር፡፡*

[2] ዘላለም ደጌኖ ኅዳር 24/1999 ቃ.መ ቡሌ ወረዳ

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ጉዳይ (case) እንደሚያመለክተው፣ የህብረተ-ሰቡ ፍላጎት፣ እምነቱና ልማዱ፣ ለተላላፊ በሽታ ምክንያት ተደርጎ ቆሻሻን ከማስወገድ ዕቅድ ጋር ምን ያህል እንደተራራቁ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ልማዱን ወደኋላ ትቶ ጥሬ መረጃዎችን ብቻ ነጥሎ በመውሰድ ለትግበራ ከመጣደፍ ይልቅ፣ ያካባቢውን ህብረተ-ሰብ ስሜቱን፣ ፍላጎቱን፣ ባህሉን፣ ልማዱንና ወጉን የሚገልፅባቸው ዘፈኖቹን፣ እንጉርጉሮዎቹን፣ ግጥሞቹን ወዘተ. ባጠቃላይ ሥነ-ቃሉን አስቀድሞ ማጤን መመርመርና ማወቅ እንደሚያስፈልግ የሚጠቁም መረጃ ነው፡፡ የተባሉት ጉዳዮች በቅድሚያ ተጠንተው ቢሆን ኖሮ፣ ምናልባት የታሰበውን ዕቅድ ውጤታማና ዘለቄታዊ ያደርገው እንደነበር መገመት ይቻላል፡፡ የተጠቀሰው ዓይነት ችግር በህብረተ-ሰቡ መካከል እንዳይከሰት፣ በአንድ ህብረተ-ሰብ ማህበራዊ ህይወት ዙሪያ የሚደረጉ የሥነ-ቃል ጥናቶች የዚያን ህብረተ-ሰብ አስተሳሰብ፣ ፍላጎትና ዝንባሌውን በቅድሚያ ለማወቅ እንደሚረዱ ተደጋግሞ የሚነሳ ሃሳብ ነው፡፡

በዚህ መሰረት ይህ ጥናት፣

ሀ. በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ በከተማም በገጠርም አሁን አሁን እየተረሱና እየተተው በመሄድ ላይ የሚገኙትን ዝርው ቃል ተረኮቻቸውን በቅርስነት ለማቆየት፣

ለ. ለአካባቢያቸው ዕድገት የሚበጁ ልማታዊ ዕቅዶች ሲታሰቡ የህብረተሰቡን ባህላዊ እሴቶች በቀላሉ ለማየት እንዲቻል ፣

ሐ. የጌዴኦን ህብረተ-ሰብ በዝርው ቃል ተረኮቹ አማካይነት ፍላጐቱን፣ ሥነ-ልቦናዊ ዝንባሌውንና ማንነቱን ለማወቅና ሌሎችም እንዲያውቁት ለማድረግ

መ. በመጨረሻም በአካዳሚያዊው የምርምር ዘርፍ ረገድ እንደአንድ ተጨማሪ አበርክቶ በመሆን፣የራሱ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ በጥናቱ አቅራቢ ይገመታል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በጌዴኦ ህብረተሰብ የመኖሪያ አካባቢዎች በሆኑ ዲላ፣ ኮቾሬ፣ ይርጋጨፌ፣ ወናጎ፣ ቡሌና ገደብ ወረዳዎች ከሚገኙ ነዋሪዎች ውስጥ፣ ተባባሪ ሆነው ከተገኙ መረጃ ሰጪዎች የተሰበሰቡ የቃል መረጃዎችን ይዟል፡፡ እንዲሁም በህብረተ-ሰቡ ጥንታዊ ታሪክ፣ ባህላዊ አስተዳደርና፣ ልማዳዊ ሥርዓቶች ላይ በተሰሩ የጽሑፍ መረጃዎች በተለይ ለጥናቱ ይጠቅማሉ የተባሉትን ነጥቦች ያካተተ ነው፡፡



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ጥናቱ የዞኑ ዋና ከተማ የሆነችውን የዲላ ከተማን ማዕከል በማድረግ የተካሄደ ነው፡፡ እንደማንኛውም የአገራችን ህብረተሰቦች ጌዴኦዎችም ጥንታዊና ሲያያዙ የመጡ ልማዳዊ ሥርዓቶች እንዲሁም የራሳቸው ዝርው ቃል ተረኮች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ እንቆቅልሾች፣ ቀልዶች፣ ልዩ ልዩ ቃላዊ ግጥሞች፣ የርግማንና ምርቃን ሥርዓቶች መለማመኛዎች፣ ወዘተ. ባለቤቶች ናቸውና እነዚህ ሁሉ መጠናት ይኖርባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የተጠቀሱት እያንዳንዳቸው ራሳቸውን የቻሉ የጥናት ዘርፎች እንደመሆናቸው በጥልቀት ይጠኑ ዘንድ ሰፊ ጊዜና ገንዘብ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም፣ ከላይ ከተዘረዘሩት የሥነ-ቃል ዘውጎች (genres) (ብርሃኑ ገበየሁ1995) መካከል፣ ይህ ጥናት በጌዴኦ ህብረተሰብ ልማዳዊ ሥርዓትና፣ ዝርው ቃል ተረኮቻቸውን በመመርመር ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው፡፡

## 1.6. ያጠናን ዘዴ

በብዙ የምርምር ስራዎች ውስጥ እንደሚታየው፣ አስፈላጊ የጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሲታሰብ ቅድመ መስክ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ቀጥሎም፣ መረጃን መሰብሰብ፣ መክልሰፍ (classify) እና ስነዳ (Documentation) ወዘተ. የመሳሰሉ የቅደም ተከተል ክንውኖች ይካሄዳሉ፡፡ በነዚህ ዙሪያ ማድረግ ስለሚገባ ቅድመ ጥንቃቄ ፈቃደ (1991፣117)፣ Dorson (1972:67)፣ Goldstein (1964:87)፣ MacDonald (1972:404) አበክረው ያስገነዘቡትን መከተል ተገቢ ይሆናል፡፡ ከላይ በተዘረዘሩት ምሁራን ሥራዎች ውስጥ የተጠቀሱትን መርሆዎች (Guidelines) መገልገል በዚህ ጥናት ውስጥ የማይታለፍ ተግባር ነው፡፡

አንድ ጥናት በሚሰባሰቡ መረጃዎች አደረጃጀት ትንተናና አሰነዳድ ብቃት ላይ ተመስርተው በሚሰጡ አስተያየቶች ብቃቱ ሊገመገም ይችላል፡፡ ይሁንና ተመራማሪው የሚፈልጋቸውን መረጃዎች ከየት ከየት ያገኛል? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ፣ በመስኩ ምሁራን ተደጋግሞ ከሚጠቀሰው ሐሳብ የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

*The folklorist obtains his primary data in three basic ways through fieldwork, from archives and by way of printed sources. Dorson (1972:465)*

አንድ ፎክሎረኛ ለሥራው የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ከመስክ፣ ከቤተ-መዘክር፣ እንዲሁም ከልዩ ልዩ ፅሁፎች ማግኘት እንደሚችል በጥቅሱ ተገልጿል፡፡ ይህን የ *'Dorson'* አስተያየት ይህ ጥናት የሚጋራው አቢይ ነጥብ ነው፡፡

በመሆኑም ለጥናቱ አስፈላጊ ሆነው የተገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ፣ ይህ በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ልማዳዊ ሥርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው ላይ የሚያተኩር ጥናት፣ በገላጭ ዘዴ (Descriptive Method) ተካሂዷል። ጥናቱ የህብረተሰቡ መኖሪያ በሆነው አካባቢ በመገኘት በድምሩ ለሰላሳ ሁለት ሰዎች ቃለ-መጠይቅ በጌዴኦፋም በአማርኛ ቋንቋም በጽሑፍና በድምፅ መረጃዎች ተሰብስበዋል (የመረጃ አቀባዮችን ዝርዝር መግለጫ ከአባሪው ይመለከቷል) የድምጽ መረጃች በካሴቶች ተቀርፀዋል ።

በጌዴኦፋ የተሰበሰቡ መረጃዎች አማርኛና ጌዴኦኛ ቋንቋን በሚያውቁ ሰዎች ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ግልጋሎት ላይ ውሏል። በተጨማሪም አስራ አንድ ከሚሆኑ ተባባሪ አባላት ጋር የቡድን ውይይት (Focus group discussion) ተደርጓል። ይህም በማስረጃነት በጽሑፉ ውስጥ ይገኛል። ከተሳትፎ ምልከታዎች የተገኙ ግንዛቤዎችም እንዲሁ ለጥናቱ ያስፈልጋሉ የተባሉትን ብቻ በመሰብሰብና በማደራጀት፣ ግልጋሎት ላይ ውለዋል። በህብረተሰቡ ማህበራዊና ባህላዊ አኗኗር ዙሪያ የተፃፉ የምርምር ሥራዎችን፣ ጽሑፎችን፣ መፅሔቶችንና በራሪ ጽሁፎችን በማንበብ፣ ከመስክ ከተገኙ ግንዛቤዎች ጋር በማስማማት፣ ጥናቱ የመስክና የቤተ-መፃህፍት መረጃዎች ጥንቅር ውጤት እንዲሆን ተሞክሯል ።

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ የመስክ መረጃዎች፣ የተሰበሰቡት በተሳትፎ ምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት በመሳሰሉ የምርምር መሳሪያዎች ነው።

የዚህ ጥናት አቅራቢ በ20/12/98 የ'ዲላ ወረዳ' ምስረታ በዓልንና በ10/06/99 በኮቾሬ ወረዳ ጨለቅለቅቱ ከተማ በተዘጋጀ ወረዳ አቀፍ የህብረተሰቡ ባህላዊ ፌስቲቫል ላይ ተገኝቶ ነበር። በሁለቱም ሥፍራዎች ሲካሄዱ የነበሩ ልዩ ልዩ ሥርዐተ- ክንውኖችን (rituals) ተከታትሏል። በሥፍራው ከነበሩ ተሳታፊዎችና የገዳ አባላት ጋር ሲያዜሙ አብሮ በማዜም፣ሲያጨበጭቡም አብሮ በማጨብጨብ ክንውኖችን ማስተዋል ችሏል።

በሁሉም አጋጣሚዎች የተስተዋለው፣ የባህላዊ አስተዳደሩ የበላይ ተጠሪ የሆኑት አባገዳ (AbbaGada) እና የካቢኔ አባሎቻቸው (ጀላባ፣ ሮጋ፣ ጀልቀባ ሐይቻ ወዘተ.የስልጣን ደረጃቸውን በገፅ 22 ይመለከቷል) በየዝግጅቱ ጥንታዊ የባህል ልብሶቻቸውን በመልበስ፣ የየራሳቸውን ረጃጅም ብትሮች ይዘው፣ ሰብሰብ ብለው ያዜማሉ። ቀጥሎም በዝግታ ወደፊት በመራመድ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

እንደገና ፈጣሪያቸውን ማገኖ( Mageno) ይለምናሉ፡፡ የምስጋና ፀሎት ማሰማት፣ለተሰበሰበው ህዝብ ምርቃት መስጠት ከሁሉ የመጀመሪያ ተግባር ነበር፡፡ ዝማሬ ፀሎት ለተሰብሳቢዎች በሚያሰሙበት ወቅት፣ ዙሪያቸውን የከበቧቸው ሁሉ ባንድ ድምፅ እነሱ የሚሉትን በመድገም ይቀበላሉ፡፡ ቀጥሎም፣ አባገዳ (የስርዓቱ መሪ)፣ እጃቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው ለሰብሉ፣ ለእንስሳቱ፣ ለአገሩ፣ ለአካባቢው ወዘተ. ሰላም፣ ጤንነት፣ ብልፅግና፣ አንድነት ተመኝተው፣ በአንፃሩ ክፉት፣ ተንኮል፣ በሽታ፣ ረሃብ፣ ጦርነት ወዘተ. ከእኛ አርቅልን (Mageno N'urraa fegiessa} እያሉ ሲማፀኑ፣ ህዝቡም ቃል በቃል እየተከታተለ አርቅልን (Fegiesse) ይላል፡፡ ሁሉም ሥርዓቱን አክብሮ ክንውኖችን (ዝማሬ፣ ፀሎት፣ ምርቃት፣ ርግማን) በጥሞና ይከታተላል፡፡ በዚህ አካሄድ ባህላዊ ሥርዓቱ፣ ህብረ ዝማሬውና ፀሎቱ ሲያበቃ የገዳ አባላት እንደየደረጃቸው የባህል ልብሳቸውን ለብሰው ተቀመጡ፡፡ በመቀጠል የየዝግጅቱ አስተባባሪዎች አስተዳዳሪዎቹና የባህል ተጠሪ የሆኑ ግለሰቦች በየተራ ንግግር አደረጉ፡፡ በሥራቱ ሂደት ማንም ሰው መናገር የሚችለው አባገዳ ሲፈቅዱለት ብቻ መሆኑ ህዝቡ ለስርዓቱ ያለውን አክብሮት ያሳያል፡፡ በኮቾሬ አንድ የእርቅ ሥርዓት ከመከወኑ በስተቀር በሁለቱም ቦታዎች የነበሩት ሥርዓቶች ተመሳሳይ ነበሩ፡፡ በሁለቱም ቦታዎች ከሥነ-ሥርዓቶቹ በኋላ፣ ሁሉም የሚሳተፉባቸው ባህላዊ ጭፈራዎችና ጨዋታዎች ለሰዓታት ያህል ቀጥለው ነበር፡፡ ሌላው ነገር ክንውኖቹ ሲጠናቀቁ፣ ልክ በተጀመሩበት አኳኋን በአባገዳ ምርቃት እንደነበር ማስተዋል ተችሏል፡፡ በጌዴኦ ህብረተሰብ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ባህላዊ አስተዳደሩ (የገዳ ሥርዓት) ለዘመናዊው መንግሥታዊ አስተዳደር፣ ህብረተ-ሰቡን በልማዳዊ ሥርዓት በመምራት ረገድ እገዛ እያደረገ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ተደማጭነቱንና ህዝበዊ-ክብሩን ዛሬም ድረስ እንደያዘ የሚገኝ መሆኑን የዚህ ጥናት አቅራቢ ባደረጋቸው የተሳትፎ ምልከታዎች መገንዘብ ችሏል፡፡

## 1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

በዚህ ጥናት ሲጠቀሱ ከሚገባቸው ችግሮች አንዱ፣ ሴት መረጃ አቀባዮችን እንደልብ አለማግኘቱ አንድ አሳሳቢ ጉዳይ ነበር ፡፡ በህብረተ-ሰቡ ቆየት ያለ ልማዳዊ ባህል መሰረት፣ ሴት ልጅ በራሷ ፈቃድ የምትወስነው ምንም ነገር የለም፡፡ ለምሳሌ ሆቴል ቤት ገብታ አትበላም፣ አትጠጣም፡፡ ባል ስራ ውሎ ሲገባ፣ እርሷ ከቤት በመዋሏ፣ ሁለቱም ባንድ ገበታ ላይ አብረው ቀርበው አይበሉም፡፡ እሷ ያቀረበችለትን ምሳ እርሱ እስኪበቃው ድረስ ከበላ በኋላ፣ የተረፈውን ይተውላታል፡፡ እርሷም ልጆች ካሉ ከእነርሱ ጋር፣ አለበለዚያም ብቻዋን ትበላለች (የይርጋጨፌ ገፅታ1992 ፣26 )፡፡ እነዚህም የሴቶች ጥገኝነት ከሚስተዋሉባቸው ጥቂቶቹ ናቸው ፡፡ ታዲያ ይህን በመሰለ ጠንክር ያለ

ልማዳዊ ሥርዓት በሚስተዋልበት ህብረተ-ሰብ ውስጥ ነፃ በሆነ ግንዛቤ ላይ የተመሰረቱ መረጃዎችን የሚሰጡ ሴቶች የሉም ባይባልም፣ በቀላሉ ለማግኘት ግን እጅግ አስቸጋሪ ጉዳይ እንደሆነበት የጥናቱ አቅራቢ ሳይገልፅ አያልፍም ሆኖም፣ ከወንዶች የሚገኙ መረጃዎችን የመሰብሰቡ ጉዳይ እንደ ቀጠለ ሆኖ ሴት መረጃ አቀባዮችን የማፈላለጉ ጥረት ግን አልተቋረጠም ነበር። በሌላ ሶስተኛ ሰው አስተባባሪነት በተደረገ ሙከራም አንድ መረጃ አቀባይ ሴት ማግኘት ተችሏል።

ከተጠቀሰው ችግር በተጨማሪ፣ በዕድሜ የገፉ መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት ረጅም ርቀት በእግር መጓዝ አለ። ከተገኙ በኋላ ደግሞ መጠራጠር አለ። በተሄደበት ሁሉ ማንነትን ገልፆ፣ ምን እንደሚጠናና፣ ስለምን እንደሚጠና ተናግሮ በማሳመን እሺታ የማይገኝበትም ጊዜ አለ። ነገር ግን እዚህን ሁኔታዎች ሁሉ ተቋቁሞ መረጃዎችን መሰብሰብ ተችሏል። የተጠቀሱት ችግሮች አንድን መስከኛ ምን ጊዜም ሊያጋጥሙት የሚችሉ እንደሆኑ የመስኩ ምሁራን አስቀድመው ይመክራሉ። የዚህ ጥናት አቅራቢ፣ ባለመታከት ችግሮቹን እስከመጨረሻው ድረስ ተቋቁሞ የሚፈልጋቸውን መረጃዎች ሰብስቦና አደራጅቶ በማቅረብ ጥናቱን ከዚህ ደረጃ ለማድረስ ችሏል።

እስካሁን ድረስ፣የጥናቱን ዋና ዋና ወይም መሰረታዊ ጉዳዮችን ማለትም፣ የጥናቱን መሰረታዊ ሃሳብ፣ ዓላማውን፣ ጠቀሜታውን፣ ገደቡን፣ ያጠናን ዘዴውን ወዘተ. በዝርዝር ተመልክተናል። በተከታዩ ምዕራፍ ደግሞ፣ ስለ ጌዴኦ ዞን መስተዳድር መልክአ ምድራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የቀረበውን ጠቅለል ያለ ገለፃ እንመልከት።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## 2.0 የጌዴኦ ዞን አካባቢያዊና አስተዳደራዊ ገጽታ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጌዴኦ ዞን መልክአ ምድር፣ የህዝብ ብዛትና አሰፋፈር፣ የህብረተሰቡ ማህበረ-ባህላዊ ህይወት፣ ተዛማጅ ጽሑፎችን በየተራ እንመለከታለን::

የጌዴኦ ዞን "የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል"ን ከመሰረቱ አስራ ሶስት ዞኖች መካከል አንዱ እንደሆነ የዞኑ ኢኮኖሚ ልማትና ፋይናንስ ቢሮ (1998ዓ.ም) መረጃ ያመለክታል:: በተጠቀሰው መረጃ መሠረት የዞኑ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 1350 (አንድ ሺህ ሶስት መቶ ሃምሳ) ስኲየር ካሬ ኪ.ሎ ሜትር ነው::

ከአዋሳ ከተማ በስተደቡብ 90 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው የጌዴኦ ዞን ዋና ከተማ ዲላ ነች:: ከተማዋ ስያሜዋን ያገኘቺው dillaa (ዴይላ) ከሚለው ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም "መገናኛ" ማለት ነው:: ዲላ፣ ጥንት ከሸዋ ወደ ደቡብ ይደረግ ለነበረው የሲራራ ንግድ ዋና መተላለፊያና የቀረጥ መሰብሰቢያ ቦታ ነበረች:: ከዚህ ስያሜ በፊት Bedechaa4[3] (በደቻ) የሚባል ትልቅ ዛፍ በዛሬው የከተማዋ እምብርት ላይ እንደነበርና ያካባቢው ነዋሪዎችም ለልዩ ልዩ አምልኮታዊ ሥርዓት በዚሁ ዛፍ ስር ይሰበሰቡ እንደነበር ይነገራል:: ቀስ በቀስ በአካባቢው የሚሰፍረው ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ወደ ከተማነት እየተለወጠ መጣ በማለት ተስፋዬ (1994:12) ውስጥ ገልፆታል::

ቀድሞ "የደራሳ አውራጃ" በመባል በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ሥር ሲተዳደር የነበረው የዛሬው የጌዴኦ ዞን መስተዳደር፣ በደቡብ፣ በምሥራቅና በምዕራብ አቅጣጫዎች ከኦሮሚያ ክልል፣ በስተሰሜን ደግሞ ከሲዳማ ዞን ጋር ይዋሰናል (Eth. Mapping Authority, 1988)::

በዞኑ አብዛኛው የእርሻ ሥፍራ የተሸፈነው በሶስት ዋና ዋና የሰብል ዓይነቶች ነው:: ከነዚህም የመጀመሪያውን ደረጃ የሚይዘው ቡና "ቡኖ" (Buno) ሲሆን፣ ከእርሱ ቀጥሎ ዋሳ (Waasa) ወይም እንሰት በሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ደግሞ ልዩ ልዩ አትክልቶች መሆናቸውን Tadesse, (2000:12) ይገልፃሉ:: ከተጠቀሱት ዕፀዋት በተጨማሪ በአካባቢው በተፈጥሮ የሚበቅሉ

[3] Bedechaa- በዛሬዋ ዲላ ከተማ መሃል ላይ የሚገኝ ትልቅ ዋርካ መሰል ዛፍ ነበር፤ዛፉ የአምልኮታዊ (አድባር) ተግባር ማካሄጃ ሆኖ አገለግሏል፣ በስፈራው ዛሬ የዲላ ሶንጎ እንደተሰራበት ይነገራል::

ማናቸውንም ዓይነት ተክሎች ህብረተሰቡ ባለመቁረጥና፣ ባለማጥፋት የሚያደርገው ልዩ እንክብካቤ ሲታይ፣ ለአካባቢው ተፈጥሮአዊ ልምላሜ አንዱ ምስጢር ነው ለማለት ያስችላል፡፡

እስከ 1998ዓ.ም መጨረሻ ድረስ የጌዴኦ ዞን ወናጎ፣ ቡሌ፣ ይርጋጨፌና ኮቸሬ በሚባሉ አራት የወረዳ አስተዳደሮች የተከፈለ ነበር፡፡ ባሁኑ ወቅት ግን ሰፋፊዎቹን ወረዳዎች በመከፋፈል የወረዳዎቹ ቁጥር ጨምሯል፡፡ ይህ ጥናት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ፣ በካርታ የተደገፈ መረጃ ይፋ ሆኖ ስላልወጣ ዝርዝራቸውን ማግኘት አልተቻለም፡፡

የጌዴኦ ህብረተሰብ መግባቢያ ቋንቋ Gedoffaa (ጌዴኦፋ) ሲሆን፣ የዚህ ቋንቋ መሠረቱ፣ "የምስራቅ ኩሻዊ ወገን ሆኖ በደጋና በቆላ እየተከፋፈለ በኂላም የደጋው በሲዳሞ አካባቢ በሚነገሩ በስድስት ቋንቋዎች ይከፈላል፡፡ እነዚህም ቋንቋዎች ቡርጂ/ደቡብ ሲዳማ፣ ደራሲኛ/ጌዴኦኛ፣ ሲዳምኛ አላቢኛ/ሻሸመኔ/ ሃዲይኛ፣ ከምባትኛ ሁሉም ደቡብ ሸዋ ናቸው፡፡" ሲሉ ሀብተማርያም ማርቆስ (1973:26) በፅፋቸው አመልክተዋል፡፡

Gedoffa (ጌዴኦፋ) ለብዙ ዓመታት አብሮት በጉርብትና ከሚገኘው የጉጂ ኦሮምኛ ቋንቋ ጋር ባለው ግንኙነት ሳቢያ በርካታ የኦሮምኛ ቃላት ተደባልቀውበት ይገኛሉ፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን፣ በርካታ ቁጥር ያላቸው ጌዴኦዎች የኦሮምኛ ቋንቋን አቀላጥፈው እንደሚናገሩ (McMlellan 1988:28) በጥናቱ ውስጥ ጠቅሰታል፡፡

## 2.1. የህዝብ ስርጭትና አሰፋፈር

የጌዴኦ ዞን አካባቢ ከፍተኛ የህዝብ ጥግግት ያለበት ነው፡፡ በዞኑ በሚገኙ ከተሞችና ገጠር አካባቢዎች የሚኖረው ህዝብ ብዛት በመኖሪያ አካባቢና በፆታ ተከፋፍሎ ሲቀመጥ እንደሚከተለው ነው፡፡

| | ከተማ | | | ገጠር | | | ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| ወናጎ | 35442 | 33932 | 69374 | 103466 | 103578 | 207044 | 138907 | 137510 | 276418 |
| ይርጋጨፌ | 10366 | 10341 | 20708 | 88764 | 88553 | 177317 | 99130 | 98895 | 198025 |
| ኮቾሬ | 10068 | 10078 | 20146 | 104506 | 105497 | 210003 | 114574 | 115575 | 230149 |
| ቡሌ | 3265 | 3417 | 6682 | 54753 | 53846 | 108599 | 58017 | 57264 | 115281 |
| ጌዴኦ ዞን | 59141 | 57768 | 116909 | 351488 | 351476 | 702964 | 410629 | 409244 | 819873 |

ምንጭ፡- ጌዴኦ ዞን ሥነ-ሕዝብ ጽ/ቤት 1998ዓ.ም (ዲላ)



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

መረጃው እንደሚያመለክተው በዞኑ የገጠር አካባቢዎች አራቱም ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች በጠቅላላው 702,964 (ሰባት መቶ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስድሳ አራት) ሲሆኑ፣ በከተሞች ውስጥ ደግሞ 116,909 (አንድ መቶ አስራ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠኝ) ሰዎች ይኖራሉ፡፡ ባጠቃላይ በዞኑ የገጠርና የከተማ አካባቢዎች የሚኖረው ህዝብ ድምር 819,873 (ስምንት መቶ አስራ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ሶስት) ነው፡፡

በሌላ በኩል የስርጭቱን ሁኔታ ስንመለከት፣ ከተጠቀሰው አጠቃላይ ድምር ውስጥ 87.5% የሚሆነው ህዝብ በገጠር፣ 12.5% የሚሆነው ደግሞ በከተሞች ክልል ውስጥ ይኖራል፡፡ ይህም በአንድ ስኳየር ኪሎ ሜትር (1sk/m2) በአማካይ ከ300-400 ሰዎች እንደሚኖሩ ያመለክታል፡፡

## 2.2. መልክዓ ምድርና አየር ንብረት

የጌዴኦ ዞን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ወጣ ገባ የበዛበት፣ ሸንተራራማና ዳገታማ የሆነ፣ አብዛኛው በተፈጥሮ በበቀሉ ዕፀዋት፣ የተቀሩትም እንዲሁ በእርሻ ዕፅዋት የተሸፈነ አካባቢ ነው፡፡ ዓመታዊ አማካይ የዝናብ መጠን ከ1200-1800 ሚ.ሰ. ሜትር የሚደርስ ሆኖ ባመት ሁለት ጊዜ የዝናብ ወቅቶች አሉት፡፡ አካባቢው ከ1200 ሜትር በላይ በአባያ ሐይቅ አቅጣጫና 2993 ሜትር በደጋማው በሐሮ ወላቡ ኩሬ አቅጣጫ ከባህር ጠለል በላይ ከፍታ እንዳለው Tadesse (2000:22) አመልክቷል፡፡

በተጠቀሰው መረጃ መሠረት የጌዴኦ ዞን፣ ሶስቱም የአየር ንብረት የበልግ፣ የክረምት፣ የበጋ ወቅቶች ያሉት ነው፡፡ አብዛኛው የደጋና የወይናደጋ አካባቢ መሬቶች በቂ ውሃ ያላቸው መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ተዳፋታማ በሆኑ በብዙ አካባቢዎች፣ በጋና ክረምት የሚፈሱ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ምንጮችና ወንዞች መኖራቸው በቂ ማስረጃ ነው ሲሉ ነዋሪዎችና የግብርና ጽ/ቤት ባለሞያዎች በተጨማሪ ይገልፃሉ፡፡

## 2.3 የዞኑ ምጣኔ ሀብት

በጌዴኦ ከቡና ቀጥሎ እንሰት በስፋት ይተከላል፡፡ ይህም በዞኑ ከሚገኘው ጠቅላላ የመሬት ስፋት በግምት ከ22,000 (ሀያ ሁለት ሺህ) ሄክታር በላይ የሚሆነውን የሚይዝ ሲሆን፣ ከጠቅላላው የመሬት መጠን 16.4% የሚሆነውን የቆዳ ስፋት የሚሸፍን ነው፡፡ እንሰት በሶስቱም የአየር

ጠባይ በቆላ፣ በደጋና በወይና ደጋ የሚበቅል ሰብል ቢሆንም፣ በደጋና ወይናደጋ የሚበቅለው ግን፣ በቆጮው ንጣትና በጣዕሙ የተሻለ እንደሆነ የከአካባቢው ነዋሪዎች ይገልፃሉ። ዋነኛ የምግብ ሰብል ለሆነው እንሰት፣ የሚሰጠው ትኩረት የተለየ እንደሆነ ከሚከተለው ገለፃ መረዳት ይቻላል።

> *"ጌዴኦ በባህላዊ አስተራረስ ዘዴው ሁሉ እንሰትን ያዘወትራል። የሄደበት ይሄድ! ያረሰበትም ይረስ! እርሻ የሚጀምረው እንሰት በመትከል ነው። ሌላው ቀርቶ ጎጆ ቀልሶ ከወላጆቹ ቤት የሚወጣ ጉብል ለሚሰራው ቤት እንኳን ምሰሶው ያርፋል ከሚባልበት ቦታ ላይ አስቀድሞ ጫር ጫር አድርጎ የእንሰት ተክል በቅድሚያ ይተክላል። ይህ ክንውን በባህሉ መሠረት የርጥብና የልምላሜ ተምሳሌት ተደርጎ ይታያል" ኦዲያኦ (1997-19)።*

እንሰት ለህብረተ-ሰቡ በምግብነት ከሚሰጠው ግልጋሎት በተጨማሪ፣ ሌሎች ጠቀሜታዎቹም እንደሚከተለው ይዘረዘራሉ ።

እነርሱም፣

- ያካባቢን የተፈጥሮ ውበት በመጠበቅ ረገድ፣ አስደሳች አካባቢ እይታን ይፈጥራል።
- ያፈር መሸርሸርን ይከላከላል።
- በተለይ ቅጠሉ እንደምንጣፍ ሆኖ ለመኝታና ጉዝጓዝ ያገለግላል።
- በተጨማሪም ለቤት ክዳንና ለገመድ መስሪያ ይውላል።
- ለከብቶች ቀለብ ይሆናል።
- ለአጥር ስራ ይጠቅማል።
- ለገመድ ማሰሪያ ይጠቅማል። በሰርግ ቤት ለተሞሸረች ልጃገረድ እንደ መጋረጃ ሆኖ ያገለግላል።[4]

በሌላ በኩል የቡና እርሻ ሌላው ዞኑን የሚያስጠራ ኢኮኖሚያዊ አለኝታ ነው። ከአጠቃላይ የዞኑ የቆዳ ስፋት 41% ወይም 57000 (ሀምሳ ሰባት ሺህ) ሄክታር መሬት የተሸፈነው በቡና ተክል ነው። በዓመት በአማካይ ከስምንት እስከ ዘጠኝ ሺ ቶን ታጥቦ የተዘጋጀና ከ14-15 ሺህ ቶን ደግሞ ያልታጠበ ቡና ከዚሁ አካባቢ ብቻ ለማዕከላዊ ገበያ ይቀርባል። በጣዕሙ ዓለም አቀፍ እውቅናን ያተረፈው የይርጋ ጨፌ ቡናም ምንጩ ጌዴኦ እንደሆነ ብርሃኑ ደያሶ የዞኑ የቡና ገበሬዎች ዩኒየን ኃላፊ ይገልፃሉ።

---

[4] ኃይሉ በየነ ኅዳር 18/1999 ዓ.ም (ቃ.መ) ዲላ

ILS LIBRARY ADDIS ABABA

በዞኑ ከእንሰትና ከቡና ተክል በተጨማሪ የተለያዩ ሰብሎችም ይበቅላሉ፡፡
ከነዚህም መካከል፡-

- ከአገዳ ሰብሎች፣-----------------------በቆሎና ማሽላ፤
- ከብርዕ ሰብሎች፣---------------------- ገብስ (በደጋና ወይና ደጋ አየር ንብረት)፤
- ከጥራጥሬ ሰብሎች፣-----------------ባቄላና አተር፤
- ከፍራፍሬ ሰብሎች፣----------------አቮካዶ፣ ማንጎ፣ ሙዝ፤
- ከሥራ ሥር ሰብሎች፣-----------ስኳር፣ድንች፣ ቦይና፣ ጎደሬና ካሳቫ የመሳሰሉት፣ ከአካባቢው የሰብል ልማት እንቅስቃሴ መካከል ሳይጠቀሱ የማይታለፉ መሆናቸውን የዞኑ ግብርና ልማት ጽ/ቤት የ1998 ዓ.ም መረጃ ያመለክታል፡፡

## 2.4 የቱሪዝም ሀብት

"ጭስ አልባው ኢንዱስትሪ" እየተባለ የሚነገርለት የቱሪዝም ሀብት፣ በአንዳንድ ያገራችን ክልሎች እየተለመደ በመሄድ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ተፈጥሮአዊ ሀብቱ ያላቸው አካባቢዎችና ክልሎችም በተወሰነ ደረጃ ገቢ እያገኙበት ነው፡፡ የጌዴኦ ዞን ከዚህ ሀብት በመጠኑ ተቋዳሽ የሚሆንባቸው የተወሰኑ ቦታዎች አሉት፡ በአገር ውስጥና በውጭ ቱሪስቶች አልፎ አልፎ ከሚጎበኙ ጥንታዊ ቅርሶችና መስህቦች የተወሰነ ገቢ እንደሚያገኝ የዞኑ ቱሪዝም ቢሮ ይገልፃል፡፡ ዞኑ በቅርስ መስህብነት ከያዛቸውና የተወሰነም ቢሆን ገቢ ከሚያስገኙለት የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

### *2.4.1. "ቱቱፈላ ትክል ድንጋዮች" Tuuttofala Stalae*

የ "ቱቱፈላ" ትክል ድንጋዮች ቅርስ፣ ከዋና ከተማዋ ዲላ በስተደቡብ በ21.2 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ በወናጎ ወረዳ በተለይ ጃንጃሞ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ የጌዴኦ ዞን ንግድ ኢንዱስትሪ መገናኛና ቱሪዝም ቢሮ የ1996 ዓ.ም መግለጫ እንደሚያመለክተው፤ ይህ ቦታ እንደ ኤሮጳውያን አቆጣጠር ከ1931-1997 ባሉት ረጅም ዓመታት 'Prof. Roger Joussamme' በተባሉ ፈረንሳዊ ተመራማሪ የሚመሩ የፈረንሳይና ኢትዮጵያውያን አርኪዎሎጂስቶች እየተቆፈረ ሲጠና የቆየ ሥፍራ ነው፡፡ በጥናቱ የተደረሰበት ውጤት የሚያመለክተው በመጀመሪያ በ8ኛውና በ9ኛው ምዕተ ዓመት እንደገና ደግሞ በ11ኛው ምዕተ ዓመት በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ማህበረሰቦች የቀብር ቦታ እንደነበረ ነው፡፡ በሥፍራውም 1000 (አንድ ሺህ) በላይ

የሆኑ የሰዎች አፅሞች፣ የተሰባበሩ የሸክላ ውጤቶች፣ የድንጋይ መሳሪያዎች፣ ከብርና ከመዳብ የተሰሩ ቀበቶዎች፣ የእጅና የእግር አምባሮች መገኘታቸው ተመልክቷል። ትክል ድንጋዮቹ በሰው ፊት መልክ የተቀረፁና በአንድ ሄክታር መሬት ላይ በቁጥር እስከ 300 (ሶስት መቶ) የሚደርሱ ለመኖራቸው መረጋገጡን መረጃው ያሳያል።

### *2.4.2. "ቱቲቲ ትክል ድንጋዮች" Tuutiti Stalae*

የ "ቱቲቲ" ትክል ድንጋዮች መስህብ የሚገኘው ከዲላ ከተማ በስተደቡብ አቅጣጫ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው። ሥፍራው በይርጋጨፌ ወረዳ በቱቲቲ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ክልል ውስጥ ይገኛል። በአካባቢው በ3 ሄክታር መሬት ላይ ከ1200 (አንድ ሺህ ሁለት መቶ) በላይ የሚሆኑና በወንድ ብልት (phallic) መልክ የተቀረፁ ድንጋዮች በብዛት ይገኙበታል። ይህ መስህብ ከ0.30 ሳንቲ ሜትር እስከ 8 ሜትር የሚደርስ ርዝመት ያላቸው ትክል ድንጋዮች የሚገኙበት መሆኑን (Gedeo Zone attractions 2003) የሚለው በራሪ ጽሑፍ ያመለክታል። የቱቲ ትክል ድንጋዮችን ከቱቱፈላ ትክል ድንጋዩች ጋር ሲነፃፀሩ የተለያዩ ቅርፆች ያሏቸው ቢሆኑም እነዚህም ያካባቢው ሰዎች የቀብር ቦታዎች ለመሆናቸው በአርኪዎሎጂስቶቹ መረጋገጣቸውን ጽሑፉ ያመለክታል።

## 2.5. ባህላዊ አስተዳደር

የአንድ ማህበረሰብ አባላት እምነታቸውን የሚመሩበት የጋራ ሥርዓት ይኖራቸዋል። ነገሮችን 'ጥሩ' ወይም 'መጥፎ'፣ ተገቢ ወይም ተገቢ ያልሆነ፣ 'አስደሳች ወይም አስከፊ' እያሉ ለመለየት የሚያስችሉ ደንቦችና እና ሥርዓቶች ሁሉ የባህሉ ገፅታዎች ናቸው።

በዚህ ጥናት ውስጥ፣ ባህላዊ የገዳ ሥርዓቱን ማየት የግድ የሚሆንበት ሁኔታ አለ። ምክንያቱም በህብረተሰቡ ማህበረ-ባህላዊ ህይወት ውስጥ ገዳ የማይገባበት ወይም የማይዳስሰው አንድም ሥፍራ የለም። በአስተዳደራዊ፣ አምልኮታዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ. ጉዳዮች ውስጥ ሁሉ ይገኛል። "የገዳ ስርዓት እንደ ፖለቲካዊ ድርጅት ሆኖ ከሥርዓተ-አምልኮ ተግባራት ጋር በቅርብ ይዛመዳል። አባ-ገዳ (Abba Gada) እና ሌሎች የገዳ ባለሥልጣናት ስለ ጦርነት እና ስለሰላም ከሌሎች ጎሳዎች ጋር በሚፈጠሩ ግንኙነቶች ወቅት ስለሚከውኗቸው ልዩ ልዩ



ILS LIBRARY

ተግባራት እየተወያዩ ይወስናሉ፡፡ ይህም የሚሆነው ጠቅላላ ጉባኤ (Ya'a[5]) ሲካሄድ ነው፡፡ ይህ ጠቅላላ ጉባኤ ደግሞ በስምንት ዓመታት ውስጥ አንድ ጊዜ የሚካሄድ ነው፡፡ የሥልጣን ሽግሽግ ለማካሄድና በባህላዊ አስተዳደሩ መዋቅሮች ላይ የሚቀመጡ ኃላፊዎች ጭምር የሚመረጡት በዚህ ስብሰባ ነው Knutson, (1967: 166)፡፡

በ1890 ዓ.ም ከዛሬ አንድ መቶ ዓመት በፊት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች፣ ጥንታዊ ጌዴኦን ጨምሮ፣ ከተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል ጋር በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት እንዲጠቃለሉ እስከተደረጉበት ጊዜ ድረስ፣ የጌዴኦ ባህላዊ አስተዳደር ለህብረተ-ሰቡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አምልኮታዊ አመራር ሲሰጥ እንደቆየ Tadesse, (2000:25) ይገልፃል፡፡

የጌዴኦ ዞን ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ኃላፊ ሆነው በሠሩባቸው ጊዜያት ወስጥ፣ በደርግ ታግዶ የነበረውን የገዳ ሥርዓት እንደገና ተመልሶ እንዲያንሰራራ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ረገድ የማይናቅ ድርሻ እንዳበረከቱ የሚነገርላቸው አቶ ጥላሁን ኢቢዶ፣ ከ18/12/98 እስከ 20/12/98 ዓ.ም. ድረስ በዲላ ከተማ ትምህርት ቢሮ በተገናኘንባቸው ጊዜያት ስለ ባህላዊ አስተዳደሩ ታሪካዊ አጀማመር፣ ስለምርጫ መስፈርቱ፣እንዲሁም ስለ ዋና ዋና ተግባራቱ የሚያውቁትን በፅሑፍና በቃል እንደሚከተለው ገልፀውልኛል ፡፡

> *በጌዴኦ ህብረተሰብ ባህላዊ አስተዳደር አፈ-ታሪክ መሰረት፣ ጥንታዊው የጎሳሎ አስተዳደር በህዝብ አመጽ ከሥልጣን ከተወገደ ወዲህ፣የገዳ-ሥርዓት ተተካ፡፡ የተተካው ይህ የገዳ አስተዳደር ሥርዓት በህዝቡ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ሆኖ የቢልባና ባሌ (Bilbanaa Baalle) ከበላያ (Belayya) ሶንጎ፣ የደላና ባሌ (Dellanna Baalle) ከሄባና ሶንጎ፣ሆነው ከሁለቱም ወገን በተወሰነ ቁጥር የሚወከሉ አባላት ያሏቸው ሁለት ህዝባዊ ምክር ቤቶች ተመሰረቱ፡፡ እነዚህም በየስምንት ዓመታት ጊዜያት ውስጥ በመፈራረቅ ጌዴኦን የሚያስተዳድሩ ናቸው፡፡ አንዱ ምክር ቤት ለስምንት ዓመታት በስልጣን ቆይቶ፣ለቀጣዩ ስምንት ዓመታት ሌላው እንዲያስተዳድርተራውን ይለቅለታል፡፡ ሁለቱ ምክር ቤቶች በአደረጃጀት ረገድ ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ የስልጣን ጊዜያቸውም በስርዓቱ ከተወሰነው ጊዜ ውጭ ሳይራዘም ወይም ሳያጥር፣ ተራቸውን እየጠበቁ ይፈራረቃሉ፡፡[6]*

በጌዴኦ የገዳ (Gada ሥርዓት ከጥንት ጀምሮ፣ ለህብረተሰቡ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ አምልኮታዊ አመራር ሲሰጥ ረጅም ዘመናትን አስቆጥሯል፡፡ ይሁን እንጂ የኋላ ኋላ ፖለቲካዊ አመራሩን ማዕከላዊ መንግስት ቢይዝበትም እስከዛሬ ድረስ ግጭቶች በህብረተሰቡ መካከል እንዳይከሰቱ

---

[5] Ya'a- በጌዴኦ ባህላዊ አስተዳደር ውስጥ እጅግ ጥንታዊና ታሪካዊ የሆነ ጉባኤ ነው፡፡ ጥንት የጌዴኦ ብሔረሰብ ሥርዓተ-አምልኮ የተደነገገበት፣ 'Woyyo' ከሰባቱ የጌዴኦ ጎሳዎች መካከል ተመርጠው ለልዩ ልዩ በሽታዎች መድኃኒት እንዲሰጡ የተመረቁበት ማንኛውም ህዝባዊ ጉዳዮች የሚመከሩበት ከጥንታዊ የ 'Gosallo' አንዱአዊ ሥርዓት ወደ 'Gada' ሥርዓት ለመሸጋገር የመከረበት ነው፡፡
[6] ጥላሁን ኢቢዶ ነሀሴ 18/98 ዲላ (ቃ.መ.)

ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ አጋጣሚ ሆኖ ቢከሰቱም እንኳን ግጭቶቹን በራሱ ደንብና ሥርዓት ይፈታቸዋል፡፡ በተጨሪም ህብረተ-ሰቡ እርስ በርሱ እንዲከባበር፣ ሰላም እንዲሰፍን፣ የህብረተሰቡ የእምነት ነፃነት እንዲከበር፣ የሚያግዙ እሴቶች እንደተጠበቁ እንዲቆዩ አድርጓል፡፡ ዛሬም ይህንኑ ተግባር በማከናወን ላይ እንደሚገኝ አቶ ተሰማ ጅባና ይገልፃሉ፡፡

## *2.5.1 የአባ-ገዳ 'Abba Gada' ምርጫ መስፈርቶች*

በጌዴኦ ማህበረ ባህላዊ አስተዳደር መዋቅር፣ ከፍተኛው የስልጣን ቦታ የሚሰጠው አባገዳ ሆኖ ለሚመረጠው ሰው ነው፡፡ ዘመናቸው ደርሶ ስልጣን ለመያዝ ከሚዘጋጁ ራባ (Raaba) ወይም ዕጩ መካከል፣ ለአባገዳ ደረጃ የሚመጥን አንድ ሰው ይመረጣል፡፡ እርሱም የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

ሀ. ምንም ዓይነት ጠባሳ በየትኛውም የአካል ክፍሉ ላይ የሌለበት፣

ለ. ትክለ-አካላቱ ዓይን፣ እጅ፣ እግር፣ ጣቶችን ጨምሮ አንድም ጉድለት የሌለበት፣

ሐ. በሚኖርበት አካባቢ በህብረተሰቡ ዘንድ፣ በብቃቱ የተመሰገነ ወይም ሥልጣኑ ይገባዋል ተብሎ የሚታመንበት፣

መ. የገዳ ሥርዓቱ የሚጠይቀውን ማህበራዊና ባህላዊ ክንውኖችን ሁሉ አሟልቶ ለመሥራት ቃል የሚገባ፣

ሠ. በሰማይ አምላክ (Mageno) የሚያምን፣

ረ. ቃለ-መሐላ ለመፈፀሙ ቡልቡሎ 'bulbulo' (የማር ብጥብጥ) በአደባባይ ህዝብ በተሰበሰበበት የቀመሰ፤ የሚሉት የመመዘኛ መስፈርቶች ናቸው፡፡ እነዚህ መስፈርቶች በመዋቅሩ ውስጥ በተዋረድ ለሚመረጡ ሌሎች አባላት ጭምር የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ዕጩዎች ቀጥሎ ለተዘረዘሩት የሥልጣን ደረጃዎች ተወዳድረው በህዝቡ ይመረጣሉ፡፡

**በጌዴኦ የገዳ ሥርዓት ሥልጣን አደረጃጀት**

Abbaa Gada ................................(አባ ገዳ)የሥርዓቱ መሪ

Ja'laaba (ጀላባ) ..........................የአባገዳ ምክትል

Suppottee Roga (ሱፖቲሮጋ) ......የሱፓ ሮጋ

Dhiibeta Roga(ዲበታ ሮጋ)...........የዲበታ ሮጋ

Rhiikatta Roga(ሪቀታ ሮጋ) ..........የሪቀታ ሮጋ

Jalqaba(ጀልቀባ)............................የሮጋ ምክትል እነዚህ

በድምሩ ሶስት ናቸው፡፡

Hayyichcha(ሐይቻ) ......................የሶንጎ መሪ

Murra(ሙራ)..................................ከበላይ የሚተላለፉ ትዛዛትንና

መመሪያዎችን ለህዝቡ ጆሮ

የሚያደርስ/ተላላኪ/ ማለት ነው፡፡


ሲሉ አቶ ጥላሁን ጨምረው ይገልፃሉ ፡፡



የዲላ ወረዳ ምስረታ በዓል ሲካሄድ ሥርዓቱ የተጀመረው በአባገዳ ምርቃት ነው ለአካባቢው ሰላም ፣ጤንነት፣ ብልፅግና፣ አንድነት ተመኝተው በመቀጠል ክፋት፣ ተንኮል፣ ረሀብ፣ ጦርነት ፈጣሪ ከእኛ ያርቅልን (Mageno nuurra Fegiesse) ሲሉ ሕዝቡም እየተከታተለ አሜን ይል ነበር ............ 20/12/98 ዲላ ዙሪያ ጌዴኦ ዞን

ከላይ በቀረበው አደረጃጀት ውስጥ እንደሚታየው፣ በእያንዳንዱ የስልጣን ደረጃ ላይ የሚገኙ ተመራጮች ኃላፊነትና የሥራ ድርሻ ተመልክቷል፡፡ የባህላዊ አስተዳደሩ መዋቅራዊ አደረጃጀት ከዚህ በታች የተመለከተውን ቅርፅ የያዘ ነው፡፡

የገዳ “Gada” አደረጃጀት መዋቅር




ምንጭ፡- የይርጋጨፌ ወረዳ አጠቃላይ ገጽታ (1992፤20)

### *2.5.2 የአባ-ገዳ ‘Abba Gada’ ዋና ዋና ተግባራት፡-*

Abba Gada ሆኖ ሥልጣን ለመያዝ የሚመረጠው ሰው፣ ከተጠቀሱት መስፈርቶች በተጨማሪ ከማናቸውም ኃጢያት የነፃ መሆን አለበት ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ሰው በተሰጠው መንፈሳዊ ኃይል ርግማኑ ውድቀትን፣ ምርቃኑ ደግሞ ውጤትን፣ ያስከትላል ተብሎ ስለሚታመን በሚሰጠው አመራር በቀላሉ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኛል ተብሎ ይታመናል Tadese,(2000:21)፡፡

ከአባ-ገዳ ‹‹Abba Gada›› ተግባራት መካከል፣

- የህብረተሰቡን የገዳ ስርዓት፣ ክንውንና ጠቅላላ ጉባዔውን መምራት፤
- በህብረተሰቡ ዘንድ ግጭት እንዳይፈጠር፣ ሰላም እንዲሰፍን፣ አዘውትሮ ‘Mageno’ን መለመን፣
- በህብረተሰቡ አምልኮታዊ ሥፍራዎች ሁሉ በመገኘት ባህላዊ ሥርዓቱን መምራት፣
- በየእርከን ደረጃው የሽግግር ሥርዓቶች (initiations) መምራት፣

አባገዳ ለጦርነት ወደ ዘመቻ አይሄድም፡፡ ነገር ግን ዘመቻው በቦባሳ 'bobbaasa'[7] (አዝማች) እንዲመራ ያደርጋል፡፡ ሽነቻ 'Cenecha' (ህዝባዊ ጦር) አስመርጦ መርቆ ወደ ዘመቻ ይሸኛል፡፡ በድል ሲመለሱም በሥርዓት "እንኳን ደህና መጣችሁ" በማለት በክብር መቀበል፣ የሚሉት ከተግባራቱ ውስጥ የሚጠቀሱ ዋና ዋናዎቹ መሆናቸው ይጠቀሳል፡፡

የጌዴኦን ባህላዊ ሥርዓት ዛሬም ድረስ እየመራ ስላለው ስለዚሁ ባህላዊ ተቋም ቀደምት እንቅስቃሴ አስተያየታቸውን የሰጡት ሌላው አዛውንት ደግሞ፣

> *በመጀመሪያ በአካባቢው ዘመናዊ አስተዳደር ባልነበረበት ወቅት የጌዴኦ ህብረተሰብ ይተዳደር የነበረው በGeda (ገዳ) ሥርዓት ነበር፡፡ ከጊዜ በኋላ የፖለቲካ ሥልጣኑን በማዕከላዊ መንግስት ቢወሰድበትም እስከ ዛሬ ድረስ ባህላዊ አስተዳደሩን ይዞ እየመራ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፣ ህብረተ-ሰቡን ልማዳዊ ሥርዓቶች በማስጠበቅ ረገድ ለምሳሌ ግጭቶችን እዚያው በአካባቢው በመፍታት፣ ሰላምን በማስፈን፣ አባዊ የእምነት ሥርዓትን ጠብቆ በመንቀሳቀስ፣ አሁንም ዘመናዊውን አስተዳደር የሚያግዝ ሰፊ ህዝባዊ መሠረት ያለው ሥርዓት እንደሆነ ነው፡፡[8]*
>
> *ጥንት ሐርሱ፣ሐዋጣ፣ገናሌ ከሚባሉ ሥፍራዎች ተነስተው ዛሬ ሀሮ-ወላቡ ወደምትባለው ደጋማ አካባቢ ዘልቀው ይኖሩ የነበሩ ሦስት ወንድማማቾች ነበሩ፡፡ እነርሱም ደራሶ፣ኡራጎና በሩ ይባላሉ፡፡ደራሶ የሁሉም ታላቅ (አንጋፋ) ነው፡፡ ከጊዜ በኋላ በእርጅና ምክንያት እየተዳከመ የመጣው አባታቸው አንድ ቀን ለኑዛዜ ሲሰበስቧቸው፤ በመካከላቸው በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት ሁሉም ወደ ተለያየ አቅጣጫ ተበታተኑ፡፡ ይሁን እንጂ የሁሉም አንጋፋ የሆነው ደረሶ፣ በሄደበት ቦታ ሁለት ሚስቶች በየተራ አግብቶ ባጠቃላይ ሰባት ልጆች ወለደ፡፡ ከመጀመሪያ ሚስቱ የተወለዱት አራት ልጆች ደረሻ፣ ዳቦኣ፣ ጕርጕርሻ፣ ሐኑማ ሲሆኑ Shole Baxxie (ሾሌ ባጤ) አራት ቤት ይባላሉ፡፡ ከሁለተኛ ሚስት የተወለዱት ሒምባኣ፣ሎጐዳና ባኮሮ የሚባሉ ሲሆኑ Sassie baxxie (ሰሴ ባጤ) ሶስት ቤት ይባላሉ፡፡ እነዚህ ሰባት ልጆች እየተራቡ መጥተው የዛሬውን የጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ማስገኘት ቻሉ (ኦዳያኦ 1997:41)፡፡ ይሁን እንጂ ደራሶ አርጅቶ ከመሞቱ በፊት የጌዴኦን መሬት ለእያንዳንዱ ልጅ መኖሪያ እንዲሆን አከፋፍሎ በመስጠቱ፣ እያንዳንዱ ጎሳ የራሱ መኖሪያ ክልል አለው፡፡ የማንኛውም ጎሳ አባላት የሆኑ ግለሰቦች ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል በነፃነት መንቀሳቀስ ይችላሉ ሲል በጥናቱ ገልፆኣል፡፡ Dagne,(1995:27).*

ስለ ጌዴኦ አካባቢያዊና አስተዳደራዊ ገፅታ፣ እንዲሁም ስለባህላዊ አስተዳደሩ ይህን ያህል ካየን፣ ቀጥለን ደግሞ ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የልዩ ልዩ ጽሑፎች ክለሳዎችን ወደ መቃኘት እንሸጋገር፡፡

---

[7] በጌዴኦ ማህበረ-ባህላዊ አስተዳደር ደንብ ህዝባዊ ጦር (Cenecha) ወደ ዘመቻ ሲንቀሳቀስ የሚመራው በአዝማች (bobbaasa) አማካይነት ነው በዚህ ጊዜ ፋጂ (faajia) "ጥሩንባ" እየተነፋ በዝማሬና በክብር ይሸኛል አቀባበሉም ተመሳሳይ ሂደትን የተከተለ ነው፡፡

[8] ቀቀቦ ሾታ ሰኔ 17/1999ዓ.ም ምችሌ ሲሶታ በመኖሪያ ቤታቸው የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

## 3.0 ክለሳ ድርሳን

የምርምር ሥራዎች ሲካሄዱ፣ የተወሰኑ ግንዛቤዎች ይገኙ ዘንድ ክለሳ ማድረግ የተለመደ አሰራር ነው። በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸው ጽሑፎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተቃኝተዋል። በተለይም፣ ስለ ዝርው ቃል ምንነት፣ ገለፃዎችን (definitions) ስለተረኮች ዓይነቶች (Tale-types) ስለ መዋቅሮቻቸው (structures)፣ ማህበራዊ ግልጋሎታቸው (functions) እንዲሁም፣ ስለታዳሚ (audience)፣ እና መቼት (setting) በሚሉ በተወሰኑ ፅንሰ-ሃሳቦች ላይ በመስኩ ምሁራን የተሰጡ አስተያየቶችን እንከልሳለን።

## 3.1 ዝርው ቃል ተረክ ምንድነው?

ስለዝርው ቃል ተረኮች ምንነት፣ የተለያዩ ምሁራንና ተመራማሪዎች በየጊዜው የተለያዩ አስተያየቶችንና ገለፃዎችን ይሰጣሉ። ለዚህ ጉዳይ ሁለት ጉልህ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። የመጀመሪያው አጥኚዎችና ተመራማሪዎች ራሱን ዘርፉን የሚመለከቱባቸው የትኩረት አቅጣጫዎች የሚለያዩ መሆናቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ፣ እነዚሁ ተመራማሪዎችና አጥኚዎች ከተነሱባቸው ዓላማዎች አንፃር ግቦቻቸውም እንዲሁ የሚለያዩ መሆናቸው ነው። Linda Degh, (1969:55) ትገልፃለች።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ቃል ተረኮችን ሰብስቦ በማጥናት ፋና ወጊ የሆኑት Jacob Grimm እና Wilhelm Grimm (1812-1818) የተባሉ ሁለት ጀርመናዊያን ወንድማማቾች ናቸው።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ አካዳሚያዊ የቃል ተረኮች ጥናት ቀስ በቀስ በየአገሩ እየተለመደና እየሰፋ በመሄዱ እነሆ፣ ዛሬ ከሚገኝበት እጅግ የተወሳሰበ የጥናት መስክ ከመሆን ደረጃ ላይ እንደደረሰ እንመለከታለን ።

እንደ ግሪሞችና ተከታዮቻቸው አስተሳሰብ ቃል ተረኮች የጥንታዊያኑ ኢንዶ-ጀርመናውያን ሚቶሎጂ ቅሪቶች ናቸው። ስለ ጀግንነት የሚተርቱም ሆኑ፣ ሌሎች ምትሃታዊ ተረቶች የተገኙት ከነዚሁ ህንድ-ጀርመናውያን ነው። ሆኖም እነዚህ ተረኮች በዚህ ሁኔታ ተገኝተው እዚያው ተወስነው አልቀሩም። ይልቁንም ሰዎች ከቦታ ቦታ የሚያደርጉት ፍልሰት፣ በርስ በርስ የባህል ግንኙነት ሳቢያ ወደ ሌላው ህብረተ-ሰብ ውስጥ ዘልቀው ለመግባባትና ዓለምን ማዳረስ ችለዋል Linda De'gh, (1969:58)።

በሌላ በኩል፣ ታዋቂው ፎክሎረኛ Stith Thompson 'ተረት' (The Folk Tale) በሚለው መጽሐፍ መግቢያ ላይ ስለ ዝርው ቃል ተረክ ምንነት ሲገልጽ፣

> *Although the term "Folktale" is often used in English to refer to the "Household Tale" or "Fairy Ttale" (The German M'archen), such as "Cinderella" or "Snow White", it is also legitimately employed in a much broader sense to include all forms of Prose Narratives , written or oral, which have come to be handed through the years. Thompson, (1946:4)*

በማለት አስፍሯል።

ከጥቅሱ እንደምንመለከተው "ፎክቴል" የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ "የቤት ውስጥ ተረቶች" ወይም "የአስማት ተረቶችን" (የጀርመኑን ማርሼ) እንደ "ሲንደሬላ" ወይም "ስኖው ኋይት" የመሳሰሉት ተረቶች መጠሪያ ነው። ነገር ግን ከዚህ ሰፋ ባለ እሳቤ ተወስዶ፣ ከጥንት ጀምሮ ሲያያዙ ለመጡ፣ የተፃፉም ይሁኑ ያልተፃፉ ዝርው ተረኮችን፣ በሙሉ የሚያጠቃልል ስያሜ እንደሆነ አመልክቷል።

በአፍሪካ ሥነ ቃል ጥናት አዘውትሮ ስሟ የሚጠቀሰው Ruth Finnegan, ከዛሬ አርባ ዓመታት በፊት፣ "የሊምባ ህብረተ-ሰብ ተረቶች ትረታ" (Limba stories and story telling) በሚል ርዕስ ምርምር ስታካሂድ ዝርው ተረክ ከሚለው ይልቅ 'Story' የሚለውን ስያሜ ተጠቅማ ነበር። ኋላ ደግሞ እንደገና በ1970 እ.ኤ.አ "ቃላዊ ሥነ-ጽሑፍ በአፍሪካ" (Oral literature in Africa) በሚለው ሥራዋ ውስጥ ለተመሳሳይ እሳቤ የተጠቀመችው ቃል *"folktale"* የሚለውን ነበር።

> *Any type of oral prose narrative from whatever society could be, and was referred to as "folktale" and thus treated as a kind of "survival" from an earlier and even more primitive state………… that all "folktales" (and thus all oral narratives) have been handed down through generations from the remote past, most probably in a word perfect form. Finnegan, (1970:3180)*

ከላይ በጥቅሱ ውስጥ እንደተመለከተው በማንኛውም ህብረተ-ሰብ ውስጥ የሚገኝ የትኛውም ዝርው ተረክ ይታወቅ የነበረው "ፎክቴል" በሚል መጠሪያ ነው። ተረክ ትዝታው የቅርብ ጊዜም ይሁን የጥንት፣ ህልውናው የሚጠበቀው በህብረተሰቡ ውስጥ ባለው ክዋኔና ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚደረገው ቃላዊ ተስተላልፎ ነው ብላለች። በሌላ ወገን አሁንም፣ ዝርው ተረክ (Prose Narrative) የሚለውን ስያሜ አስመልክቶ የተሰጠውን ገለፃ ስንመለከት፣

> *Prose narrative, I propose is an appropriate term for the wide spread and important category of verbal art which include myths, legends and folktales. These three forms are related to each other, in that they are narratives in prose, and this fact distinguishes them from proverbs, riddles, ballads, poems, tongue twisters and other forms of verbal art on the basic of strictly formal characteristics. Bascom, (1996:3)*

ሲ.ል. *Bascom,* ሃሳቡን አስፍሯል። በርሱ ገለፃ መሠረት፣ እነዚህ ሰፊ ስርጭት ያላቸውን ሚቶች፣ ሌጀንዶችና ተረኮች በአንድ አካቶ ለሚይዝ ወሳኝ ምደባ "ዝርው ተረክ ብዬ ያቀረብኩት ስያሜ ተገቢነት ያለው ነው። የተጠቀሱት ሦስቱም ዘርፎች ቢሆኑ በዝርው ቅርጽ መገኘታቸው በራሱ፣ የርስ በርስ ዝምድናቸውን የሚያሳይ ነው። በዚህም የተነሳ ከሌሎች የሥነ-ቃል ቅርፆች ማለትም፣ ከምሳሌያዊ ንግግር፣ ከእንቆቅልሾች፣ ባላዶች፣ ግጥሞች፣ ውረፋዎች እና ከመሳሰሉ ቃላዊ ጥበባት ይለያሉ፤ በማለት የበኩሉን አስተያየት ሰጥቷል።

ስለ እያንዳንዱ ፅንስ ሃሳብም ከዘሁ ጋር አያይዞ ሲገልፅ፣ ሚት (Myth)፣ ከሃይማኖትና ከእምነት ጋር የተያያዙ ይዘቶች ያሏቸው ተረኮች ናቸው። ልዕለ-ሰባዊ ሃይል (Supernatural) ያላቸው ገፀ-ባህርያት፣ የሚሳተፉባቸው በጣም ጥንታዊ የሆኑ ትረካዎችን ከወደፊት ተፈፃሚነታቸው አንፃር በማያያዝ የሚተረክ ነው። አፈ-ታሪክ (Llegend) ከፊል ፈጠራዊና ከፊል ታሪክ ቀመስ የሆኑ፣ በአርኣያነታቸው ሊጠቀሱ የሚችሉ ጀግና (Hero) ገፀ-ባህርያት የሚሳተፉበት ነው። በይዘት ረገድ ስንመለከተው፣ የአሁኑን ወይም የቅርቡን ጊዜ ከዱሮው ጋር በማያያዝ የሚያቀርብ የትረካ ዓይነት ነው። ይህም በመሆኑ ከሚት ይልቅ የአፈ-ታሪክ ዘመኑ በአንፃራዊነት የቀረበ ነው።

በመጨረሻ ተረቶች (Folktales) ከሚነገሩበት ዓላማ አኳያ ሲታዩ ስነምግባርንና በጎ ነገርን ለማስተማር፣ የየጊዜውንና የየማህበረሰቡን ጉዳዮችና ልማዶች መሠረት አድርገው የሚፈጠሩና የሚተረቱ ናቸው። አስቀድሞ ከተጠቀሱት ከሚትና ከሌጀንድ ይልቅ፣ ከህብረተሰቡ ዕለት ተዕለት ኑሮና ገጠመኝ እንዲሁም ባህላዊ ሥርዓት ጋር ሰፋ ያለ ቁርኝት ያላቸው መሆናቸውን ሰፋ አድርጎ ያብራራል።

## 3.2 የተረክ ዓይነቶች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ውስጥ ለማየት የምንሞክረው የተወሰኑ ዝርው ቃል ተረኮችን አይነቶችን ለአብነት ያህል በመጠቃቀስ ለማመልከት ያህል እንጂ፣ ስለዝርው ቃል ተረኮች በሙሉ ለመተንተን ድፍረቱ ኖሮን አይደለም።

በዚህ የጥናት መስክ በተደጋጋሚ ስሙ የሚነሳው፣ ፎክሎረኛው Stith Thompson፣ "The Folk Tale" በሚለው መጽሐፉ ውስጥ፣ 1946 (415-487) ውስጥ ስለተረክ ዓይነቶች፣ ሰፋ ያለ

ዝርዝሮችንና ገለፃዎችን አቅርቧል፡፡ይሁን እንጂ ዋና ዋና የምንላቸውንና ከርዕሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ብቻ እያነሳን መጠነኛ ገለፃ በየአንዳንዱ ላይ ለማቅረብ እንሞክራለን፡፡

ዝርው ቃል ተረኮችን በየፈርጅ በየፈርጃቸው እየለዩ ማጥናት የተመራማሪዎች የብዙ ጊዜ ጥረት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ተሳክቶለት ባይዘልቅለትም የመጀመሪያ ሙከራ የተደረገው በ1864 J.G. Von Hahn በተባለ ሰው አማካይነት ነበር፡፡ ከእርሱም በኋላ እንዲሁ በትረካ ሂደት ውስጥ ቁልፍቃላት (catch words) እየተጠቀሙ ተረኮችን የመሰየም እንቅስቃሴ ይታይ የነበረው Joseph Jacobs በተባለ ሰው አማካይነት ቢሆንም ዳግመኛ ይህም እንደበፊቱ አለመሳካቱን ቶምሰን ይገልፃል፡፡

ከተደጋጋሚ ሙከራዎች በኋላ፣እ.ኤ.አ. በ1923 ፊንላንዳዊው 'Finnish', Antti Aarne፣ የተባለ ፎክሎረኛ፣ 'ka'arle Krohn'; 'Oskar Hackman', 'Axel Olrik', 'Johannes Bolte' እና 'C.W.Von Sydow' ከተባሉ ምሁራን ባገኘው ርዳታና ምክር ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳካ የተረክ ዓይቶች (The Type of the Folk-Tale) እየለየ በማውጣት ማሳየት ችሎአል፡፡ ሆኖም የዚህ ሰው ሥራ ግን ታትሞ የወጣው እርሱ ከሞተ ከአምስት ዓመታት በኋላ ነበር፡፡ Aarne 'ዓይነት' (type) የሚለውን ፅንሰ-ሃሳብ ደግሞ፣ Thompson

*A type is a traditional tale that has an independent existence. It may be told as a complete narrative and does not depend for its meaning on any other tale. Thompson, (1946:415)*

በማለት ይገልፀዋል፡፡

በጥቅሱ የሰፈረው ሃሳብ እንደሚያመለክተው 'ዓይነት' የሚባለው አንድ ተረክ በትርጉምም ሆነ በትረካ፣ ከሌላ ተረክ ወስዶ ወደራሱ መጨመር ሳያስፈልገውና ራሱን ችሎ የሚነገር/የሚቀርብ ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ የ Aarne 'Type Index' እጅግ በርካታ ቁጥር ለነበራቸው (በወቅቱ የአውሮጳና የህንድ) ቃል ተረኮች ዓይነቶችን ለይቶ ለማሳየት በቀላሉ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል አልነበረም፡፡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ 'Thompson' ከርሱ ቀደም ሲል 'Aarne' በሄደበት አቅጣጫ ተከትሎ ጠለቅ ያለ ተጨማሪ ጥናት አካሄዷል፡፡ እርሱም Aarne ያልደረሰበትን አዲስ ስልት አገኘ፡፡ይህም በቃል ተረኮች መካከል ተመሳስሎና ልዩነቶችን በቀላሉ እየለዩ በአይነት በአይነታቸው ለማስቀመጥ የሚያስችል ሞቲፍ ኢንዴክስ (Motif-Index) የሚባል ነበር፡፡ ይህ ስልት ድርጊትን (Action)፣ ገፀ-ባርያትን (Characters)፣ የትረካ አጋጣሚን (Narrative incidents)

መሰረት ያደረገ አካሄድ ነው፡፡ Thompson በ1936 እ.ኤ.አ በዚህ መንገድ ተጠቅሞ፣ ዝርው ተረኮችን ከፋፍሎና መድቦ አሳይቷል፡፡ ይህ ስልት በወቅቱ ሁሉንም የተረክ ዓይነቶችን በቀላሉ ከፋፍሎ በየምድብ በየምድባቸው ለማሳየት አገልግሏል፡፡

የሁለቱ ምሁራን ጥምር ሥራ በአንድነት "Aarne-Thompson Types of the Folk-Tale" በሚል መዘጋጀቱ እነሆ እስከዛሬ ድረስ ዝርው ቃል ተረኮችን ለማጥናት በሚነሱ ተመራማሪዎች ሁሉ ሳይጠቀስ የማይታለፍ ሆኗል፡፡ በ Thompson የተረክ ዓይነቶች መዘርዝር 'Index of Tale-Types' ገፅ 481-487 ውስጥ እንደተመለከተው፣ እንስሴ ተረኮች (Animal Tales)፣ ተራ ተረኮች (Ordinary folktales)፣ ፌዝና ቀልዶች (Jokes and Anecdotes) ተብለው በሦስት ዋና ዋና ምድቦች ተከፍለዋል፡፡ በእያንዳንዱ ዋና ምድብ ስር ተዋረዱን ተከትለው የተቀመጡ ንዑሳን ዝርዝሮችንም አስቀምጧል፡፡ በእያንዳንዱ ምድብ ስር ስለሚገኙ ቃልተረኮች ይዘት የተወሰነ ግንዛቤ ይኖረን ዘንድ፤ ከዚህ በታች ባጭር ባጭሩ እንመልከታቸው፤

## I. እንስሴ ተረኮች

በዚህ ምድብ ስር የሚገኙ ቃል ተረኮች ፣ አንበሳ፣ ጅብ፣ ተኩላ፣ ቀበሮ፣...ወ.ዘ.ተ. ስለመሳሰሉ የዱር አራዊት ባህርያት የሚገልፁ፣እንዲሁም ውሻና ቀበሮ፣ ድመትና አይጥ፣ አንበሳና ፈረስ፣ ተኩላና በግ......የመሳሰሉ እንሰሳትና አራዊት ገፀ-ባህርያት፣ ባላጋራ ሆነው የሚፋለሙባቸው ናቸው፡፡

በሌላ ንዑስ ምድብ ደግሞ ገፀ ባህርያቱ ሰውና ጅብ፣ ሰውና ዘንዶ፣ ቀበሮና ሰው የሚሳተፉባቸው ሲሆኑ፣ ከእንሰሳትም እንዲሁ ውሻ፣ ዶሮ፣ ፍየል፣ በግ፣ ዳክዬ፣ ከአዕዋፍ ወፎች፣ ዳክዬዎች፣ ርግቦች፣ ኩኩ መለኮቴ......ወ.ዘ.ተ. ከአሦችም እንዲሁ ራሳቸው አሦችና ሌሎች እንሰሳት ጎራ ለይተው የሚፋለሙባቸው ዝርው ቃልተረኮች ይገኙባቸዋል፡፡

## II. ተራ ተረኮች

በዚህ ምድብ ስር ሦስት ንዑሳን ዝርዝሮች የሚገኙ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ንዑስ ምድብ ምትሃታዊ ተረኮች (Tales of Magic) የሚባሉትን ስንመለከት፣ ገፀ-ባህርያቱ ልዕለ-ሰባዊ ኃይል ያላቸው ጀግኖች (Heros) በመሆን ተቀናቃኞቻቸውን 'Adversaries' ያለምንም ፍርሃት ፊት ለፊት የሚፋለሙ ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ ተረኮቹ፣ እጅግ የረቀቀ ብልሃትንና ዘዴኛነትን የሚጠይቁ

ስልቶችን፣ ለምሳሌ ከአንበሳ ቅንድብ ፀጉር ነጭቶ ማምጣት፣ በዘንዶ ከመበላት አደጋ ማምለጥን፣ በርካታ የጠላት ሠራዊትን ፊት ለፊት ገጥሞ ድል መንሳት... ወዘተ የመሳሰሉ ግዳጆችን የሚፈጽሙ ገፀ-ባህርያት የሚገኙባቸው የተረክ ዓይነቶች ናቸው።

በሁለተኛው ንዑስ ምድብ የሚገኙት ሃይማኖታዊ ተረኮች ናቸው። የእነዚህ ተረኮች ይዘቶች ስለይቅር ባይነትና ጭካኔ፣ ስለጽድቅና ኩነኔ፣ ስለ ሠናይና እኩይ ምግባራት፣ ስለገነትና ስለሲኦል ኑሮ ወዘተ. ምንነትና ልዩነቶቻቸውንም በንፅፅር እያደረጉ በማቅረብ የሚተርኩ ተረኮችን ያካትታሉ።

በሦስተኛው ንዑስ ምድብ የሚገኙት ኖቬላ (Novella Tales) ተረኮች ናቸው። እነዚህ ተረኮች ጀግነትን፣ ደፋርነትን በቃል መፅናትን፣ ጥበበኝነትን፣ ዘዴኝነትን፣ የዋህነትን፣ ፍቅርን ወዘተ. ዋነኛ ጭብጦቻቸው በማድረግ ለታዳሚዎች የሚቀርቡ የተረክ ዓይነቶች ናቸው።

III. ፌዝና ቀልዶች

በዚህ ምድብ የሚገኙት ደግሞ ቀልድ አዘል ተረቶች (Stories) ሲሆኑ፣ እነርሱም ንዝህላልነትን፣ መሞኘትና ማሞኘትን፣ ሀብትና ድህነትን፣ ስንፋናና፣ የዋህነትን፣ የመሳሰሉ ሰዋዊ ባህርያትን ለመግለጽ የሚያገለግሉ የተረክ ዓይነቶች እንደሆኑ Thompson አመልክቷል ።

## 3.3 የተረክ መዋቅር

የተረኮችን ውስጣዊ አወቃቀር (ቅርፅ) በመመርመርና በዛም ላይ ተመስርቶ ስለምንነታቸው ንድፈ ሃሳባዊ ትንታኔ የመስጠት እንቅስቃሴ የተጀመረው ከ1960ዎቹ ቀደም ባሉት ጊዜያት ውስጥ እንደሆነ Dorson (1971:34) ይገልፃል። አያይዞም በዚህ ዙሪያ የመጀመሪያ ሙከራ ያደረገው ጀርመናዊው 'Andre Jolles' "Einfache Formen" (1930) በሚለው መጽሐፉ እንደሆነ ይገልፃል። ከእርሱ በመቀጠል 'Lord Raglan' "The Hero" (1936) በሚለው መጽሐፍ ውስጥ የትረካ ሁነቶችን (episodes) በተራ ቅደም ተከትል አንደኛ ስለ----- ሁለተኛ፣ ስለ--- ---ሶስተኛ ስለ----እያለ፣ በማውጣት በተረኩ ውስጥ የሚገኙ ሁነቶችን በየተራ ለማሳየት ሞክሯል።
እዚህ ላይ መታወስ ያለበት ነገር ቢኖር፣ በአንድ ተረክ ውስጥ የሚገኙ ሁነቶች ብዛት የሚዘረዘረው፣በተረኩ ርዝመትና ማነስ ላይ በመወሰን ነው። ተረኩ ትንሽ ከሆነ የሚዘረዘሩት ሁነቶችም ቁጥር አነስተኛ ይሆናል። ተረኩ ረጂም ከሆነም በዚያው መጠን የሚወጡት

ዝርዝሮች ይበዛሉ። ይሁን እንጂ፣ ከነዚህ ሁለቱ ሰዎች ሥራዎች የተሻለ የሚባለው ሩሲያዊው Vladmir Propp, (1958)በፃፈው "The Morphology of Folktale" በሚለው መጽሐፍ ውስጥ የተገለፀው ሥራ ነው። እርሱም በአንድ ተረክ ላይ 'ገቢራዊ መዋቅራዊ ትንታኔ' (applied structural analysis) በማካሄድ የተረኩን ውስጣዊ አወቃቀር በቀላሉ ማሳየት እንደሚቻል ይገልፃል። የእርሱን ሥራ ከ 'Raglan' የሚለየው ነገር የተረኮችን ውስጣዊ አወቃቀር ለማሳየት፣ ተግባር (Function) መሠረት አድርጎ ማቅረቡ ነው። ይኸውም በአንድ ተረክ ውስጥ የሚገኙትን ገፀ-ባህርያት፣ ጀግና (Hero) እና መሰሪ (Villain) በማለት ከከፋፈለ በኋላ፣ የእያንዳንዱን ገፀ-ባህርያት የድርጊት ተሳትፎ ለየብቻ ነጣጥሎ በቅደም ተከትል በቁጥር በማስቀመጥ የተረኩን መዋቅራዊ አደረጃጀት በቀላሉ ሊያመለክት ችሎአል። በዚህ ሥራውም እንደ Alan Dundes የመሳሰሉ ታዋቂ ፎክሎረኞችን ድጋፍ አግኝቷል።

ተረኮች በሙሉ ማለት እንችላለን የራሳቸው የሆነ ያጀማመር ሥርዓት (መግቢያ)፣ እና በመጨረሻም ደግሞ፣ ማብቂያ (መደምደሚያ) መያዛቸው በራሱ የተግባቦታዊ ፋይዳው አካል እንደሆነ Ben Amos ሲገልፅ፣

> *The narrator, is likely to preface his tales with cautionary clues such as opening or closing formulae, special vocabulary and phrases inserted in the body of the story, which enable the listeners to grasp the real nature of the message and not to confuse fiction with reality. Ben Amos, (1982:51)*

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው ትረካ ከመካሄዱ በፊት ተናጋሪው ተረኩን ለመጀመር አስቀድሞ የሚያቀርበው የመክፈቻ ሐረግ (በአማርኛ ተረት ተረት... እንደሚባለው መሆኑ ነው) ካሰማ በኋላ ይሁንታን ከታዳሚዎች ሲያገኝ ክንውኑን ይቀጥላል። ከትረካ በኋላ የሚያስቀምጠው የመደምደሚያ ሐረግ (ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ.....እንደሚባለው) አድማጮችን አነቃቅቶ ቁም ነገሩን ከዋዘኛው እየለዩ እንዲያጣጥሙ አድርጎ ያበቃል።

በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ላይ Finnegan,

> *The opening and closing formulas, in various forms, are common in all areas of Africa. Conversely the opening formulas serve to rouse the interest of the audience. Some times eliciting a formal response from them as well as setting the mood for the start of the narration. Finnegan, (1970:380)*

ስትል ገልፃለች። በጥቅሱ የተገለፀው ሃሳብ ከዚህ ቀደም ሲል Ben-Amos ካነሳው ጋር የሚቀራረብ መሆኑን ማየት እንችላለን። የመግቢያና የመደምደሚያ ቀመሮች ያሏቸው ተረኮች በብዙ ያፍሪካ አገሮች ውስጥ የሚታዩ ናቸው። በተለይ ደግሞ የመክፈቻ ቀመሮች፣

የታዳሚዎችን የማድመጥ ፍላጐት የሚቀሰቀሱ፣ታዳሚዎችም የይሁንታ ምላሽ በመስጠት ለማድመጥ ቀልባቸውን ዝግጁ የሚያደርጉባቸው እንደሆኑ ከጠቀሜታ አንፃር ገልፃለች።

## 3.4 የተረክ ግልጋሎት

በማንኛውም ህብረተ-ሰብ ውስጥ የሚገኙ ዝርው ቃል ተረኮች የሚነገሩባቸው ዓላማዎችና የሚያበረክቷቸው ግልጋሎቶች እንዳሏቸው ተደጋግሞ ተገልፆአል። ቀጥለን በዋቢነት በምንጠቅሳቸው ምሁራን ሥራዎች ውስጥ ስለ ቃል-ተረኮች ግልጋሎት Bascom ሲገልጽ፣

> *A tale is not a dictated text with interlinear translation, but a living recitation delivered to a responsive audience for such cultural purposes as reinforcement of custom and taboo, release aggression through fantasy, pedagogical explanations of the natural world and application of pressures for conventional behavior Bascom(1969:21)*

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው አንድን ቃል ተረክ ላይ ላዩን ብቻ በግልብ ተደምጦ የሚታለፍ አይደለም። ይልቁንም በታዳሚዎች አእምሮ ዘልቆ ሊቀረጽ የሚችል ቃለ-ነቢብ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። እንዲህ በመሆኑም ያንድ ህብረተ-ሰብ አይነኬው (taboo) እና ልማዳዊ ሥርዓቱ (cultural norms) በነበሩበት ፀንተው እንዲቆዩ ማጠናከሪያዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ የሰዎችን ቁጣና ንዴት ጭምር በማብረድ፣ የተፈጥሮንና የፍጥረታትን (Nature and Creatures) ምንነት በመግለፅ ረገድ ሰፊ ግልጋሎት ያላቸው ናቸው። በተጨማሪም ህብረተ-ሰቡ ሠናይ ብሎ የተቀበላቸውን ምግባራት ወደ ተከታዩ ትውልድም እንዲዘልቁ ማድረጊያ ስልቶች መሆናቸው ይገለፃል። በዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ፣ Finnegan,

*Stories for instance, are told to educate and socialize children, or by drawing a moral, to warn people not to break the norms of the society.* Ruth Finnegan, *(1970:330)*

በማለት ገልፃለች። በጥቅሱ እንዳመለከተቺው፣ ተረኮች የሚነገሩት ልጆች ማህበራዊ ህይወትን እንዲለማመዱ ለማስተማር፣ ወይም ደግሞ የሕብረተ-ሰቡ የቆዩ ልማዶች ሳይዛቡ ወደፊት እንዲቀጥሉ ለማድረግ ወይም በከንቱ እዳይታበዩ ለማስጠንቀቅ በታቀደ ዓላማ ሲሆን ግብረ ገባዊ አቀራረብን በተከተለ መንገድ ነው።

በአፍሪካ በተለይ በሴራሊዮን፣ የሊምባ ቃል ተረኮችን (Limba stories) ስትመረምር፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ቃልተረኮች ለምን ዓላማ እንደሚነገሩ ያገኘችውን መረጃ እንዲህ በማለት ገልፃለች፣

> *The listeners are told that they can learn a lesson from the experience of the animals in the tale that, say, one should not be rude to one's mother-in-law, that men's words are more weighty than women's, that strangers should be treated well, that it is ill-advised to oppress the weak, or even that determination sometimes triumphs over virtue. Finnegan, (1966:40)*

በጥቅሱ ውስጥ እንደተመለከተው፣ ታዳሚዎች በቃል ተረኩ ከሚሳተፉ እንስሳት ገፀ-ባህርያት ዕጣ ፈንታ ልምድ እንዲያገኙ ትምህርት እንዲቀስሙ ነው። ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል መልካሙን መንገድ ይዞ እንዲሄድ ይፈለጋል። በባህሉ፣ የባል እናትን (አማትን) ማክበር የተቀደሰ ምግባር ቢሆንም ከሴቶች በበለጠ ሁናቴ የወንዶችን ቃል መጠበቅና መፈፀም ደግሞ ከሁሉም የሚልቅ ክዋኔ እንደሆነ በተረኮቹ ይገለፃል። ከተጠቀሱት በተጨማሪ፣ ለአካባቢው ባይተዋር የሆኑ ሰዎችን በትህትና ማስተናገድ፣ ደካሞችን መርዳት፣ ከክፋት ይልቅ ቀና መንገዶችን መከተል በማንኛውም ጊዜ ቢሆን አማራጭ የሌለው መሆኑን ለማስገንዘቢያ እንደሚያገለግሉ አብራርታለች።

## 3.5 የተረክ ታዳሚ

ለዝርው ቃል ተረኮች ክዋኔ፣ የታዳሚዎች (አድማጮች) መኖር አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው። ተራኪና ታዳሚ የማይነጣጠሉ አካላት ናቸው። ተራኪ ያለ ታዳሚ፣ ተረክ ደግሞ ያለ ክዋኔ ህልውና የላቸውም። ይህን ሃሳብ የሚያጠናክረው Ben-Amos (1982፡13)

*For Narratives to happen, two social conditions are necessary: both the performers and the audience have to be in the same situation and be part of the same reference group.*

ይላል። ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው ተረክ እንዲከወን ከተፈለገ ሁለት ማህበራዊ ጉዳዮች መሟላት ይኖርባቸዋል። እነርሱም ተረክ አቅራቢዎች (ከዋኖች) እና ታዳሚዎች (አድማጮች) ናቸው። ለቃል ተረኩ ክዋኔ ሁለቱም በቅርብ ርቀት መገኘት ይኖርባቸዋል።

ታዋቂው ፎክሎረኛ፣ Dorson, *(1972:25)* እንዳመለከተው።

*Without audience, story telling cannot function. It is meaningless from its living presentation, or performance, to a responding audience. Dorson,*

በቀረበው ገለፃ መሠረት፣ ትረካ ያለታዳሚ ፋይዳ የለውም። ህልውናም ትርጉም የሚኖው ታዳሚዎች ሲኖሩት ነው። የአንድ ተረክ ህልውና የሚወሰነው በክዋኔና በታዳሚዎች መኖር እንደሆነ ቀደም ሲል ገልፀናል። ይሁንና በተለይ የታዳሚዎች ዕድሜ፣ ፆታቸው እና ያቀራረቡ ሁኔታዎች የተረኩን ዓይነት ይወስናሉ ምን ዓይነት ተረክ ? ለየትኛው የህብረተሰብ ክፍል ይቀርባል? የሚሉ ጥያቄዎች አስቀድመው መልስ ሊያገኙ ይገባል። ምክንያቱም ሁሉም የየራቸው ገደብ (ክልል) ስላላቸው ነው። በዚህ ዙሪያ Ben Amos, የሰጠው አስተያየት፣

*The Audience itself, be it children or adult, men or women, a stable society or an accidental grouping, affects the kind of folklore genre and the manner of presentation. Ben Amos, (1982:3)*

ሲል ገልፆኣል።

ከጥቅሱ መገንዘብ እንደሚቻለው፣ የአንድ ትረካ ታዳሚዎች ህፃናት ይሁኑ አዋቂዎች፣ ሴቶች ይሁኑ ወንዶች፣ ነባር ይሁኑ በድንገት የተሰባሰቡ፣ እያንዳንዳቸው የተረኩን ምንነት ብቻ ሳይሆን ያቀራረቡን ሥርዓትና ዓይነቱን ጭምር ይወስኑታል። በማለት ቀደም ሲል የተነሳውን ሃሳብ ያጠናክራል።

## 3.6 የተረክ መቼት

ስለተረኮች መቼት ወደመተንተን ከመሄዳችን በፊት፣ መቼየት (Setting) የሚለውን ቃል መግለጽ አስፈላጊ ነው። ቃሉ ከሁለት ነጠላ ቃላት የተመሰረተ ነው። መቼ? የሚለው ጊዜን የሚያመለክት ራሱን የቻለ ቃል ሲሆን፣ የት? የሚለው ደግሞ ስፍራን አመልካች ሌላ ቃል ነው። ሁለቱ በማጣጣም 'መቼት' የሚለውን ቃል አስገኝቷል። ታዲያ የተረኮች 'መቼት' የሚለው ቃል በዚህ አገባቡ ተረኮች የሚነገሩባቸውን ቦታና ጊዜ የሚያመለክት ነው።

እንደሚታወቀው ተረኮች የሚነገሩባቸው ቦታዎችም ሆኑ ጊዜያት በሁሉም ህብረተሰቦች ዘንድ ተመሳሳይ አይደሉም። ከዘመን ዘመን ከቦታ ቦታ፣ ከህብረተ-ሰብ ህብረተ-ሰብ፣ ይለያያሉ። ለመሆኑ ቃል ተረኮች የሚነገሩት በየት በየት ሥፋራ ነው? ለዚህ ጥያቄ ምላሽ

*Narratives can be told during the day time in the market place, the country store, and the street corner: or at night in the village square, the parlor and the coffee house. Ben-Amos (1982:11).*

በማለት አቅርቧል። ከገለፃው መረዳት እንደሚቻለው፣ ተረኮች እንደየህብረተሰቡ ልምዳዊ ሥርዓት የሚነገሩባቸው ጊዜያትም ሆኑ ቦታዎቹ ይለያያሉ። ቀን በመገበያያ ቦታዎች፣

በአደባባዩች፣ አረፍ በመባያ ሥፍራዎች፣በቡና ሥርዓት ላይ ሊቀርቡ የሚችሉ መሆናቸው ነው። ይህም የሚያሳየን የቃል ተረኮችን መቼት የሚወስነው የህብረተ-ሰቡ ልምዳዊ ሥርዓት እንደሆነ ነው። በአህጉራችን አፍሪካ የሊምባ ህብረተ-ሰብ ተረኮችን መቼት ስንመለከት

> *Limba stories are most frequently told in the evenings, after the sun set…………The most popular time is at full-moon when people go to bed late, but at other times too stories are told either under the stars, or since people like to see as well as hear the narrator, by the light of a paraffin lamp or blazing fire. Finnegan, (1966:64)*

Finnegan እንደተገለፀችው በሊምባ ህብረተ-ሰብ ውስጥ ተረኮች የሚነገሩት አብዛኛውን ጊዜ ከመሸ ወይም ጀምበር ከጠለቀች በኂላ ነው። በጣም የተለመደው ጊዜ እንዲያውም በምሽት ሙሉ የጨረቃ ብርሃን ሲኖር ነው። በነዚህ ጊዜያት ሰዎች ወደ መኝታቸው የሚሄዱት ሌሎች ጊዜያት በጣም ዘግይተው ነው። የጨረቃ ብርሃን በሌለበት ጊዜ ተረክ የሚቀርብ ከሆነ፣ ተራኪና አድማጭ ፊት ለፊት እየተያዩ እንዲሆን በከዋክብት ብርሃን፣ በኩራዝ፣ ወይም እሳት እያነደዱ በመሞቅ እንደሚከናወን ጠቅሳለች።

## 3.7 የዝርው ቃል ተረኮች ጥናት በሀገራችን

በሌላ በኩል ከ1982 ጀምሮ በአ.አ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ውስጥ እየተካሄደ ያለው የድህረ-ምረቃ ኘሮግራም፣ ለሥነ-ቃል ጥናት ዘርፍ እየተበረታታ መሄድና ቀድሞ አነስተኛ ቁጥር የነበራቸው ተመራማሪዎች ቁጥር ዛሬ ይበልጥ እየበረከቱ እንዲመጡ ረድቷል። በዚህ መሠረት ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሰሎ ካላቸው መካከል፣የአብዱልቃድር ሐጂ ጃማ "Some Cultural Elements As Reflected In Somali Folk Tales" (1982)፣ የመላክነህ መንግሥቱ "The Major Themes And Motifs of Southern Agaw Folk Tales"(1990)፣የተስፋዬ ገብረማርያም "A Study of Major Themes In Jablawi Folk Tales"(1990)፣የሳህሉ ኪዳኔ "Borana Oromo Oral Prose Narratives: A contextual study"(1996)፣ የባይለየኝ ጣሰው "Anyuaa Oral Prose Narratives"(1999) የሚሉትን ሥራዎች በየተራ እንቃኛለን።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ጥናታዊ ሥራዎች፣ በእርግጥ በመልከአ ምድራዊ አቀማመጣቸው በተለያዩ ህብረተ-ሰቦች ሥነ-ቃሎች ላይ የተካሄዱ ናቸው። ይሁን እንጂ ደግሞ በአንድ የሥነ-ቃል ዘውግ (genre) ላይ ያነጣጠሩ ስራዎች መሆናቸው ያመሳስላቸዋል። የጊዜ፣ የቦታ፣ የአጥኚዎች ትኩረት፣ የአገላለጽ ስልት ወዘተ. ልዩነታቸው ገሃድ ነው። ተመራማሪዎቹ ካነሱአቸው ርዕሰ-ጉዳዮች አንፃር ስንመለከታቸው፣ የአብዱልቃድር፣ የመላክነህና የተስፋዬ



LIBRARY ABABA UNIV

ሥራዎች በተረኮች ጭብጣዊ ትንታኔ (Thematic Analysis) ላይ ተመስርተው የህብረተሰቡን ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ በመመርመር አኳያ ይመሳስላሉ።

መላክነህ የሰበሰባቸውን ተረኮች በ8(ስምንት) ዋና ዋና ጭብጦች (Major themes) ከፋፍሎ በመተንተን ተረኮቹ የሚነገሩባቸውን ምክንያቶችና ዓላማዎቻቸውን አመልክቷል። በጥናቱ ሂደት ተረኮች ተደጋጋሚ ጭብጦች እንዳሏቸው የተመለከተ ሲሆን የህብረተ-ሰቡን መልካም እሴቶች በማስተማር፣ የወጣቶችን ሰብዕና በበጎ አቅጣጫ ለመቅረጽ እንደሚያገለግሉ ገልፃኣል።

ከመላክነህ ጋር ተመሳሳይ አካሄድ እንዳለው የምናየው የተስፋዬ የጃብላዊ ህብረተ-ሰብ ተረኮች ትንታኔ ስልት ነው። ተስፋዬ፣ ሁሉም ተረኮች በጋራ የሚጋሯቸው ባህርያት ያሏቸው መሆናቸውን አመልክቷል። የጃብላዊ ህብረተሰብን ርዕዮተ-ዓለም፣ ልምድ፣ ወግ፣ ተስፋ፣ ምኞት ወዘተ. በሚገባ መገንዘብ የቻለው በተረኮቻቸው ላይ ባደረገው ጭብጣዊ ትንታኔ ጥናት አማካይነት እንደሆነ ይገልፃል።

በሌላ በኩል፣ አብዱልቃድር ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች የሰበሰበበት መቼት (setting) ጅጅጋ ስደተኞች ካምፕ (1982፡23) ውስጥ ብቻ መሆኑ ውሱን ያደርገዋል። ስለሆነም ሁሉንም የሶማሌ ክልሎች የሚሸፍኑ ተፈላጊ ነጥቦችን (elements) ያሳያሉ ብሎ ደፍሮ መናገር የሚያስቸግርበት ሁኔታ ይታይበታል። ይህም ምናልባት ስደተኞቹ ከአንድ አካባቢ ብቻ የመጡ ከሆነ ስርጭቱም በዚህ ልክ የተወሰነ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ የተረኮቹ ጭብጦች ትንታኔ በማህበራዊ ዓውዶቻቸው ላይ የተመሰረቱ መሆን እንዳለባቸው የዘርፉ ምሁራን ደጋግመው የሚያሳስቡበት ጉዳይ ቢሆንም ጥናቱ ለዚህ ነገር ትኩረት ሳይሰጥ በአንድ ውሱን መቼት የተካሄደ ነው።

ከላይ በዝርዝር ከተጠቀሱት ጥናቶች መካከል፣ ለየት ያለ አካሄድ (approach) የምናየው በሳህሉ ኪዳኔ የቦረና ኦሮሞ ዝርው ቃል ተረኮች ጥናት ውስጥ ነው። ሳህሉ ዝርው ተረኮችን ከማህበራዊና ባህላዊ አውድ አንፃር በስፋትና በጥልቀት ተመልክቷል። ለአንድ ፎክሎረኛ ቃለ-መጠይቅ ዓይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን (Dorson, 1972:407-428; Goldstein, 1965:76) ይገልፃሉ። ይሁን እንጂ እርሱ በጥናቱ ውስጥ ይህን ስልት መጠቀም አለመጠቀሙን አልጠቀሰም። የቦረና ኦሮሞ ተረኮች አካባቢያዊ/ወንዛዊ ክልሰፋዎች (Indigenous classifications) ከማህበራዊ ዓውዳቸው አኳያ በመመርመር 'Duri Duri'፣'Mamaksa' እና 'Arga-

Ageti' ተብለው በአካባቢው ቋንቋ የተሰየሙ ዘውጎች (genres) መሆናቸውንና እያንዳንዳቸውም የተለያዩ ማህበራዊ ግልጋሎቶች እንዳሏቸው አመልክቷል ።

በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ዝርው ቃል ተረኮች ላይ በስፋት የተሰሩ ሥራዎች እንደሌሉ ቀደም ሲል በመግቢያው ላይ ተገልፆአል። ይሁን እንጂ፣ በሌሎች የሥነ-ቃል ዘርፎቻቸው (geners) ላይ ከተሰሩት መካከል፣ ስለጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓት Knutson (1967)፣ ስለህብረተ-ሰቡ ታሪክና አሰፋፈር ላጵሶ ጌ ዴሌቦ (1982) እና McClellan Charles (1988)፣ ስለ ጌዴኦ ማህበራዊና ልማዳዊ ሥርዓት አደረጃጀት Demissie Woressa (1988)፣ ስለ ጋብቻ ዓይነቶችና የቤተ-ሰብ አመሰራረት Dagne Shibru, (1995) ስለ ጥንታዊ የጌዴኦ ልቅሶ ሥርዓት ጥላሁን ኢቢዶ (1982ዓ.ም)ወዘተ. የመሳሰሉ ሥራዎች በማስረጃነት ከሚጠቀሱት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

በሌላ በኩል ስለ ጌዴኦ ሥነቃል በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ቅኝት ካደረጉት ሰዎች መካከል Wedekind Klaus, (1977:197) አንዱ ነው። እርሱም በጥናቱ ሂደት 77(ሰባ ሰባት) ያህል የዘፈን ግጥሞችን ሰብስቦ ከነዚህ ውስጥ ከፊል ያህሉን ብቻ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ለመመለስ ጥረት ቢያደርግም ሁሉንም አጠናቅቆ አላዘጋጀም። Klaus, በዝርው ቃል ተረኮች ጥናት ረገድ የተወሰነ ጥረት አድርጓል። በጌዴኡፋ (Geduffa) ቋንቋ ያሰባሰባቸው በቁጥር 10(አሥር) ያህል ቃል ተረኮች ይገኛሉ። በእርሱ የተደረጉት እነዚህ ሙከራዎች የሥነ-ቃል ጥናት በሃገራችን ባልተስፋፋበት ወቅት በመሆኑ በቅርስነት ለወደፊት ጠቀሜታ ሊኖራቸው ይችላል።

በሌላ በኩል፣ የአኙዋ ቃል ተረኮችን በመስክ በተደገፈ መረጃ ላይ ተመስርቶ ጥናት ያካሄደው ባይለየኝ ጣሰው፣ በምልከታ፣በቃለ-መጠይቅና በቡድን ውይይት አማካይነት የመስክ መረጃዎች መሰብሰቡን ገልፆኣል። በጥናቱ ሂደት ተረኮች በመገኛ ቋንቋ ውስጥ ያላቸው አውዳዊ አገባብ እንዳይፋለስ ጥንቃቄ ማድረጉንም አመልክቷል።

የባይለየኝ ዝርው ቃል ተረኮች ጥናት አካባቢያዊ/ወንዛዊ ክልሰፋን (Indigneous classification)፣ የተረኮቻቸውን ስያሜ፣ በዕድሜ ለይ የተደረጉ ግደባዎችን (Delineation) መርምሮ በማመልከት ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ፣ በአካባቢው ቋንቋ 'Leera'፣'Wae' እና 'Angade' በመባል የተሰየሙ ዘውጎችን (Ethnic geners) ለይቶ ማውጣት ችሏል። ከዚህም በላይ በእያንዳንዳቸው መካከል የሚታዩ ትስስሮችን ጭምር መገንዘብ መቻሉን በጥናቱ አመልክቷል።

በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ዝርው ቃል ተረኮች የሚደረገው ጥናት ስለህብረተ-ሰቡ ጥንተ-አመጣጥ አንድ የመመልከቻ መንገድ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። የማንኛውም ህብረተሰብ ዝርው ቃል ተረኮች ጥናት ከተጠኚው ህብረተ-ሰብና ከሥነ-ቃል ጥናት ዓላማ እንዲሁም የጥናት መስኩን እንዲታወቅ ለማድረግ በሚያበረክቱት ፋይዳ ተመሳስሎዎች የመኖራቸውን ያህል ልዩነቶችም ይኖሯቸዋል።

በመሆኑም፣ ይህ ጥናት፣ የዝርው ቃል ተረኮችን ምንነት፣ ጎሳዊ ምደባዎችን (Ethnic categories) አካባቢያዊ ስያሜዎችን መርምሮ በማመልከት ረገድ ከሳህሉና ከባይለየኝ ሥራዎች ጋር ተመሳሳይነት አለው። ከሌሎቹ የሚለይበት ደግሞ፣ የጌዴኦ ህብረተሰብ ዝርው ቃል ተረኮችና ልማዳዊ ሥርዓቶቻቸው ባሏቸው ግኙነቶች ላይ ተመርኩዞ የግንኙነቶቹን ምንነት በመመርመር የሚያመለክት በመሆኑ ነው። ስለሆነም በዚህ ረገድ የሚስተዋለውን ክፍተት በማጥበብ የበኩሉን ድርሻ ያበረክታል ተብሎ በአጥኚው ይገመታል።

ከዚህ በላይ በክለሳ ድርሳን ውስጥ፣ ስለ ዝርው ቃል ተረኮች ምንነት በተለያዩ የመስኩ ምሁራን ከተፃፉ መፃሕፍት ውስጥ ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ የተወሰኑ ግንዛቤዎች ተገኝተዋል። ቀጥሎ ደግሞ፣ የህብረተ-ሰቡን ልማዳዊ ሥርዓቶች ወደ ምንቃኝበት ምዕራፍ እንሸጋገራለን።



ሶንጎ፣ ለህብረተሰቡ ያንድነቱ መግለጫ፣ ያብሮነቱ ማረጋገጫ፣ የዕውቀትና የህይወት
ልምዶቹ መለዋወጫ ማዕከል (Center) ነው፡፡ የዲላ ሶንጎ 1999 ዓ.ም.

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## 4.0 የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓት

ስለ ጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች ለመረዳት፣ በቅድሚያ በነባሩ ልማዳዊ ሥርዓቶቻቸው ላይ የተወሰነ ቅኝት ማድረጉ ለተሻለ ግንዛቤ ያዘጋጀናል። ለመሆኑ እነዚህን ሁለት የሥነ ቃል ዘውጎች ምን ያገናኛቸዋል? ለሚለው ጥያቄ ቢያንስ የሚከተሉትን ሶስት ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። አንደኛ ስለዝርው ቃል ተረኮች ስንናገር፣ ተረኮቹ ከተነገሩባቸው ባህላዊ ዓውድ ውጪ ርቀን እንዳንሄድ፣ ሁለተኛ፣ የህብረተሰቡ ሥነ-ልቡናዊ አመለካከት፣ ማለትም ፍላጎቱ፣ የሚጠላውና የሚወደው፣ ዝንባሌውና ምኞቱ ወዘተ. ከሚገለፅበቸው የተለያዩ መንገዶች መካከል ዝርው ቃል ተረኮችም መገኘታቸው፣ ሦስተኛ፣ ዝርው ቃል ተረኮችና ልማዳዊ ሥርዓቶች፣ ተደጋጋፊዎችና አንዱ ያንዱ መገለጫ በመሆናቸው ነው። ይህን ተደጋጋፊነት ፈቃደ፣ 1991ዓ.ም."፤

> *በተለይ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ፋቡላዎች ፣ የተጠንቀቅ ትረካዎች እና ኑዛዜያዊ ዘፈኖች የአኗኗርን ሥርዓት፣ ምግባርና ብልሃት ያስተምራሉ። የአበላል፣ የአጠጣጥ፣ አለባበስ፣ የአቀማመጥ፣ የአነጋገር፣ የአካሄድ ሥርዓትን ያሳውቃሉ። በህይወት ውስጥ የትጋትን፣ የለጋስነትን፣ የህብረትን ጥቅም አጥብቀው ይሰብካሉ። የልጆችንንና የወጣቶችን ባህርይ ገና ከለጋነታቸው ለመቅረፅም ያገለግላሉ።*

በማለት ዝርው ቃል-ተረኮች የህብረተሰቡን ልማድና ወግ መግለፅ ብቻ ሳይሆን፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው መልሰው ወጣቱን ትውልድ ለማስተማርና ለማነፅም እንደሚያገለገሉ ገልፀዋል። እንዲህ ከተባለ ደግሞ፣ ይህ የሚሆነው በየትኛው ህብረተሰብ ባህልና ወግ ውስጥ ነው? በአንድ ወይስ በሁሉም? የሚሉ ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀርም። ከላይ የተጠቀሱት ልማዳዊ እሴቶች በሁሉም ህብረተሰብ ውስጥ በተመሳሳይ ሁናቴ አይከወኑም። ከቦታ ቦታ፣ ከህብረተሰብ ህብረተሰብ፣ ይለያያሉ። ጉዳያችን ስለጌዴኦ ህብረተሰብ ዝርው ቃል ተረኮች በመሆኑ፣ የምናነሳውም ስለ እነሱ ባህል ብቻ ይሆናል ማለት ነው። በተጠቀሰው ህብረተሰብ ውስጥ ሽማግሌዎችና አዛውንት ለወጣቱ ትውልድ ልምዶቻቸውንና ገጠመኞቻቸውን፣ በልዩ ልዩ ሥነ-ቃሎቻቸው (ተረት፣ እንቆቅልሽ፣ ምሳሌያዊ ንግግርወዘተ.) የሚገልፁባቸው አማካይ ሥፍራ አላቸው ። ይህም በአካባቢው አጠራር ሶንጎ (Songo) ይባላል። ከልማዳዊ ሥርዓቶቹ መካከል፣ ቁጠላ "Qexxla" (አምልኮታዊ ጭፈራ)፣ ፋጬ "facie" (ጥፋትን አምኖ መናዘዝ)፣ ጐንዶሮ "Gondoroo"( ሥራተ- እርቅ) የመሳሰሉ ባህላዊ ሥርዓቶች አስፈላጊ በሆኑባቸው ጊዜያት ሁሉ በዚህ ሥፍራ ይከውናሉ። ከተጠቀሱት በተጨማሪ፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለህብረተ-ሰቡ ባህላዊ ጋብቻ፣ እንዲሁም ስለጥንታዊው የሀዘን ሥርዓታቸው በየተራ እንቃኛለን።

## 4.1 የሶንጎ "SONGO" ማህበራዊ ግልጋሎት

ሶንጎ በጌዴኦ ህብረተሰብ ህብረተሰብ ዘንድ፣ የልማዳዊ ሥርዓቶቹ መከወኛ አማካይ ሥፍራ በመሆን ይታወቃል። በዚህ ሥፍራ ከሚካሄዱ ዋና ዋና ክዋኔዎች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

1. አባቶች ጀግንነትን፣ ጋሻ አያያዝና አመካከት፣ ጦር አወራወር፣ ከጠላት ማምለጥን፣ አደንን፣ ዘመቻና ድልን ለተተኪዎቻቸው የሚያሳዩበት፣በልዩ ልዩ ቃል ተረኮች ወጣቶችን የሚመክሩበት፣ በእጅ ሙያ የሚያሰለጥኑበት፣ ስፍራ ቢኖር Songo ነው። በህብረተሰቡ ልማድ መሠረት ጠዋት ገበሬው ወደ እርሻው ተሰማርቶ ሲሰራ ውሎ ወደ ቤቱ ከተመለሰ በኋላ ያገኘውን ተመግቦ ያካባቢውን ውሎ ለማወቅ የሚያቀናው ወደ ሶንጎ ነው። ከባልንጀራው ወይም በዕለቱ ከመጣ አልፎ ሂያጅ እንግዳ ጋር ተገናኝቶ በዕለቱ ስለሰማው፣ ስላየው፣ ስለአጋጠመው ሁሉ ጠይቆ ይረዳል። በዚህም እንደ መረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል።
2. የባህላዊ አስተዳደር ሥርዓት ታላቅና ታናሽ፣ ወጣትና አዛውንት እየተለዩ ተከባብረው በሥርዓት እንዲኖሩ ደንብ የሚወጣበትና ደንቡም በተግባር የሚውልበት፣ ጽሕፈት ቤት ነው ማለት ይቻላል። አቤቱታና ዳኝነት የሚታይበት፣ እርቅ የሚካሄድበት፣ በጥፋተኛው ላይ እስከ ሞት ደረጃ የሚደርስ ብይን የሚሰጥበት፣ ባህላዊ ያስተዳደር ተቋም በመሆን ያገለግላል፤
3. ህብረተ-ሰቡ የገዳ ሥርዓት በሚፈቅደው ደንብ እየተመራ ሥራተ-ፀሎት የሚፈጽመው ቄጠላ «qeexala» (አምልኮታዊ ዝማሬ) የሚያካሄደውም ሆነ ለአምላኩ ሥርዓተ-መስዋዕት የሚያከናውነው በዚሁ ስፍራ ነው። በተጨማሪ በአገሩ ላይ በሽታ፣ ድርቅ፣ ረሃብ፣ ጦርነት የመሳሰሉት ማህበራዊ ጠንቆች እንዳይከሰቱ ያካባቢው ነዋሪዎች እየተሰበሰቡ አምላካቸውን የሚለምኑበት፣ ነው።
4. ሶንጎ (Songo) የዕደ-ጥበብ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤትም በመሆን ያገለግላል። ለምሳሌ አንድ ሰው የመጥረቢያ ዛቢያ፣ የዶማ እንጨት ወዘተ. እንዴት እንደሚጠረብ እንዴት እንደሚዋደድ የማያውቅ ከሆነ፣ ሌላ ባለሙያ ተቀብሎት እያሳየ ያስተካክልለታል። የቡሉኮ ወይም የነጠላ ዘርፍ መቋጨት ለማያውቅም ቢሆን፣ ከስፍራው ድረስ በመሄድ ዕውቀቱ ባላቸው ሰዎች እየታገዘ ይለምዳል።

ሌሎች የዕደ-ጥበብ ሙያዎችም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚማሩበት ተቋም ሆኖ ያገለግላል፡፡

5. በሶንጎ 'Songo' ወጣቶች ባህላዊ አለባበስን፣ የህብረተሰቡን ጌጣጌጦች አጠቃቀማቸውን ጭምር በድርጊት ሲከወን የሚያዩበት ሥፍራ ነው የሚሉት ሳይጠቀሱ የማይታለፉ ናቸው (የጌዴኦ ብሔረሰብ ትውፊት 1991፡72-75)፡፡

ይህ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት፣ በዞኑ ከአምስት መቶ በላይ አገልግሎት የሚሰጡ ሶንጎዎች እንዳሉ ለአጥኚው በቃል ቢነገረውም ከተወሰኑት በስተቀር ሁሉንም ቆጥሮ አላረጋገጠም፡፡ በጥቅሉ የጌዴኦ ሶንጎ 'Songo' የህብረተሰቡን ቁሳዊና ባህላዊ እሴቶችን ጠብቆ ለማቆየትና ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ትልቅ ድርሻ ያለው ተቋም እንደሆነ በደረሰባቸው ሁሉ መመልከት ችሏል፡፡ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዞኑ ባህል ቢሮ እየተካሄደ ያለው ያደረጃጀት ሥራ ይሁን የሚያሰኝ ነው፡፡ ጥንታዊ አልባሳት፣ የምግብና የመጠጥ፣ መሳሪያዎች፣ የወግ ዕቃዎች ወዘተ. የመሳሰሉትን በየሶንጎዎቹ ተቀምጠው እንዲጎበኙ እያደረጉ ያሉት እንቅስቃሴ፣ ወደፊት ሶንጎዎች የህብረተሰቡ የመረጃ ማዕከል 'resource center' ሆነው እንዲያገለግሉ ያስችላቸዋል የሚል ግምት ያሳድራል፡፡

ከጌዴኦ ሶንጎ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ግልጋሎት የሚሰጥ ባህላዊ ተቋም በአኙዋ ብሔረሰብ መኖሪያ ውስጥም ይገኛል፡፡ ባይለየኝ ጣሰው "Anyuaa Oral Prose Narratives"(1999 : 56) በሚለው ጥናታቸው ውስጥ እንዳመለከቱት፣

> *Wii-maac is an institution in which the Anyuaa assure their collective and individual wellbeing. It is a symbol of Unity and survival. It is the vehicle of communal ways of living. Food is shared at Wii-maac. Knowledge is also shared at Wii-maac. The Anyuaa en-culture their children around the Wii-maac. In general occasions principles of Wii-maac produce appropriate social settings for performances of Oral prose narratives in particular and oral-literature in general.*

አኙዋ በመኖሪያ አካባቢያቸው ተሰባስበው ሃሳባቸውን የሚለዋወጡባቸው ደስታ፣ ሀዘን፣ ችግር፣ ረሀብ፣ ጦርነት፣ ድርቅ ወዘተ. የመሳሰሉ ህይወት ፈታኝ ውጣ ውረዶች ሲያጋጥሟቸው፣ ሁሉም በአንድነት ሆነው በድፍረት የሚጋፈጡባቸው ዊ-ማች (Wii-Maac) የሚባሉ የህብረተ-ሰቡ የጋራ መገልገያ ሥፍራዎች መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም የአኙዋ Wii-Maac እና የጌዴኦ songo የሚባሉት ማህበራዊ ተቋማት፣ የህብረተ-ሰቡ ያንድነት መግለጫ፣ ያብሮነት ማረጋገጫ የዕውቀትና የህይወት ልምድ ማስተላለፊያ ማዕከላት መሆናቸውን መገንዘብ እንችላለን፡፡

## 4.2 ቄጠላ ‹Qeexla› (አምልኮታዊ ጭፈራ)

በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ የተረጋጋና ጤናማ ማህበራዊ ህይወትን የሚያናጉ ድርቅ፣በሽታ፣ ረሃብ፣ ጦርነት የመሳሰሉ ተፈጥሮኣዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶች በድንገት ሲያጋጥሙ፤ ወደፈጣሪ የተማፅኖ ፀሎት ይደረጋል። ይህም ቄጠላ Qeexla[9] ይባላል። (የጌዴኦ ብሔሰብ ትውፊት፣1991) የተጠቀሱት ዓይነት ክስተቶች በአጋጣሚ ቢፈጠሩ፣ በአባገዳ ትዕዛዝ በየአካባቢው ባሉ ሶንጎዎች ህብረተ-ሰቡ በነቂስ ወጥቶ አምልኮታዊ ህብረ-ዝማሬ ያካሂዳል።

በክንዋኔው ወቅት ሁሉም የህብረተ-ሰብ ክፍል (ከልጅ እስከ አዋቂ) የሚሳተፉበት ሥርዓት ነው ይሆናል። እንደክስተቱ ከባድነት እስከ አራት ቀን ድረስ በተከታታይ የሚቀጥል ሥርዓት ሊሆን ይችላል። በነዚህ ጊዜያት እርሻ አይታረስም ሌላም ማንኛውም ሥራ አይሰራም።

እያንዳንዱ ሰው እንጨት እንደ "ችቦ" በመሥራት ወደ ላይ አድርጐ ይዞ ሥርዓቱ ወደሚከናወንበት ሶንጎ ወስዶ ይቆልላል። በአካባቢው በሚገኙ ዎዮ (Woyyo)[10] (የአምልኮታዊ ሥርዓቱ መሪ) አማካይነት ፈጣሪን የመለመን (Mageno Kadhata) ክዋኔ ይደረጋል። በማለት ሐይቻ ማሞ ገደቾ ስለሥራቱ ጠቅለል አድርገው ይገልፃሉ።

ቀጥለውም፣ የተቆለለው እንጨትና ቅጠላ ቅጠል እሳት ይለኮሰበትና ይነዳል ቀጥሎም ይጨሳል። ከዚያም የጭሱ አቅጣጫ ይታያል። እያንዳንዱ ሰው ከሚነደው እሳት አንዳንድ እንጨት በመያዝ Dukuba Nooirra fageesi, Beela Nooirra fagessi (በሽታ አርቅልን፣ ረሃብ አርቅልን የመጣውን መጥፎ ነገር አርቅልን ወዘተ.) እያለ በዝማሬ ዙሪያውን ይዞራል። ጭሱ የሚሄድበት ቦታ አንድ መጥፎ አጋጣሚ የሚመጣበትን አቅጣጫ ነው ተብሎ ስለሚታመን፣ ሁሉም ወደዚያው አቅጣጫ በመዞር ቂድ "Qiid" (ይወገድልን፣እዚያው ይቅር! ወደእኛ አይምጣብን) እያሉ በመደጋገም ያዜማሉ። በዚህ ሁኔታ ተማፅኖኣቸውን አሰምተው የያዙትን እንጨት ወደ ተባለው አቅጣጫ ወርውረው ወደ ነበሩበት ተመልሰው ዝማሬ ፀሎታቸውን ይቀጥላሉ። ሥራቱ የሚያበቃው ለMageno መስዋዕት በማቅረብ ነው። ይኸውም፣ ጥቁር በግ ተፈልጎ ይመጣና በመጀመሪያ ዓይኑ ይጠፋል፣ ቀጥሎ ቀንዱ ይሰበራል፣ በመጨረሻም አንገቱ ታርዶ እሳት ውስጥ እንዲንጨረጨር ይደረጋል። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ "እግዚኦ ከሃረብ፣ ከድርቅ ከጦርነት ከበሽታ አድነን ሰላሙን አምጣልን" እያለ ድምፁን ከፍ አድርጎ በአንድነት ልመናውን ያሰማል። ሥርዓቱ የሚያበቃው እንደአጀማመሩ ሁሉ ባካባቢው ዎዮ ምርቃት ከተካሄደ በኋላ ሐይቻው ደግሞ ህዝቡን ወደየቤቱ ያሰናብታል ( የጌዴኦ ብሔረሰብ ትውፊት1991:60)።

---

[9] Qeexala - በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ህይወት እናጊ ክስተቶች ሲፈጠሩ (Mageno) መለማመኛ ህብረ ዝማሬ ነው።
[10] Woyyo (ዎዩ) - በጌዴኦ ባህላዊ አስተዳደር ውስጥ አምልኮታዊ ሥራዎች የሚያከናውኑ ናቸው።

## 4.3.ፋጩዮ (Facie)

በሰዎች ማህበራዊ ህይወት ውስጥ በየጊዜው የሚከሰቱ ክፉም ይሁኑ መልካም አጋጣሚዎች ይኖራሉ። በጥቅሉ መልካም አቅጣጫዎች ተከትሎ መሄድ ከጥፋት መራቅ ሲሆን፣ ከዚህ በተቃራኒ አቅጣጫ መጓዝ ደግሞ በጥፋተኝነት ሊያስፈርጅ ይችላል። እያንዳንዱ ህብረተ-ሰብ ጥፋተኞችን የሚያርምበትና የሚያስተካክልበት የራሱ የሆኑ ባህላዊ ደንቦችና ወጎች ይኖራሉ። ጌዴኦዎችስ? በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ውስጥ Facie[11] (ፋጩዮ) ጥፋትን አምኖ በህዝብ ፊት መናዘዝ ማለት ሲሆን፣ በሌላ መልኩ ይህ ሁኔታ ሓሰት ጠፍቶ እውነትና ሐቅ እንዲስፋፋ የማበረታቻ ስልት ነው ማለት እንችላለን። በማንኛውም የዕድሜ ደረጃ የሚገኝ ሰው ባሳለፋቸው የህይወት ዘመናቱ ውስጥ በድብቅ ለሚፈፅማቸው ጥፋቶች ለምሳሌ ነፍስ መግደል፣ ፍርድ ማዛባት፣ ዝሙት መፈፀም፣ የሌላ ሰው ንብረት ለራስ ማድረግ፣ የፈጣሪን ትዕዛዝ አለመፈፀም የወሰን እንጨት ነቅሎ መጣል፣ የወፍ እንቁላል መስበር ወዘተ. ለመሳሰሉት ሁሉ ፋጩዮ ማደረግ ማህበራዊ ግዴታ ነው። አንድ ወንድ ወይም ሴት እነዚህን በመሳሰሉ ተግባራት ተሳትፎ/ተሳትፋ ለማንም ሳይነገር ተደብቆ ከቆየ/ች በኑሮው/ዋ ላይ የልታሰበ ችግር ሊከሰት ይችላል ተብሎ ይታመናል። ስለሆነም ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት፣ በሚገኘው አጋጣሚ ፋጩዮ (Facie) ማድረግ ይኖርበታል/ባታል። ነገር ግን "ሳደርግም ሆነ ስፈፅም ማንም አላየኝም፣ አልተሰማብኝም አልታወቀብኝም" ተብሎ ተደብቆ ቢቆይ፣ ልጅ ወይም ከብት ይሞታል፣ ሰብል ይበላሻል፣ ሌላም ሌላም። ይህ ችግር አንድ ጊዜ ብቻ ተከስቶ የሚቆም አይደለም። እየተደጋገመ ለከፋ አደጋ ይዳርጋል። ከዚህ ችግር ለመታደግ በፊት ለፊት ይፋ ወጥቶ መናዘዝ (ንስሐ መግባት) ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ መፍትሔ የለውም ተብሎ በህብረተሰቡ ይታመናል በማለት ሐይቻ አለማየሁ ቦኮ ስለ ፋጩዮ በሰፊው ይገልፃሉ።

ቀጥሎ የምንመለከተው ቃል-ተረክ ከላይ የተገለፀውን ልማዳዊ ሥርዓት በህብረተሰቡ ውስጥ ይበልጥ ለማስረፅና ለማጠናከር እንዴት እንደሚያገለግል የሚያመለክት ነው።

> *ትዳር መስርተው የሚኖሩ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ። ከዕለታት አንድ ቀን የታላቅየው ሚስት ድንገት ሳይታሰብ ሞተች። ባልዬው ጥቂት ጊዜ ቆየና ልጁን እንድታሳድግለት ሌላ ሚስት አገባ። ጥቂት ዓመታት አብረው እንደኖሩ እሱም ሞተ። በዚህ ጊዜ የታናሽየው ሚስት ከእንግዲህ የወንድምህን ሀብት አንተ ወርሰህ ሀብታም ሆነህ መኖር ነው ብላ ነገረችው። እሱም "እንዴት ሆኖ የወንዴሜ ልጅ እያለ! ይህማ እማይሆን ነገር ነው" በማለት ይመልስላታል። "እርሱን ለኔ ተውልኝ" አለችና ተንኮል ማውጠንጠን ጀመረች። አንድ ቀን ወደ Songo ትሄድና "የባለቤቴ ታላቅ ወንድም ልጅ ደፈረኝ" ብላ ለሽማግሌዎች*

---

[11] Facie በህዝብ ፊት ጥፋትን አምኖ መናዘዝ ማለት ነው።

*ትናገረች። ልጁም ተጠርቶ 'Facie' (ፋጬ) እንዲያደርግ ይጠይቁታል። ነገሩ ፍፁም ሐሰት መሆኑን ደጋግሞ ተናገረ። ሽማግሌዎቹም «እንግዲህ በደንባችን መሠረት ነውር ሥራ ሰርቶ እውነቱን ሳያወጣ የቀረ ሰው ይረገማል።» አሉና "እውነትን በሐሰት ደብቆ ወደ እኛ የመጣ ከሳሽም ይሁን ተከሳሽ በቁሙ ይቀበር" ብለው ተራግመው እነሱን ወደየመጡበት ሸኟቸው። ከዕለታት ባንድ ቀን ሴትዮ ውሃ ልትቀዳ ወደ ወንዝ ስትወርድ ሳታስበው አንድ እግሯ ንቃቃት ውስጥ ይገባል። ብትጎትተው ከመውጣት ይልቅ ጭራሹኑ ወደ ውስጥ እየሰመጠ ሄደ። በትጮህ ሰዎች ሊያወጧት ቢሞክሩም አልቻሉም። እንዲያውም ሌላው አካሏም ቀስ በቀስ ወደ ውስጥ እየገባ በቁሟ ሰምጣ ሞተች ይባላል።*[12]

ከላይ በቀረበው ቃላዊ ተረክ የምንገነዘበው ነገር፣ ህብረ-ተሰቡ ስለ ፋጬ የያዘውን አመለካከትና አስተሳሰብ ማጠንከሪያ በመሆን እንደሚያገለግል ነው። ማንኛውም የዚህ ማህበረሰብ አባል፣ ምን ጊዜም ሐቅንና እውነትን ይዞ፣ ከሐሰትና ከድብቅነት ርቆ፣ የሚኖርበትን ዘዴ ይዞ እንዲጓዝ ከሚደረጉ ስልቶች መካከል አንዱ መሆኑን እንመለከታለን። ፋጬ በተለይ ወጣቱን ትውልድ በመልካም ሥነ-ምግባር እያነፁ ለማሳደግ ከፍተኛ የስነ-ልቦናዊ ጠቀሜታ ያለው ማህበራዊ እሴት ሆኖ እንደሚያገለግልም መገመት ይቻላል።

በ 7/6/99ዓ.ም በኮቾሬ ወረዳ ጨለለቅቱ ከተማ ውስጥ ያገኘሁት ሰው (ስሙ እንዲገለጽ አልፈለገም) እውነተኛ ነው ያለውን አንድ ገጠመኝ እንደሚከተለው ነግሮኛል፤

*"ጊዜው በደርግ አስተዳደር ውስጥ የሆነ ነው። ለግዳጅ ዘመቻ ወደ ግምባር ሊሄድ የተነሳ አንድ የዚሁ ከተማ ነዋሪ የሆነ ሰው እርሱ ግዳጁን ፈጽሞ እስኪመለስ ድረስ ቤቱን እንዲያይለት አደራ ብሎት ሄደ። ባለአደራውም እየተመላለሰ ወጣ ገባ ሲል ከዘማቹ ሚስት ጋር ተላመዱ። ከሁለት ዓመት በኋላ ከግዳጅ ተመለሰ። ቤተሰቡን ሁሉን በደህና ስላገኛቸው ጓደኛውን አመስግኖ እንደ ድሮው ጓደኝነታቸውን ቀጠሉ። ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ የባለ አደራው የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ይሞታል። በባህሉ መሰረት በድብቅ የሰራው ነገር እንዳለ እዲናዘዝ (ፋጬ) አጥብቆ ሲመረመር አደራውን አፍርሶ ከዘማች ጓደኛው ሚስት ጋር መወስለቱን ተበዳይና ሽማግሎዎች በተገኙበት ተናዘዘ። ተበዳይም ይቅርታ እንዲያደርግለት ሽማግሎዎች አግባብተውና አስማምተው በሰላም እንዲኖሩ አደረጉ" ብሏል።*

## 4.4.ጎንዶሮ (Gondoroo)

በጥንታዊ የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓት፣ ውስጥ ወንጀሎች የአካል ጉዳትና የነፍስ ግድያ፣ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም በድንገት ወይም በስተት የተፈፀሙና በዝግጅት ሆን ተብሎ ታስቦበት የተፈፀሙ የሚሉ ናቸው። ሁኔታዎችን በመፍታት ረገድም ሁለት አቅጣጫዎች እንዳሉ ይገለፃል። ድርጊቱ ድንገተኛና በስህተት የተፈፀመ መሆኑ ከተረጋገጠ ዳኖ "Daano"

[12] ጉቱ ሴጌ ኅዳር 23/1999ዓ.ም ይርጋጨፌ



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

/ድንገተኛ/ ተብሎ በጎንዶሮ "Gondoroo[13] ይፈታል:: ይህም ማለት የደረሰው አደጋ ሳይታሰብና በድንገት የተከሰተ ስለሆነ ተመልሶ እንዳያገረሽ የመጨረሻ እልባት የሚሰጥበት ሥርዓት ነው:: ጠቡ ከቀላል ጉዳት እስከ ህይወት ማጥፋት ሊደርስ ይችላል:: የእርቁ ስርዓትም እንደሁኔታው የራሱ ደረጃ አለው:: ለምሳሌ አለመግባባቱ ከሞት መልስ ከሆነ የሰፈር ሽማግሌዎችና የአካባቢ ነዋሪዎች በተገኙበት ውይይት ይካሄዳል:: ስምምነት ላይ ሲደረስ፣ በግ ወይም ፍየል ታርዶ ጠበኞቹ በሽማግሌዎቹ ፊት ቀርበው አራራ "araraa" (እርቅ ይውረድ) እየተባለ አራሪ ደዳ "hariidhdha" ቅቤ ወይም ደም በግምባር የመቀባት ሥርዓት ይካሄዳል:: ከዚያም የታረደው ስጋ በእርቁ ላይ የተገኙ ሰዎች ከበሉ በኋላ፣ እርቁ የሰመረ እንዲሆን ተመኝተው ይለያያሉ::[14]

አለመግባባቱ ህልፈተ-ህይወትን ያስከተለ ከሆነ፣ ደግሞ ከአካባቢ ሽማግሌዎች 'hayyicha' (ሐይቻ) እና "woyyo" (ዎዩ) አብረው ይቀመጣሉ:: በሽምግልናው ላይ የሚገኙ ሰዎች ብዛት በርከት ያሉ ሆነው አስቀድሞ ከተሰጠው ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ሥርዓቱ ጠንከር ያለ ነው:: የሚመለከታቸው ሰዎች በተገኙበት በሁለቱ ደመኞች መካከል ሰፋ ያለ ክርክር ማካሄድ የተለመደ ነው:: ሁሉም ወገን ስሜቱን አውጥቶ ይናገራል:: በመጨረሻ በዳኞቹ ውሳኔ ሰጪነት አብቅቶ በህብረት qiide" (ነገሩ ይቀዝቅዝ) እየተባለ የእርቅ ስርዓቱ ይጀመራል::

በዚህ ሥርዓት ላይ የሚታረደው ከብት በመጠኑ ከፍ ያለ ነው:: አስቀድሞ የሚደረጉ የሁለቱ ደመኞች ስምምነት በቃል ደረጃ ከተካሄደ በኋላ፣ ነፍሰ ገዳዩ የታረደውን ከብት ቆዳ ውስጡን ገልብጦ ለብሶ በህዝቡ ፊት እንዲቆም ይደረጋል:: የዚህ አንድምታ ግለሰቡ ሰላማዊ ህይወት ማቃወሱን፣ ስህተት መፈፀሙን ባጠቃላይ ከህረተ-ሰቡ ባህል በተቃራኒው መንገድ መሄዱን ለማመልከት ነው:: ቀጥሎ በሟች ወገንና በገዳይ መካከል፣ lafe" (አጥንት) ይቀመጣል:: ከዚያም በ"woyyo" አማካይነት አጥንቱ «Gondoroo» እየተባለ ይሰበራል:: «ውሾን ያነሳ ውሾ» እንደሚባለው ሆኖ «ቂም በቀል አንይዝም፣ ወደ አለፈና ወደ ተረሳ ነገር ዳግመኛ ብንመለስ እንደዚህ አጥንት ይስበረን» ብለው ይምላሉ:: ከዚያም ሁሉም የተዘጋጀውን ምግብ በልተው በምንም ዓይነት ላይፈላለጉ ቃል ገብተው በዎዮ ምርቃት ሥርዓተ እርቁ እንደሚጠናቀቅ ይገልፃሉ::

---

[13] Gondoroo ዳግመኛ በማይመለስና በማያገረሽ ሁኔታ የእርቅ ሥርዓት መፈፀም ማለት ነው::

[14] ሽንጡ ሎሌ ሰኔ 15/1999ዓ.ም ወናጎ

በሌላ በኩል ሆን ተብሎ ታስቦና ተዘጋጅቶ በማን አለብኝነት በግፍ ሰው የገደለ ከሆነ፣ በየደረጃው ባሉ የገዳ መዋቅሮች ተረጋግጦ ተጠያቂ ይሆናል:: እንዲያውም በጥንታዊ ጌዴኦ ህብረተሰብ በዚህ ዓይነት ሰው በግፍ የገደለ ተጠያቂ ነውና ጠብቁት፣ ቀልቡት፣ እስከመባል ድረስ ለቤተሰብ ትዕዛዝ ይሰጥ ነበር ይባላል:: ከፍርድ በፊት በወንጀለኛው ላይ በቀል እንዳይወስድበት ወደ አካባቢው የገዳ ባለሥልጣን ሄዶ እስከውሳኔው ድረስ እንዲቆይም ይደረግ ነበር:: እዚያም እንደ አንድ የቤተሰብ አባል ሆኖ ይቆያል እንጂ እስር ቤት ብሎ ነገር የለም:: በፍርዱ እለት ወንጀለኛው ህዝብ ወደ ተሰበሰበበት ሶንጎ (songo) ቀርቦ የመጨረሻ ፍርድ ያገኛል::

የሞት ቅጣት የተበየነበት ከሆነ፣ «ጥብሮ» ከሚባል እንጨት ከነገቷቸው የተመነገሉ ጫፎቻቸው እንደገና መጫወቻ ዱላ ጠፍጠፍ ያለቅርጽ ያላቸው ዱላዎች ለያዙ ጎረምሶች ይሰጣል:: እነዚህ ጎረምሶች ጎሳን መሠረት ባደረገ መስፈርት የሚውጣጡ ናቸው:: ወንጀለኛው ቅጣቱን ወደሚቀበልበት ከሶንጎው ትንሽ ራቅ ወዳለ ሥፍራ ይወስድና ለወገራ በሚያመች ሁኔታ እንዲዘጋጅ ይደረጋል:: እርምጃ እንዲወስዱ ጎረምሶቹ በሐይቻዎች ሲታዘዙ ሁሉም ተጠንቅቀውና ተዘጋጅተው ባንድ ጊዜ ዱላቸውን ያሳርፉበታል:: ሟች ሕይወቱ እስከማይልፍ ድረስ ዱላው የሚደጋገመው በዚሁ ዓይነት አካሄድ ነው:: ቀድሞ ወይም ኋላ ቀርቶ መምታት ተጠያቂነትን ስለሚያስከትል አይፈቀድም:: በመጨረሻም «ወንጀለኛን ሕዝብ ይዞ፣ ህዝብ ፍርድ ሰጥቶ፣ ህዝብ ራሱ ገደለው ይባላል» አበቃ:: ጠያቂም ተጠያቂም የለበትም:: ይህን የመሰሉ የፍትህና ሌሎች ባህላዊ ክንውኖች እስከ 1950ዎቹ መጀመሪያ ድረስ ሲካሄዱ ቆይተዋል (ኦዳ ያኣ 1997፡45)::

የፍትህ መጓደል በአንፃሩ ኢ-ፍትሃዊነት መሥፈኑን ያሳያል:: ታዲያ የጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ለወጣቱ ትውልድ ትክክለኛ ፍርድ የሚያስተምረው እንዲህ ብቻ ሲሆን ነው በማለት አይደለም፣ ይልቁንም ተቃራኒውን ኢፍትሃዊ ክዋኔዎችን በትረካ በመግለፅ እያዝናናና እያዋዛ ቁምነገሩን ያስቀስመዋል:: በዚህ ትረካ ማነው የበደለ ? ማነው የተበደለ? እያለ ትክክለኛ ፍርድ ምን ማለት እንደሆነ እራሱ እንዲያመዛዝን ቦታ ይሰጠዋል:: እስቲ የሚከተለውን ተረክ እንመልከት፤

> *ባንድ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ በጣም የሚዋደዱ ሁለት ጓደኞሞች ነበሩ:: አንድ ቀን ክፉኛ በመጣላታቸው የተነሳ ለገላጋይም አስቸግረው ለየብቻ ይኖሩ ጀመር:: የእነዚህ ሰዎች ጠብ በጣም የከረረ በመሆኑ ለአካባቢው ገላጋዮችም አስቸግሮ ነበር:: የኋላ ኋላ ወደ ሶንጎ 'Songo' ይቀረብ ተባለና ሶንጎ ቀረበ:: ነገሩ ከዚህ ደረጃ እንደ ደረሰም እያንዳቸው ተጠይቀው ምክንያታቸውን ካስረዱ በኋላ ግራ*

*ቀኙ ታይቶ እንዲታረቁ ሲጠየቁ አንደኛው ተስማምቶ «እሺ እታረቃለሁ» አለ፡፡ ሁለተኛው ግን አሻፈረኝ ብሎ በእምቢተኝነቱ ፀና፡፡ በዚህ መካከል ለሰይጣን ስለት አድርጋ ልጅ የወለደች አንዲት ሴት ድንገት መጣችና «እባካችሁ ልጅ መውለድ አቅቶኝ ብቸገር ለሰይጣን ተሳልኩ፡፡ እንዳጋጣሚም ሰምሮልኝ ወለድኩ ታዲያ አሁን ይህን ልጅ ለማን ክርስትና ልስጥ ሁሉም ሰው ጉዳዩን ስለሚያውቅ እምቢ አለኝ» እያለች መፍትሔ እንዲሰጧት ትለምናቸው ጀመር፡፡ በዚህ መካከል ለእርቅ ሲለመን የነበረው ሰውዬ በእምቢታ አቋሙ ፀንቶ እርቁን ረግጦ ወጥቶ ሄደ፡፡ እነዚያ ለአስታራቂነት የተቀመጡት ሽማግሌዎች ሁኔታውን ተመካከሩና ሴትየዋን እንዲህ አሏት፡፡ «ይህን ያንቺን ልጅ ወስደሽ ለዚያ አሁን ከዚህ ወጥቶ ለሄደው ሰውዬ ስጪው ሲጠይቅሽም እነርሱ አዘውኝ ነው በይው፡፡» ብለው ወደርሱ ላኳት፡፡ እርሷም ፈጥና ሰውዬው የሄደበትን አቅጣጫ ተከትላ ስትደርስበት እንደተባለችው 'የእኔ ልጅ ክርስትና አባት አንተ ነህ' አለችው፡፡ እሱም ተመልሶ ወደ ሽማግሌዎቹ መጣና ለምን እንደሆነ ቢጠይቃቸው «በእኛ ባህል በተደጋጋሚ ሲለመን እርቅን እምቢ የሚል ሰይጣን ብቻ ነው፡፡» አሉት፡፡ በዚህ ጊዜ ክፉኛ ደንግጦ ይቅርታ ይጠይቃል፡፡ ቀጥሎም ከጓደኛው ጋር እርቁን ፈጽሞ ወደ ቤቱ ሄደ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምረው እንደዱሮው በሰላም አብረው መኖራቸውን ቀጠሉ ይባላል፡፡*[15]

በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ ሰዎች በሃሳብ ላይጣጣሙ አልፎ ተርፎም ሊጋጩ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሁኔታዎች ሲከሰቱ መፍትሔ አፈላልጎ ሰላም ማስፈን የተለመደ አካሄድ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ትረካ ይዘት እንደሚያመለክተው፣ በሚዋደዱ ሁለት ጓደኛሞች መካከል ጠብ ተፈጥሮ ተለያይተው ይኖራሉ ሁኔታውን ወደ ነበረበት ለመመለስ የአካባቢው ህብረተ-ሰብ ሊሸመግላቸው ቢሞክርም በአንደኛው እምቢተኝነት ሊሳካ አልቻለም፡፡ ነገሩ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ተሸጋግሮ እልባት ሲያገኝ ደግሞ የይቅርባይነት ልብ ኖሮት መታረቅ እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡ ነገር ግን በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ እጅግ ትልቅ ቦታ ያለውን የእርቅ ሥርዓት አሻፈረኝ ብሎ መታበይ እንደማይቻል ሽማግዎች በእምቢተኛው ላይ የወሰዱት ርምጃ ለሌላው ትምህርት ይሆናል፡፡

*በህዳር ወር 1999 ዓ.ም በዲላ ዙሪያ ወረዳ ቱምቲቻ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ጐርሶና ሐዴሞ በተባሉ ጎሳዎች መካከል ህልፈተ-ህይወት ያስከተለ ግጭት ተከስቶ ነበር፡፡ በእርቅ ሥራቱ (ጎንዶሮ) ሲካሄድ ከገዳይ ወገን ስድስት፣ ከሟችም ወገን እንዲሁ ስድስት በድምሩ አስራ ሁለት ሰዎች እንዲገኙ አደረግን፡፡ ከሁለቱ ጎሳዎች ውጭ የሆኑ ደግሞ አሥር ሰዎችን ታዛቢ አስቀመጥን፡፡ ከሁለቱም ወገኖች ገንዘብ ተዋጥቶ አንዲት ዱለቻ (መውለድ ያቆመች ላም) ተገዛች፡፡ እርቁ እስኪፈፀም ድረስ ባዶ መሬት ላይ እየተቀመጥን ችግሩን መረመርን፡፡ ጉዳዩን የሚያውቁ ምስክሮች ሲመጡ በቅድሚያ በእኛ ፊት "ፈጣሪ (ማገኖ) እውነት ያናግረኝ፣ ያየሁትን እንጂ ያላየሁትን አልመሰክርም" እያሉ እውነቱን ይናገራሉ፡፡ በዚህ ዓይነት ጉዳዩን ካጣራንና ሁለቱን ወገኞች በቅድሚያ በቃል ካስማማን በኋላ የተገዛችው ዱለቻ ላም ታርዳ ጎንዶሮ ተደርጎ በቂም በቀል ዳግመኛ ላይፈላለጉ እርቅ ተፈጽሞ ሥጋውም እዚያው ተበልቶ አስታርቀን ተለያየን፡፡ ጉዳት አድራሹ በመንግሥት ቁጥጥር ስር ይገኛል፡፡ ግጭቱ የመጨረሻ እልባት ያገኘው መጋቢት 9/1999 ዓ.ም ነው፡፡ (ሐይቻ አለማየሁ በኮ)*

---

[15] ቀቀቦ ሾታ ነሀሴ 20/1999ዓ.ም ምቾሌ በመኖሪያ ቤታቸው በሁለተኛ ዙር ቃ.መ.

## 4.5. የጌዴኦ ባህላዊ ጋብቻ

ጋብቻ እንደየህብረተ-ሰቡ ባህል የተለያየ ነው፡፡ በአንዳንዱ ህብረተሰብ ውስጥ "አንድ ወንድ ለአንድ ሴት" የሚለው ደንብ የጠበቀ ሲሆን፣ በሌላው ደግሞ "አንድ ወንድ ለብዙ ሴቶች" ወይም ብዙ ወንዶች ለአንዲት ሴት እንዲሆኑ ይፈቅዳል፡፡ ምንም ይሁን ምን ጋብቻ የተጋቢዎች የግል ጉዳይ ሆኖ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ በሆኑ ሁኔታዎች ላይ የወላጆችን ዕውቅናና ተቀባይነት እንዲሁም የህብረተሰቡን ይሁንታ የሚሻ ተቋም ነው፡፡

በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ውስጥ ጋብቻ እንደ ተፈጥሮአዊ ግዴታ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ አግብቶ ልጅ መውለድ፡ በህብረተሰቡ ዘንድ አይቀሬ ብቻ ሳይሆን መፈፀም ያለበት ተፈጥሮአዊ ግዴታ ተደረጎ እንደሚታይ Dagne, (1995:41) ይገልፃል፡፡ ይህም የጋብቻን መንፈሳዊ እሴትነት (Spritual Value) የሚያመለክተና መሆን ያለበት የፈጣሪ 'Mageno' ትዕዛዝ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በህብረተ-ሰቡ ባህል መሰረት በተመሳሳይ ጎሳዎች መካከል ጋብቻ መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡ ከሙሽራው ቤተሰቦች አንፃር ወንድየው በቂ መተዳደሪያ ንብረት (መሬት፣ እንስት፣ ቡና እንዲሁም መኖሪያ ቤት) ሁሉም ባይሆን በከፊል እንዲኖረው ይጠበቃል፡፡ ይህም ለወደፊቱ ሴቷ በምትወልዳቸው ወንዶች ልጆች አማካይነት በሚደርሳት የመሬት ውርስ በእርጅናዋ ጊዜ መጦር ትችላለች ተብሎ ይታመናል፡፡ ጋብቻ የራስን ዘር ከመተካት በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ይዞታንና የማንነት ማረጋገጫ ነው፡፡ "በህብረተ-ሰባችን ባህል መሠረት ካላገቡት ይልቅ ያገቡት ሙሉ የህብረተ-ሰብ አባላት ሆነው ይከበራሉ፡፡ ትልቅ ሰው ለመባል ከዕድሜ ይልቅ ጋብቻ ሚዛን የደፋ ነው፡፡"[16]

ከሁሉም በላይ ደግሞ ልጅ ሀብት ነው፡፡ ምንም የሌለው ድሃ እንኳን ቢሆን ልጅ ለመውለድ ያለው ጉጉት ከፍተኛ ነው፡፡ አንድ ሰው በወጣትነት ዕድሜው ልጅ ወልዶ የእገሌ አባት መባልን እንደ ትልቅ ማዕረግ ይቆጥረዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ ለባልና ሚስት ትዳር መረጋጋት ትልቁ ጉዳይ ልጅ ወልዶ ስም ማስጠራት ነው፡፡ ልጅ ሳይተኩ መሞት ዘርን ማቋረጥ ነው፡፡ ይህ ደግሞ መጥፎ አጋጣሚ ማስከተሉ ብቻ ሳይሆን ሙታንን እንደማስደብ ይቆጠራል፡፡[17] በህብረ-ተሰቡ ውስጥ ልጅ ወልዶ የእገሌ አባት መባል እጅግ የሚያጓጓ መሆኑን የሚገለፀው ቃል-ተረክ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

---

[16] ሐይቻ አለማየሁ ቦኮ ሰኔ 17/1999 ዓ.ም ዲላ ዙሪያ
[17] አታራ ሲዳሞ ኅዳር 22/1999ዓ.ም ዎቻማ ገ/ማ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

*ትዳር መስርተው የሚኖሩ ባልና ሚስት በአንድ ሀገር ውስጥ ይኖሩ ነበር። እነዚህ ተጋቢዎች ዕድሜያቸው ለአካለ መጠን ይድረስ እንጂ ምንም የህይወት ልምድ የሌላቸው የትዳርን ምንነት የማያውቁ ነበሩ። በተለይ ደግሞ ልጅ እንዴት እንደሚያድግ ምንም ዕውቀት አልነበራቸውም። በዚህ ሁኔታ አብረው ሲኖሩ ልጅ ይወልዳሉ። ባካባቢያቸው ያሉ ሰዎች «እነዚህ ሁለቱም ራሳቸው ልጆች ልጅ መውለዳቸው እንዴት አድርገው ሊያሳድጉ ነው» እያሉ ይገረሙ ነበር። የወለደችውን አራስ ጎረቤቶች በባህሉ መሰረት ዩያ Yuuya /እንኳን የልጅ ክብር አገኘሽ/» እያሉ መርቀው። (እንኳን ማርያም ማረችሽ እንደማለት ነው።) ጥቂት አጫውተዋት ለመሄድ ሲወጡ ደግሞ«ልጅሽ የከብት ጭራ ይያዝ፣ የከብት ጭራ ተከትሎ የሚያድግ ይሁን።» እያሉ መሰናበት የተለመደ ነው። ይህንን ምርቃት የሰሙ ባልና ሚስት እጅግ ተደሰቱ። ማታ ማንንም ሳያማክሩ ለብቻቸው ሆነው «እንግዲህ ልጃችን አድጎልን የእገሌ አባት እንድንባል፣ የባለ ወተቷን ላም ጭራ አስይዘን እንልቀቀው፣ ይህን ባናደርግ ምርቃቱን እንዳልተቀበልን ተቆጥሮ ይሞትብናል።» ብለው ተማከሩ። ከጥቂት ቀናት በኋላ «በምርቃቱ መሰረት የልጃቸውን እጅና የላሚቷን ጭራ በገመድ አቆራኝተው ለቀቁት። ላሟ ጭራዋን ወዲያና ወዲህ ባወዘወዘች ቁጥር ህፃኑ ግራ ቀኝ ተላግቶ ሞተ። እነሱም በሆነው ሁሉ በጣም አዘኑ፡ ይባላል፡፤*

ከተረከ እንደምንመለከተው፣ትዳር መስርቶ ልጅ በመውለድ የእገሌ አባት ለመባል ጉጉት ከሁሉ ነገር ቀድሚል። ነገርግን ልጅ ወልዶ፣ እንዴት ማሳደግ እንዴት መንከባከብ እንደሚችሉ ብስለቱ ይጎድላቸዋል። በመሆኑም የመጨረሻ ውጤቱ እነሆ አሳዛኝ ሆነ። የተረከ ይዘት እንደሚያመለክተው፣ አንድ ነገር ከማድረግ በፊት ረጋ ብሎ ማሰብን፣ አርቆ ማስተዋልን፣ ማውጣት ማውረድን የሚያስገነዝብ ነው።


በዚህ ህብረተ-ሰብ ልጅ የሚወደድበት ሌላም ምክንያት አለ። በአገሩ ላይ ረሃብ፣ ድርቅ፣ በሽታ ድንገት የተከሰተ እንደሆን፣ ገና ያላገቡ ደናግል ሴቶችና ወጣት ወንዶች ልጆች በአዛውንቶች ፊት እንዲሰበሰቡ ይደረግና መገኖ ከደታ "Mageno Kahdetta" (ፈጣሪ ልመና) ይደረጋል። ልጆች ኃጢአት ለመስራት ያልደረሱ በመሆናቸው ንፁህ ናቸው። ፈጣሪ እነርሱን አይቶ ይራራልንና ምህረቱን ያወርድልናል። ይህ ከቁጠላ በተጨማሪ ነው ። ከጥንት ጀምሮ በባህላችንም የቆየ እምነት ነው ይላሉ።[18]

በጌዴኦ ባህላዊ ልማድ አንድ ወንድ ኢኮኖሚያዊ አቅሙ እስከፈቀደ ድርስ ብዙ ሚስቶች ማግባት ይችላል። ይህን ልምድ ከሚያበረታቱት አንዱ "አንድ ሚስትና አንድ ዓይን ያለው ሰው እኩል ናቸው" የሚለው አባባል ነው። አንዷ ባትኖር ወደ ሌላዋ ለመሄድ ያመቻል። በመሆኑም ባልየው ራሱን በአንድ ቦታና በአንድ ሚስት ላይ ከመወሰን ይልቅ ሀብትና መሬቱን ለየሚስቶቹ ያከፋፍላል። በሞት፣በፍቺ ወይም በበሽታ ምክንያት ለሚፈጠሩ አጋጣሚዎች አስቀድሞ የመዘጋጀት ስልትም ሊሆን ይችላል።

---

[18] ሐይቻ ማሞ ገደቾ ነሀሴ 15/1998ዓ.ም ዲላ

ILS LIBRARY … UNIVERSITY




*"የረገጥከውና የቆምክበት ቦታ ሁሉ ወርቅና ብር ነው ። ብር ፍለጋ ብለህ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ የለብህም ይሉኝ ነበር አባቴ እኔም ከዚህ ትምህርት አግኝቼ ባለሁበት ሆኜ ጠንክሬ መስራቴን ቀጠልኩ። ይኸው ሀብትም ዕድሜም ሰጥቶኝ ለዚህ በቃሁ።" አቶ ቀቀቦ ሾታ የ100 ዓመት ዕድሜ ባለፀጋ*

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሰፋ ባለ መልክ ሃሳባቸውን ያካፈሉኝ የህብረተ-ሰቡ አውራ የዕድሜ ባለፀጋው አቶ ቀቀቦ ሾታ ናቸው። በ17/10/99 ዓ.ም ምችሌ ሲሶታ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ተገኝቼ ባነጋገርኳቸው ወቅት ከፈረስ ላይ ወድቀው የግራ እግራቸው ጭን መጋጠሚያ በመውለቁ በወጌሻ እየተረዱ እቤት ውለዋል። ረዘም ዘና ያሉ፣ የተደላደለ ሰውነት ያላቸው፣ ከህመማቸው በስተቀር እርጅናው ብዙም ያልተጫናቸው፣ ንቁና ተጫዋች ሰው ናቸው። ስስ ፂማቸውን አሳድገው አንድ ጊዜ ለየብቻ ሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ ላይ አገናኝተው ይገምዷቸዋል። ጨዋታቸው ሁሉ ወደ ድሮ ጉብዝና፣አዳኝነትና አነጣጥሮ ተኳሽነታቸው የሚያደላ ነው። ማንኛውም የተጀመረ የውይይት ርዕስ ሁሉ ይህን ሳይነካ አይቋጭም።

*"መኖሪያዬ በቀድሞ ወናጎ በአሁኑ ዲላ ዙሪያ ወረዳ ምችሌ ቀበሌ ውስጥ ነው። ትዳር ከያዝኩበት ጊዜ አንስቶ እስከዛሬ ድረስ ዘጠኝ ሚስቶች አግብቻለሁ። በጠቅላላው 85(ሰማኒያ አምስት) ልጆች ወልጃለሁ። ከነዚህ መካከል 36(ሠላሳ ስድስት) ወንዶችና 23(ሃያ ሶስት) ሴቶች በድምሩ 59 ልጆች በህይወት አሉ። ካገባኋቸው ሚስቶቼ መካከል የመጀመሪያዋ ብቻ በሞት ስትለይ የቀሩት ቢያረጁም በህይወት አሉ፣ እያንዳንዳቸው የመኖሪያ ቤት፣ የእርሻ ማሳና የቤት ቁሳቁስ የተሟላላቸው ናቸው። አሁን አብሬያቸው የምኖረው ወደ ኋላ ጊዜ ካገባኋቸው ከሦስቱ ጋር ነው። በባህላችን ደንብ ታናሽ ወይም ኋላ የተገባች ሚስት መጀመሪያ የተገባችውን በታላቅነቷ ታከብራለች፤ ትታዘዛታለች። እኔ ከአንደኛዋ ወደ ሌላኛዋ ቤት የምሄደው በየአራት ቀን ቆይታ አንድ ጊዜ ነው። በእያንዳንዱ ቤት የሚፈለገው ሁሉ ስላለ ከእኔ ጋር ይዤው የምሄደው ምንም ነገር የለም። ዓመት በዓል በሆነ ጊዜ በሁሉም ቤት ይደገሳል። እኔም ካንዷ ቤት ትንሽ፣ ከሌላዋም እንዲሁ ትንሽ፣ ትንሽ እየቀመስኩ ሁሉንም አዳርሳለሁ። ተሰባስቦ መጫወት ባስፈለገ ጊዜ ዋናው የመገናኛ ቦታ Angaffa (የመጀመሪያ) ባለቤቴ ቤት ውስጥ ነው የሚሆነው። እስከ ዛሬ ድረስ እኔ አንዷን ሚስቴን ተጭኜ ለሌላኛዋ አላዳላሁም። እነርሱም ተጣልተው ይቅር የተባባሉበት ጊዜ የለም"*

ሲሉ ድሮ በልጅነታቸው የነበራቸውን የልጅ ፍላጎት ማርካታቸውን ገልፀዋል፡፡ ተመሳሳይ መንገድ የሚከተሉት የ60 ዓመቱ ሰው ሐይቻ አለማየሁ በኩም በአንድ ሚስት የተወሰኑ አይደሉም፣ እርሳቸውም "እኔ በየተራ ሁለት ሚስቶች አግብቼ ከሁለቱም አሥራ አራት ልጆች ወልጃለሁ፡፡ ሁለቱንም እየተንከባከባኩ አብረን እንኖራለን" ሲሉ ገልፃዋል፡፡ ከአዛውንቱ የህይወት ልምድና ገጠመኝ የምንገነዘበው ድርብ ጋብቻና ልጆችን አብዝቶ የመውለድ ሁኔታ በህብረተሰቡ ይሁንታን ያገኘ ባህል መሆኑን ነው፡፡

በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ አምስት የጋብቻ ዓይነቶች ይታወቃሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ በጣም የሚዘወተረውና መደበኛ የሚባለው ከዳ "Kadha" (የፈቃድ ጋብቻ) የተባለው የተጋቢዎች ወላጆች ፈቅደው የሚካሄድ የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ የተቀሩት አራቱ የጋብቻ ዓይነቶች ሐዋዴ "Hawadie"፣ ቡታ "boota"፣ ዳላ "dala" እና ኪንጢቾ "kinticho" የሚባሉት ናቸው በማለት Dagne, (1995:39) ይገልፃል፡፡ ስለእያንዳንዱ የጋብቻ ዓይነት ምንነት የተወሰነ ግንዛቤ ይኖረን ዘንድ ለመመልከት ያህል፤ ሐዋዴ-ከቤተሰብ ዕውቅና ውጭ ሁለቱ ተጋቢዎች አስቀድመው በውጭ በመስማማት ከጨረሱ በኋላ ለቤተሰቦቻቸው የሚያሳውቁበት ነው፡፡ ቡታ- አንድ ለአካለ መጠን የደረሰ ወንድ ልጅ ሊያገባት የፈለጋትን ሴት ልጅ በመጥለፍ የሚደረግ ገብቻ ነው፡፡ ዳላ- ባል ሲሞት ወንድየው በእርሱ እግር ተተክቶ ሴትዮዋን አግብቶ የሚኖርበት ሥርዓት ነው፡፡ ኪንቲቾ- ሚስቱ የሞተችበት ወንድ ከሟች እህቶች መካከል አንዷን የሚያገባበት ሁኔታ ነው፡፡ በህብረተሰቡ ባህላዊ ልማድ መሰረት፣ አንድ ወንድ ሚስት ለማግባት ሲነሳ፣ ሀብትና ንብረት የማፍራት ጉዳይ ለጋብቻ የሚደረጉ ዝግጅቶችን ከሚያፋጥኑ ሁኔታዎች መካከል ወሳኝነት ያላቸው ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ባንፃሩ ለጥሎሽ ወይም ለወላጆች የሚደረግ ስጦታ፣ ለሰርግ መሰርጊያ የሚሆን ገንዘብ የሌላቸው ትዳር ፈላጊ ወንዶች በጥንት ጊዜ ይደረግ የነበረው ሥነ-ሥርዓት ቀጥሎ በቀረበው ትረካ እንደምንመለከተው ነበር፡፡

> *በጥንታዊው የጌዴኦ ህብረተ-ሰብ አንድ ለአቅመ አዳም የደረሰ ወጣት ማግባት ለፈለጋት ልጃገረድ የሚያስፈልጉ ወጪዎች መሸፈኛ የሌለው ከሆነ፣ ብልሃት ማፈላለግ ግዴታው ይሆናል፡፡ ይኸውም Warraye[19] (ዋራዬ) የምትባል ወፍ የምትገኝበትን ቦታ ያፈላልጋል፡፡ ይቺን ወፍ እንደምንም ብሎ ይዞ ወይም ገድሎ ከክንፎቿ ላይ ላባዎቿን ነቅሎ በኪሱ ያደርግና ልጅቱን የሚያገኝበትን አጋጣሚ ይጠብቃል፡፡ ልጅቷ ገበያ ስትሄድ ወይም ወንዝ ስትወርድ ጠብቆ ድንገት እርሷ ሳታየው የወፏን ላባ በፀጉሯ ውስጥ ሻጥ ያደርግባታል፡፡ እርሷም አስቀድሞ መጠንቀቅ ነው እንጂ አንዴ የወፏ ላባ በፀጉሯ ላይ መሰካቱን ካየች የእርሱ ከመሆን ሌላ አማራጭ የላትም በባህሉ መሠረት የ 'Warraye' ላባ የተደረገባትን ልጃገረድ ማንም ለጋብቻ እንዳይጠይቅ ደንቡ ይከላከላል ይህን ያደረገ ወጣት ድል በመቀዳጀቱ ልቡ በኩራት ይሞላል፡፡ ምንም የሌለው በመሆኑ፣ በሰንጋ ምትክ እምቧይ ያርድና በተፈለገ ጊዜ አግብቶ ወደ ቤቱ ይወስዳታል፡፡[20]*

---

[19] warraye - ዘወትር እንደልብ የማትገኝ በዓመት ውስጥ በተወሰኑ ጊዜያት ብቻ ብቅ የምትል ብርቅዬ ውፍ ነች፡፡

[20] ቀቀቦ ሾታ ነሀሴ 20/1999ዓ.ም ሁለተኛ ዙር በመኖሪያ ቤታቸው

## 4.6 ባህላዊ የሀዘን ሥርዓት

እንደሌሎች የአገራችን ህብረተ-ሰቦች በጌዴኦም ለሟች የሚደረጉ ባህላዊ የልቅሶና የሀዘን ሥርዓቶች አሉ። አንድ ሰው በሞት ሲለይ እንደ ዕድሜው ወይም የሥልጣን ደረጃው የሚደረግ የልቅሶ ሥርዓት አለ። ስለሟቹ የጎሳ ታሪክ፣ ጀግናም ከሆነ ስለጀግንነቱ፣ ስለሙያው፣ አካላዊ ገፅታው፣ስለ ለጋስነቱና ስለ ቸርነቱ ትዝታዎች እየተወሱ የልቅሶ ግጥሞች ይደረደራሉ።

ሟች ህፃን ወይም ትልቅ፣ ጀግና ወይም ተራ ሰው የመሆኑ ጉዳይ በልቅሶ ሥርዓቱም ላይ ልዩነት ያመጣል። ይህ ብቻም ሳይሆን የቀብር ሥርዓቱ ዝግጅትም ይለያል። ልጅ ሲሞት አስከሬኑን እጉድጓድ ውስጥ የሚያስቀምጠው አባት ነው። ከዚያም አፈር ይመለስበትና ሥርዓቱ ያበቃል። ለልጅ ልቅሶ ዳስ አይሰራም። ድንኳን አይጣልም። ከቀብር መልስ ተቆልቶ በቅቤ የታሸ ቡና የልጁ አባትና እናት እንዲበሉ ይደረጋል። ይህም ተዝካር መሆኑ ነው። ከዚህ በኋላ እናትም ሆነች አባት፣ ከልጅነት ጀምሮ እስከ ደረሱበት ዕድሜ ደረጃ ድረስ፣ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ፣ የፈፀሙት ጥፋት ቢኖር እንዲናዘዙ ይገደዳሉ። ሟች ሴት ልጅ ከሆነች በእናት በኩል፣ ወንድ ልጅ ከሆነ ደግሞ በአባት በኩል ለየብቻ ምርመራ ይደረግባቸዋል። በህብረተ-ሰቡ ልማዳዊ እምነት መሠረት እንደ ጥፋተኛ የሚያስቆጥሩት ቀደም ሲል ፋጬ በሚለው ርዕስ ውስጥ የተጠቀሱት ሲሆኑ፣ መፍትሄውም እንደተመለከተው፣ በይፋ በመናዘዝ ነው ሲሉ ጥላሁን ኢቢዶ (1982፡13-15) ጥናታቸው ውስጥ ገልፀዋል።

በሌላ በኩል ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ የሚጋራው ተጨማሪ አስተያየት እንደሚያመለክተው ደግሞ፣ አንድ ሰው በሽተኛ ሆኖ ህመሙ ሲፀናበት ኃጢአቱን ተናዞ ሥራተ-ንስሐ መፈፀም አለበት። ህይወቱ ሲያልፍ ባጠገቡ የሚገኝ የቅርብ ዘመድ በአፉ ቅቤ ይጨምራል። ይህም ሟችን በሰላም የመሰናበቻ ምልክት ነው። ከዚህ በኋላ የግንዘት ሥርዓት ይፈፀማል። ልቅሶ ከመጀመሩ በፊት የቤቱ የቀኝ ጉበን ይፈርሳል። ሰውየው በህይወት እያለ የሚለብሰው ቡሉኮ ከውጪ በኩል ጣሪያው ላይ ይደረጋል። ሟች ሴት ከሆነች የሚፈርሰው የግራው ጉበን ነው። ከየአካባቢው ልቅሶ የሚመጣ ወይም በአካባቢ የሚያልፍ ሰው ሟች ማን እንደሆነ ሳይጠይቅ በነዚህ ምልክቶች ብቻ ማወቅ ይችላል። እነዚህ ዝግጅቶች እስከሚፈጸሙ ድረስ የሚካሄደው ድምፅ አልባ ልቅሶ Fixxssaa[21] (ፊጤሳ) ነው። የሚፈለገው ነገር ሁሉ ተደርጎ፣ ዘመድ ተሰባስቦ፣

---

[21] Fixxssaa -ድምፅ ሳያሰሙ የሚደረግ የለሆሳስ ልቅሶ ነው።

ከተለቀሰ በኋላ አስከሬኑ ወደ ቀብር ሲሸኝ፣ ባል ከሆነ፣ ሚስቱ ከወገቧ በላይ ራቁቷን ሆና አንገቷ ላይ ገመድ አስራ ወደ ቀብር ትሄዳለች ሴት ከሆነች ደግሞ ባልየው የሚለብሰውን ቡሉኮ ጫፍ ጫፉን ቋጥሮ ይሄዳል፡፡ በነዚህ ምልክቶች ሀዘንተኞቹን ለይቶ ማወቅ ይቻላል፡፡[22]

ከቀብር በኋላ ማንም ሰው ቀጥታ ወደ ቤቱ ከመመለሱ በፊት ሟች ቤት ደርሶ እጁን መታጠብ አለበት፡፡ አለበዚያ ዝም ብሎ ከሄደ በገዛ እጁ ሞትን ወደ ራሱ ቤት እንደጠራ ይቆጠራል፡፡ ሲሉ ሐይቻ ሐሜሶ ኮሬ ይገልፃሉ፡፡ ይሁንና የሟች ሁኔታ በዚህ ካበቃ፣ የሀዘንተኞችን ዕጣ ፈንታ ደግሞ ቀጥለን እንመልከት፡፡

የሰው ልጅ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ያረጃል፣ ይሞታል፡፡ ይህን ተፈጥሮአዊ ሁኔታ የተለያዩ ህብረተ-ሰቦች በተለያየ ሁኔታና ሥርዓት ይገልፁታል፡፡ መወለድን በሃሴት እንደሚቀበለው ሁሉ፣ ሙትን በልቅሶና በሀዘን ይሸኙታል፡፡ ሟችን ለመሸኘት በተለያዩ ህብረተሰቦች የተለያዩ ዝግጅቶችና ሥርዓቶች የመደረጋቸውን ያህል፣በአንዳንዱ ህብረተሰብ ወስጥ ደግሞ ከሟች ጋር አብረው ከሚኖሩት አንዱ (ባል ወይም ሚስት ሊሆኑ ይችላሉ) ምድራዊ ዋጋ የሚከፍሉበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በጥንታዊ የጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ውስጥ፣ የሀዘንተኞች ዕጣ ፈንታ የሚከተለውን ይመስል ነበር፡፡

> *ባሏ የሞተባት ሴትም ሆነች ሚስቱ የሞተችበት ወንድ Bussedie[23] (ቡሰዴ) ይባላሉ፡፡ ሴቷ ቡሰዴ ከወንዱ ቡሰዴ የበለጠ ተፅዕኖዎች አሉባት፡፡ ሴቷ ባሏ ከሞተበት ዕለት አንስቶ "ነፃ" እስከምትወጣበት ጊዜ ድረስ፣ መኝታዋ መሬት ላይ ነው፡፡ሰው ቤት ስትሄድ እንደሰው ተቆጥራ መቀመጫ አይሰጣትም፡፡ ሰውነቷን አትታጠብም፡፡ ጥፍሯን አትቆረጥም፡፡ በሀዘኗም እንኳን ፀጉሯን የሚላጫት ካለ የሟች ወንድም አለበለዚያም የቅርብ ዘመድ ነው፡፡ ባጠቃላይ በዚህ ጊዜ ከማህበራዊ ህይወት የተገለለች ነች ለማለት ይቻላል፡፡ ይህች ሴት ይህን ከመሰለ የመገለል ኖሮ የምትላቀቀው ከተዝካር (አንድ ዓመት) በኋላ ነው፡፡ የሟች ተዝካር ከወጣ በኋላ ገላዋን ታጥባ፣ በሰውነቷ ላይ ሁሉ የሚገኘውን ፀጉር ላጭታ ወደ ቤቷ ተመልሳ፣ የሀዘን ልባሷን ቀይራ፣ ተቀባብታ ራቅ ወዳለ አካባቢ ትሄድና ሁለተኛ መገናኘት ከማትችለው ሰው ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ፈጽማ ትመለሳለች፡፡ ከዚህ በኋላ "ነፃ' ተብላ ከተቀረው ህብረተ-ሰብ ጋር በመቀላቀል የተለመደውን ህይወቷን ትቀጥላለች፡፡እነዚህ የተጠቀሱት የማግለል ተግባራት ለወንዱ ቡሰዴም የሚሰራ ነው፡፡ ሆኖም ወንዱ የሴቷን ያህል ክብደት አይታይበትም፡፡[24]*

---

[22] ሐይቻ ሐሜሶ ኮሬ ነሀሴ 15/1998ዓ.ም ዲላ ሶንጎ

[23] Bussedie- በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ባህልዊ አስተዳደር ባል ወይም ሚስት በሞት ሲለይ ከማንኛውም ማህበራዊ ኑሮ የተለየ/ች ሰው ነው፡፡

[24] አሰገደች ነጋሽ ነሀሴ 16/1998ዓ.ም ዲላ

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ በሀዘንተኞች ላይ የሚደርስባቸው ማህበራዊ ተፅዕኖ እጅግ ከባድና አሰቃቂ እንደሆነ ማየት ይቻላል። ሐዘንተኛው/ዋም በንፅህና እጦት በሚፈጠር ችግር ሊደርስ የሚችል አደጋና ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ከህብረተሰቡ ተገልሎ/ላ መቆየት፣ በራሱ የሚያደርስባቸውን ሥነ-ልቡናዊ ጫና መገመት ይቻላል።

በዚህ ጥናት ጥኩረት የተሰጣቸውን ጥቂት የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓቶችን ተመልክተናል። በመቀጠል ደግሞ ስለዝረው ቃል ተረኮቻቸው መረጃ አቀባዮች የሰጧቸውን አስተያየቶች እንመልከት።

## 5.0 የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች በመረጃ አቀባዮች ግንዛቤ

ቃል ተረኮች ጥንታዊ የሰው ልጅ ቅርሶች ሲሆኑ፣ ህልውናቸው የሚታወቀው በክዋኔ፣ በቃላዊ ተስተላልፎና በታዳሚዎች መኖር ነው። ቃል ተረኮች ያንድን ህብረተሰብ ልማዳዊ ሥርዓት ለማጠንከር ይነገራሉ። የሚቀርቡትም የማህበረ-ሰቡን ዕለታዊና መደበኛ ተግባራት በማያውኩበት ሰዓት እንደሆነ፣ ሁሉም የሚያነሷቸው ነጥቦች መሆናቸውን ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳኑ ውስጥ ተመልክተናል። ነጥቦቹ በሁሉም ዘንድ መነሳታቸው ደግሞ ሁሉም ተመራማሪዎች የሚጋሯቸው አስተያየቶች እንደሆኑ ለመረዳት ይቻላል።

ከላይ ነጥብ በነጥብ የተጠቀሱትን ግንዛቤዎች መሰረት አድርገን ወደ ጌዴኦ ህብረተሰብ ዝርውቃል ተረኮች ስንሸጋገር ደግሞ፣ ዋና መሰረታችን ከሰዎች የምናገኛቸው መረጃዎች ናቸው። መረጃ አቀባዮች በዘመናቸው የሚያውቋቸውን፣ የሚያምኑባቸውን፣ የሚከውኗቸውንና፣ የዘመናቸውን ገጠመኞች ከሚገልፁባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መካከል አንዱ፣ ቃለ-መጠይቅ እንደሆነ በብዙ ተመራማሪዎች የሚታወቅ ዘዴ ነው። ስለሆነም ከመረጃ ሰጭዎች ጋር ፊት ለፊት እየተገናኙ በመወያየት ስለ ባህሉ ብቻ ሳይሆን በባህሉ ውስጥ ስለሚገኙ ልዩ ልዩ ትዕምርቶችም (symbols) ትርጉም ሰፊና ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ሊያስገኝ እንደሚችል ይታመናል ።

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ቃለ-መጠይቆች በጽሁፍ ተዘጋጅተዋል። (አባሪውን ይመለከቷል)። በተጨማሪ፣ በጥያቄና መልሱ ሂደት ውስጥ እዚያው በዚያው የተፈጠሩ ተጨማሪ ጥያቄዎችም እንደነበሩ ሊታወቅ ይገባል። ከሌሎች መረጃ አቀባዮች በተለይም ከፍ ያለ ዕውቀትና ችሎታ አላቸው ተብለው ከሚገመቱ ሰዎች የሚፈለጉ መረጃዎች የተሰበሰቡት ደግሞ በፅሁፍና በድምፅ (በካሴት) በመጠቀም ነበር።

በዚህ ምዕራፍ የተካተቱት ዝርዝር ሀሳቦችም የተገኙት ከራሳቸው ከመረጃ ሰጪዎች አንደበት ነው። ቃለ ምልልሶቹ የሚያካትቱት ከርሰ ጉዳዩ ጋር ቀጥታ ግንኙነትያላቸውንና አንኳር አንኳሮቹን ብቻ እንጂ የተነፈሱትን ሁሉ አያጠቃልልም። ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡላቸውን ጥያቄዎችና እነርሱም የሰጧቸውን መልሶች ከዚህ ቀጥሎ፣ በየተራ እንመለከታለን።

IES LIBRARY

1. አንድን ተረት ለማቅረብ/ለመናገር የሚያነሳሱ ምክንያቶች ምንድናቸው?

ተረትን ለመተረት አጋጣሚ አለ ተስተላልፎ አለ፣ ክዋኔ አለ ተደራሲያን አሉ። እነዚህ ነገሮች ይኖራሉ። ስለዚህ ተራቹን የሚገፋፋው አንድ ሁኔታ ነው። ባንድ አካባቢ የመሰብሰብ ሁኔታ በሀዘን ወይ በልቅሶ ምክንያት ወይም ደግሞ በሰርግ ጊዜ ሊሆን ይችላል። በአካባቢ ወይም አንድ ነገር ተሰርቆ ወይም አውጫጭኝ ሊኖር ይችላል። ሰዎች ሊሰበሰቡ ይችላሉ ስለዚህ የተለያዩ ባህርያትን የሚያቅፉ ሰዎችን ህይወት ለመግለጽ ሲባል ተረት ይተረታል። ለማስታረቅም ሲባል ተረት ይበረታታል። አንድ ሰው ከተጣላ ወይም ደግሞ አንድን ሰው ከሌብነት ለማንፃት ሲባል፣ እንደገና ደግሞ ሐሰት የሚናገረውን ሰው ሞት መኖሩን መጥፎ መሆኑን ወደ እውነት እንዲመለስ ለማድረግ ይነገራል። እስከነተረቱ ምንድነው የሚባል ምሳሌ አለ። “ዳኞች ወንዙ ውስጥ ያለውን ስር እንኳን ይቆርጣሉ” እንደሚባለው የተደበቀውንና ማንም ሰው ማወቅ የማይችለውን ነገር በተረት አማካይነት ጎርጉረው ያወጣሉ። እንደነዚህ ያሉ ተረቶች በአጋጣሚ የሚተረቱት ናቸው ለማለት ነው።

ስለዚህ ተራቹ ማነው? በዚህ አካባቢ ምናልባት እንደሽማግሌ ሆኖ ለመምከር የሚፈልግ ሰው ወይ ደግሞ ለማስተማር የፈለገ ሰው፣ እና የተዳፈነ የህብረተ-ሰቡን አንድ ጥበብ ገፍፍቶ ለመናገር ሲል የሚተርክ ሰው ሊሆን ይችላል። ይህ ሰው አንደበተ ርቱዕ ሊሆን ይችላል። ዋናው እንግዲህ ዖታው ምንድነው? ብለህ ከጠየቅህ <u>ባብዛኛው በጌዴኦ ብሔረሰብ ተራኪዎች ወንዶች ናቸው።</u> (ስርዝ የተጨመረ) ዕድሜ ደግሞ እንደሁኔታው ነው። አሁን ለምሳሌ አረጋውያን ይኖራሉ፣ መካከለኛ ዕድሜ ያላቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ወጣቶችም ይኖራሉ፤ ወጣቶች ግን በተለይ ከብቶች ሲያግዱ ከብት በሚያግዱበት ጊዜ በተለይ ዘፈን ይዘፍናሉ፣ ዜማዎችን ይፈጥራሉ። እንደገና ተረቶችን ይተርታሉ። በአጋጣሚ ትላልቆቹ ለትናንሾቹ ለማስተማር ሲባል ነው። ዋናው እንግዲህ እዚያ በእረኝነት ቦታ ልጆች ከቤት የሰሟቸውን እርስ በርሳቸው ያወራሉ በዚህ ዓይነት ዖታና ዕድሜ ይኖራሉ ማለት ነው።

በሶንጎ ከሆነ አደባባይ ስለሆነ ያው ቅድም እንደነገርኩህ ከሥራ መልስ ነው ተረት የሚተረተው ጥበብ ማስተማሪያም የሆነ እንደሆነ ከሥራ በኋላ ነው። አሁንም ቢሆን ወንዶች ብቻ ናቸው። ለሴቶች የተሰጠ ባህል አይደለም። በአኮመኖዬ ሥርዓት መገርሰስ በጎሳሎ የተሰጠ ሥርዓት አለ። ያ ህግ የወንዶችን የበላይነት የሚያሳይ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ ያ የጎሳሎ ደንብ serra እስካሁን ድረስ እየሰራ ያለ ነው።

2- በጌዴኦ ህረተሰብ ውስጥ ተረቶች ከየት ተገኙ/መጡ ይባላል?

ተረቶች ከአባቶች የተወረሱ ናቸው ይባላል። ከቅድመ አያቶች ይወረሳሉ ዋቤኮ (Wabeko) የሚባሉ አሉ። ዋቤኮ ማለት ጥበበኞች ማለት ነው። እነሱ ፈጥረውም የሚናገሩ ናቸው። ከአባቶች ከአያቶች ከቅድመ አያቶች ሲያያዙ የመጡ የሚወረሱ ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ እንጂ በአጋጣሚ በአንድ ጊዜ ብቻ



IES LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

*የሚፈጠሩ አይደሉም ምናልባት ወጥ ላይሆኑ ይችላሉ። ከሰው ወደ ሰው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ እየነቀሰ፣ እየጠበበ ይሂድ እንጂ የባህሉን ማንነት የሚገልጽ ተረት ሊኖር ይችላል።*

*ተረት ሁልጊዜም በመልመድ ነው የግድ ት/ቤት ገብተህ አስተማሪ ቀጥረህ መፃህፍት ተዘጋጅቶ እንደመደበኛ ትምህርት የሚሰጥ አይደለም። በመልመድ ነው። መልመድ ሲባል የትኛውም ቦታ በእረኝነት፣ ወንጀል ሰርተው ጫካ የተደበቁ ሰዎች እንኳን ቁጭ ሲሉ ልዩ ልዩ ተረቶችን ያወራሉ። ተረት የሚቀርብበት ቦታ የተወሰነ አይደለም።*

### 3- በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ተረት መናገር መቼ የተጀመረ ሂደት ነው?

*ተረት መተረት በጣም የቆየ ነው። ዛሬም በገጠር አካባቢ ይሰራበታል። በተለይ በገጠር ለማስተማሪያነት የሚያገለግል ነው።*

### 4- ተረት የሚነገርባቸው ቦታዎችስ?

*ቦታዎቹ እንግዲህ በእረኝነት ቦታ፣ በጫካም፣ ማታ ማታ ደግሞ የደከመውን አእምሮ ለማሳረፍ ቁጭ ብለው አባት ለልጁ ይነግራል። በተለይ በቤት ውስጥ የሚነገሩ ተረቶች አስተማሪዎች፣ መካሪዎች ናቸው። ከሚነገሩ ተረቶች ልጆች ትምህርት አግኝተው ራሳቸውን እንዲያስተካክሉ ለማድረግ ነው።*

*ለምሳሌ አንድ ልጅ ሰነፍ ከሆነ ስለ ስንፍና የሚገልጽ ተረት ይተረታል ጎበዝ ከሆነም ጀግንነቱን፣ ወንድነቱን፣ አልበገር ባይነቱን፣ እነዚህን ሁሉ የሚገልፁ ተረቶች ይተረታሉ ። በተለይ ደግሞ ለወንዶች ዕድሜያቸው ወደ 16 እና በላይ ሆነው ነጠር ነጠር የሚሉ አሉ አይደለም፤ አልታዘዝም የሚሉ፣ እነዚያን ለመምከር ለማስተማር የሚነገር ተረትም ይቀርባል። ተረት በወላጆች፣ ተረት በአረጋውያን ተረት በእረኞች ተረት በአካባቢ በሶንጎ ሲቀመጡ ይነገራል።* [25]

### 5- የጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ተረኮች ምን ምንድ ናቸው?

*'Xingo' የሚባለው አንድ የሥነ-ቃል ዘርፍ ነው። ህብረተ-ሰቡ ይህን የሥነ-ቃል ዘርፍ ለምን ይጠቀምበታል? ብለን ስንጠይቅ የዕውቀት አድማሱን እንዲያሰፋና በአንዳንድ አሳሰፈላጊ ድርጊቶች ሕዝቡ በሚጋጭበት ጊዜ ያበዚህ ዙሪያ ለቀረቡልኝ ጥያቄዎች አንዳንድ ነገሮችን መግለጽ እሞክራለሁ። ሥነ-ቃል ከሁሉም ደግሞ ንን ግጭት ለማስወገድ በየመሃሉ በማስገባት ወደ ተኣማኒነት ወይም ተጨባጭ መረጃ በመስጠት ህዝብን በማስማማት ሥራ የሚሰራ ይሆናል።*

[25] ጥላሁን ኢቢዶ ስለ ጌዴኦ ቃል ተረኮች ቃለ መጠይቅ ነሐሴ 18/1998ዓ.ም ዲላ ካሴት ቁጥር 1/ለ ገፅ ( 2–6 )

*Xingo መክፈቻም አለው መዝጊያም አለው:: Xingo ዝም ብሎ የሚቀርብ አይደለም ህዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ይህን ዕውቀት ትፈልጋላችሁ ወይ በሚል ዓይነት ተናጋሪው ይጠይቃል እነርሱም ከተስማሙ እርሱ ይቀጥላል:: አድማጮቹ ፈቃደኛ መሆናቸው ከተረጋገጠ አቅራቢው ይቀጥላል:: በመጨረሻም እኔ የራሴን ጨርሻለሁ እናንተም ተናገሩ ጨምሩ ይላቸዋል::*

## 6- በጌዴኦ ህብረተሰብ ቃል ተረክ ላይ ከ Xingo ሌላ የሚታወቅ አለወይ?

*በዚህ ህብረተ-ሰብ ውስጥ ከ Xingo ሌላ Mammassa (መማሳ) አለ እንዲሁም Hibbo (ሂቦ) (እንቆቅልሽ ማለት ነው) አሉ:: ዋናዎቹ ክፍፍሎች (ምድቦች) እነዚህ ናቸው:: ህብረተ-ሰቡ የሚጠቀምባቸው በአብዛኛው እነዚህ ናቸው:: በአብዛኛው ሽማግሌዎች በ Songo ሲቀመጡ የሚጠቀሙባቸው ናቸው::በእኛ ህብረተሰብ ውስጥ ሶንጎ ማለት አስተዳደራዊ አካል ነው:: በጥንታዊ የጌዴኦ ህብረተ-ሰብ የራሱ ‹‹ጽ/ቤት›› በመሆኑ የሚታወቀው ይኸው ሶንጎ ነው::*[26]

## 7- በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ባህል መሠረት ተረቶች የሚተረቱት የት ነው?

*ተረቶች የሚተረቱት ሽማግሌዎች በተገኙበት፣ አዋቂዎች ሁሉ ባሉበት ተረቶች ይነገራሉ:: በሶንጎ ለዳኝነት ሽማግሌዎች የሚቀመጡበት፣ ታላላቅ ሰዎች የሚገኙበት አደባባይ ነው:: በዚህ ቦታ የተጣሉትን የሚያስታርቁበት፣ አንዳንድ ጊዜ ከሥራ መልስ እዚያ ተቀምጠው ዕረፍት በሚያደርጉበት ወቅት ተረቶች ይነገራሉ፡*

## 8- የተረቶች ሲያሜ ወይም የራሳቸው መጠሪያ ካላቸው ምን ምን ይባላሉ?

*ለልጆች የሚሆኑ በቤት ውስጥ የሚነገሩ 'Xingo' ይባላሉ:: እነዚህ አባቶች ልጆቻቸውን እንዲማሩ ለማድረግ የሚነገሩ ናቸው:: Xingo ማለት እግዲህ ካለፉት አባቶች ተላልፈው የመጡ ነገሮችን ለልጆቻቸው እያጫወቱ እንዲማሩ፣ ዕውቀት እንዲቀስሙ፣ ብልህነትና ጥበብን እንዲለምዱ የሚያደርጉበት ነው::*

*አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ አዋቂዎች ትልልቅ ሰዎች በተገኙበት ሽማግሌዎች በተቀመጡበት የሚነገሩት 'Mammasaa' መማሳ ይባላሉ:: Hibbo "እንቆቅልሽ" የሚባሉም አሉ::*

## 9- ተረቶች ሲነገሩ ምን የተለየ ዝግጅት ይደረጋል?

*በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ተረት ለመናገር ምንም የሚዘጋጅ ነገር የለም:: ዋናው ነገር የሚፈለገው የሰውዬው ዕውቀት ነው:: ይህም ሰውዬው በረጂም ጊዜ ውስጥ የሰበሰበው ነው:: የሰው ምርጫም አለ እገሌ አዋቂ ነው፣ እገሌ እንዲህ ነው፣ የሚባል ነገር አለ:: አዋቂ ከሆነ የሚናገራቸው ነገሮች ሁሉ 'ተረት' ሆነው*

---

[26] ደግፌ ሀብቴ ቃለ መጠይቅ ሰኔ 18/1999ዓ.ም ዲላ ካሴት ቁጥር 7/ለ ገፅ 21.

*ይቀርባሉ። አዋቂነት የሚታየው እዚያ ላይ ነው እንጂ የተለየ ነገር አይኖርም። ተረት ከአዋቂዎች የሚገኝ ነገር ነው። ነገር ከሚያውቁ (gaffe) ሰዎች የሚገኝ ነው። ተረትን ከአባት፣ ከእናት ወይም በወሬ ሲተላለፍ የመጣውን ይዘው የሚያቆዩ ሰዎች አሉ።*

*አንዳንዶቹም ተረት እንናገራለን ብለው የሰሙትን ብቻ መልሰው የሚናገሩ አሉ። ይህ ግን ተቀባይነት አይኖረውም። ለተረት ዋና ዋና ሰዎች አሉ። እገሌ እንዲህ አለ፣ እገሌ እንዲህ አለ፣ ብለው አሳድረው አቆይተው የሚናገሩ ሰዎች አሉ።*

## 10-የተረት ተናጋሪ ሰዎች ሲናገሩ እንዴት ነው? እንዴት ይከወናሉ?

*ተረት ለመናገር የተለየ አካላዊ እንቅስቃሴ አያደርጉም። በተቀመጡበት ይናገራሉ እና አድማጭ ጆሮ ሰጥቶ በደንብ ያዳምጥ እንጂ ልዩ እንቅስቃሴ የለም። እንቅስቃሴ የሚኖረው እንደፉከራ ወይም ትልቅ ሰው ሲሞት በእንቅስቃሴ እንዲህ ነበር፣ እንዲህ አለው፣ በዚህ ይታወቅ ነበር፣ እያሉ ያለፈውን እያነሱ ቤተ-ሰብን ለማሳዘንም ወይም የሰውዬውን ስም ከፍ ለማድረግ የሚናገሩበት ጊዜ አለ።*

## 11-አድማጮች እነማናቸው?

*አድማጮች ሁሉም የህብረተሰብ አባላት ናቸው። ወንዶች ባደባባይም፣ በሶንጎም፣ በሥራ ቦታም፣ በእረኝነት ቦታም ይሰማሉ። ሴቶች ግን በልቅሶ ቦታ ሲሰበሰቡ፣ በህዘን ቤት ውስጥም ሲሰበሰቡ፣በሰፊው በትኩረት ይሰማሉ። በየቤት ውስጥ የሚነገሩት ግን ለሁሉም ለቤተ-ሰቡ አባላት ለወንዶችም ሴቶች ልጆችም በጋራ የሚቀርቡ ናቸው። በቤት ውስጥ በተለይ ለልጆች የሚቀርቡት 'Xingo' ተረቶች በአውሬዎችና በእንስሳት እየመሰሉ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ ተረቶች በውስጣቸው ትምህርት ያዘሉ ናቸው። አዋቂዎቹ በእነሱ ውስጥ የነበረውን ወደ ልጆቻቸው የሚያስተላልፉት በተረት በመጠቀም ነው።*

## 12-በጌዴኦ ህረተሰብ ተረቶች ለምን ይጠቅማሉ ተብሎ ይታመናል?

*አዎ አሁን እኔ የምናገረው የድሮውን ነው። በአሁኑ አስተሳሰብ ተረት በጣም እንደሚጠቅም አድርገው ነው የሚወስዱት። የድሮዎቹ እንዴት ያሰባሉ? ስንል የድሮዎቹ ሰዎች እንደዕውቀት አድርገው ነው የሚወስዱት። ሌላ መጽሐፍ የለም። በጽሑፍ የሚያስቀምጡት ምንም ነገር የለም። ግን በዚህ ባንደበታቸው ባነጋገር እገሌ ከየት መጣ? ይህ ነገር እንዴት ተፈጠረ? እያሉ ነገር አዋቂዎች ጨዋታ አዋቂዎች የሚያቀርቡት ነው። ተረቶች የዕውቀት፣ የልማድ ማስተላለፊያዎች ናቸው።*

*እንደታሪክ የሚነገሩም ስላሉ ከአያት ከአባት እየተያያዙ ወደ ልጅ የሚተላለፉበት ነው። ተረቶች በዕድሜ ከፍ ባሉ፣ ሽማግሌዎችና አዛውንቶች ይነገራሉ።*



IES LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

*በተለይ 'Mammassa' እርቅ በያዙበት ወቅት ሁለቱን ወገኖች የሚያስታርቅ ያዋቂዎች ተረት ይቀርባል። "በዚያን ዘበን"፣ "በዚህ ጊዜ ... እንዲህ ሆኗል" እያሉ ይናገራሉ።*

**13-ጉረቤቶች እየተገናኙ ተረቶችን የሚያዳምጡበት ሁኔታ አለ ወይ?**

*በጌዴኦ ሀረተሰብ ተረት ለማድመጥ ብለው ቀጠሮ አይዙም። ነገር ግን ጉረቤቶች ሁል ጊዜ በልቅሶም፣ በሠርግም ስለሚገናኙ በተገናኙበት ሁሉ ተረትን ሊያወሩ ይችላሉ ግን ሆን ብለው ለዚህ ነገር ቀጠሮ አይዙም።*

**14-በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ውስጥ የተረኮች መከወኛ ቦታና ጊዜ (መቼት) አስመልክቶ ተረቶች የአደባባይና የቤት ውስጥ መሆናቸውን ገልፀውልኛል። እስቲ በሀዘን ቤት ስለሚደረጉ/ስለሚነገሩ ተረቶች ይንገሩኝ?**

*በልቅሶ ላይ በተለይ ከቀብር በኋላ ከሆነ በጨዋታ የሚቀርብ/የሚነገር ነው። ይህም ሁኔታው የሚፈጥረው ነው። በተለይ ደግሞ በሀዘን ቤት የሚነገረው ሰዎችን ለማፅናናት፣ ለማረሳሳት ሲባል ሃሳባቸውን አቅጣጫ ለማስለወጥ ነው። ሰዎቹ ሀዘኑን እንዲረሱ የሚደረግበት ነው።[27]*

*ሲሉ ይገልፃሉ።*

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ፣ቃልተረኮች በጌዴኦ ህብረተሰብ ውስጥ እንዴት ይቀርባሉ? መቼ ይቀርባሉ? የት ይቀርባሉ? ለሚሉ ጥያቄዎች ከመረጃ ሰጭዎች የተገኙ ምላሾችን እንመልከት።

## 5.1 የጌዴኦ ቃል ተረኮች ክዋኔና መቼት

በህብረተሰቡ ውስጥ የሚነገሩ ቃል ተረኮችን ክዋኔና መቼት ለማወቅ በተደረገ እንቅስቃሴ፣ ጠቃሚ አስተያየቶችን ለመሰብሰብ የተቻለው፣ በጽሑፍና በቃል (አባሪውን ይመለከቷል) ነው። በቡድን የሚደረጉ ውይይቶች ጠቃሚ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ሲሆኑ፣ የተደበቁ ነገሮች ቢኖሩ እንኳን በግልጽ እንዲወጡ ይረዳሉ። ከዚህ በተጨማሪ የተጠኚውን ህብረተ-ሰብ ባህል ጠለቅ ብሎ ለመረዳት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ Mullen, (1992:14-15)። ክዋኔ የሥነ-ቃል መሠረታዊ ባህርይ ነው። ባንድ ባህል ውስጥ እንኳን ለተለያዩ የሥነ-ቃል ዓይነቶች ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ የክዋኔ ስልቶች ሊኖሩ ይችላሉ በማለት Finnegan, (1976:3-5) የሙሉንን

[27] ሽንጡ ሶሌ ቃለ መጠይቅ ሰኔ 18/1999ዓ.ም ወናጎ ከተማ ካሴት ቁጥር 7/ሀ ስክርብ ገፅ (13–20)

አስተያየት ታጠናክራለች። ተረቶች ከተራቶች አንደበት እየፈለቁ ለታዳሚዎች የሚነገሩ ቃላዊ-ጥበባት እንደመሆናቸው ለተሰተላልፎኣቸውም አንደኛው ምክንያት ይኸው ቃላዊነታቸው ነው።

በሌላ በኩል ክዋኔ እንደ ህብረተ-ሰቡ ባህልና፣ እንደ ሥነ-ቃሉ ቅርጽ የሚለያይ እንደመሆኑ መጠን የተሳታፊዎቹም የተሳትፎ መጠንና አስተዋፅኦ እንደዚሁ ይለያያል። በተግባር ሲከወኑ ለማየት ተፈጥሮአዊ መቼቱ በማይፈቅድበት ሁኔታ በሰው ሰራሽ (Artificial) ዘዴ በመጠቀም ያገኙትን መሰብሰብ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው።

የቡድን ውይይት፣ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ሆኖ ግልጋሎት ላይ የዋለ መሳሪያ ነው። በዚህ ጥናት ያካባቢው (የጌዴኦ) ተወላጆች የሆኑና ባህሉን የሚያውቁ ሰዎችን መልካም ትብብር በመጠየቅ፣ ቀደም ተብሎ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ የተደረገበት አካሄድ ነበር። ለዚህም ምክንያቱ፣ እነዚህ ሰዎች ልምዳቸውንና ገጠመኞቻቸውን መሰረት አድርገው፣ የተሳሳተውን እንዲያስተካክሉ፣ የጎደለውን እንዲሞሉ፣ ባጠቃላይ ይሁንታቸውን ለማግኘት ሲባል የተደረገ ነበር። በዚህ እሳቤ መሰረት፣ ከዞኑ የተለያዩ ወረዳዎች ተውጣጥተው በዲላ ዩኒቨርሲቲ የ1999 ዓ.ም የክረምት ትምህርት ፕሮግራም ተሳታፊዎች ውስጥ አስራ አምስት ያህል ተባባሪዎች በዞኑ የባህልና የቋንቋ ኤክስፐርት በአቶ ደግፌ ሃብቴ አስተባባሪነት ለቡድን ውይይት ፈቃደኝነታቸውን ቢገልፁም በአካል የተገኙት ግን አስራአንድ ብቻ ናቸው። ይህም ሊሳካ የቻለው፣ አስተባባሪው ራሳቸው የፕሮግራሙ ተሳታፊ ስለነበሩ ሲሆን፣ የአካባቢ ተወላጅነት፣ ልማዱንና ሥርዓቱን ማወቅ፣ እንዲሁም የትምህርት ደረጃቸው ከፍ ያለ መሆኑ ለተሻለ ውይይትና ገለፃ የሚያግዙ መሆናቸው፣ ፈቃደኝነታቸውና ለሥራው ያላቸው ትብብር፣ የአባላቱ የምርጫ መስፈርቶች ነበሩ። በመቀጠል፣ ለነዚህ ተባባሪዎች ስለጥናቱ አስፈላጊው ገለፃ ከተደረገላቸው በኋላ፣ ስለ ህብረተ-ሰቡ ዝርውቃል ተረኮች ክዋኔ (Performance) እና፣ ግልጋሎት (Functions) እንዲሁም በህብረተ-ሰቡ ውስጥ አሁን ስለሚገኙበት ሁኔታ ጽሁፋዊ መጠይቆች ቀርበውላቸው ምላሽ ሰጥተዋል። በተጨማሪም አንድ ጊዜ በጋራ በመሆን ሰፊ ውይይት ተደርጎ መረጃዎችን በማጠናከር ረገድ ጠቃሚ ግንዛቤ ማግኘት ተችሏል።

ከዚህ በታች ከተራ ቁጥር 1–11 ድረስ ተዘርዝረው የቀረቡት አስተያየቶች፣ የተናጠል ሳይሆኑ የጋራ ውይይት በተካሄደበት ወቅት፣ እያንዳንዱ ተናጋሪ ካቀረበው አስተያየት፣ መካከል በሌሎች

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

አባላት ድጋፍ ያገኙት ብቻ ተመርጠው እዚህ ላይ የሰፈሩ መሆናቸው እንዲታወቅ ያስፈልጋል። በዚህ መሰረት፣ የተሰበሰቡ መረጃዎች፣ ቀጥለው የተመለከቱት ናቸው።

*ድሮ በልጅነቴ አባቴ ተረት ይነግሩኝ ነበር። እርሳቸውም ከአባታቸውና ከሌሎች ሽማግሌዎች የሰሙትን ነው። ጊዜውም ማታ እራት ከበላን በኋላ የእንቅልፍ ሰዓት እስከሚደርስ ነው። አባቴ ድርብ ቡሉኮ(Ejja)[28] ለብሰው በራሳቸው መቀመጫ (Motie)[29] ላይ ሆነው የሰሙትንና የልምዳቸውን ጨምረው እንደሚነግሩኝ ይገልፁልኝ ነበር።[30]*

*ድሮ አባቴና አያቶቼ ተረት ይነግሩኝ ነበር። እነርሱም ሲወራ ከሰሙት ያገኙትን ነው። ተረት ቀንም፣ማታም ሊተረክ ይችላል። እቤት በሶንን፣በእርሻ ቦታ፣በልቅሶ ቤት ይተረካል። ለትረካ የሚደረግ የተለየ ሥርዓት አላጋጠመኝም። "Xingo, xinganni" /ተረት ተረት/ ተብሎ ይጀመራል። ተራች በአደባባይ ከሆነ ቡሉኮና የባህል ሱሪያቸውን በመልበስ በመቀመጫቸው ላይ ይቀመጣሉ። እኛም ዙሪያውን ከበን እናዳምጥ ነበር። ተረቱ የሚቋጨው "Gateeken gaafi gawi, anee okkone baro ebelote hine" "ባልተረተ ሰው አናቱ ላይ ቀንድ ይብቀል ስሜ እገሌ ነው።" ብሎ የራሱን ስም ይጠራል። በዚህ ጊዜ እኛ እንሳሳቃለን። እኔ እንደማስታውሰው ተረት በመናገር ረገድ ሁለቱም ፆታዎች ድርሻ አላቸው።[31]*

*ድሮ ታላላቆቼ ከአባቶቻቸው የሰሟቸውን ተረቶች ይነግሩኝ ነበር። ጊዜውም ማታ ጀንበር ከጠለቀች በኋላ ሁላችንም ተሰብስበን እቤት በምንገባበት ሰዓት ነው። ስፍራው ካልጨለመ ከደጃፋችን ፊት ለፊት ባለች የመሰባሰቢያ ሜዳ ከጎረቤት ልጆች ጋር ሆነን ተቀምጠን ይነገረናል። የተነገረውን ተረት በጽሞና አድምጦ መልሶ መናገር ያልቻለ፣ "አይጥ ብላ" ተብሎ ይሳቅበታል። ማታ ከሆነ ተራች ሞቴ ላይ ተቀምጦ ቡሉኮ ይለብሳል። እንደ ተረቱ አይነትና ሆኔታ በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ገላጭ ምልክቶችን እያሳዩን ድምፃቸውን እየለዋወጡ ይነግሩናል። ተረቱ ሲነገረን የተለየ ሥነ-ሥርዓት ባይኖርም፣ አንዳንድ ጊዜ ቡና ይቀርብ ነበር። የተረቱ ተናጋሪዎች አብዛኛውን ጊዜ በዕድሜ ታላቅ የሆነ ወንድ ወይም ሴት ነች።[32]*

---

[28] Ejja - ከጥጥ የሚሰራ ባለ አራት ፈርጅ ቡሉኮ ሲሆን ይህን የሚለብሱ ሀይቻዎች፣ አዛውንቶች ሀብታሞችና ትላልቅ ሰዎች ናቸው። በተለይ አረጋውያና በሶንን ተቀምጠው ወግ ሲያወጉ፣ ዳኝነት ሲቀመጡ፣ በልቅሶ ላይ ሲሆኑ ይህን ቡሉኮ(ኤጃ) ለብሰው ነው።

[29] Motie - ከእንጨት ተጠርቦ የሚሰራ ባለ ሦስት እግር ባህላዊ መቀመጫ

[30] በቀለ ማሩ- ነሀሴ 20/1999 ኮቾሬ ወረዳ

[31] ሚደቅሳ ሩፎ ነሀሴ 20/1999ዓ.ም ወናጎ ወረዳ ካሴት ቁጥር10 ስርክብ ገፅ 30

[32] ታደስ ገርማሞ ነሀሴ 20/1999ዓ.ም ዲላ ከተማ የሽግግር አስተዳደር

ድሮ ጎረቤታችን የነበሩት የጓደኛዬ አያት ተረት ይተርቱልን ነበር። እርሳቸው ተረቱን ከየት እንዳገኙት አልነገሩኝም። ብዙውን ጊዜ ወደ ማታ አካባቢ ነበር የሚነግሩን። እርሳቸው ቤት አጠገብ ባለችው ትንሽ ሜዳ ላይ እሳቸው ቡሉኮ ለብሰው ወንበራቸው ላይ ይቀመጣሉ። እኛም ከበናቸው እንቀመጣለን የሚነግሩንንም በእሺታና በሳቅ እንከታተላለን። ተረት የሚነግሩን ብዙውን ጊዜ ከሴቶች ይልቅ ወንዶች መሆናቸውን አስታውሳለሁ።[33]

ድሮ አባቴ ሌሎች ሲያወሩ የሰሙትን እያስታወሱ ይተረቱልን ነበር። እኛም ቀን ውሃ በመቅዳት፣ከብቶች በመጠበቅ፣ ጠጣና ዝንጀሮ ከሰብል በመጠበቅ፣ ሥራ ላይ ስለምንውል የሚተረትልን ማታ ማታ ብቻ ነው። ተረቱ ሲጀመር xingo, xingo ተብሎ ይጠየቃል። እኛም 'xing' በማለት ምላሽ እንሰጥና ወዲያው ዝም ብለን እንቀመጣለን እርሳቸው ቡሉኮኣቸውን ለብሰው በ Motie ላይ ይቀመጣሉ። እኛ ዙሪያውን ተቀምጠን እናዳምጣለን በሚተርቱበት ወቅት ማንኛውንም አካላዊ (እጅ፣ዓይን) እንቅስቃሴና የድምፅ መለዋወጥ ያደርጋሉ። የአውሬም ከሆነ እንደ አውሬው ድምፅ ያወጣሉ። እኛ ደግሞ በጉጉት ዝም ብለን እስከሚያበቁ ድረስ እናዳምጣለን።[34]

ድሮ በልጅነቴ እናቴ፣ የወንድና የሴት አያቶቼ፣ ከቀደምት አባቶቻቸው የሰሟቸውን ተረቶች፣ ሁሉም የቤተ-ሰብ አባላት ተሟልተው በሚሰባሰቡበት ቡሉኮ ደርበው ጊዜ እሳት ዳር ተቀምጠው 'xing' ይነግሩናል። እኛም በፀጥታ እንከታተላለን እንደተረቱ ሁኔታ እርሳቸው አካላዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ትዝ ይለኛል። ዓይናቸውን ያጉረጠርጣሉ ድምፃቸውን ጎርነን ያደርጋሉ። በዚህ ጊዜ እውነት እየመሰለን እንፈራለን። ተረቱ በሚነገርበት ወቅት አዋቂዎች ቡና እየጠጡ፣ እኛ ደግሞ ቆሎ እየበላን ነው። ተረት በሁለቱም ፆታ በተለይ በዕድሜያቸው ገፋ ባሉ ሰዎች ሲነገር አውቃለሁ።[35]

ወላጆቼ ልዩ ልዩ ተረቶችን የሚነግሩኝ እኔ መልካም ስነ ምግባር እንድይዝ፣ ታዛዥ፣ አስተዋይ፣ ንቁ እንድሆን ይመስለኛል። ይህን ሁኔታ ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው አንድ ሰው የተሟላ ስብዕና ኖሮት እንዲያድግ፣ መጥፎውን ነገር ትቶ ጥሩ ሰው እንዲሆን ተረቶች ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው እላለሁ። በተለይ ህፃናት ፀባያቸው እንዲስተካከል በጣም ይረዳሉ ብዬ አምናለሁ። ባሁኑ ጊዜ ተረቶች አለመተረታቸው ወይም ደግሞ እየቀሩ መሄዳቸው ታዳጊዎች ባብዛኛው ባህርያቸው 'እየተበላሸ' ለመሄዱ

---

[33] ትዕግሥቱ ከበደ ነሀሴ 20/1999ዓ.ም ገደብ ወረዳ

[34] አሻግሬ ተሾመ ነሀሴ 20/1999ዓ.ም ዲላ ካሴት ቁጥር 10 ስክርብ ገፅ 30

[35] ከፍያለው በራ ነሀሴ 20/1999ዓ.ም ጌዴኦ ዞን መስተዳደር

*አንዱ ምክንያት ይመስለኛል። ስለሆነም ተረት በመናገር ሀገናት ጠባይ እንዲሻሻል ማድረግ ይገባል እላለሁ።*[36]

*በልጅነቴ ይነገረኝ የነበረው ተረት፣ ለእኔ ትልቅ መልዕክት ነበረው። በእኔ አስተያየት ተረት የተፈለገውን መልዕክት ለማስተላለፍ ይረዳል ብዬ አምናለሁ። ለልጆች የአእምሮ ብስለት፣ የንግግርና ሃሳብ የማፍለቅ ችሎታቸው ከፍ እንዲል ያረዳቸዋል። ተረት ለጥንቃቄ፣ ለተዝናኖት፣ ባህላዊ ጉዳዮችን በተዘዋዋሪ መንገድ ለተተኪው ትውልድ ለማሳተላለፍ የሚያገለግል ነገር ነው።*[37]

*እንደማስታውሰው ልጅ ሆኜ ተረት ይነገረኝ የነበረው እኔን ዝም ለማሰኘት ለማስደሰትና ለማጫወት ነው። አሁን አሁን ሳስበው ብዙ ትምህርት ይገኝበታል። በተረት ልጅን ማስተማር፣ ታሪክን ማሳወቅ ይቻላል። በድሮ ጊዜ ተረቶች ከፍተኛ ቦታ ነበራቸው። በተረት የሚቀርቡትን ሁሉ እንደ እውነተኛ አድርጌ እወስዳቸው ነበር። በሰፈራችን ተረት ተናጋሪዎች በችሎታቸውና በዕውቀታቸው ይከበራሉ፣ ይወደሳሉ። ባሁኑ ጊዜ ግን ተረቶች በስፋት ስለማይነገሩ በመሞት ላይ ናቸው።*[38]

*ተረት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የተለያዩ የህብረተሰብ ገፅታዎችን እንዳውቅ ረድቶኛል። በእኔ አመለካከት፣ ተረት ያንድን ህብረተ-ሰብ ባህሉን፣ ቋንቋውን፣ ኑሮውንና ማህበረሰባዊ እሴቶቹን፣ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፊያ መንገድ ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ተረቶች ባይተረቱ ደግሞ፣ መጪው ትውልድ ያለፈውን ዘመን ታሪክ ለመረዳት የሚያስቸግር ይመስለኛል። አሁንም ቢሆን፣ ዘመናዊ ትምህርት ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች፣ ሽማግሌዎች በሚያገኙት አጋጣሚ ሁሉ፣ የህይወት ልምዳቸውን በተረት መልክ እያስተላለፉ ይገኛሉ። በአጠቃላይ ሳየው፣ በአሁኑ ጊዜ ለተረት የሚሰጥ ትኩረት ያነሰ ነው። ቢነገርም በአብዛኛው ጆሮ የሚሰጥ ባለመኖሩ አገልግሎቱ ቀንሷል።*[39]

*የህብረተ-ሰባችንን ወግና ባህል እያወቅሁ እንዳድግ፣ ጆብዱ እንድሰራ፣ ከአስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታዎች በዘዴ ማለፍ እንድችል፣ በሥራዬ እንደጐበዝ፣ ሥርዓት*

---

[36] ከፍያለው ቦሩ ነሀሴ 20/1999ዓ.ም ዲላ ዩኒቨርሲቲ

[37]ወርቁ ማሞ ነሀሴ 21/1999ዓ.ም ዲላ ዙሪያ አምባ ቀበሌ ገ/ማ ካሴት ቁጥር 10 ስክርብ ገፅ (30–35)

[38] ትዕግሥት ከበደ ነሀሴ 22/1999ዓ.ም ገደብ ወረዳ

[39] ሚደግሳ ሩሮ ነሀሴ 21/1999ዓ.ም ወናጎ

*ጠብቄ እንዳድግ ረድቶኛል ቤተሰቦቼ ተረት ይነገሩኝ ነበር። እንደኔ አስተያየት ተረቶች በሰው ፊት ሃሳብን በአግባቡ ለመግለጽ ይጠቅማሉ። ጉበዝ ለመባል፣ ጥሩ ሥነ-ምግባር ለመያዝ፣ የህብረተ-ሰቡን ታሪክና ማንነት ጠንቅቆ ለመረዳት፣ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ ብዬ አምናለሁ። ባሁኑ ጊዜ ተረቶችን ከሚናገሩ ሰዎች መካከል በዕድሜ የገፉት ካልሆኑት በስተቀር በአብዛኛው በወጣቶች ዘንድ ስለማይዘወተሩ ቀስ በቀስ እየተረሱና እየቀሩ በመሄድ ላይ ናቸው።*[40]

## 5.2 የጌዴኦ ቃል ተረኮች ማህበራዊ ግልጋሎት

የጌዴኦ ማህበረ-ሰብ አባላትን በተለይም ልጆችንና ወጣቶች ተቀባይነት ባላቸው የሥነ-ምግባር መመዘኛዎች ለማነጽ፣ የተዛቡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ወይም በደሎችን ለመቃወም፣ መሰላቸትን አስወግዶ የተዳከመ አእምሮን ዘና ለማድረግ በተረኮቹ ይጠቀማል፣ መሠረታዊ አገልግሎታቸውም ይኸው ነው። ከተጠቀሱት በተጨማሪ፣ ቃል ተረኮች ከሚያበረክቷቸው ግልጋሎቶች መካከል፣ ህብረተ-ሰቡ መልካም በሚላቸው የስነ-ምግባር ባህርያት ትውልድን ለመቅረጽ፣ ልማዳዊ እሴቶቻቸውን (ፋጬ፣ ጎንዶሮ፣ ባህላዊ ጋብቻ፣ ጥንታዊ የሀዘን ሥርዓት) ለማጠንከር፣ ማህበራዊና ባህላዊ ህይወቱ ምን እንደሆነ ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስረዳበት፣ ጠቅለል ባለ አነጋገር ጠቃሚና ጎጂ ሥነ-ምግባራትን የሚያስተላልፈው በቃላዊ ተረኮቹ ነው። ምክንያቱም ተረኮች የተጠቀሱትን ማህበራዊ ጉዳዮች ከማስተናገድ ውጭ ፋይዳ እንደሌላቸው Finnegan, (1970፡ 329-330) ትገልፃለች።

ስለጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ዝርውቃል ተረኮች ስናነሳ፣ ጥንተ-አመጣጣቸው (Origion) ከአባቶች፣ ከአያቶችና ከቅድመ-አያቶች በቃል ሲተላለፉ እስከዛሬ እንደደረሱ ተገልጿል። ከዚህ በተጨማሪ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ በሚገኙ ጥበበኞችና ብልሃተኞች አማካይነትም በየጊዜው እየተፈጠሩ ግልጋሎት ላይ እንደሚውሉ በመረጃ ሰጭዎች ተጠቅሷል። ምንም ይሁን ምን ቃል-ተረኮቹ ከዘመን ዘመን፣ ከሰው ሰው እየተሸጋገሩ እስከዚህ መድረሳቸው ቀደም ሲል የተፈጠሩበትን ምክንያት ብቻ ሳይሆን ለምን ዓላማና ግብ እንደዋሉ ማወቅ አስችሏል።

ከዚህ በላይ ስለ ጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች የመረጃ አቀባዮችን አስተያቶች፣ ስለ ተረኮቻቸው ክዋኔና መቼት፣ እንዲሁም ማህበራዊ ግልጋሎቶቻቸውን ተመልክተናል። በተከታዩ ምዕራፍ ደግሞ በጥናቱ የተደረሰባቸውን ግንዛቤዎች እንቃኛለን።

---

[40] አሻግሬ ተሾመ ነሀሴ 21/1999ዓ.ም ዲላ ካሴት ቀጥር 10 ስክርብ (30–35)

## 6.0 በጥናቱ የተደረሰባቸው ግንዛቤዎች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዋነኛ ትኩረታችን፣ የጥናቱ ግኝቶች ሲሆኑ፣ የልማዳዊ ሥርዓቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው ያሏቸውን ተደጋጋፊነት የምናይበት፣ እንዲሁም በናሙናነት (sample) የተመረጡ የመማሳና የጢንጎ ቃል ተረኮች ይዘቶችን ትንታኔዎች፣ እና የተሰበሰቡት ተረኮች የይዘት ተመሳስሎ ምደባዎች፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ቀደም ሲል በመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ አስተያየቶች እንዳመለከቱት፣ በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ውስጥ ተረት ተናጋሪዎች አብዛኛውን ጊዜ በዕድሜ የገፉ ወንዶች መሆናቸውን ሁሉም የሚጋሩት ሃሳብ ነው። እነርሱም ቢሆኑ ተረኮችን ከቀደምቶቻቸው (ከአባት፣ ከአያት ወይም ሌሎች) ሲነገሩ እንደሰሙ ጠቅሰዋል። የተረት መንገሪያ ጊዜም ቢሆን በአብዛኛው ማታ ማታ የእንቅልፍ ሰዓት እስከሚደርስ ድረስ ሲሆን፣ ስፍራውም በቤት ውስጥ ወይም ከደጃፍ ላይ መሆኑ ተመልክቷል። ተራቾች ኤጃ (ባህላዊ ቡሉክ) በመልበስ፣ ሞቴ “Motie” የሽማግሌዎች መቀመጫ ላይ ተቀምጠው ነው። ታዳሚዎችም፣ በተረክ ነጋሪዎቻቸው ዙሪያ ወይም ፊት ለፊት በመሆን እንደሚያዳምጡ ገልፀዋል። ክዋኔውን ስንመለከት፣ እንደሚቀርበው የተረክ ዓይነትና፣ ሁኔታ ተራኪዎች ልዩ ልዩ የሰውነት ክፍሎቻቸውን (እጅ፣ ዓይን፣ እግር ወዘተ.) ያንቀሳቅሳሉ። እንደተረኩ ዓይነት የድምፅ መለዋወጥ እንደሚያደርጉ ተገልጾአል። በማንኛውም ቦታ ለተረክ ነገራ ተብሎ የተለየ ሥርዓት ባይደረግም፣ታዳሚዎች (ልጆች) ትረካውን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ በጉጉት እንደሚያደምጡ ተጠቅሷል። ስለተረክ ፋይዳ መረጃ ሰጭዎቹ የየራሳቸውን ገጠመኝ አስታውሰዋል። እነርሱ (መረጃ ሰጭዎች) ተረኮች እየተነገሯቸው ማደጋቸው፣ መልካም ሥነምግባር እንዲይዙ እንደረዳቸው፣ ክፉውንና በጎውን መለየት እንዳስቻላቸው፣ ለአእምሮአቸው ተዝናኖትን፣ ስለባህላቸው ዕውቀትን፣ እንዳስገኘላቸው ገልፀዋል ። በመጨረሻም፣ የዛሬው ትውልድ ለተረኮች ነገራ (story telling and listening process) ያለው ዕድልና አጋጣሚውም ቢሆን እጅግ ያነሰ ነው። ይህ በመሆኑም፣ እነርሱ ከተረኮች ያገኟቸውን ጠቀሜታዎች፣ ያሁኑ ትውልድ እያጣ ነው የሚል ስጋታቸውን ገልፀዋል። ይህ የሚያሳየው በጌዴኦ ህብረተሰብ ወስጥ ዝርው ቃል ተረኮች እየተተዉና እየተረሱ በመሄድ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ተሰብስበው በቅርስነት መያዝ እንዳለባቸው ነው።

IES LIBRARY

## 6.1 ጎሳዊ ምደባዎች

ስለ ጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ዝርው ቃል ተረኮች በተሻለ ሁኔታ ለማጥናት፣ በልማዳዊ ሥርዓቱ ውስጥ ያላቸውን ማህበራዊ ግልጋሎት (social-function) ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በተረክ ነገራ (Story-telling) ሂደት ዕድሜ፣ ቦታና፣ጊዜ ለተረኮች ጎሳዊ ምደባ (Ethnic Category) መስፈርቶች በመሆን የሚያገለገሉባቸው ጊዜያት አሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው ለአዋቆችና ለልጆች የሚነገሩ ቃልተረኮች በጊዜና በቦታ የሚለያዩና ተመሳሳይ እንዳልሆኑ ነው፡፡ ጎሳዊ ምደባዎች ስንለም ህብረተሰቡ ለቃል ተረኮቻቸው የሰጧቸውን ስያሜዎች፣ ከፍፍልና ዓይነታቸውን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት፣ የጌዴኦ ህብረተሰብ ዝርው ቃል-ተረኮች መማሳ (Mammassa) እና ጢንጎ (Xingo) ተብለው እንደተሰየሙ የጥናቱ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ፣ ስለእያንዳንዳቸው በምሳሌዎች እያስደገፍን እንመለከታለን፡፡

### 6.1.1 መማሳ (Mammassa)

መማሳ፣ ሽማግሌዎችና አዛውንቶች አለመግባባቶችን ለመፍታት እርቅ ሲቀመጡ፣ እንዲሁም በልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ ውይይቶችን ሲያካሂዱ፣ ሁኔታዎችን ፈር ለማሲያዝ በነገር አዋቆች የሚነገሩ ናቸው፡፡ የመከወኛ ስፍራዎን በተመለከተም፣ ያካባቢው ህብረተ-ሰብ በሶንጎ (Songo) ሲሰበሰብ፣ ጋፌ (gaffe) ወይም ዳኘነት ሲካሄድ ወዘተ እና በመሳሰሉ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ሁሉ የሚዘወተሩ ቃል ተረኮች ናቸው፡፡ የመማሳ ተረኮች በማንኛውም አጋጣሚ የሚቀርቡ በመሆናቸው የጊዜ ግደባ የለባቸውም፡፡ እነዚህ ተረኮች በአብዛኛው ልጆችን አያሳትፉ እንጂ ፣ሕብረተሰቡ ካለፉት ትውልዶቹ በመውረስ ሠናይ ብሎ ከሚጎዝባቸው መንገዶች ለሚያፈነግጡ፣ ሠላምን ለሚያደፈርሱ፣ ምክርን ለማይቀበሉ፣ በማንኛውም መልኩ እምቢተኝነትን የሚከላከሉባቸው ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ፣ በመማሳ "Mammasa" ቃል ተረኮች ስር ንዑሳን ዘርፍ ሆነው ሊካተቱ የሚችሉ ሚታዊ (Mythic) እና አፈታሪክ (legend) ይዘቶች ያሏቸው ተረኮች እንዳሉ የመስክ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የጌዴኦ ህብረተ-ሰብ በዙሪያው የሚያየውን ተፈጥሮን (መሬት፣ ሰማይ፣ ፀሐይ፣ ደመና፣ ዕፅዋት፣ ወንዞች፣ ወዘተ.) እና ከእነርሱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ልዩ ልዩ ክስተቶችን (ዝናብ፣ መብረቅ፣ ውሃ ሙላት፣ ድርቅ፣ ረሃብ ወዘተ.) የመሳሰሉ ሁነቶችን የኬት መጣ (origion) ጥያቄዎች በራሱ አተያይ፣ በራሱ ግንዛቤ፣ የሚያብራራባቸው ሚታዊ ተረኮች

(Mythic tales) ያለት ህብረተሰብ ነው። ቀጥሎ በዋቢነት የተጠቀሱት ቃል-ተረኮች ለዚሁ መረጃ በመሆን እንዲያገለግሉ የቀረቡ ናቸው።

### *6.1.1.1 መማሳ ተረክ አንድ*

### *የጌዴኦ ወንዞች አፈጣጠር*

> *በጌዴኦ ውስጥ የሚገኙ ወንዞች ሁሉ መነሻቸው ሐሮ ወላቡ "Haroo Woolabu" ነው ይባላል። በጥንት ጊዜ ከዚህ ኩሬ ውስጥ አንድ ነጭ በሬ ከነነፍሱ ወጣ። ይህ በሬ እዚያው አካባቢ ሳር እየበላ ከሐሮ ውሃ ሲጠጣ ቀና ብሎ ወደ ቀኝ ዞር ሲል ከአፉ የሚንጠባጠበው ውሃ እርሱ ከቆመበት አቅጣጫ፣ በስተቀኙ የሚገኙ የጌዴኦ ወንዞች ተፈጠሩ። እንደገና በሌላ ጊዜ አሁንም እየጠጣ ቀና ብሎ ወደ ግራ ዞር ሲል በስተግራ ያሉት ወንዞች ተፈጠሩ። ዛሬ በዞኑ ዳገታማና ተዳፋታማ ሥፍራዎች በጋ ከክረምት የሚፈሱት የጌዴኦ ወንዞችና ጅረቶች የተፈጠሩት በዚህ ሁኔታ ነው ይባላል።[41]*

ጥንታዊው ሰው በዙሪያው ለሚያያቸው ተፈጥሮአዊ ክስተቶች በራሱ አተያይና ግንዛቤ እየተመራ፣ እነዚህ ነገሮች የመጡት ከዚህ ነው፣ እነዚያኞቹ የተገኙት በዚህ ሁኔታ ነው። እንዲህ የሆኑት ደግሞ በዚህ የተነሳ ነው እያሉ የራሳቸውን ማብራሪያ ይሰጣሉ። የዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ሚታዊ ተረኮች ከሰብስቡ፣ $M_{3}$ , 8 , 9 , 15 , 16 ይመለከቷል። ከተጠቀሱት በተጨማሪ፣ ህብረተ-ሰቡ በወጉ የሚያስታውሳቸውን ታሪካዊ አጋጣሚዎችና ድርጊቶች (events)፣ እንዲሁም ታሪክ ቀመስ ክስተቶችን፣ በአፈ ታሪኮቻቸው (legends) ይገልፃሉ። ቀጥሎ የምንመለከተው ቃልተረክ ለዚሁ ማስረጃ ነው።

### *6.1.1.2 መማሳ ተረክ ሁለት አኮመኖዬ*

> *በጥንታዊ ጌዴኦ አኮመኖዬ የምትባል ንግሥት ነበረች። በእርሷ ዘመን የቤት ውስጥ ሥራዎችንና የተወለዱ ልጆችን ጭምር ተንከባክቦ የማሳደግ ሥራ የወንዶች ነበር። ባንፃሩ የሴቶች ሥራ ቀለል ቀለል ያሉና ብዙም ጉልበትን የማይጠይቁ ነበሩ። ንግሥት አኮመኖዬ ማንኛውም ጉልበት የሚጠይቁ ሥራዎችን የምታሰራው ወንዶችን ብቻ እየመረጠች ነበር። በዚህ ሁኔታ ሲኖሩ ከዕለታት አንድ ቀን ወንዶችን በሙሉ ሰበሰበችና አንግጤ (Anxxaxie) ከስንደዶ ምንም ያህል በማይወፍር እንጨት ከምድር ከፍ ከሰማይ ዝቅ ያለ ቤተ-መንግስት ባስቸኳይ ስሩልኝ ስትል ቀጭን ትዕዛዝ አስተላለፈች። እነርሱም እንዴት መስራት እንደሚችሉ መላ ማፈላለግ ጀመሩ። ምድረ ወንድ ተጨነቀ። እርሷን የሚያስደስታት ነገር ከዚህ በላይ የለም ይበልጥ አስቸጋሪና ፈታኝ ሥራዎችን እየፈለገች ወንዶችን እያስጨነቀች ማሰራት የዘወትር ተግባሯ ነው። ሆኖም በዚህ ከውሃ የቀጠነ ትዕዛዝዋ የተማረሩ ወንዶች እያደር ሥርዓቱን ለመለወጥ ትግል ማድረግ ጀመሩ። እርሷን በማጥፋት አገዛዟን ለመቀየር በየጊዜው ቢመክሩም መላው በቶሎ ሊገኝ አልተቻለም። አንድ ቀን እርሷ*

[41] ፊጤ በዳሳ ኅዳር 22/1999ዓ.ም ዎቻማ ቀበሌ ገ/ማ

> *በሌለችበት ወንዶች በድብቅ ተሰብስበው ሲመክሩ ዋሉ፡፡ መላው ጠፍቶባቸው ሊበተኑ ሲሉ፣ አንድ ድንክዬ ድሃ ሰው በዚያ አካባቢ ሲያልፍ ጠሩትና ሁኔታውን አስረዱት፡፡ እርሱም ያለውን ብልሃት እንዲያካፍላቸው አግባቡት፡፡ በነገሩ ጥቂት አሰበና እንዲህ አላቸው፡፡ «አኮመኖዬ በማትኖርበት ጊዜ ጠብቃችሁ አንድ ጥልቅ ጉድጓድ ቆፍሩ፣ ስትቆፍሩም ከእናንተ በስተቀር ሌላ ወገን እንዳያይ በምስጢር ይሁን፣ ከጉድጓዱ የሚወጣውንም አፈር ምንም ሳይቀር ከአካባቢው አርቁ፡፡ በጉድጓዱ ላይ ምንጣፍ አድርጉበት በመጨረሻም የእርሷን* Motite *(መቀመጫ) በላዩ ላይ አስቀምጡበት፡፡ ቀጥሎ ውሃ በእንስራ ሞልታችሁአፍሉና ተጠባበቁ፡፡ እንደተለመደው አኮመኖዬ መጥታ የተለመደውን ትዕዛዝ ለማስተላለፍ* Motite *ላይ ለመቀመጥ ስትሞክር ጉድጓድ ውስጥ ትወድቃለች በዚህ ጊዜ የፈላውን ውሃ ቶሎ ቶሎ አፍሱባት በዚህ ጊዜ ሕይወቷ ያልፋል፡፡» ሲል ተናገረ፡፡ እነርሱም እንደተባሉት አደረጉ፡፡ ነገር ግን አኮመኖዬ እገዛ ያላደረጉላትን ሴቶች ከመሞቷ በፊት አኮመኖዬ "ከእንግዲህ ቀሚሳችሁን ወደቀኝ መዥርጡ! ምን ጊዜም ከወንዶች በታች ሁኑ!" ብላ ረግማቸው ሞተች፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሴቶች የበላይነት አክትሞ በወንዶች ቁጥጥር ሥር ሆኑ ይባላል፡፡*[42]

ተረኩ ሴቶች አስተዳደራዊ የበላይነቱን ይዘው የመሩትና ያስተዳደሩበት ዘመን እንደነበር የሚተርክ ነው፡፡ ባንድ በኩል እዚህ ደረጃ መድረሳቸው ጥንካሬያቸውን የሚያሳይ ሲሆን፣ ከውሃ በቀጠነ ትዕዛዝዋ ሳቢያ ደግሞ የምታስተዳድራቸው ሰዎች አመፅ ቀስቅሰው ለወድቀት መብቃቷ እንደአለመቻል የምፀት ያስመስለዋል፡፡ ነገር ግን አኮመኖዬ እንደ ንግስተ ሣባ የጌዴኦ ጥንታዊ ንግሥት (Legendary Queen) እንደነበረች በአፈ-ታሪክ ይነገራል፡፡ የዚህ ዓይይነት ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው አፈ-ታሪኮችን፣ ከአባሪ ስብስቡ ውስጥ በተለይ $M_{2,4,6,7,10,11,13,14}$ ይመለከቷል፡፡

## 6.1.2. ጢንጎ (Xingo)

ሌላው የቃል ተረኮች ምድብ፣ በየመኖሪያ ቤቶች፣ በየዛፎች ጥላ ሥር፣ በየደጃፉ ላይ፣ በእረኝነት ቦታና፣ በሀዘን ቦታዎች የሚነገሩት፣ ጢንጎ "Xingo" የሚባሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ተረኮች በዕድሜ የተገደቡ ሆነው አብዛኛውን ጊዜ ከስራ ሰዓት ውጭ የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ተረት ነጋሪ/ተረተኛ/ መሆን "የአዋቂነት መለኪያ" ሆኖ በሚታይበት ማህበረ-ሰብ ውስጥ ከአባቶች፣ ከአያቶች፣ ከቅድመ-አያቶቻቸው ወዘተ. የሰሟቸውን ልዩ ልዩ ገጠመኞች ሥርዓትና ልምዶቻቸውን ለወጣቱ ትውልድ ማስተላለፊያ መንገዶች ናቸው፡፡ ከግልጋሎታዊ ዓላማ (Functional Objective) አንፃር፣ እንደዛሬ ት/ቤቶች ባልተስፋፋባቸው ዘመናት፣ ተረኮች በማህበራዊ ህይወት ልምዶቻቸውን ካዳበሩ ግለሰቦች፣ ሽማግሌዎችና አዋቆች፣የተለያዩ ዕውቀቶች ማስተላለፊያ መንገዶች እንደነበሩ በመረጃ ሰጪዎች ተገልፆአል፡፡

---

[42]ጥላሁን ኢቢዶ ኅዳር 20/1999ዓ.ም ዲላ

በጌዶኦ ህብረተ-ሰብ ውስጥ ቃል ተረኮች ለተለያዩ ዓላማዎች ግብ መምቻ እንደሚያገለግሉ ቀደም ሲል ተመልክቷል፡፡ በዚህ ጥናት በተሰበሰቡ የጢንጎ 'Xingo' ቃል ተረኮች አብዛኞቹ ስለ ልዩ ልዩ እንስሳትና አራዊት ባህርያት የሚገልፁ ሲሆኑ፣ ሰውና እንስሳ፣ ሰውና አራዊት በገፀ-ባህርያትነት ጎራ እየለዩ የሚፋለሙባቸው ናቸው፡፡ ይህም የሚያመለክተው፣ "Thompson" እንሰሴ ተረቶች" ብሎ ከመደባቸው ዝርዝሮች ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው ነው ለማለት እንችላለን፡፡

በተለይ በምዕራቡ ዓለም ህብረተ-ሰብ ውስጥ ለተዝናኖታዊ ግልጋሎት የሚመረጡት እንሰሴ ተረቶች (Animal tales) ናቸው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት እንሰሴ ተረቶች ባብዛኛው ልጆችን ለማዝናናትና በቀልዶች እያዋዙ ቁም ነገሮችን እንዲቀስሙ ለማድረግ ምቹ በመሆናቸው ነው ስትል Finnegan, (1970:343) ትገልፃለች፡፡ ይህን አመለካከት የሚጋሩት አንድ ያገራችን ምሁር አስተያየታቸውን ሲያቀርቡ፣

> *ተረቶችን በአቀራረባቸው መልክና ቅርጽ ስናስተውላቸው ከተራው ንግግርም ሆነ ከዘፈኖችና ከግጥሞች የተለየ ዓመል እንዳላቸው እንገነዘባለን:: ተረቶችን ልዩ የሚያደርጋቸው ዋነኛው ጠባያቸው ግዑዛን ፍጥረቶችና በተለይም እንስሳት እንደ ሰው አፍ አውጥተው መናገራቸው የሰው ሥራና የሰው ጠባይ ማግኘታቸው ነው፡፡ ይኸም ትልቅ ሳይኮሎጂካዊ ጥበብ የተሞላው ዘዴ ነው፡፡ ሰው በራሱ ያለው ዐመል አድላዊነት ስለሚያጠቃው በትክክል ሊገመግመው አይችልም፡፡ ስለዚህ የራሱን ጠባይና ጉድለት ከውስጥ አውጥቶ በእንስሳት ላይ ቢያስቀምጠው በገለልተኛ ዓይን በትክክል ተመልክቶ ቁምነገር ያዘለ ትምህርት ሊያገኝ ይችላል፡፡ በእንስሳት ሲስቅ በራሱ የሚስቅ መሆኑን አይገነዘበውም:: በራሱ ሲነገር የሚያስቆጣው ነገር በእንስሳት ሲነገር ያስደስተዋል፡፡ በራሱ ሲነገር የሚያሳፍረው ነገር በእንስሳት ሲነገር ያዝናናዋል:: በወገኖቹ ሲደርስ የሚያሳዝነው ነገር በእንስሳት ሲነገር አያሳዝነውም (ሀብተማርያም (1973፡4)::*

በማለት ይገልፃሉ፡፡ በእርግጥም ይህ እውነታ በብዙዎች ዝርው ቃል ተረኮች ውስጥ የሚታይ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ሁለት የውጭ ምሁራን እንደተገለፀው፣ እንስሳት ገፀባህርያት ሆነው በሚታዩባቸው፣ የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች ውስጥ ተመሳሳይ ክዋኔዎችን እናያለን፡፡ ይህም ለምሳሌ ትናንሽ እንስሳት (ጥንቸል፣ ጦጣ፣ ቀበሮ ወዘተ.) ትልልቆቹን (አንበሳ፣ ጅብ፣ ዝሆን ወዘተ.) የመሳሰሉትን በማሞኘትና በማቁል አምልጠው ሲሄዱ ወይም ወደ ገደል ሲገቡ ይታያሉ፡፡ ትላልቆቹም በሞኝነታቸው ተታልለው ካላሰቡት የችግር ወጥመድ የሚገቡበት ሁኔታ አለ፡፡ ግዝፈት የቂልነትና የሞኝነት መገለጫ ሆኖ የመቅረቡ ሁኔታ በርግጥ ሊያስቅ፣ ሊያስቆጭ፣ አልያም ሊያስደምም ይችላል፡፡ ቁምነገሩ፣ልጆችን ከማዝናናት ባሻገር ብልሃትን/ብልጠትን እንዲቀስሙ የማስተማሪያ ስልት መሆኑ ላይ ነው፡፡ እነዚህን በመሰሉ ቃል

ተረኮች የሰው ልጅ ውስጣዊ ባህርዩንና ጉድለቱን በመመልከት የሚያስተካክልበትን ስልት ለመቅሰም እንደሚገለገልበት ከላይ የቀረበው የሀብተማሪያም ማርቆስ አስተያየት ያስረዳል፡፡

### *6.1.2.1 ጢንጎ (Xingo) ተረክ አንድ*

> *በዱሮ ጊዜ ዝንጀሮና ጅብ ስለ ቁንጅና አንስተው ሲወያዩ፣ «እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ» ተባብለው ይወራረዳሉ፡፡ ዳኝነት የሚሰጣቸው «ሰው» እንዲሆን ተስማሙና ያካባቢያቸውን አንድ ገበሬ አግኝተው አንተ "ዳኝነት ስጠን" አሉት፡፡ እርሱም እኔ በምሰጣችሁ ፍርድ የምትስማሙ ከሆነ እሺ ይላቸውና ተስማምተው ይለያያሉ፡፡ ትንሽ ቆየት ብሎ ጅብ ወደ ገበሬው ይሄድና እኔን ቆንጆ ነህ ብለህ ባትፈርድልኝ ጥጆችህን እበላብሃለሁ፡፡» አለውና ሄደ፡፡ ቀጥሎም ዝንጀሮ መጣና ለኔ ባትፈርድልኝ ሰብልህን በሙሉ አበላሽዋለሁ፡፡» አለውና ተመልሶ ሄደ፡፡ ገበሬውም የሁለቱንም ዛቻ በሚገባ ካጤነ በኋላ፣ ምን ማድረግ እንዳለበት እያሰለሰለ እስከ ቀጠሮው ጊዜ ቆየ፡፡ ጅብና ዝንጀሮም ውሳኔያቸውን ለመስማት መጡ፡፡ ገበሬው አንድ ባንድ ለብቻ ጠራቸውና እኔ የምሰጠው ትክክለኛ ፍርድ ነው፡፡ አሸናፊው ወገን የሚለየው በቁንጥጫ ነው እንጂ በሌላ አይደለም፡፡» ሲል ነገራቸው፡፡ እሱ ፍርድ ሲሰጥ ተከራካሪዎች ጀርባቸውን ወደ እሱ መልሰው እንዲቆሙ አዘዛቸውና ተስማሙ፡፡ በታዘዙት መሠረት ፊታቸውን አዙረው እንደቆሙ በመሀላቸው ሆነና በሁለት እጆቹ ሁለቱንም ድብን አድርጎ ቆነጥጣቸው፣ በዚህ ጊዜ «እኔ አሸነፍኩ፣ እኔ አሸነፍኩ» እያሉ በየፊናቸው እየፈነጠዙ ሄዱ፡፡ ገበሬውም ከብቱንና ሰብሉን በዘዴ አተረፈ ይባላል፡፡*[43]

የተረኩ ይዘት አንድ አስቸጋሪና ሕይወት ፈታኝ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም፣ እንዴት በዘዴ ማምለጥ እንደሚቻል የሚያስተምር ነው፡፡ እንደተመለከተው፣ ቁንጅናን ለመዳኘት በእንስሳቱ የተመረጠው ገበሬ፣ ከሁለት ላንዳቸው ቢፈርድ፣ ፈተና ይጠብቀዋል፡፡ ስለዚህ ከዚህ አጣብቂኝ መውጣት አለበት፡፡ አሰበ/አሰላሰለ ራሱንና ንብረቱን ማዳን የሚችልበት ዘዴ መጣለት፡፡ እንዲህም አላቸው "ማንኛውም ተፎካካሪ መቆንጠጡን ወደ ኋላ ዞሮ ማየት የለበትም፡፡" በዚህ ስምምነት ዳኛ የሆነው ሰው በውርርዱ ጊዜ ሁለቱንም ድብን አድርጎ ቆነጠጣቸው በዚህ ጊዜ "እኔ ነኝ ቆንጆ እኔ ነኝ ቆንጆ" እያሉ በመሮጥ ወደ የቦታቸው ሄዱ፡፡ ሰውዬውም በዘዴ ራሱንና ንብረቱን ማትረፍ ቻለ ይባላል፡፡ የዚህ ተረክ ይዘት የሚያስተላልፈው መልዕክት የሰው ልጅን ብልህነት የእንስሳትን ሞኝነትና ተታላይነት ነው፡፡

ከዚህ ቃል ተረክ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ከስብስቡ X1፣ X4፣ X6፣ X7፣ X13፣ X30፣ X35 ይመለከቷል ፡፡

---

[43] ወርቁ ማሞ ነሀሴ 21/1999ዓ.ም ዲላ

## *6.1.2.2 ጢንጎ ተረክ ሁለት*

*አሥር ልጆች የነበሯቸው አንድ ሽማግሌ ነበሩ:: እሳቸውም ምንም የሚበሉትና የሚለብሱት ስለሌላቸው ልጆቻቸውን ሁሉ በየመንደሩ አስቀጥረው ይኖሩ ነበር:: አንድ ቀን ሽማግሌው ታመው ሊሞቱ ሲሉ ልጆቼን ጥሩ ልናዘዝላቸው ብለው ሰው ይልካሉ:: ልጆቹም መልዕክቱ ሲነገራቸው «አባታችን ምንም የሌለው ደሃ ነው ምን ይናዘዝልናል? እንዲያው ብቻ ሄደን ቀብረነው እንመለስ::» ይሉና ይሄዳሉ:: አባትየውም ሁሉም ልጆቻቸው እንደመጡ ካረጋገጡ በኋላ "ኑ! ወደ እኔ" አሏቸው እነርሱም አንድነት ተሰብስበው ቀረቡ:: «በሉ አሁን እያንዳንደችሁ አንዳንድ ብትር አምጡ::» ብለው አዘዟቸው:: ልጆቹም እንደታዘዙት አንዳንድ ብትር ፈልገው ይዘው መጡ:: እያንዳንዱ የያዙትን ብትር ሁለት ሁለት ቦታ እንዲሰብሩ ነገሯቸው እነሱም  እንደታዘዙት አደረጉ:: ሽማግሌው "አሁንም አንዳንድ በትር ፈልጋችሁ አምጡ" አሏቸውና አመጡ:: "ለሁለተኛ ጊዜ ስበሩ" አሏቸውና ሰበሩ:: "የተሰበሩትን በሙሉ አንድ ላይ ሰብስቡና እሰሩ" አሏቸው እነሱም አንድ ላይ ሰብስበው አሰሩ:: ከዚያ በኋላ ከታላቁ ልጅ ጀምረው ተራ በተራ ይህን እስር እንደገና ስበሩና አሳዩኝ አሉና አዘዘ :: ያንን እስር ሁሉም ለመስበር ቢሞክሩ አቃታቸው:: ሽማግሌውም በዚህ ጊዜ «ልጆቼ አሁን እንደሞከራችሁት እያንዳንዳችሁ ለየብቻችሁ የሆናችሁ እንደሆነ እንደመጀመሪያዎቹ ብትሮች ሆናችሁ በቀላሉ ትጠቃላችሁ አንድነትና ህብረት ካላችሁ ግን እንደዚህ ስብስብ ማንም አይነካችሁም ስለዚህ አንድነት በመካከላችሁ ይሁን ህብረታችሁ አይጥፋ ብለው መርቀዋቸው ሞቱ ይባላል::*

ምን ጊዜም ቢሆን ከተናጠል ልፋትና ትግል ይልቅ አንድትና ህብረት የበለጠ ውጤትን ሲያስገኙ ይታያል:: ለልጃቸው የሚያወርሱት ምንም ነገር የሌላቸው አንድ አባት፣ በታመሙ ጊዜ ኑዛዜያቸውን እንዲሰሙ ልጆቻቸውን በሙሉ ጠሩ:: ልጆችም ከአባታቸው የሚያገኙት ምንም ውርስ እንደሌለ ቢያውቁም ዝም ብለው አልቀሩም:: ልጆቹ በመጡላቸው ጊዜ አባታቸው አንዳንድ ብትር ይዘው በመምጣት ሁሉም በእርሳቸው ፊት እንዲሰብሩ አዘዟቸው:: እነርሱም እንደታዘዙት አደረጉ:: ቀጥለውም የተሰባበሩትን አንድ ላይ አድርገው እንደገና እንዲሰብሩ አዘዙ:: መጀመሪያ በተናጠል ለየብቻ የነበረው ብትር በቀላሉ ሲሰበር ስባሪዎቹን ግን አንድ ላይ አድርጎ እንደገና ለመስበር የተደረገው ጥረት እጅግ ከባድ ሆኖባቸዋል::

ሽማግሌው በተረቱ አማካይነት ለልጆቻቸው ያወረሱት ዘላቂ ጥቅም የሚያገኙበትን የህብረት ጠቀሜታ እንጂ ጊዜያዊ ቁሳዊ ጥቅምን አልነበረም:: የተረኩ ይዘት "ካንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ" የሚለውን ምሳሌያዊ ንግግር የሚያስታውስ ነው:: ጥቃትን በአስተማማኝነት ለመከላከል፣ ችግርን ለመቋቋም ከብቸኝነት ይልቅ በህብረት ከተናጠል ይልቅ በጋራ መስራት ከሁሉም መብለጡን ያስተማሩበት ነው::
የመልካም ሥነ ምግባር እና ግብረገባዊ እሴቶች ማስተማሪያዎች የሆኑ፣ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ከስብስቡ በተለይ x2፣ x18፣ x20፣ x21፣ x34 ይመለከቷል ::

### 6.1.3 የ ጢንጎ እና መማሳ ቃል ተረኮች ልዩነትና ተመሳስሎ

ጢንጎ "Xingo" እና መማሳ "Mammassa" በሚባሉ የጌዴኦ ዝርው ቃል-ተረኮች መካከል፣ በአቀራረብ፣ በዓይነት፣ በዕድሜ፣ በቦታና በጊዜ የተገደቡ ልዩነቶች አሉ። ይህም ማለት ለአዋቆችና ለልጆች በይዘትም በአቀራረብም ተመሳሳይ የሆኑ ተረኮች ሊቀርቡ አይችሉም ማለት ነው። የአዋቆች ላዋቆች፣ የልጆችም ለልጆች ይቀርባሉ። ይህ ማለት ግን ያንዳቸውን አንዳቸው አይሰሙም ማለት አይደለም። በሁለቱ መካከል የሚታዩትን ልዩነቶች ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል።

| ዓይነት | ተራኪ | ቦታ | የመቅረቢያ ጊዜ |
|---|---|---|---|
| Mammassa | ሽማግሌዎች አዛውንቶች | አደባባይ እርቅ ዳኝነት (Songo) | ቀን |
| Xingo | በማንኛውም ዕድሜ ክልል በሚገኙ | በቤት ውስጥ እረኝነት ቦታ በሀዘን ቤቶች | ማታ ቀን |

ምንጭ፣ የመስክ መረጃዎች ጥንቅር

ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው፣ መማሳ በሽማግሌዎችና በአዛውንቶች የሚነገር ነው። አብዛኛውን ጊዜ የሚቀርበው በአደባባይ ሲሆን ግልጋሎቱም በልዩልዩ ሰበብ አስባብ የተጋጩ ሰዎችን ለማስታረቅ፣ ወይም ደግሞ ዳኝነት ሲካሄድ እንዲሁም በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ነው።

በሌላ በኩል፣ ጢንጎ በማንኛውም እድሜ ክልል ሰዎች፣ ወይም በማንኛውም ፆታ ይነገራል። ከጊዜ አንፃር ከተመለከትነውም ጢንጎ ቀን ወይም ማታ ማታ ከስራ መልስ እስከ መኝታ ባሉት ጊዜያት የሚነገሩ ናቸው። ስፍራውም በቤት ውስጥ፣ በእረኝነት ቦታ፣ ወይም ደግሞ በሀዘን ቤቶች ውስጥ እደሚሆኑ መረጃ ሰጪዎች አመልክተዋል።

## 6.2 የጌዴኦ ተረኮች መዋቅር

የተረኮችን አቀራረብ (ቅርፅን) በሚመለከት፣ በብዙ ህብረተሰቦች ዘንድ የሚከተሉት አካሄድ አለ። ለምሳሌ በአማርኛ ቋንቋ አንድ ተራች "ተረት ተረት" ብሎ ለመናገር የሚያደርገው ዝግጅት የተለመደ አጀማመር ሲሆን "ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ" የሚለው ደግሞ የተለመደ ያጨራረስ ቀመር ነው። በዚህ መሠረት የጌዴኦ ተረኮችን መዋቅር ስንመለከት፡-

በዚህ እሳቤ፣ ከጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች መማሳን ስንመለከት፣ አጀማመሩ፣ "በዚያን ዘበን… …ድሮ … …."፣ ጥንት ፣ በማለት ይጀምርና የታዳሚዎችን ይሁንታ ሳይጠብቅ በዚያው ቀጥሎ "እንዲህ ሆነ … … በደስታ አብረው ኖሩ… … ይባላል፡፡" ይልና በመድረክ ላይ ካለው ርዕሰ ጉዳይ ጋር በአሉታዊም ይሁን በአዎንታዊነት ያያይዘዋል፡፡

በሌላ በኩል፣ ጢንጎ ተረኮችን ከወሰድን ፣አጀማመሩ እንደ መማሳ ሳይሆን፣

ተራኪ 'Xingo xingani' (ተረት ልናገር ወይ) ሲባል፣

ታዳሚ 'Xingo' (ተናገር/ሪ) ይባላል፣

ከዚህ በኋላ፣ ተራኪ ተረኩን ተናግሮ ሲያበቃ፣

"anin mansha beddi'

Gateekin gaafi gawwi"

"በእኔ ጆሮ ይተከል

በሌላው ቀንድ ይብቀል" በማለት ይደመድማል፡፡

ታዳሚዎችም በመደነቅ፣ በመገረም ወይም እንደሁኔታው በቁጭት ያሰላስላሉ፡፡ ይህ አቀራረብ ትረካውን አንድ ሰው ብቻ ተናግሮ በዚያው እንዳያበቃ ወይም እንዳይቆም ነው፡፡ እያንዳንዱ ታዳሚ ቀንድ እንዳይበቅልበት በየተራ እየተቀባበለ የሚያውቀውን እንዲናገር ማድረጊያ ስልት ነው ይላሉ፡፡ እስካሁን ዝርው ቃል ተረኮቹን ተመሳስሎና ልዩነቶቻቸውን ተመልክተናል፡፡ በህብረተሰቡ ማህበረ -ባህላዊ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ፋይዳ እንመልከት፤

> *ዘወትር ተደስተው የሚኖሩ ሁለት ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ እነዚህ ሰዎች በኑሮአቸው ምንም ያልተጓደለባቸው ናቸው፡፡ እሷ በቤት ውስጥ በምታከናውናቸው ሥራዎች ሁሉ እርሱ ከአጠገቧ አይለይም፡፡ በስለው የሚቀርቡ ነገሮች ስታዘጋጅ፣ "ካላዘጋጀሁ" እንጀራም ስትጋግር፣ "ካልጋገርኩ"፣ ወጥ ስትሰራ "ማማሰያ ካልያዝኩ"፣ ስታቦካ "ዱቄት ካላቀረብኩ"፣ እያለ በእያንዳንዱ ስራዋ ውስጥ ጣልቃ መግባቱን ግን አጥብቃ ትጠላበት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ «ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም» እንደሚባለው የዚህ ሰው ድርጊት በባህሉ የማይወደድና qurranjo "ሴት አውል" እንደሚያሰኝ፣ ደጋግማ ብትነግረው "ተው" እያለች ብትመክረውም ምንም ሊያሻሽል አልቻለም፡፡ እሷ በምትሰራቸው ስራዎች ሁሉ ጥልቅ ስለሚልባት ብቻ ሳይሆን ባለመተው ትበሳጭ ነበር፡፡ አንድ ቀን በዚህ ዓመሉ የተነሳ ታኮርፍና ወደ ወላጆቿ ዘንድ ጥላው ሄደች፡፡ እርሱም በማግስቱ ተከትሏት አማቾቹ ቤት መጣ፡፡ እንደደረሰም ሚስቱ መኖሯን አረጋገጠ፡፡ የልጅቷ ወላጆችም አማታቸውን ወደ ቤት አስገቡት፡፡ ተረጋግተው ጥቂት ከቆዩ በኋላ ምንም እንዳላደረጋት ልቦናው ስለሚያውቅ «ኸረ ለመሆኑ አኩርፋ የመጣችበት ምክያንት ምን በደል ተፈጽሞባት ነው?» ሲል ለአማቾቹ ጥቄውን አቀረበ፡፡ እርሷም በወላጆቿ ስትጠየቅ «ባለቤቴ ሌላ ምንም በደል ያደረሰብኝ የለም፡፡ ነገር ግን፣ ሁልጊዜ በምሰራው የሴት ስራዎች ሁሉ ጣልቃ ስለሚገባ ያስጨንቀኛል፣ ሁኔታው በባህላችንም ቢሆን qurranjo (ቁራንጆ) ስለሚያሰኝ፣ የእገሊት ባል እኮ «እንደዚህ*



ADDIS ABABA UNIVERSITY ... LIBRARY

*ነው» እየተባለ ስም እንዲሰጠኝ አልፈልግም።» በማለት መለሰች። ነገሩ በአማቾቹ ፊት ሲነገር እጅግ አፈረ። ቀስ ብሎ ብድግ አለና ሾልኮ ከአካባቢው ጠፋ። ነገሩ ከአማቾቹ አልፎ በአካባቢው ህዝብ መዘባበቻ እንዳይሆን ስለሰጋ ዳግመኛ አልተመለሰም። ዓመል ያመጣል ከመሐል የሚባለውም ይኸው ነው።*

በተጠቀሰው ቃል ተረክ እንደምንመለከተው፣ ከየግል ባህርያቸው በስተቀር ምንም ሳይጎድልባቸው በመልካም ሁኔታ ይኖሩ የነበሩ ባልና ሚስት የኋላ ኋላ ይኸው የግል ባህርይ ወደ ውጭ በመውጣቱ ሳቢያ ለፍቺ ተዳርገዋል። ነገሩ ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስስ አይለቅም እንደሚባለው ምንም እንኳን እርሱ ቢያምንበትም በህብረተ-ሰቡ ተቀባይነትና ድጋፍ ካላገኘ "ፀያፍ" ብሎ ይነቅፈዋል።

የተረኩ ይዘት ነገሮችን ከግል ብቻ ሳይሆን ከህብረተ-ሰቡም አንፃር ተመልክቶ ሚዛናዊ አቋም መያዝ እንደሚገባ ያስገነዝባል። ከዚህም ሌላ አንዱ የሌላውን ባህርይ ችሎ መሸፈንም ይገባል። ሁኔታዎችን ፈጥኖ ወደ ውጭ ከማውጣት በፊት ረጋ ብሎ መወያየት አስፈላጊ መሆኑን ያስተምራል።

ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውንና ድብቅ ባህርያትን አውግዘው በምትኩ ግልፅነትን የሚያስተምሩባቸው ከስብስቡ x15፣ x16፣ x19፣ x28 ይመለከቷል።

*በዱሮ ጊዜ አንድ ባለጸጋ ሰው በአንድ አገር ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ሰው ሲሞት ሀብትና ንብረቱን የሚያወርሰው ምንም ልጅ አልነበረውም። ልጅ ማግኘ ት የዘወትር ፀሎቱ ነበር፣ ሆኖም ምኞቱ ሊሳካለት ባለመቻሉ ሥራው ሁሉ እያገባ መፍታት ብቻ ሆኖ ቀረ። ይሁን እንጂ እያገባ ከሚፈታቸው ሴቶች መካከል ከአንዷም እንኳን መውለድ ሳይችል እስከሽምግልና እድሜው ዘለቀ። የኋላ ኋላ ግን በሽምግልና ዕድሜ ደረጃው ላይ እያለ አንዲት ልጃገረድ አግብቶ ጥቂት ጊዜያት አብረው እንደኖሩ በጠና ታመመ። እርሱም የሰውነቱን ሁኔታ ገምቶ በተኛበት ቦታ አዲሷን ሚስቱን ጠርቶ አጠገቡ ካስቀመጣት በኋላ እንዲህ አላት «ይኸውልሽ እኔ ህመሜ የበረታ ነው፤ የምድንም አይመስለኝም፤ አሁን አንቺ ፀንሰሻል፤ የምትወልጂውም ወንድ ልጅ ነው፤ እዚህ በግቢያችን ባለው ትልቅ ዛፍ ስር ብዙ ወርቅና ብር አኑሬአለሁ፤ የተፀነሰው ልጅ ተወልዶ ካደገ በኋላ፣ ይህን ምስጢር ንገሪው፤ ከዚያ በፊት አንቺም ሆንሽ ሌላ ሰው ይህን ነገር መንካት የለበትም።» ብሎ ያደራ ቃል ተናገረ። ሰውዬው ይህን በነገራት በሶስተኛው ቀን ይሞታል። እንደነገዛዜው ጥቂት ወራት ቆይታ ወንድ ልጅ ወለደች። ልጁን በማሳደግ ሂደት ውስጥ እያለች በችገራት ጊዜ የወርቅና የብሩ ጉዳይ ትዝ እያላት ለተወሰነ ጊዜያት ብትቆይም ግን ልጁ እስከሚያድግ ድረስ አላስቻላትም። ልጁስ ለምን ይሰቃያል? አለችና ከውጭ ሰው ቀጥራ የዛን ትልቅ ዛፍ ስሩን ብታስቆፍር፣ ብታስቆፍር፣ የተባለውን ወርቅና ብር ልታገኝ አልቻለችም። ተስፋ ሳትቆርጥ በተከታታይ፣ በስፋትም፣ በጥልቀትም፣ አስቆፍራ ዛፉን ጭምር ብታስነቅለው እንኳን ለማግኘት ሳትችል ቀረች። እሷም «ባሌ ዋሽቶኝ ነው እንጂ ማግኘት ነበረብኝ።» ትልና ተስፋ ቆርጣ አርፋ ልጇን ማሳደግ ቀጠለች። ልጁ አባትየው በነገራት ዕድሜ ደረጃ ላይ በደረሰ ጊዜ ለማንኛ ውም ኑዛዜውን መንገር አለብኝ አለችና አንድ ቀን ይህንኑ ሚስጢር ለልጁ ትነግረዋለች። ልጁም «እናቴ ሆይ አባቴ ይህን በነገረሽ ጊዜ የት ሆኖ ነበር?»*

*ሲል ጠየቃት። እርሷም አስታወሰችና «እዚህ ቦታ ላይ ነበር» ብላ ታሞ ተኝቶ የነበረበትን ሥፍራ አመለከተቻው። ልጁም ያንን ቦታ ቆፈር ቆፈር ቢያደርገው በርካታ ወርቅና ብር ተገኘ። እሷም ከቶ ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ደጋግማ ብታሰላስል ሚስጢሩን ማግኘት አልቻለችም። ልጁ ግን «ይኸውልሽ እናቴ፣ አባቴ ሲናዘዝ ትልቁ ዛፍ ያለው ሌላ ሳይሆን ራሱን ነው። ከስሩ ያለውም ታሞ ተኝቶበት የነበረበትን ቦታ ነው።» ብሎ ተናገረ። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ያገኙትን ወርቅና ብር እየተጠቀሙ በደስታ መኖር ጀመሩ ይባላል።*

ከላይ የቀረበው ቃል ተረክ ይዘት የሚያመለክተው፣ ለአንድ ነገር ቶሎ መጓጓት፣ የሰዎች ተፈጥሮአዊና ባህርያዊ መለዮው መሆኑን ነው። እንዲህ ስለሆነም ከአግባብ ውጭ እንዳይሆን እርጋታንና ታጋሽነትን ይጠይቃል። በተረኩ እንደተጠቀሰው ሴትዮዋ ባሏ ከመሞቱ በፊት በሆዷ ፅንስ መያዟን ገልፃለት ነበር። ጊዜው ደርሶ ልጁ ተወለደ። ባል ከመሞቱ በፊት ብዙ ወርቅና ብር መሬት ውስጥ መቅበሩንና ልጁ ሲያድግ ያባቱን ኑዛዜ እንድታሳውቀው አደራ ብሎ ይህ ቃል ትቶ አልፏል። እርሷ ግን ችግሯን መታገስ ቃሏን መጠበቅ አላስቻላትምና ቆፈረች አስቆፈረች ምን ብትደክም ግን አላገኘችም ቃል ነውና ጊዜው ሲደርስ ግን እንደኑዛዜው አካሄድ የተባለው ወርቅና ብር ተነኘ። ለቀጣዩ ኑሮኣቸውም የሚበጅ ሊሆን ቻለ።

ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ተስፋ ሳይቆርጡ እስከመጨረሻው ድረስ በጽናት በዝለቅ እንደሚገባ የሚያጠናክሩባቸው ከስብስቡ x5፣ x7፣ x14፣ x25፣ x27፣ x29 ይመለከቷል።

በመሠረቱ በሰው ልጅ የማህበራዊ ኑሮ ታሪክ ውስጥ የተለያዩ ትውልዶችን እንደሰንሰለት በማያያዝ ህብረተሰባዊ ህልውናቸው እንደይናጋ ሲያደርጉ የኖሩት መፃሕፍት ሳይሆኑ ትውፊት መሆናቸውን አትኩሮ ማሰብ ያስፈልጋል፡ በማለት ታደሰ ታምራት (1973፡5) ገልፀዋል።

*በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ውስጥ ተረቶች የሚነገሩባቸው የራሳቸው ዓላማዎች አሏቸው። ከህይወትና ከሥራ ልምድ የተገኙ ዕውቀቶችን፣ ግብረ-ገባዊ ምግባራትን፣ ትልቅ ትንሽ ሳይባል በህብረተ-ሰቡ ውስጥ ለማስተላለፍ ረድተዋል እየረዱም ነው። በተለይ እንደዛሬ ዘመናዊ ትምህርት ባልተስፋፋበት ዘመን ለእርስ በርስ መማማሪያ የዕውቀት ማስተላለፊያ ሆነው አገልግለዋል።*[44]

በህብረተ-ሰቡ ውስጥ ዝርው ቃልተረኮች ለተለያዩ ዓላማዎችና ግልጋሎቶች እንደሚነገሩ በተደጋጋሚ ተገልፆአል። ለማጠቃለል፣ ከመስክ የተገኙ የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣
ይዘቶቻቸው፣

[44] ፀጋዬ ኦብሴ ነሀሴ 27/1999ዓ.ም ዲላ

AAU IES LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

የህብረተሰቡን ልማዳዊ ሥርዓቶች (ፋጬን፣ ጎንዶሮን፣ ቁጠላን ወዘተ.) መግለጫ ብቻ ሳይሆኑ፣ ማጠናከሪያም በመሆን፤ እነዚሁ ልማዶች ዘለቄታ ይኖራቸውም ዘንድ መላልሰው በህዝቡ ውስጥ እንዲተከሉ በማገልገል፤ ጉብዝናን፣ ጀግንነትን፣ አልበገር ባይነትንና ደፋርነትን፣ የመሳሰሉ ባህርያትን በማበረታታት፤እንዲሁም የህብረተሰቡን ሰናይ ምግባራት በሁለንተናዊ መልካቸው ለማስረፅና፤ ትክክለኛ ብሎ ከተቀበላቸቸው መንገዶች የሚያፈነግጡትን ወገኖች ለመገሰፅ የሚያገለግሉ እንደሆኑ መገንዘብ ተችሏል።

## ማጠቃለያና ይሁንታ

በዚህ ጥናት የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው ያላቸውን ግንኙነትና ተደጋጋፊነታቸውን በተለያዩ መረጃዎች ለማየት ተችሏል።

ለአብነት በጥናቱ ውስጥ ከተጠቀሱት የህብረተ-ሰቡ አምልኮታዊና ልማዳዊ ሥርዓቶች መካከል፦ ፋጬ፡ (Facie) ጥፋትን አምኖ ፊት ለፊት መናዘዝ የሚለው አንዱ ነው። መጥፎ ነገር ሰርቶ/ታ ፋጬ የማያደርግ፣ ወይም ለማድረግ ድፍረቱ የሌለው የህብረተሰቡ አባል ራሱን ብቻ ሳይሆን የቤተ-ሰቡን አባላት ጭምር ለማንኛውም ዓይነት አደጋ ያጋለጠ ነው ተብሎ ይታመናል። ከእንደዚህ ዓይነቱ ሥጋት የመላቀቂያ መንገድ ደግሞ ቢቻል ህብረተ-ሰቡ ሰናይ ያላቸውን መንገዶች መከተል ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ማንኛውም ዓይነት ጥፋት ቢፈፀም አእምሮአዊ ንፅህና (cleansing) መጎናፀፍ የሚቻለው ፋጬ በማድረግ ብቻ ነው። ሌላው ጎንዶሮ ሲሆን፣ ጎንዶሮ (Gondoroo) ከተራ አለመግባባት እስከ ህልፈተ-ህይወት ድረስ ለሚከሰቱ ግጭቶችና አለመግባባቶች እልባት የሚያገኙበት የፍርድ ሥርዓት ነው። ዘመናዊነት ቀስ በቀስ እየተካው እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ህብረተ-ሰቡ ራሱን በራሱ እየዳኘና ተገቢ ያለውን ፍርድ እየሰጠ በጎንዶሮ ሥርዓት ሲዳኝ ቆይቷል። ይህ ሥርዓት የሥልጣን ገደቡ ይነስ እንጂ ዛሬም ድረስ ይሰራበታል። ቄጣላ (Qeexla) የጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ሰላማዊና የተረጋጋ ማህበራዊ ኑሮውን የሚያናጉ ድርቅ፣ ረሃብ ፣ ጦርነት ፣ በሽታ፣ የመሳሰሉ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ሲያጋጥሙ፣ ህብረተሰቡ በአንድነት እየተሰባሰበ ማጌኖ (Mageno) የሚማፀንበት ሥርዓት ነው።

ከተጠቀሱት በተጨማሪ፣ ባህላዊ ጋብቻቸውና የሀዘን ሥርዓቶቻቸው ምን እንደሚመስሉና እንዴት እንደሚከናወኑ በጥናቱ ውስጥ የተቃኙ ናቸው። ጥንታዊ የጌዴኦ ህብረተ-ሰብ አባቶች ከየት ተነስተው፣ ዛሬ ከሚገኙበት ቦታ እንደደረሱ የሚገልጹ፣ ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ እንደ "ብሔራዊ መዝሙር" የሚዘወተር ባህላዊ ዜማ አለ ይህም፤

"Harssun fulliee Hawaxeen Fullenie
Nuoo Jillatie Hado…..ohooh"

ፍቺውም፣

"ሐርሱና ሐዋጣ የእኛነታችን መገኛ ናቸው፣
ዛሬም ትዝታቸው በእኛም ውስጥ አለ።"

የመዝሙሩ ይዘት ሲብራራ፣ ጥንት የህብረተሰቡ አባቶች ሐርሱ፣ ሃዋጣ በሚባሉ ደጋማና ለም በሆኑ ስፍራዎች ይኖሩ ነበር ይባላል፡፡ አካባቢያቸው እየለማ ቁጥራቸውም እየጨመረ ሲሄድ፣ ቀስ በቀስ ወደ Haroo Walabu (ሐሮ ወላቡ) ዘለቁ፡፡ ቀጥሎም ወደ ዛሬው... የጌዴኦ የወይና ደጋና ቆላማ ወረዳዎች እየተሰፋፉ መጡ፡፡ በዚያ የተማከለ አስተዳደር ባልነበረበት ዘመን፣ ብሔረ-ሰቡ ይመራና ይተዳደር የነበረው፣ በራሱ 'Geda' ባህላዊ አስተዳደር ሥርዓት ነበር፡፡ ህዝቡ ራሱን ችሎ የራሱን እምነት እያራመደ "aayyokie aabbokie...Mageno" "የእናት ያባቴ አምላክ ትናንት የነበርክ፣ ወደፊትም የምትኖር" እያለ የዕለት ሥራውን እያከናወነ ኑሮውን ይገፋል፡፡

ጥንትም ሆነ ዛሬ፣ የጌዴኦ ህብረተ-ሰብ ልማዳዊ፣ (ባህላዊ) አምልኮታዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወቱ የሚቆራኝበት የራሱ ማህበራዊ ተቋም አለው፡፡ ይህም በአካባቢው ስያሜ ሶንጎ (songo) የሚባለውና እያንዳንዱን መንደር በቅርብ ርቀት ያማከለ ስፍራ ነው፡፡

እያንዳንዱ ሶንጎ አንድ መሪ ሐይቻ (Hayycha) ይኖረዋል፡፡
በዚህ ስፍራ፣

- የባህላዊ አስተዳደሩ ደንቦች የሚወጡበት፣ ደንቦቹም በተግባር የሚውሉበት፣
- ዳኝነት የሚታይበት እርቅ የሚካሄድበት ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ላይ ቅጣት የሚወሰንበት፣
- የዕደ ጥበብ ሙያዎች ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፉበት፣
- በአካባቢው ህይወት ፈታኝ ሁኔታዎች (ድርቅ፣ ረሃብ፣ በሽታ ጦርነት) ሲከሰቱ ነዋሪዎቹ ተሰባስበው Mageno (አምላክን) የሚለምኑበት፣
- አባቶች ሽማግሌዎችና አዛውንት ለወጣቶች ስለህይወት ገጠመኞቻቸው ስለህብረተሰቡ ባህልና ወግ በቃል ተረኮቻቸው የሚያስተምሩበት፣

ባህላዊ ተቋም በመሆን አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል እንደጥንቱ ባይሆንም፣ ዛሬም እነዚሁ ተግባራት እየተከናወኑበት ለመሆኑ በጥናቱ ተጠቅሷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮችን ምንነት ከመናገራችን አስቀድሞ፣ ስለዝርው ቃል ተረኮች ምንነት በተለያዩ የመስኩ ምሁራን የተሰጡትን አስተያየቶች መቃኘት ለዚህ ጥናት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቶ ነበር፡፡

በዚህም መሰረት ስለዝርው ቃል ተረኮች ገለፃ፣ ስለተረኮች ዓይነቶች ወዘተ.፣ ከመፃህፍት የተገኙ ግንዛቤዎች በመረጃነት ተጠቅሰዋል።

የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች መማሳ (Mammassa) እና ጢንጎ (Xingo) ተብለው በሁለት ጉሳዊ ምደባዎች እንደሚገኙ ጥናቱ ያመለክታል።

በህብረተሰቡ ውስጥ የሚያበረክቱትን አገልግሎት ስንመለከት፣

መማሳ

- የህብረተ-ሰቡን ጥንተ አመጣጥ (origion) የታላቅና የታናሽ ልጆች ያደረጓቸውን የዘመናት ጉዞ ከየት ተነስተው የት እንደደረሱ በመግለጽ ቃላዊ መረጃ ሆነው ያገለግላሉ።
- የህብረተ-ሰቡን ልማዳዊ ደንቦችና ሥርዓቶች (ፋጬ፣ ጎንዶሮ) ለማጠንከር ያገለግላሉ።
- በሚታዊ ተረኮች አማካይነትም የፈጣሪውን (Mageno) ተረዳኢነት እንዲሁም፣ በቸርነቱ ርህራሄውን በቁጣው ደግሞ ችግር፣ ረሃብ፣ ድርቅ፣ ጦርነት በመሳሰሉት እንደሚቀጣ ለመግለጽ ያገለግላሉ።
- ስለጌዴኦ ጥንታዊ ነገሥታት (አኮመኖዬ፣ ጉሳሎ ወዘተ) ዝና በአፈ-ታሪክ ለመግለጽ ያገለግላሉ።
- በዙሪያው ከበውት የሚገኙትን ወንዞች፣ ዝናብ፣ ፀሐይ፣ ልምላሜና ድርቅ ለመግለጽ ያገለግላሉ።

በጢንጎ አማካይነት ደግሞ፣

- ሞኝ ወይም ተታላይ እንዳይሆኑ ብልሃትን፣
- እምቢተኞች ወይም አፈንጋጮች እንዳይሆኑ ሥነ-ምግባርንና ግብረገብነትን፣
- ድብቅ እንዳይሆኑ ግልፅነትን፣
- አድሏዊ እንዳይሆኑ የትክክለኛ ፍርድ ምንነትን፣
- መኖር በራሱ ለሚጠይቀው ረጂምና እልህ አስጨራሽ ፈተና ባጭሩ ተስፋ ሳይቆርጡ እስከመጨረሻው እንዲዘልቁ ፅናትን፣ ያስተምሩባቸዋል።

በአወቃቀር ረገድ ሲመረመሩ የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች በተለይ ጢንጎ (Xingo) ከመማሳ በተለየ የመደምደሚያ አካሄድ እንዳላቸው ተመልክቷል። የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች ይዘቶቻቸው ሲመረመሩ፣ የህብረተ-ሰቡ ልማዳዊ ሥርዓቶች (እሴቶች) ለማጠንከርና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ለመትከልም የሚያገለግሉ ሆነው ተገኝተዋል።

እነዚህ በህብረተ-ሰቡ ውስጥ እጅግ የጎላ ሚና የነበራቸው ዝርው ቃል ተረኮች ከ1890ዓ.ም ወዲህ ባሉት ዓመታት ውስጥ ወደ አካባቢው በመጡ ሃይማኖቶች (ፕሮቴስታንት፣ ክርስትና፣ እስልምና ወዘተ.) እንዲሁም በዘመናዊ ት/ቤቶች መስፋፋት ሳቢያ ቀስ በቀስ እየተተውና እየተረሱ መጥተው ጭራሹኑ ወደ ማይነገሩበት ደረጃ እንደደረሱ በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ።

የዚህ ጥናት ይሁንታ፣ አሁን አሁን እየተተውና እየተረሱ በመሄድ ላይ ያሉትን የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮችና ልማዳዊ ሥርዓቶቻቸው ጭራሽኑ ደብዛቸው ከመጥፋቱ በፊት፣ የሚገኙትን ቶሎ ቶሎ በመሰብሰብ፣ ቀደም ላሉትና ላሁኖቹ እንደትዝታ፣ ለነገዎቹና ለመጪዎቹ ደግሞ እንደማስታወሻ እንዲሆኑ በቅርስነት ለማኖር፣

በጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓቶች ውስጥ ህብረተሰቡ አጥብቆ ሊይዛቸውና ሊከተላቸው የሚገቡ፣ ሰላም፣ ፍትህ፣ እውነትና ሐቅ እንጂ፣ ግጭት አድሎአዊነት፣ ሐሰትና ክህደት የእርሱ አለመሆናቸውን እንዲገነዘብ ማድረጊያ ጠቃሚ እሴቶች እንዳሏቸው መረጃዎች ያመለክታሉ። ስለሆነም፣ እነዚህ ታውቀውና በሌሎችም እንዲታወቁ በማድረግ ረገድ ጥናቱ የራሱ ድርሻ ይኖረዋል። በዚህ ሳቢያም ለሌሎች የሥነ-ቃል ጥናቶች መነሻ በመሆን ሊያገለግል እንደሚችል የጥናቱ አቅራቢ ይገምታል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## መዘርዝር /Bibliography/


ሀብተማርያም ማርቆስ፣ 1973፣ "የተረቶች መልክና መልዕክት" በ1973ዓ.ም ለትውፊት ሴሚናር የቀረበ፤ አ.አ በስቴንስል ተባዝቶ የተጠረዘ፡

ላጵሶ ጌድሌቦ፣ 1982፣ የኢትዮጵያ ረጅም የህዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ አንደኛ መፅሐፍ፣አ.አ. ንግድ ማተሚያ ቤት።

ብርሃኑ ገበየሁ፣ 1995፣ "የስነ ቃል ምንነት፣ ዘውጎችና አተናተን"፤ በወጣቶች፣ ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር የተዘጋጀ አገር አቀፍ የስነ-ቃል ወርክሾኘ ላይ የቀረበ፤ ከግንቦት 12-14 ቀን 1995፣ ናዝሬት፣ያልታተመ።

ተስፋዬ ካሳው፣ 1994፣ "የዲላ ከተማ አመሠራረት ታሪክ" ለመጀመሪያ ዲግሚያ የቀረበ፤ ዲግፅ፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ።

ታደሰ ታምራት፣ 1973፣ "አፋዊ ታሪክ መሠረቱ ዘዴውና ምስክርነቱ፣" በ1973 በአ.አ.ዩ. ለትውፊት ሴሚናር የቀረበ፣ አ.አ በስቴንስል የተባዛ።

የወጣቶች ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር፣ 1995፣ የኢፌዲሪ የባህል ፖሊሲ፣ አ.አ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

የይርጋጨፌ ወረዳ ባህልና ማስታወቂያ 1992፣ የይርጋጨፌ ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ፣በታይፕ ተፅፎ የተባዛ።

የጌዴኦ ዞን ማህራዊና ኤኮኖሚ ልማት፣ 1996፣ የሥነ-ሕዝብ መልከኣ ምድራዊ መረጃዎች፤ በዞኑ ቢሮ በታይፕ ጽሑፍ የተዘጋጀ ጥራዝ፣ ሰኔ 1996፣ ዲላ።

የጌዴኦ ዞን ግብርና ልማት ጽ/ቤት፣1998 ፣ የጌዴኦ ዞን ዋና ዋና ሰብሎች፣ በዞኑ ቢሮ በታይፕ ጽሑፍ የተዘጋጀ ጥራዝ፣ ዲላ።

የጌዴኦ ዞን ማስታወቂያና ባህል፣ 1997፣ "ኦዳ ያኣ ቅጽ 1" በዞኑ ባህል ዋና መምሪያ በዓመት አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ዓመታዊ መጽሔት፣ ዲላ።

ጥላሁን ኢቢዶ፣ አብርሃም አሰፋና ሽንጡ ሎሌ፣ 1991፣ "የጌዴኦ ብሔረሰብ ትውፊት" በታይፕ ተጽፎ በስቴንስል የተባዛ፣ ዲላ።

ፈቃደ አዘዘ፣ 1991፣ የሥነ-ቃል መምሪያ፤ በኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፣ አ.አ።

Abdulkadir Haji Jama, 1982, "Some Cultural Elements As Reflected in Somali Folktales", M.A. Thesis, (SGS) Addis Ababa University (AAU).Unpublished

Bascom, William, 1996, "The Forms of Folklore: Prose Narratives, 1-16", Source: Anthropology, Folklore, and Myth. ed. by Robert A. Segal: University of Lancaster, Garland Publishing, INC. New York and London.

Bayleyegne Tasew, 1999, "Anyuaa Oral Prose Narrativies, Ethnic Genres and Social Functions" M.A Thesis, SGS, AAU.Unpublished.

Ben-Amos, DAN, 1982, "Folklore in Context: Essays", South Asian Publishers, Pvt.Ltd, New Delhi.

Dagne Shibru, 1995, "Marriage and Family System Among The Gedeo of Southern Ethiopia", Department of Sociology and Social Administration, AAU, Unpublished.

Degh, Linda. "ORAL FOLKLORE: Folk Narrative." Source: Dorson, (ed.), 1972, (53-83).

Demissie Woressa, 1988, "Gedeo Traditional Social and Legal Organization", Department of Sociology and Social Administration, AAU, Unpublished.

Dorson, Richard, M. (ed), 1972, Folklore and Folk Life: An Introduction, Chicago and London: The University of Chicago Press.

Ethiopian Mapping Authority, 1988, Southern Nations Nationalities and Peoples' Regional State, In The National Setting.

Fekade Azeze, 1984, "Ethiopian Oral Literature: A Preliminary Review and Bibliography", Eighth International Conference of Ethiopian Studies. Nov, 26-30/84, AAU, IES.

Finnegan, Ruth, 1970, Oral Literature in Africa, Oxford: Clarendon Press.

Gedeo Zone Tourism, Parks and Hotel Desk, 2003, "Gedeo Zone Attractions, Tourist Guide Map", English and Amharic Written Brochure, Dilla.

Goldstein, Kenneth G., 1964, A Guide for Fieldworkers in Folklore. Hatboro, Penna., and London: Folklore Associates and Herbert Jenkins.

Knustsson, K.E., 1967, "Authority and Change: A Study of Kallu Institution Among The Mecha Galla of Ethiopia." Geterberg: Printed in Sweden.

Mac Donald, A. Donald. "Fieldwork: Collecting Oral Literature." Source: Dorson, (e.d.), 1972 (404-430).

Mc Clellan, Charles W. 1988, State Transformation and National Integration, Gedeo and the Ethiopian Empire 1895-1935, by the Board of Trustees, Michigan State Univ. African Studies Center, Michigan State university.

Melakneh Mengistu, 1990, "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folk tales" M.A. Thesis SGS, AAU, Unpublished.

Mullen, Patrick B., 1992, "Mollie Ford: How the old teach the Young." Dept. of Ethiopian, Languages and Literature. M.A. in Eth. Literature and Folklore, Reader for ETLi. 624: Field Work in Folklore (Teaching Material), selected and compiled by, Fekade Azeze, March 2003.

Okpewho, I., 1992, African Oral Literature. Bloomington and Logan, Utah: Utah University Press.

Oring, Eliot, 1986, Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction, Logan, Utah: Utah University Press.

Propp, Vladmir, 1984, Theory and History of Folklore, Translated by Ariadna Y.Martin and P.Martin and Others, Edited with An Introduction and Notes, by Anatoly Liberman, Minneapolis: University of Minnesota Press.

Sahlu Kidane, 1992, "Borana Oromo Folktales, A Contextual Study." M.A. Thesis, SGS, Addis Ababa University (AAU).Unpublished.

Tadesse Kippie Kanshie, 2000, "Five Thousand Years of Sutainability? A Case Study On Gedeo Land Use." M.A. Thesis, SGS, A.A.U.Unpublished.

Tesfaye G/Mariam, 1990, "A study of the Major Themes in Jablawi Folktales", M.A. Thesis, SGS, AAU, Unpublished.

Thompson, Stith, 1946, The Folktale. University of California Press.

Wedekind, Klaus, 1997, "Gedeo Folklore: A song Collection, A Partial Transcription and Translation of 77 Gedeo songs." Addis Ababa, Unpaged Typescript.

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | ዕድሜ | ፆታ | ሥራ | አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ቀቀቦ ሾታ | 100 | ወ | ግብርና | ምችሌ ሲሶታ |
| 2 | ሐይቻ ጂቢቾ ቦረሜ | 68 | ወ | ‹‹ | ‹‹ ‹‹ |
| 3 | ‹‹ አለማየሁ ቦኮ | 63 | ወ | ‹‹ | ዲላ ዙሪያ |
| 4 | ‹‹ ማሞ ገደቾ | 70 | ወ | ‹‹ | ‹‹ ‹‹ |
| 5 | ‹‹ ሐሚሶ ኮሬ | 63 | ወ | ‹‹ | ‹‹ ‹‹ |
| 6 | ‹‹ ጌቱ ሴጌ | 79 | ወ | ‹‹ | ሆሩ በተላ |
| 7 | ብርሃኑ ደያሶ | 48 | ወ | የጌዴኦ ቡና ልማት ዩኒየን ሥ/አ | ዲላ |
| 8 | ዘላለም ደጌኖ | 39 | ወ | የመንግሥስት ሠራተኛ | ጨኮ |
| 9 | ኃይሉ በየነ | 42 | ወ | ‹‹ | ዲላ |
| 10 | ሽንጡ ሎሌ | 57 | ወ | ‹‹ | ወናጎ ከተማ |
| 11 | ዳዊት ሞገስ | 38 | ወ | ‹‹ | ዲላ |
| 12 | ደግፌ ሀብቴ | 40 | ወ | ‹‹ | ‹‹ |
| 13 | አሰገደች ነጋሽ | 78 | ሴ | -- | ‹‹ |
| 14 | ፀጋዬ ኦብሴ | 51 | ወ | ከጌዴኦ ልማት ማህበር | ‹‹ |
| 15 | ጂግሶ በቀቴ | 48 | ወ | መምህር | ‹‹ |
| 16 | ተሰማ ጂባና | 48 | ወ | ግብርና | ይርጋጨፌ |
| 17 | ትርፌ ተሰማ | 47 | ወ | ‹‹ | ሁንጢቻ /ማ |
| 18 | ታደሰ ቱምሶ | 45 | ወ | ‹‹ | ይርጋጨፌ |
| 19 | ኩቤ ቡቡ | 71 | ወ | ‹‹ | ዎቻማ ገ/ማ |
| 20 | ፊጋ በዲሴ | 89 | ወ | ‹‹ | ‹‹ ‹‹ |
| 21 | አታራ ሲዳሞ | 80 | ወ | ‹‹ | ‹‹ ‹‹ |
| 22 | ወርቁ ማሞ | 47 | ወ | ‹‹ | ኮቾሬ |
| 23 | ጥላሁን ኢቢዶ | 56 | ወ | የመንግሥት ሠራተኛ | ዲላ |

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

## በጽሑፍ፣በድምፅ (ቃለ መጠይቅ) እንዲሁም በቡድን ውይይት የተሳተፉ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 23 | በቀለ ማሩ | 34 | ወ | የጌዴኦ ኪነት ባልደረባ | ኮቸሬ |
| 24 | ሚደቅሳ ሩፎ | 38 | ወ | የመንግሥት ሠራተኛ | ወናጎ |
| 25 | ታደሰ ገርማሞ | 35 | ወ | ‹‹ | ዲላ |
| 26 | አሻግሬ ተሾመ | 30 | ወ | ‹‹ | ዲላ ዙሪያ |
| 27 | ትዕግሥት ከበደ | 36 | ወ | ‹‹ | ገደብ ወረዳ |
| 28 | ከፍያለው ቦራ | 40 | ወ | ‹‹ | ኮቸሬ |
| 29 | አበበ ፀጋው | 29 | ወ | መምህር | ቡሌ |

## በትርጉም ሥራ የተባበሩ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 30 | ደምሴ ወትዬ | 45 | ወ | ገ/ማ/ሊ/መንበር | ከጌዴኦፋ ወደ አማርኛ በቃል ማስተርጎም |
| 31 | ዕድሉ ሴጌ | 32 | ወ | መምህር | ‹‹ ‹‹ ‹‹ ‹‹ |
| 32 | መኮንን ተስፋዬ | 31 | ወ | የመንግሥት ሠራተኛ | ከጌዴኦፋ ወደ አማርኛ የጽሑፍ ሥራ |

## የተረኮች ስብስብ

### M1. የጌዴኦ ዘር ሐረግ

ጌዴኦ ዛሬ ከሰፈረበት ደጋማ አካባቢ ጥንት ሶስት ወንድማማቾች ይኖሩ ነበር። እነርሱም ደራሶ፣ ኡራጎና ቦሩ ይባላሉ። አባታቸው በእርጅና እየደከመ ስለሄደ ለኑዛዜ ሰበሰባቸውና ኑዛዜውን አሰምቶ በሞተ ጊዜ በመካከላቸው አለመግባባት ተፈጠረ። በዚህ አለመግባባት የተነሳ ሁሉም ወደተለያዩ አቅጣጫዎች ተበታተኑ። ከእነርሱ መካከል ለአባትዬው የመጀመሪያ ልጅ ወይም አንጋፋ የሆነው ደራሶ ሆኖ ለዛሬው የጌዴኦ ኅብረተ-ሰብ አባት ሆነ። ኡራጎ ደግሞ የዛሬዎቹ የጀምጀም አላዱ ጉጂዎች አባት ሆነ። ቦሩም፣ ለቦረና ጎሣዎች አባት ሆነ ተብሎ በአፈታሪክ ይነገራል።

አንጋፋው ደራሶ ሁለት ሚስቶች በየተራ አግብቶ በጠቅላላው ሰባት ልጆች ወለደ። ከመጀመሪያ ሚስቱ አራት ልጆችን ወለደ። እነርሱም ደረሻ፣ ደቦኣ፣ ጎርጎሻ፣ ሐኑማ የሚባሉ ሲሆኑ በጌዴኡፋ ሾሌ ባጤ (Sholle bexxie) አራት ልጆች ይባላሉ።

ከሁለተኛዋ ሚስት የተወለዱት ደግሞ ሒምባኣ፣ ሎጎዳ፣ ባካሮ ሰሴ ባጤ (Sassie bexxie) ሶስት ልጆች ሲሆኑ፣ በድምሩ ሰባት ናቸው። እነዚህ ልጆች የዛሬዎቹን የጌዴኦ ኅብረተ-ሰብ ጎሳዎች (Torbaane Gosa) ለማስገኘት የበቁ ናቸው ተብሎ ይነገራል።

### M2 የጌዴኦ ህብረተ-ሰብ አመጣጥ

ጥንት የጌዴኦ አባቶች ከሰሜናዊ አቅጣጫ የአባይን ወንዝ ተሻግረው እንደመጡ ይነገራል። ፈጣሪ ማገኖ (Mageno) የአባይን ወንዝ ለሁለት ከፍሎ አረፋውን እንደ ድንጋይ አድርጎ አሻገራቸው። ሆኖም የደረሱበት ቦታ ባዶ መሬት በመሆኑ ሰዎቹ መሬቱን መደብደብ ጀመሩ። ቅሬታቸውን ፈጣሪ ሰምቶ እናንተ ወደ ለምለም ስፍራ ወደ ደቡብ ትሄዳላችሁ አላቸውና ጎሽ እንዲመራቸው ታዘዘላቸው ። እርሱም እየመራ አምጥቶ ከሐሮ ወላቡ አደረሳቸው።

በሐሮ ወላቡ በሚኖሩበት ጊዜ በመካከላቸው ምንም ግጭት አልነበረም። ሁሉ ንም ችግሮቻቸውን እርስ በእርስ በመመካከር ይፈቱ ነበር። ውሎ አድሮ ግን ያን እየመራ ያመጣቸውን ጎሽ አንድ ተንኮለኛ ሰው በጦር ወግቶ ገደለው። በዚህ ድርጊት ማገኖ 'Mageno' አዘነ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በህብረተ-ሰቡ መካከል ስምምነት እንዲጠፋ አደረገ:: በመካከላቸውም ጠብና ግጭት ተጀመረ:: ጎሹን የገደለው ሰውዬ ውገኖች ዓይናቸውን የታወሩ፣ እግራቸው ሽባ የሆኑ፣ አካለ ስንኩላን ልጆችን ይወልዱ ጀመር:: በጌዴኦ ህብረተ-ሰብ አካለ ስንኩላን የሆኑ ሰዎች የተፈጠሩት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የመጣ ነው እንጂ ከዚያ በፊት አልነበረም እየተባለ ይነገራል ::

**M3. ቡሌ ወረዳ ለምን ለም ሆነች?**

ከጌዴኦ ዞን ወረዳዎች ቡሌ በልምላሜዋ ትታወቃለች:: ይህቺ ወረዳ ልምላሜዋን ይዛ እስከዛሬ የኖረችበት አንድ ንግር ስላላት ነው ይባላል። ይህም ንግር (ወደፊት ይሆናል የሚባል ትንቢት) እንደዚህ ነው:: ማገኖ (Mageno) አንድ ቀን ወደ ምድር የወረድኩ እንደሆነ ይህቺ ስፍራ ማረፊያዬ ትሆናለች " ብሎ ስለባረካት ነው ተብሎ በአፈታሪክ ይነገራል::

**M4. ቡና ለምን ሦስት ጊዜ ይፈላል?**

በአገራችን ቡና ሦስት ጊዜ የሚፈላው ለምን ይሆን ብለው ይገረሙ ይሆናል:: ጥንት አቦል፣ ቶናና በረካ የተባሉ ሶስት ጓደኛሞች በገዳም ውስጥ ይኖሩ ነበር:: ከዕለታት አንድ ቀን እነዚህ የገዳም አዛውንት በበረሃ ውስጥ ሲጓዙ በጣም ይራባሉ:: እነዚህ ሰዎች በጉዞ ላይ እያሉ ቀያይ ፍሬዎችን ያዘሉ ወፍ ጠላሽ ተክሎች ያጋጥሟቸዋል:: በዚህ ጊዜ ረሃቡን ለማስታገስ አቦል፣ ተሽቀዳድሞ እነዚያን ቀያይ ፍሬዎች ሸምጠጥ ሸምጠጥ አድርጎ መብላት ጀመረ:: በጣም ስለጣፈጠው ሌሎቹም እንደሱ እንዲበሉ ነገራቸው:: ነገር ግን ቶና «እነዚህን ፍሬዎች ከጥሬ ይልቅ ቆልተን ብንበላ ይሻላል» ሲል ሀሳብ አቀረበ። እነርሱም ተስማሙና ፍሬዎቹን ለመቁላት መሸምጠጥ ሲጀምሩ፣በረካ፣ በበኩሉ የተቆላውን አፍልቶ መጠጣት እንደሚሻል ሌላ አሳብ አቀረበ:: ሦስቱም በዚህ ሀሳብ ተስማሙና የሸመጠጡትን የቡና ፍሬ ቆልተው አፍልተው መጠጣት ቀጠሉ:: ለጊዜው ረሃባቸውን አስታግሰው ጥንካሬም አግኝተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: አቦል (የመጀመሪያ)፣ ቶና (ሁለተኛ) በረካ (ሦስተኛ) እየተባለ ቡና ሦስት ጊዜ መፈላት የተጀመረው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው ይባላል::

**M5. አኮመኖዬ**

በጥንታዊ ጌዴኦ አኮመኖዬ የምትባል ንግሥት ነበረች:: በእርሷ ዘመን የቤት ውስጥ ሥራዎችንና የተወለዱ ልጆችን ጭምር ተንከባክቦ የማሳደግ ሥራ የወንዶች ነበር:: ባንፃሩ የሴቶች ሥራ ቀለል ቀለል ያሉና ብዙም ጉልበትን የማይጠይቁ ነበሩ:: ንግሥት አኮመኖዬ ማንኛውም ጉልበት የሚጠይቁ ሥራዎችን የምታሰራው ወንዶችን ብቻ እየመረጠች ነው::



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በዚህ ሁኔታ ሲኖሩ ከዕለታት አንድ ቀን ወንዶችን በሙሉ ሰበሰበችና አንጣጤ (Anxxaxie) ከስንደዶ ምንም ያህል በማይወፍር እንጨት ከምድር ከፍ ከሰማይ ዝቅ ያለ ቤተ-መንግስት ባስቸኳይ እንዲሰሩላት:: ቀጭን ትዕዛዝ አስተላለፈች:: እነርሱም እንዴት መስራት እንደሚችሉ መላ ማፈላለግ ጀመሩ:: ምድረ ወንድ ተጨነቀ:: እርሷን የሚያስደስታት ነገር ከዚህ በላይ የለም:: ይበልጥ አስቸጋሪና ፈታኝ ሥራዎችን እየፈለገች ወንዶችን እያስጨነቀች ማሰራት የዘወትር ተግባሯ ነበር::

በዚህ ውሃ ቀጠነ ትዕዛዝዋ የተማረሩ ወንዶች እያደር ሥርዓቱን ለመለወጥ ትግል ማድረግ ጀመሩ:: እርሷን በማጥፋት አገዛዝዋን ለመቀየር በየጊዜው ቢመክሩም መላው በቶሎ ሊገኝ አልተቻለም:: አንድ ቀን እርሷ በሌለችበት ወንዶች በድብቅ ተሰብስበው ሲመክሩ ዋሉ:: መላው ጠፍቶባቸው ወደ መበተኛቸው አቅራቢያ አንድ ድንክዬ ድሃ ሰው በዚያ አካባቢ ሲያልፍ ጠሩትና ሁኔታውን አስረዱትና እርሱም ያለውን ብልሃት እንዲያካፍላቸው አግባቡት::

እርሱም በነገሩ ጥቂት አሰበና እንዲህ አላቸው:: «አኮመኖዬ በማትኖርበት ጊዜ ጠብቃችሁ አንድ ጥልቅ ጉድጓድ ቆፍሩ፣ ስትቆፍሩም ከእናንተ በስተቀር ሌላ ወገን እንዳያይ በምስጢር ይሁን፣ ከጉድጓዱ የሚወጣውንም አፈር ምንም ሳይቀር ከአካባቢው አርቁ:: በጉድጓዱ ላይ ምንጣፍ አድርጉበት በመጨረሻም የእርሷን ሞቴ (Motite) (መቀመጫ) በላዩ ላይ አስቀምጡበት:: ቀጥሎም ውሃ በእንስራ ሞልታችሁ አፍልታችሁ ተጠባበቁ:: አኮመኖዬ መጥታ የተለመደውን ትዕዛዝ ለማስተላለፍ ሞቴዋ ላይ ለመቀመጥ ስትሞክር ጉድጓድ ውስጥ ትወድቃለች:: በዚህ ጊዜ የፈላውን ውሃ ቶሎ ቶሎ ስታፈሱባት ሕይወቷ ያልፋል::» ሲል መከራቸው:: ተናገረ እነርሱም እንደተባሉት አደረጉ:: አኮመኖዬ ይህን መሰል ሴራ ሲሸረብባት እገዛ ያላደረጉላትን ሴቶች ከመሞቷ በፊት "ከእንግዲህ ቀሚሳችሁን ወደቀኝ መዥርጡ! ምን ጊዜም ከወንዶች በታች እንጂ የበላይ አትሁኑ !" ብላ ረገመቻቸው ሞተች:: የሴቶች የበላይነት አክትሞ በወንዶች ቁጥጥር ሥር የሆኑት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው ይባላል:: (ተራኪ ጥላሁን ኢቢዶ)

**M6. ጎሳሎ ( Goosallo)**

በጌዴኦ ባህላዊ አስተዳደር ሥርዓት ጥንታዊው የእማዊ ዘመን ሲያበቃ በቦታው የተተካው የጎሳሎ አስተዳደር ነበር ይባላል:: ይህ አስተዳደር ገደብ ያልነበረው የትውልድ ሐረግ ነበረው :: አንዱ ጎሳሎ ሲሞት፣ በሌላ አንድ ጎሳሎ እየተተካ ለረጅም ጊዜ የሚሄድ ነበር:: በዚህ አስተዳደር

ውስጥ የበላይነቱን ይዞ የሚመራው ሰው የራሱ ተግባራት ነበሩት፡፡ አዘውትሮ ለህዝቡ ማገዮን ይለምናል፡፡ ሰዎች ወደ አደን ሲወጡ መርቆ ይሸኛል፡፡ ሲመለሱ እንደዚሁ በጎውን በመመኘት ይቀበላል፡፡ አጥፊዎችን ይረግማል፡፡ ህዝቡን በሥልጣናዊ ትዕዛዛቱ ሥር ለማስተዳደር ጥረት ያደርጋል፡፡

በዚህ አስተዳደር ይሰራባቸው የነበሩ ደንቦችና ልማዶች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- የተወለዱ ልጆች በእናታቸው ሳይሆን በአባታቸው እንዲጠሩ፣
- የንብረት ሀላፊነትና ማስተዳደር የወንዶች እንጂ የሴቶች እዳይሆን እንዲሆን፣
- የህዝብ መሰብሰቢያ ሶንጎዎችን ማደራጀት፣
- ስብሰባዎች በወንዶች ብቻ እንዲመሩ የሚሉት ጥቂቶቹ ነበሩ፡፡ ሁሉንም ነገር ቀስ በቀስ በወንዶች ቁጥጥር ሥር እንዲውል በማድረግ የወንዶችን የበላይነት ማረጋገጥ ተቻለ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እነዚህ ባህላዊ ደንቦች በሥራ ላይ በመዋል እስከዛሬ ድረስ ሊደርሱ ችለዋል እየተባለ ይነገራል፡፡

**M7. ሙርጋ ጎሳሎ (Murqa Goosallo)**

ሙርጋ ጎሳሎ የመጨረሻው የጎሳሎ ዘረ ሐረግ ነው፡፡ በእርሱ የአገዛዝ ዘመን የህዝቡ ቁጥር ከበፊቱ በጣም ጨምሮ ነበር፡፡ በዚህም ሳቢያ ቀድሞ የነበረው የርስ በርስ መረዳዳትና መተጋገዝ ቀርቶ አባት ልጁን፣ ልጅም አባቱን የረሳበት ዘመን ሆነ፡፡ ባጠቃላይ ሰዎች ከመተዳደሪያ ሥርዓታቸው ያፈነገጡበት፣ ከሙርጋ ጎሳሎ ቁጥጥርና ትዛዝ ውጭ እየሆኑ የመጡበተ ወቅት እየታየ መጣ ፡፡ ሁኔታውን ለመቆጣጠር ሲል ሙርጋ ጎሳሎ በሚወሰዳቸው ርምጃዎች ቀስ በቀስ አምባገነናዊ ገጽታው እየተከሰተ መጣ፡፡

በድርጊቱ የማይደሰቱ ሰዎች ቁጥር እየበረከተ መጣ፡፡ በሥርዓቱ ያልተደሰቱና ለውጥ የሚፈልጉ ወገኖች በየጊዜው ቢያጉረመርሙም ሥር ነቀል ለውጥ ማምጣት አልቻሉም፡፡ መቼም የተንኮል ጥበበኞች አይጠፉምና ውሎ አድሮ አንድ መላ አገኙ፡፡ አንድ ቀን አንድ ጥልቅ ጉድጓድ በምስጢር ቆፍረው አዘጋጁና በሚስጢር ሲጠባበቁ ቆዩ፡፡ አንድ ቀን ሳያስበው ድንገት ጎሳሎ ተያዘና በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ በቁሙ ተቀበረ፡፡ ከዚያም ዙሪያው ታረሰና ደብዛው እንዲጠፋ ተደረገ፡፡

ሙርጋጎሳሎ በዚህ የህዝብ አመፅ ከሥልጣን ተወገደ። ከርሱ በኋላ፣ ህዝብ መክሮ ይሁን ባለው መሪ መተዳደር ጀመረ። ህዝብ የመከረበትና የተስማማበት የገዳ ሥርዓት መሪ መምረጥ የተጀመረው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው ይባላል።

**M8. ዝናብ ለምን ይዘንባል?**

የሰማይ አምላክ የሆነው መገኖ ( Mageno) ጥንት በምድር ላይ ከሰዎች ጋር አብሮ ይኖር ነበር ይባላል። ከጊዜ በኋላ ከሰዎች ጋር በምድር የሚያደርገውን ኑሮ ተወና ወደ ሰማይ ወጥቶ ከጸሐይ፣ ከደመናና ከንፋስ ጋር አብሮ መኖር ጀመረ። ይሁን እንጂ እነዚህም ቢሆኑ ውሎ አድሮ መገኖን የሚያስቀይም ድብቅ ባህርያቸው ቀስ በቀስ እየተከሰተ መጣ ። በዚህ ድርጊታቸው ቅር የተሰኘው ማገኖ ፍርድ ሰጣቸው ። ፀሐይ ብርሃኗ እንዲህ የሚያንፀባርቀው እንዳትታይ ፊቷን ለመደበቅ ሰትል ነው። ዝናብ ሆኖ የሚወርደው ደመና በቁሚ ቁልቁል የምትለቀው ሽንት ነው። ሁልጊዜ ከዝናብ በፊት ሰማይ የሚያስገመግመውና መብረቅ የሚያጓራው ንፋስ እነርሱን በየቤታቸው ሲያሯሩጣቸው ነው ይባላል ። (ተራኪ ትርፌ አለኝታ)

**M9. Mageno( ማገኖ )**

በጥንት ጊዜ ማገኖ በመሬት ላይ ከሰው ልጆች ጋር አብሮ ይኖር ነበር ይባላል። በቅርቡ ስለሚያገኛቸው ሰዎችን ሁሉ በችግራቸው ይረዳቸዋል። የታመሙትን ያድናል፣ የተወለዱ ያድጋሉ የተዘራ ሰብል ይበቅላል፣ የደረቀ ይለመልማል። ሁሉንም በቅርበት እያየ ችግራቸውን ወዲያው ይታደጋቸው ነበር።

ይሁን እንጂ ሰዎች ተመስገን እያሉ በሰላም ከመኖር ይልቅ ዘወትር በጥፋት ላይ ይሰማሩ ነበር። በዚህ ድርጊት ቅር ተሰኝቶ መገኖ (Mageno) ወደ ሰማይ አረገ። ከዚያ በኋላ ሰዎች በከፍተኛ ችግር ላይ ወደቁ። ላለፈ ተግባራቸው ይቅር እንዲላቸው አዘውትረው ተማፀኑ። ሆኖም መገኖ ካረገ በኋላ ማንኛውንም የሰው ልጅ ችግር በቀጥታ እርሱ ሳይሆን ዋቤኮ (Wabeeko) በሚባሉ የምድር አዋቂዎች በኩል ብቻ እንዲሆን የተደረገው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው። የሰው ልጅ ችግር ላይ ሊወድቅ የቻለው የፈጣሪን ተራዳኢነት ባለመረዳቱ ነው እተባለ ይነገራል።

**M10. የሶንጎ አጀማመር**

ጥንት በሲዳማ የየሰፈሩ እረኞች አንድ ላይ በመሆን ዳስ እየሰሩ «ሆያ ሆ» «ሆያ ሆ» እያሉ ሲጫወቱ ይውሉ ነበር:: ጨዋታው አብቅቶ ማታ ወደ የቤታቸው ሲበተኑ ቀን የሰሩትን ዳስ አፍርሰው ይለያዩ ነበር:: ይሁንና ሁልጊዜ ዳሱን እያፈረሱ እንደገና በነጋታው ሌላ አዲስ ዳስ መስራቱ እየሰለቻቸው ስለሄደ፣ ይቅር ተባባሉና መፍረሱ ቀረ:: ለሁሉም አማካይ በሆኑ ስፍራዎች ጠንከር ያሉ ዳሶችን ተሰሩ:: ከመካከላቸው አባት ወይም እናት ያልሞተበት ልጅ ተመርጦ የጨዋታው መሪ ሆኖ ይሾማል፡፡ በዚህ ዓይነት ለረጅም ጊዜ ሲካሄድ ቆይቶ ቀስ በቀስ ይህ የእረኞች የቡድን ጨዋታ በዱር ብቻ መወሰኑ ቀርቶ፣ ለአካባቢው ህብረተሰብ መልካም ምኞትንና ምርቃት ወደ መስጠት ሥርዓት እያዘነበሉ ሄዱ፡፡ በየሰፈሩና በየቤቱ እየዞሩ ዝናብ እንዲዘንብ፣ መካኖች እንዲወልዱ፣ የተወለዱ ህጻናት በጤና እንዲያድጉ፣ ሰላም እንዲሰፍን ወዘተ. በመሳሰሉ ማህበራዊ ጉዳዩች ውስጥ እየገቡ በቡድን መሪያቸው አስተባባሪነት ምርቃት መስጠት እያዘወተሩ መጡ:: በየሚዞሩባቸው ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ለምርቃቱ በረከት እንዲሆን ተቀቅሎ የሚበላ «ዱባ» ይሰጧቸው ነበር::

በኅብረተ-ሰቡ ባህል መሰረት «ልጆች ወደ አምላክ የቀረቡ ንጹህ ናቸው» ተብሎ ስለሚታመን፣ በእነርሱ ላይም ይህ እምነት ይበልጥ እየጠነከረና ስር እየሰደደ ሄደ:: እንዲያውም እነዚህ ልጆች የሚናገሩት ሁሉ በፈጣሪ እየተመሩ ስለሆነ ምርቃታቸውም ሆነ ርግማናቸው ይደርሳል እየተባለ መፍራት ተጀመረ :: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እያደር እየዋለ ቀደም ሲል ይሰጧቸው በነበረው ዱባ ምትክ ለእርሻ ያልደረሰ ወይፈን ይበረከትላቸው ጀመር:: በጊዜ ብዛት ከልጆች ይልቅ ሽማግሌዎችና አዛውንት ተተኩ ::ሥፍራውም ሶንጎ የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ዛሬ ከሚገኝበት ደረጃ ለመድረስ በቅቷል እየተባለ ይነገራል::

**M11 የፍስሃ ገነት ከተማ ስያሜ**

በይርጋጨፌ ወረዳ የምትገኘው የፍስሃ ገነት ከተማ ይህን ስያሜ እንዴት እንዳገኘች የሚነገር አንድ አፈታሪክ አለ:: ጥንት ያካባቢው ገገር ሆኖ የተሾመ አንድ ሰው በመጀመሪያ ፍስሐ የተባለ ወንድ ልጅ ወለደ:: ቀጥሎ ደግሞ ገነት የተባለች ሴት ልጅ ወለደ:: ታዲያ ወላጆች ሁለት ልጆች ያፈሩበትን ይህን አካባቢ የሚያስታውሱበት አጋጣሚ እንዲሆን ከተማዋን «ፍስሐ ገነት» ብለው ሰየሟት:: ይህቺ ከተማ የዛሬውን መጠሪያዋን ያገኘችው በዚህ ሁኔታ ነው እየተባለ ይነገራል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

**M12 የጌዴኦ ወንዞች አፈጣጠር**

በጌዴኦ ውስጥ የሚገኙ ወንዞች ሁሉ መነሻቸው ሐሮ ወላቡ "Haroo Woolabu" ነው ይባላል:: በጥንት ጊዜ ከዚህ ኩሬ ውስጥ አንድ ነጭ ከብት ከነነፍሱ ከዋሻ ወጥቶ በእዚያው አካባቢ ይኖር ነበር። ይህ ከብት ሳር እየበላ ከቃሮ ወላቡ ውሃ ሲጠጣ ቀና ብሎ ወደ ቀኝ ዞር ሲል ከአፉ የሚንጠባጠበው ውሃ እርሱ ከቆመበት አቅጣጫ፣ በስተቀኝ የሚገኙት የጌዴኦ ወንዞች ተፈጠሩ:: እንደገና በሌላ ጊዜ ሳሩን ውሃውን ሲጠጣ፣ ቀና ብሎ ወደ ግራ ዞር ሲል በስተግራ ያሉት ወንዞች ተፈጠሩ:: ዛሬ በዞኑ ዳገታማና ተዳፋታማ ሥፍራዎች በጋ ከክረምት የሚፈሱት የጌዴኦ ወንዞችና ጅረቶች የተፈጠሩት በዚህ ሁኔታ ነው ይባላል::

**M13 ደካ ደነባ /Daka Dannaba/**

በኮቾሬ ወረዳ የጨለቅለቅቱ ከተማን መሐል ለመሐል ከፍሎ የሚያልፍ አንድ ወንዝ ደካ ደነባ እየተባለ ይጠራል:: ወንዙ ስያሜውን ያገኘው ጥንት "በካሮ"፣ "ሎጎዳ"፣ "ሒምባኣ" የሚባሉ የጌዴኦ ጎሳዎች በዚያ አካባቢ አብረው ይኖሩ ነበር:: እነርሱም በአደን ይሁን በሌላ የዘመቻ ሥራ ያገኙትን ማንኛውንም ነገር አምጥተው የሚከፋፈሉት በዚህ ወንድ ዳርቻ ነበር::

እነዚህ ጎሳዎች ያገኙትን ይዘው መጥተው ላላገኙት እኩል አካፍለው ይለያያሉ:: ደካ ደነባ "Daka Dannaba" ማለት « ያገኙትን ማካፈል ማለት ነው» ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ወንዝ ደካ ደነባ እየተባለ መጠራት ጀመረ ይባላል::

**M14 ቡና እንዴት ተገኘ?**

ቡና ተፈልቶ በትኩስነቱ የሚጠጣ በብዙ የሀገራችን ክፍል የሚገኝ ተክል ነው:: በአፈታሪክ እንደሚነገረው በመጀመሪያ የቡና ፍሬ አገኘ የሚባለው "ካልዲ አወቀ" የተባለ ኢትዮጵያዊ የፍየል እረኛ ነው:: ከዕለታት አንድ ቀን ፍየሎቹ የአንድ ዛፍ ፍሬ ከበሉ በኋላ ሲዘሉና ሲፈነጥዙ በማየቱ እጅግ ተገርመና ከተክሉ ፍሬ ቀጥፎ ለመቅመስ ወሰነ። የፍሬውን ጣዕምና ማነቃቃቱን አይቶ በሰፈሩ ለሚኖሩት መነኮሳት አሳወቀ::

በዚህ መንስኤ ቡና ነኮሳቱ ለሚያደርጉት የረጂም ሰዓት ፀሎት፣ ንቃትና ብርታት የሚሰጣቸው መሆኑ ታወቀ:: ቀስ በቀስ ሌላውም ሰው እያወቀው ሄዶ መጠጣት ተጀመረ::

እረኛው ካልዲ ባጋጣሚ ያገኘው ይህ ተክል በዓለም ተወዳጅ ጣዕም ያለው አረቢካ የሚባለው የቡና ዓይነት ነው እየተባለ በአፈ ታሪክ ይነገራል።

**M15. ሞት እንዴት መጣ**

በጥንት ጊዜ ሰውና ሌሎች ፍጥረታት በሙሉ አብረው በሰላም ይኖሩ ነበር። ምንም ዓይነት ጠብና ጭቅጭቅ በመካከላቸው አልነበረም።

ውሎ አድሮ እባብ በሰው ልጅ ላይ ቅናት ጀመረች። ከእለታት ባንዱ ቀን እባብ ሰውን እንዲህ አለችው። «እኔና አንተ በሩጫ እንፎካከር ያሸነፍክ እንደሆነ ዘላለም ትኖራለህ፣ ካላሸነፍክ ግን ሞት ያንተ ትሆናለች» አለችው። እርሱም በልቡ አሁን ካንቺ ጋር ምን የሚሉት እሽቅድድም ነው? እኔ በሶስት አራት እርምጃ የምጨርሰውን አንቺ መቼ ልትደርሺ ነው? አለና እምቢ ላለማለት ብቻ ተስማማቶ ይለያያሉ።

የውድድሩ ዕለት ደረሶ ሁለቱም ቀረበው ውድድሩ ተጀመረ። በመጀመሪያ እባብ ወደፊት ስትገሰግስ ሰው ግን አንድ ሁለት ጊዜ ተራመደና ትቶ ሌላውን ሥራ ቀጠለ ተስፋ ያልቆረጠችው እባብ ግን ከቦታው ደረሰችና አሸናፊ ተባለች። እንደ ውርርዳቸው እባብ ባረጀች ቁጥር ቆዳዋን እየገለፈፈች ስትኖር የሰው ልጅ ግን ንቆ በመሸነፉ ሞትን በገዛ እጁ አመጣ እየተባለ ይነገራል።

**M16. የበቅሎ መሀንነት**

ጥንት ገና ዓለም ስትፈጠር ሰማይና ምድር በጣም ተቀራርበው ይኖሩ ነበር ይባላል። ሰማይ የፈጣሪ መቀመጫ ሲሆን ምድር ደግሞ የሰው ልጅ መኖሪያ ነበረች። ፈጣሪ ለሰዎችና ለእንሰሳት እንዲህ ቅርብ በመሆኑ የለመኑትን ሁሉ ወዲያው ይፈጽምላቸዋል። በዚያን ጊዜ በምድርና በሰማይ መካከል የነበረው ግንኙነት የሚካሄደው በዝናብ አማካይነት ነበር። የውሃ እጦት፣ ድርቅ፣ ረሃብ፣ የሚባሉ ነገሮች በዚያን ጊዜ ከቶ አይታወቁም። በጋ ከክረምት የሚባል ነገር የለም። ሁልጊዜ ስለሚዘንብ ስፍራው ሁሉ ለምለም ነው።

ከለምለሙ ሳር እየበላች ጥጋብ የተሰማት አንዷት በቅሎ፣ ዝናቡን እንዲያቆም ለሰማይ ነገረችው። ሰማይ ግን ዝናቡን የሚሰጠው ለሁሉም በመሆኑ መዝነቡን ቀጠለበት።

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

በሁኔታው የተናደደችው በቅሎ የፈጣሪን መቀመጫ በኋላ እግሮቿ ስለረገጠችው ወደ ላይ ራቀ፡፡ ፈጣሪም በዚህ የበቅሎ ድርጊት ተናድዶ «መሐን ሁኚ» ብሎ ረገማት፡፡ በቅሎ መሃን ሆና የቀረቸው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው ይባላል፡፡

**M17. ሐሰተኛ ምላስ**

ከዕለታት አንድ ጊዜ ትዳር መስርተው የሚኖሩ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ፡፡ አንድ ቀን የታላቅየው ሚስት ድንገት ሳይታሰብ ሞተች፡፡ ባልዬው ጥቂት ጊዜ ቆየና ልጁን እንድታሳድጋት ሌላ ሚስት አገባ፡፡ ጥቂት ዓመታት አብረው እንደኖሩ እሱም ሞተ፡፡ በዚህ ጊዜ የታናሽየው ሚስት ከእንግዲህ የወንድምህን ሀብት አንተ ወርሰህ ሀብታም ሆነህ መኖር ነው ብላ ነገረችው፡፡ እሱም "እንዴት ሆና የወንዴሜ ልጅ እያለ! ይህማ እማይሆን ነገር ነው" በማለት መለሰላት፡፡

"እርሱን ለኔ ተውልኝ" አለችና ተንኮል ማውጠንጠን ጀመረች፡፡ አንድ ቀን ወደ ሶንጎ (Songo) ሄደችና ለገዳ አባላት "የባለቤቴ ታላቅ ወንድም ልጅ ደፍሮኛልና ፍርድ ይሰጠኝ " ስትል ተናገረች፡፡ በባህሉ መሠረት ልጁ ተጠርቶ ቀረቦ ፋጬ (እውነቱን እንዲናዘዝ ) ተጠየቀ፡፡ እርሱ ግን ነገሩ ፍፁም ሐሰት መሆኑን ደጋግሞ ገለጠ፡፡

ሽማግሌዎቹም «እንግዲህ በደንባችን መሠረት ሃጢአት ሰርቶ እውነቱን ሳያወጣ የቀረ ሰው ይረገማል » አሉ፡፡ "እውነትን በሐሰት ደብቆ ወደ እኛ የመጣ ከሳሽም ይሁን ተከሳሽ በቁሙ ይቀበር" ብለው ረግመው እነሱን ወደ የመጡበት ሸኟቸው፡፡

ከዕለታት ባንድ ቀን ሴትዋ ውሃ ልትቀዳ ወደ ወንዝ ስትወርድ ሳታስበው አንድ እግሯ ንቃቃት ውስጥ ገባ፡፡ ብትጎትተው ከመውጣት ይልቅ ጭራሹኑ ወደ ውስጥ እየሰመጠ ሄደ፡፡ ጮኸች፤ ሰዎች ሊያወጡላት ቢሞክሩም አልቻሉም፡፡ እዲያውም ቀስ በቀስ ሌላው አካሏም ወደ ውስጥ እየገባ እየሰመጠ ሄዶ በቆመችበት ሰምጣ ሞተች ይባላል፡፡ ሐሰተኛ ምላስ እሷ ጥላ ሆና ክፉ ነገር ታናግራለች የሚባለውም ይህ ነው፡፡

ጢንጎ ተረኮች "Xingo Narratives"

**X1. የዝንጀሮና አይጥ ውል**

በድሮ ጊዜ አንድ ባለፀጋ ትልቅ ሰርግ ደገሰ። በሰርጉም ላይ ዝንጀሮና አይጥ ይተዋወቁና ባልንጀራሞች ይሆናሉ። በየጊዜውም ስለኑሮኣቸው ሁናቴ እየተገናኙ ይወያዩ ነበር። አንድ ቀን እንደልማዳቸው ሲገናኙ አይጥ ዝንጀሮን «እኛ የራሳችን የምንለው ንብረት ሳይኖረን ዕድሜያችንን ፈጀነው አይደለም?» ሲለው ዝንጀሮም መልሶ «ካልክስ እኔም ዘወትር በጣም የሚቆጨኝ ጉዳይ ቢኖር ይኸው ነገር ነበር» አለና ወዲያው «ታዲያ ለምን የኛ የግላችን የሆነ ሀብት አይኖረንም?» ሲል መልሶ ጠየቀው። አይጥም በዝንጀሮ ሃሳብ ተስማማ ሁለቱም በተስማሙበት ሃሳብ መሠረት በጋራ አርሰው አምርተውና ሰብስበው ባንድነት ለማከማቸት ወሰኑ። ወደ ስራው እንደገቡም በመጀመሪያ አንድ ማሳ ገብስ ዘሩ። ሰብሉም ሲደርስ ተወቃና ባንድ ጎተራ ተከተተ። የጎተራው ሰብል ሌላ ወገን እንዳይዘረፍባቸው በተራ በተራ ለመጠበቅ ተስማሙ። በመጀመሪያ አይጥ ለመጠበቅ በራሱ ፈቃደኛ ሆነ።

ዝንጀሮም በሃሳቡ ተስማምቶ ወደ ግል ስራው ተሰማራ። አይጥ ጎተራውን እየጠበቀ ሳለ ድንገት አንድ ሃሳብ መጣለት። ይህም ጎተራውን ከስሩ ሰርስሮ ጉድጓድ መቆፈርና እህሉን ወደ ጉድጓዱ ማስረግ ፈለገ። እንዳሰበውም ጉድጓዱን ቆፈረና ቀስ በቀስ እህሉን እያሰረገ ጎተራውን ባዶ አስቀረው። በሌላ ጊዜ ዝንጀሮ ተራው ደርሶ በመጠበቅ ላይ እያለ፣ አይጥ ድንገት መጣና «እስቲ እህላችንን አውጥተን ሸጠን እንካፈል» አለው። ዝንጀሮም «እሺ» አለና ተነስተው ጎተራውን ከፍተው ቢያዩ ጭብጥ የሚሞላ እንኳን አልተገኘም። ዝንጀሮ በጣም ደነገጠ። አይጥ እንደመናደድ አለና «እህሉን አንተ ሳትኖር ጎተራ ከፍቶ የወሰደው ቢኖር ነው እንጂ በእኔ ጊዜ ምንም አልሆነም። እኔ ከዚህ ሳልንቀሳቀስ ጠብቄ አስረክቤሃለሁ እያለ መደንፋት ጀመረ።

ዝንጀሮ ጎተራውን ጥሎ የትም አለመሄዱን ስለሚያውቅ ከቶ እንዴት ሊሆን ቻለ? በማለት ተጨነቀ። «ታዲያ አሁን ምን ይበጀናል?» ሲል አይጥ ጠየቀ። ዝንጀሮም «እኔ እንደሆን ከዚህ ንቅንቅ ሳልል በጥንቃቄ ነው የጠበቅሁት ሲል አይጥ መለሰለት። «አየህ አቶ ዝንጀሮ እንግዲያውስ አንድ ሃሳብ መጣልኝ በማን ጊዜ የጎተራው እህል እንደተዘረፈ እውነቱን ለማግኘት ያፍ ክርክር የትም አያደርሰንም። እውነትና ሐሰቱን የሚያውቀው ማገኖ (ፈጣሪ) ብቻ ነው። ሆኖም ማንኛችን እውነተኛ እንደሆንን ለመለየት እንዲቻል አንድ ባዶ ቤት ውስጥ ሁለታችንም ገብተን ይዘጋብንና ከውጭ እሳት ይለኮስ እውነተኛ የሆነው ምንም ሳይነካው ከእሳት ውስጥ

ይወጣል። ሐሰተኛው ግን ይቃጠላል አለው። ዝንጀሮምየልቡን ኀዕህና ያወቃልና በቀረበው ሀሳብ ተስማማ።

በስምነታቸው መሰረት ሁለቱም ከአንድ የሳር ጎጆ ውስጥ ገቡና ከውጪ እሳት ተለኮሰባቸው። አይጥ ቶሎ ብሎ ወደ ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ ሲሰወር ምስኪኑ ዝንጀሮ ግን በእሳቱ ነበልባል ካሁን አሁን ነፍሴ ተለየችኝ እያለ ከፍተኛ ጭንቀት ያዘው። ከየት መጣ የማይባል ከባድ ዝናብ ድንገት መዝነብ ጀመረ። እየተቀጣጠለ የነበረው ጎጆ እሳቱ ጠፋ ዝንጀሮም ሳይቃጠል ተረፈ አካባቢው ሁሉ በጎርፍ ተጥለቀለቀ። አይጥ በቆፈረው ጉድጓድ ሳይቀር ዘልቆ ሲገባ ገብሱ ወደ ውጭ እየተንሳፈፈ ወጣ። አይጥም በጎርፉ ውሃ ሞተና ሬሳው ተንሳፍፎ ተገኘ። ተንኮል ተንኮለኛውን ይዞ ይጠፋል የሚባለው እንደዚህ ነው።

**X2. እሺታ**

በህይወቱ "እሺ" ከማለት በስተቀር 'እምቢታን' የማያውቅ አንድ ቅን ሰው ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ከጓደኞቹ ጋር ሲጫወት በህይወቱ የተጠየቀውን ሁሉ ከመፈፀም በቀር አንድም ቀን እምቢ አለማለቱን ነገራቸው። ከጓደኞቹ መካከል አንደኛው ይህን ጉዳይ ሰምቶ ይዞ ቆይቶ ልየው አለና በሌላ ጊዜ ተመልሶ መጥቶ «ወንድሜ ይህ የያዝከው ጦር እኮ የኔ ነው» ይለዋል። እምቢ ማለትን የማያውቀው እሺታም «ያንተ ከሆነ እሺ ውሰድ» ብሎ ሰጠው።

አሁንም በሌላ ጊዜ ቆይቶ ይመጣና «ይህ የምታጭድበት ማጭድ እኮ የኔ ነው» ሲለው እሱም «እሺ» ብሎ እንዲወስደው ይፈቅድለታል። ብዙ ጊዜ ቆይቶ እንደገና ተመልሶ ይመጣና ሚስቱን «ይቺ እኮ በመጀመሪያ የኔ ሚስት ነበረች። አንተ ያገባሃት ከእኔ በኋላ ስለሆነ እኔ መልሼ መውሰድ አለብኝ» ይለዋል። አሁንም «እሺ» ይልና ሚስቱን ይሰጠዋል። ከዚህ ሁሉ በኋላ እሺታ አንድ ነገር ትዝ አለው። «ይህ ሰው ለአራተኛ ጊዜ ከመጣብኝ ቤቴን ያስለቅቀኛል፣ ልጆቼንም ይወስድብኛል፣» አለና ልጆቹን ይዞ ወደ ሩቅ አገር ተሰደደ። በጉዞው አጋጣሚ ልጆቹ ራሳቸውን ችለው ያለ እርዳታ መሻገር ከማይችሉበት አንድ ትልቅ ወንዝ ደረሱ።

ሁለቱን ልጆቹን በየተራ ወንዙን ለማሻገር አሰበና፣ መጀመሪያ ትልቁን ልጅ እንኮኮ ብሎ ካሻገረ በኋላ ሁለተኛውን ልጁን ለማሻገር ወንዙን እየተሻገረ ሳለ፣ በመካከል ላይ በድንገተኛ ደራሽ ውሃ ይወሰዳል። ውሃው የተወሰነ ርቀት ከወሰደው በኋላ ሳይሞት ከነህይወቱ ወደ አንድ ዳርቻ

ተፋው። በተፈጠረው ሁኔታ ራሱን የሳተው ሰውዬ ነፍሱ መትረፏን ሰተያስታውስ፣ ከዚያ በፊት ግን ምን እንደሆነ ሲያስታውስ አልቻለም።

ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ወደ ንጉሱ ዘንድ ሄዶ ለማገልገል ወስኖ ይሄዳል። እንደደረሰም ንጉሱ ሁኔታውን አይቶ እሺታ የሚለውን ስም እሱም ያፀናለታል። «በል እንግዲህ ወደ እግዚአብሄር ዘንድ ሄደህ መልዕክቴን አድርስልኝ እኔ የአንድ አገር ብቻ ገገር ሆኜ የምቀመጠው እስከመቼ ድረስ ነው? ለምን ግዛት አይጨመርልኝም?» ብለህ ጠይቅና «መልሱን ቶሎ ይዘህ ተመለስ» ብሎ ላከው። እሺታም መልዕክቱን ወደ እግዚአብሄር ለማድረስ ጉዞውን ጀመረ።

በመንገዱ ላይ አንዲት ወፍጮ በመፍጨት የምትተዳደር ሴት አገኘቼውና ወዴት እንደሚሄድ ጠየቀችው። እርሱም በነገራት ጊዜ ተገረመችና «እባክህ ለኔም እስከመቼ ድረስ በዚህ ሥራ እተዳደራለሁ? ስለዚህ ከዚህ እንዲያወጣኝ ለእግዚአብሔር ንገርልኝ» አለችው። እርሱም እሺ እጠይቃለሁ ብሏት መንገዱን ቀጠለ።

ቀጥሎም አንድ ሳር አጫጅ ዘንድ ደረሰ እሱም እሺታን ወዴት እንደሚሄድ ቢጠይቀው ወደ እግዚአብሄር ዘንድ መሆኑን ነገረው። እሱም «እንግዲያው እኔ እድሜ ልኬን ሳር አጫጅ ሆኜ የምኖረው ለምን እንደሆነ ጠይቅልኝ።» አለው። እሱም እሺ አለውና አልፎት ሄደ።

በመቀጠል መንገዱ ላይ ያገኘው ሰው በአንድ በሬ ብቻ የሚያርስ ገበሬ ነበርና ወዴት እንደሚሄድ ቢጠይቀው። እሱም ወደ እግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን ነገረው። እሱም በበኩሉ «እባክህ አንድ በሬ እንዲጨምርልኝ ለእግዚአብሔር ንገርልኝ» አለው። እሱም እሺ አለውና ሄደ።

ቀጥሎ ያገኘው ሰው ሁለት በሬዎችን ጠምዶ በማረስ ላይ ከሚገኝ ገበሬ ጋር ነበር። እሱም ወዴት እንደሚሄድ በጠየቀው ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን ነገረው። ገበሬውም በበኩሉ «እኔ እስከመቼ ድረስ በሁለት በሬዎች ብቻ አርሳለሁ? ሌሎች ሁለት በሮች እንዲጨምርልኝ ንገርልኝ» አለው። አሁንም እሺ ብሎት አልፎት ሄደ።

ቀጥሎ ያገኘው ሰው በአራት በሬዎች የእርሻ ስራውን ከሚያከናውን ገበሬ ጋር ነበር። እሱም ወዴት እንደሚሄድ በጠየቀው ጊዜ ወደ እግዚአብሄር ዘንድ ለማገልገል መሆኑን ነገረው። «እንግዲያውስ ባገኘኸው ጊዜ እኔ እስከመቼ በአራት በሬዎች ብቻ ሳርስ እኖራለሁ? አራት በሮች

ጨምረህ ስምንት አታደርግልኝምን ወይ?» በልልኝ አለው:: እርሱም እንደተለመደው እሺ ብሎት አሁንም ወደፊት መንገዱን ቀጠለ::

በመጨረሻ እሺታ ራሱን እግዚአብሔርን ያገኘውና ወዴት እንደሚሄድ ጠየቀው «ለእርሱ አገልጋይ ለመሆን እንደመጣ ተናገረ» እሱም መልሶ «ለምን ዓይነት አገልግሎት?» ቢለው «ማንኛውንም ጌታዬ እንድፈፅም ያዘዘኝን ሁሉ ነው::» ሲል መለሰለት:: «እንግዲያውስ ለማገልገል የመጣኸው ከእኔ ዘንድ ከሆነ አሁን በመጣህበት አኳኋን ተመልሰህ የምልህን እየነገርክ ትሄዳለህ::» አለውና ትኩር ብሎ ቢያየው ሰውዬውም እንደልማዱ እሺ አለ::

«በመጀመሪያ በአራት በሬዎች ጠምዶ ለሚያርሰው ገበሬ በዚሁ ተግቶ እንዲሰራ ንገረው:: ባለሁለት በሬዎች ብቻ ላለው ሌላ ሁለት እንደምጨምርለት ንገረው:: ባለ አንድ በሬ ብቻ ላለው አንድ ሌላ ጨምሬ ሁለት እንደማደርግለት ንገረው:: ለሳር አጫጁ ሰው ግን ለእንስሶቹ ሳር አጭዶ ሳያበላ በሀሰት በልተዋል እያለ ያም ማዋሉን እንዲተው ንገረው:: ለወፍጮ ፈጪዋም ቢሆን እንደዚሁ የሚሰጣትን እህል እያፈሰሰች ካባከነች በኋላ ፈጭቼ ጨረስኩ እያለች ሐሰት መናገሯን እንድታቆም ንገራት::

በመጨረሻ ወደዚህ ለላከህ ንጉስ ግዛት የመጨመር ጉዳይ የራስህን አባት ጠይቀው ብለህ ንገረው » ብሎ ላከው:: በዚህ መሰረት ለሁሉም የእግዚአብሔርን ምላሽ እየነገረ መጥቶ ንጉሱ ዘንድ ደረሰ ንጉሱም እግዜር ካለው ቃል ሌላ ምን ተስፋ አለኝ አለና አባቱን ለመጠየቅ ሲሄድ በድንገት ወድቆ ሞተ::

ንጉሱ ወራሽ ስላልነበረው እሺታ ዙፋኑን ወርሶ ንጉስ ሆነ:: አገሩን በማስተዳደር ላይ አዲስ ንጉሥ ነግሷል ማለትን የሰሙ ሁለት ልጆች ለአገልግሎት ወደ እርሱ ዘንድ መጡ:: አባታቸው በውሃ መወሰዱን እንጂ ለንጉሥ አገልጋይነት ስለመምጣቱ አንዳቸውም አያውቁም:: ከብዙ ጊዜ ቆይታ በኋላ በአገልጋይነት የገቡት የራሱን ልጆች እንደሚመስሉ ሆዱ ጠረጠረ:: ነገር ግን ምንም ሳይገልፅላቸው በዘዴ ሊፈትናቸው አሰበና ገላውን እንዲያጥቡት አዘዘ:: እነሱም እንደ ታዘዙት ገላውን በማጠብ ላይ እያሉ፣ በአባታቸው ሰውነት ላይ ድሮ በህፃንነታቸው የሚያውቁትን ጠባሳ አይተው ሁለቱም ድንግጥ አሉና ጠየቁት:: እሱም ምንም ሳይደብቅ ነገራቸው:: በተፈጠረው አጋጣሚ በመደነቅ አባትና ልጆች እየተላቀሱ ተሳሳሙ:: ከዚያን ቀን ጀበሮ አገልጋይነታቸው ቀርቶ ሁሉም በደስታ አብረው መኖር ጀመሩ ይባላል::

### X3. ሐረግና ዋርካ

የዋርካ ዛፍ በተፈጥሮው ግዙፍ ሲሆን ቅጠሉ በጋ ከክረምት የማይደረቅ፣ ብዙ ውሃ ይዞ ለረጂም ጊዜ ማቆየት የሚችል፣ በቀላሉ ለድርቅ የማይጋለጥ ነው፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ወፍ ከአንድ ትልቅ ዋርካ ላይ ተቀምጣ እየተከተከች ስትበላ አንድ የሐረግ ፍሬ አምልጣ በዋርካው ባላ ውስጥ ወደቀች፡፡ በርጥበት የተነሳ ይህች የሐረግ ፍሬ ቀስ በቀስ ለምልማ ሥር እያወጣች ሄደች፡፡ ቀስ በቀስ እየለመለመች የላይ አካሏም ዋርካው ላይ እየተጠመጠመ ዕድገቷን ቀጠለች፡፡

ይህቺ ሐረግ ስሯ ወደ ውስጥ እስከሚዘልቅና ከላይም በዋርካው ላይ በደንብ እስከምትጠመጠም ድረስ ቅጠሏን በደንብ አላበቀለችም፡፡ ቀስ በቀስ በጊዜ ብዛት እየተጠናከረች ስትመጣ፣ ዋርካው በበኩሉ ምግቡም ሆነ ውሃው እያነሰና እየተቀነሰበት ሄደ፡፡ በዚህ ሁኔታ ዋርካ እየጠወለገ ሄዶ ቅጠሎቹም መርገፍ ጀመሩ፡፡ የዋርካውን ምግብ እየተሻማች የምትበላው ሐረግ እየለመለመች ሄደች፡፡ በየዋህነቱ ያስጠጋት ዋርካ ግን እያደር እየጠወለገና እየደረቀ ሄደ ይባላል፡፡ ይህ ተረት እባብ ትንሽ ነች ተብሎ ጭንቅላቷ አይረገጥም፡፡ የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚያሳይ ነው፡፡

### X4. ጦጣና ዝንጀሮ

ከዕለታት አንድ ቀን አንበሳ 'ጋሻ' ለማሰራት ፈለገና ጦጣና ዝንጀሮን ለስብሰባ ጠራቸው፡፡ በስብሰባው ላይ ጦጣ ሃሳቧን እንድትሰጥ ፈልጎ ቢጠይቃት የለም ጌታዬ ታላቃችን የሆነው ዝንጀሮ አለና እርሱ በቅድሚያ ይናገር ስትል መልስ ሰጠች፡፡ አንበሳም ጥቂት አሰበና ለየብቻ ማነጋገሩን መርጦ ዝንጀሮን ለብቻው ጠርቶ «አየህ እኔ አሁን ጋሻ ለመስራት እፈልጋለሁ ከእንስሳት ሁሉ ጠንካራ የሆነው ቆዳ የቱ ነው?» ብሎ ጠየቀው፡፡

ዝንጀሮም «ለዚህ ሥራ በጣም የሚስማማው የጦጣ ቆዳ ነው፡፡» ሲል መለሰለት፡፡ ቀጥሎም ጦጣን ለብቻ ጠርቶ ጠየቃት «ለእሷም ጌታዬ እኔ ቆዳ ለዚህ የሚሆን አይደለም ይኸው እንደሚያዩት አጅግ የሳሳ ነው ከእኔ ይልቅ የዝንጀሮ ቆዳ በውፍረትም በጥንካሬም ይበልጣል እስቲ ራስዎ በደንብ ይመልከቱ፡፡» ብላ ገልጣ አሳየችው ዝንጀሮም የጦጣን ተንኮል ቀደም ብሎ ያውቃልና ምናልባት በእኔ ላይ ያስፈረደችብኝ እንደሆነ ብሎ በመጠርጠር አስቀድሞ ወደ ጫካ ገባ፡፡ እንደፈራውም አልቀረ አንበሳ የጦጣን መልስ አምኖ ዝንጀሮን አስከበበና አሲያዘው፡፡ ቀጥሎም ካራ አስመጥቶ ለጦጢት ሰጣትና «በይ ግፈፊና ቆዳውን አምጪልኝ» ብሎ አዘዛት፡፡ እርሷም እንደታዘዘችው ለመግፈፍ በቢላ ነካ ስታደርገው «ኧ» እያለ ዓይኑን እያቁለጨለጨ



ADDIS ... ILS LIBRARY

እያቃሰተ ለመናት ። እርሷም በለፈለፉ ባፍ ይጠፉ! በለፈለፉ ባፍ ይጠፉ! እያለች ሸረካከተቺው ይባላል።

**X5. ቆቅና አውራ ዶሮ**

በድሮ ጊዜ ዶሮና ቆቅ በአካላዊ ተመሳስሎአቸው የተነሳ ጓደኛሞች ለመሆን ፈልገው ነበር ይባላል። አንድ ቀን ቆቅ ዶሮን «እባክህ ጓደኞሞች ሆነን አብረን እንኑር» ብሎ ይጠይቀዋል። ዶሮም መልሶ "ለመሆኑ ምን ተቸግረህ ነው?" ሲል ቆቅን ጠየቀው ቆቅም «የኔ ችግር ብዙ ነው ከላይ ንስር አሞራ በድንገት መጥቶ ልጆቼን ይለቅምብኛል። ማታም አውሬ መጥቶ ያስቸግረኛል። በዚህ ላይ ብርዱም ይገርፈኛል። ጠዋት ጠዋት ጤዛውና ውርጩ አንገፍግፎኛል። ስለዚህ ከነዚህ ሁሉ ችግሮች ለመዳን ስል ካንተ ጋር በቤት ውስጥ መኖር እፈልጋለሁ።» አለው። አያይዞም «በቅድሚያ ያንተን ቤት ካሳየኸኝ የእኔን ደግሞ ቀጥዬ አሳይሃለሁ ከዚያ በኋላ ወዳጅነታችን ይጠነክራል።» በማለት  አስረዳው። አውራ ዶሮ ጥቂት ካሰበ በኋላ "ብቻ እኔም ዘንድ ችግር እንዳለ ልታውቅ ይገባሃል" ሲለው፣ ቆቅም መልሶ «ምንም ይሁን ከእኔ የማይሻል ኑሮ የለም» አለውና በቅድሚ የዶሮን ቤት ለማየት ተስማሙ።

ወደ ቤት ከመሄዳቸው አስቀድሞ ግን «በእኔ ቤት ውስጥ ብዙ ነገሮች አሉ በጎች፣ ፍየሎች፣ ጥጆች፣ እነዚህ ሁሉ እኔ ከማድርበት ቆጥ ስር በቅድሚያ ይገባሉ። እኔ ከገባሁ በኋላም እሳት ስለሚነድ በቤቱ ውስጥ ጭስ ይጨሳል። ታዲያ ይህን ሁሉ ታግሰህ ከእኔ ጋር መቀመጥ ከቻልክ ብቻ ነው መሄድ የምንችለው።» አለው። ቆቅም በሃሳቡ ተስማማና አብረው ወደ ዶሮ ቤት ሄዱ። ልክ እንደተባለው በቅድሚያ እንስሳቱ ከገቡ በኋላ ዶሮች በቆጣቸው ላይ ሲሰፍሩ ቆቅም አብሮ ሰፈረ። የቤቱ እመቤት እራት ለማዘጋጀት ጭስ ስታጫጭስ ቆቅ ያልለመደው ጉዳይ በመሆኑ ተጨንቆ አውራ ዶሮን ቢያማክረው። ቻል፣ ታገስ፣ አሁን ያበቃል፣ እያለ ነገረው። እንደምንም ይታገስና ጭሱ አብቅቶ እንቅልፋቸውን እንደጀመሩ አውራ ዶሮ የመጮሂያ ሰዓቱ ደርሶ ክንፉን አርበትብቶ ሁለት ጊዜ ኩኩሉ ብሎ ጮኾ እንዳበቃ፣ ቆቅም ቀጠለና እኔም እንደልማዴ ልጩህ፣ ብሎ ዶሮን ጠየቀው። አውራ ዶሮ ግን "የለም አይሆንም" ብሎ ቢከለክለው ቆቅ አሻፈረኝ ብሎ መጮሁን ቀጠለ። በዚህ ጊዜ የቤቱ ባለቤት ዛሬ" ደግሞ ብሎ ብሎ ቆቅ ግን ክልከላውን ከዶሮቹ ጋር ገብቶ ይጮህብ ጀመር።" አለና ሚስቱን ከእንቅልፏ ቀሰቀሰ ። እርሷም ቆቅ እንዳገባ እሳት አንድዳ አረጋገጠችና ቶሎ ውሃ አፈላች። የቤቱ ጌታም ቢላውን አዘጋጅቶ መጣና ሊያርደው ሲይዘው "ምነው ጓዴ ዝም አልከኝ" ብሎ ዶሮን ቢማፀነው "ቀድሞውንም አልሰማም አልታገስም

ብለኸኛልና እዚያው አንተው ቻለው" አለው ቆቅም ታርዶ ተበላ። "ምከረው ምከረው እምቢ ባለ መከራ ይምከረው" የሚባለው ምሳሌያዊ አነጋገር የሚያሳይ ተረክ ነው።

**X6. ጭንቀት ብልሃትን ይወልዳል**

በድሮ ጊዜ ሰው ከነህይወቱ ለአውሬዎች የሚገበርበት አንድ አገር ነበር ይባላል። ይህ የሚደረግበት ምክንያትም ያካባቢው አራዊት በሙሉ ተሰባስበው ግምባር በመፍጠር ያካባቢውን ህዝብ እንዳይተናኮሉ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው።

ይህ የሰው ግብር ከየጎሳው አንዳንድ እያለ ዙሩን እየጠበቀ የሚካሄድ ነበር ። ከብዙ ጊዜ በኋላ አንድ ተራ የደረሰበት ሰው ለአውሬ ግብር እንሚሆን በተነገረው ጊዜ ሰውዬው ከፍተኛ የሆነ ጭንቀትና ፍርሃት ያዘው። በቆመበት፣ በተቀመጠበት፣ በተኛበት ቦታ ሁሉ ጭንቀቱ አላስቀምጥ አለው። ካካባቢው እንዳይሰወር ባለተራው አንጼ ከታወቀና ከተነገረ በኋላ ያካባቢው ህዝብ በሙሉ በዓይነ ቁራኛ ቀን ከሌሊት ይጠብቀዋል። ስለዚህ ማምለጫም ስለሌለው ጭንቀቱ ይበልጥ እየጨመረበት ሄደ።

በዚህ ናላው ዞሮ ህሊናው በተናወጠበት ሰዓት አንድ ነገር ድንገት ብልጭ አለበት «ግዴለም የራሴን ብልሃት እጠቀማለሁ።» አለና በአውሬ የመበያውን ቀን ይጠባበቅ ጀመር። እንደ ማይደርስ የለም ደረሰና ሰውዬው ለአራዊቱ ተሰጠ። አውሬዎች መሃል እንደተጣለ አውሬዎቹ ከመብላታቸው በፊት እያንዳንዱ ከሚጥመው ወገን ጀምሮ እንዲበላ እያንዳንዱን ጠየቃቸው። በቅድሚያ የተጠየቀው አውሬ «እኔ የሚጥመኝ ደም ስለሆነ እሱን ከጠጣሁ ለሌላው ግዴለኝም።» አለ። ሁለተኛው ሲጠየቅ ደግሞ «እኔ ሁለት እግርና አንድ ታፋ ብቻ ካገኘሁ ለሌላው ግዴለኝም።» አለ ሶስተኛው አውሬ ሲጠየቅ «እኔ ደግሞ ደሙን ጠጥቼ፣ ሥጋውን በልቼ፣ አጥንቱን ቆርጥሜ፣ መቅኑን ከመጠጥኩ ብቻ ነው የምረካው።» በማለት ተናገረ። «እንዴ! እንዲህ ከሆነማ የኔንም፣ የእርሱንም፣ ጠቅልለህ ልትወስድብን አይደለም እንዴ!» ተባባሉና በመካከላቸው ጠብ ተፈጠረ። አውሬዎቹ እርስ በእርስ ሲነካከሱ ሰውዬው ከመሐላቸው አምልጦ ወደ ቤቱ ሄደ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሰው ብልሃት ከአውሬ ብልሃት የሚበልጥ በመሆኑ አውሬ ሰውን እየፈራ በተቻለው ሁሉ ላለመቅረብ በመወሰኑ ምክንያት የሰውና የአውሬዎች መኖሪያ ተለያይቶ ቀረ ይባላል።

ADDIS ABABA U... ILS LIBRARY

## X7. ጸሐይና እንስሳት

በጥንት ጊዜ በምድር የሚኖሩ እንስሳት በሙሉ ለመመካከር ተሰባሰቡ ይባላል፡፡ የምክራቸው ዋና ጉዳይም «የፀሐይን ቁጥር መጨመር አለብን» የሚል ነበር፡፡ ለዚህም ምክንያታቸው «ፀሐይ አንድ ብቻ በመሆኗ ሌሊት ሌሊት ቅዝቃዜና ውርጭ አሰቃየን፡፡ ስለዚህ ቀንም ሌሊትም ብርሃንና ሙቀት ለማግኘት እንድንችል የፀሐይ ቁጥር እንዲጨምርልን እንፈልጋለን፡፡» የሚል ነበር፡፡

ይሁን እንጂ የመጨረሻ ውሳኔ ለማስተላለፍ ከተሰብሳቢዎች መካከል ጥንቸል የደረሰቻው ዘግይታ ነው፡፡ እነርሱም በጉዳዩ ላይ እየተወያዩ ጠበቋት፡፡ እርሷም ስትጠበቅ፣ ቆይታ ሰውነቷን ውሃ ውስጥ ነክራ ሁለመናዋ ርሶ እያለከለከች ደረሰች፡፡

«እኛ ፀሐይ አንድ ብቻ ስለሆነችብን ሌሊት ሌሊት ወደ ቤቷ ስትገባ ውርጭና ቅዝቃዜ ጨረሰን፡፡ ስለዚህ ሌላ ሁለተኛ ፀሐይ እንደሚያስፈልገን ሁላችን ተስማምተናል፡፡ “ታዲያ በዚህ ጉዳይ ላይ ያንቺ ሃሳብ ምንድነው?” ሲሉ ጠየቋት፡፡

ጥንቸልም ተረጋግታ ጥቂት እንደማሰብ አለችና ቀጥላ «ከአንድ ፀሐይ በተጨማሪ ሌላ ፀሐይ እንዲጨመር መስማማታችሁን ተረድቼአለሁ፡፡ ይሁን እንጂ የእኔ ሐሳብ ደግሞ ከዚህ የተለየ ነው፡፡ እኔ ወደዚህ ስብሰባ ለመምጣት ከሩቅ ቦታ ተነስቼ ስገሰግስ ውዬ ላብ በላብ ሆኜ ልብሴ ሁሉ ርሶ ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ እያለ እንደደረስኩ አይታችኋል፡፡ ይህ የሆነው ታዲያ በዚችው ባንድ ፀሐይ ሙቀት የተነሳ ነው፡፡ ሌላ ሁለተኛ ጸሐይ የሚደገም ከሆነ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ገምቱ፡፡» ስትል ተናገረች፡፡ በዚህ ጊዜ ከተሰብሳቢዎቹ ከፊሎቹ የየራሳቸው ገጠመኝ ትዝ አላቸውና «አዎን ልክ ነው አንዷ የቀን ፀሐይ ይህን ያህል ያደከመች ሁለት ቢሆኑማ ጭራሹንም ትንፋሽ አጥተን ቀን ከሌሊት በሙቀት እንጨነቃለን ስለዚህ የፀሐይ መጨመር አያስፈልገንም» ሲሉ ሃሳቧን ደገፉላት፡፡ በተደረገው ከፍተኛ ክርክር የጥንቸልን ሃሳብ የሚደግፉ ተሰብሳቢዎች ቁጥር በመብለጡ የተነሳ፣ ተጨማሪ ፀሐይ የማስፈለጉ ጥያቄ ውድቅ ሆነ፡፡ እስከዛሬ ድረስ ፀሐይ አንድ ብቻ ሆና የቀረችው በዚህ ምክንያት ነው ይባላል፡፡

## X8. ሌባን መያዝ በዘዴ

በዱሮ ጊዜ በአንድ መንደር ውስጥ በሌብነት ተግባር የሚተዳደር አንድ ሰው ነበር፡፡ የመንደሩ ነዋሪዎች በሚፈጸመው ድርጊት ሁል ጊዜ ቢናደዱም፣ ሌባውን ከመካከላቸው ለይተው

ለማውጣት የሚያደርጉት ሙከራ አይሳካም፡፡ ከመካከላቸው ሌባው የትኛው እንደሆነ ለይተው ማወቅ አቅቷቸው ግራ ተጋብተው ብዙ ጊዜ ይኖሩ ነበር፡፡

አንድ ቀን ሌባው እንደ ልማዱ ከመንደረተኛው መሃል ያንዱን ንብረት ሰርቆ ወሰደ ፡፡ ይህ የተሰረቀበት ሰው ግን እንደሌሎች ዝም ብሎ አላለፈውም፡፡ መንደርተኛውን በሙሉ ጠርቶ አውጫጪኝ እንዲቀመጡ አስደረገ፡፡ ከመካከላቸውም አዛውንቶች የጠፋባቸውን ንብረት እንዲያጠያይቁለት ተመረጡ፡፡ የሰውየውን ንብረት ማን እንደወሰደ ወይም ሌባውን ያውቁ እንደሆነ እንዲጠቁሙ ሁሉንም ሰው በየተራ ጠየቁ፡፡

ይሁን እንጂ እገሌ ነው የሚል አንድም ሰው አጡ፡፡ ድካማቸው ሁሉ ከንቱ ሆነባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውዬው በጣም ተናደድና ለህዝቡ «ንብረቴን የሰረቀብኝ ሰው እዚሁ ካገኘሁት እንድገድለው ፍቀዱልኝ » ሲል ጠየቀ፡፡ እነርሱም «እኛ የተቻለንን ደክመን ልናገኝ አልቻልንም፡፡ ነገር ግን ሌባው እዚሁ መካከላችን ካለ እንድትገድለው ፈቅደናል ግን እንዴት ታውቀዋለህ» ብለው ቢጠይቁት «እኔ ጦሬን ይገፍ ወደርሱ ስንደረደር የሚደነግጠው ሰው ነው ሌባው፡፡» አላቸው እነርሱም ተስማሙና ባንድነት ቃላቸውን ሰጡት፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውዬው ጦሩን አስተካክሎ በቀኝ እጁ ያዘና «እዚህ መካከላችን ንብረቴን የሰረቀ እኔ የምጠረጥረው ሰው አለ፡፡ ንብረቴን በሰላም ካልመለሰልኝ በዚህ ጦር ሕይወቱ ታልፋለች፡፡» ብሎ ሲያበቃ ጦሩን እየሰበቀ ወደኋላው እያፈገፈገና እየተንጎራደደ ይፎክር ገባ፡፡ በመቀጠልም ጦሩን እየሰበቀ ዓይኑን እያጉረጠረጠ ወደ ሰዎቹ እየተንደረደረ ሲመጣ ይህን የተመለከተ አንድ ሌባ አውቆብኝ ሊገድለኝ ነው ብሎ ከህዝቡ መካከል ፈትለክ ብሎ ሩጫውን ቀጠለ፡፡ ባለ ንብረቱ ተከታትሎ ሊወጋው ሲል ሽማግሌዎቹ አባረህ ያዘው እንጂ አትግደለው አሉት፡፡ እሱም ሌባውን ይዞ ከፊታቸው ለፍርድ አቀረበው፡፡ የወሰዳቸውን ንብረቶች አንድም ሳያስቀር በሙሉ እንዲመልስ አደረጉ በዘዴ የተያዘውን ሌባ ሰርቶ እንዲበላ መክረውና ቃል አስገብተው ለቀቁት ይባላል፡፡

**X9. የሴቶች የመሪነት ስልጣን ማጣት**

ዱሮ ዱሮ ሴቶች የመሪነት ስልጣን እንዲሰጣቸው ወንዶችን ጠይቀው ነበር ይባላል፡፡ ወንዶችም «ለዚህ ጥያቄአችሁ ምላሽ የምንሰጣችሁ መክረን ነው፡፡» ይሉና ሶንጎ ተቀመጡ፡፡ ከምክክሩም በኋላ እንግዲህ እኛን በትክክል የምታስተዳድሩን ከሆነ ያለምንም ማንገራገር የመሪነቱ ስልጣን ለቀንላችኋል በሉ ስራችሁን ጀምሩ አሉና ለቀቁላቸው፡፡ ገና በመጀመሪያው ቀን ከብቶቻቸውን ነድተው ጓዛቸውን ጭነው ወደ ሌላ አካባቢ መኖሪያቸውን መቀየር እንዳለባቸው ሴቶች መከሩና

ወንዶች ሁሉ ለሥራ እንዲዘጋጁ አዘዙ። ወንዶች ተዘጋጅተው እየተጠባበቁ እያሉ፣ የመጀመሪያዋ ሴት ተነሳችና «በሉ እንግዲህ የመሄጃ ጊዜ ደርሷልና ጓዙንም ከብቱንም ሰብስቡና እየነዳችሁ እንሂድ» ስትል ትዕዛዝ ሰጠች። ወንዶችም ትዕዛዙን ተቀብለው መንገድ ሲጀምሩ ሲዘጋጁ ሁለተኛዋ ሴት መጥታ «ጎበዝ አሁን ራሴን ቅቤ ስለተቀባሁ በዚህ ጠራራ ፀሐይ መሄድ አንችልም ወደማታ ጥላ ሲበርድ ጉዞ እንጀምራለን» ስትል ሌላ ትዕዛዝ አስተላለፈች ይሁን ብለው ጉዞው ቆመ። ወደ ማታ አካባቢ ደግሞ ሌላዋ ተነሳችና «አሁን ጊዜው እየመሸ ስለሆነ እግራችንን ለእሾህና ለዕንቅፋት ሲሳይ ማድረግ ስለሚሆን ከመሸ ጉዞ አይደረግም» አለችና ጉዞውም በዚህ ሁኔታ ሁሉም ሳይሳካ ቀረ። ወንዶች ይህን ያልተቀናጀ የሴቶች አመራር በጥሞና ከተከታተሉ በኋላ «ሌላም ከዚህ የበለጠ ጉዳይ ቢከሰት በእነርሱ ፋክክርና ችላ ባይነት ኅብረተ-ሰባችን ችግር ላይ ሊወድቅ ይችላል» ብለው ቀድሞ የሰጧቸውን የመሪነት ሥልጣን መልሰው ወሰዱባቸው። ሴቶች የመሪነትን ሥልጣን ያጡት በገዛ ራሳቸው ድክመት እንጂ ፣ በወንዶች ጭቆና ብቻ አይደለም እየተባለ ይነገራል።

**X10. ሌባና ዳኛ**

በድሮ ዘመን በአንድ መንደር ውስጥ ብቻውን የሚኖር አንድ ሰው ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ሌባ መጥቶ ንብረቱን ሰርቆበት ሄደ። ስለጠፋው ንብረቱ ሊያመለክት በመንደሩ ወዳለው አንድ ዳኛ ዘንድ ሄዶ የሆነውን ነገር ሁሉ ተናገረ። ዳኛውም «ለመሆኑ ማን እንደሰረቀብህ ታውቀዋለህ?» ሲል ሰውዬውን ጠየቀው። እሱም «ኧረ ጌታዬ ማን እንደሰረቀኝ ባለማወቄ መጣሁ እንጂ ባውቅማ ኖሮ እዚህ ምን ያመጣኝ ነበር?» ሲል መለሰ።

ከዚህ በኋላ ዳኛው በመንደሩ ነዋሪ የሆኑትን ሁሉ እንዲሰበስቡ ጥሪ አስተላለፈ። የመንደሩም ነዋሪዎች አንድም ሳይቀሩ ተሰበሰቡ። ዳኛው ለእያንዳንዱ የመንደር ነዋሪ ርዝመቱ እኩል የሆነ በትር ከሰጣቸው በኋላ እንዲህ ብሎ ተናገረ። «እንግዲህ በዚህ መንደራችን ነዋሪ ከሆነ አንድ ግለሰብ ንብረት ተዘርፏልና ከመካከላችን ሌባውን ማውጣት አለብን። ዛሬ ለእያንዳንዱ ሰው አንዳንድ ብትር ይሰጣል። ላስገነዝባችሁ የምፈልገው ነገር ቢኖር ዛሬ የተሰጣችሁን ብትር ነገ ጠዋት ሁላችሁም ይዛችሁ ትመጣላችሁ። ስትመጡ ሌባ የሆነው ሰው በትር ዛሬ ማታ በአንድ ክንድ አድጎ ያድራል። ስለዚህ ሌባውን በቀላሉ እንለየዋለን።» ብሎ የመንደሩን ነዋሪዎች አሰናበታቸው።

ADDIS ABABA UNIV. ILS LIBRARY

ሌባው ግን ዳኛው ያለው ነገር ምናልባት እውነት ቢሆን ብሎ በመጠራጠር ወደ ቤቱ እንደተመለሰ ከብትሩ አንድ ክንድ ያህል ቆረጠ አሳጠረው:: በነጋታው ሁሉም ሲመጡ የሌባው ብትር ብቻ አንድ ክንድ አጥሮ ተገኘ:: ሌሎቹ ግን የተሰጣቸውን እንደተሰጣቸው በትክክል አስረከቡ:: በዚህ ዘዴ ሌባውን በቀላሉ በቁጥጥር ስር ማዋል ተቻለ ይባላል::

**X11. ሰውና ነብር**

በአንድ አካባቢ በእርሻ ሥራ የሚተዳደር አንድ ገበሬ ነበር:: ይህ ሰው ከእርሻ ሌላ ከብትም ያረባል:: አንድ ቀን ነብር ከጫካ ወጥቶ ከሰውዬው ፍየሎች መካከል አንዷን ሲበላ እረኛው የእርዳታ ጩኸቱን ያሰማል:: በዚህ ጊዜ ያካባቢው ነዋሪዎች ዱላ እና ጦር ይዘው በመውጣት ነብሩን ለመግደል ያባርሩታል:: እርሱም እግሬ አውጭኝ አለና ሲሮጥ አንድ ገብስ የሚወቃ ገበሬ ዘንድ ደረሰ:: ገበሬውም ነብሩን ምነው ምን ሆነሃል ? ምን ልርዳህ? ብሎ ጠየቀው:: ልቡ በሲቃ የሚመታው ነብርም «እባክህ ወንድሜ የዛሬን አድነኝ:: ርቦኝ አንድ ፍየል ብበላ ያካባቢው ሰዎች ተሰብስበው ዱላና ጦር ይዘው ሊገድሉኝ እየተከታተሉኝ ነውና እባክህ ህይወቴን አትርፍልኝ::» አለው::

«እንግዲያውስ እዚህ ስልቻ ውስጥ ግባና ተደበቅ እኔም ከጠየቁኝ አላየሁም ብዬ እመልሳቸዋለሁ::» አለውና ስልቻ ውስጥ ገብቶ ደበቀው:: ሰዎቹም እየተሯሯጡ መጥተው ገበሬውን «ፍየላችንን የበላ አንድ ነብር በዚህ አልፎ እንደሆነ ንገረን::» ብለው ጠየቁት እርሱም «አላየሁም» ሲል መለሰላቸው እነርሱም “በሌላ አቅጣጫ ሄዶ አምልጦናል” ብለው ወደ መጡበት ተመለሱ::

ገበሬውም ሰዎቹ በጣም ርቀው መሄዳቸውን ካረጋገጠ በኋላ ስልቻውን ፈትቶ ነብሩን ለቀቀው:: ነገር ግን ነብሩ «ከእንግዲህ ጊዜው መሽቷል፤ ምግብ ማግኘት አልችልምና አንተኑ መብላት አለብኝ::» አለው:: ሰውዬውም ደነገጠና «ህይወትህን ባተረፍኩ እንዴት ካልበላሁህ ትለኛለህ?» ብሎ ቢጠይቀው ነብሩ አሻፈረኝ ብሎ ክርክር ገጠሙ::

በመጨረሻ ጉዳዩን ወደ ዳኛ ለማቅረብ ተስማሙና አራዊት በሙሉ ተሰበሰቡ:: ከመካከላቸው ዝንጀሮ ሚዳቋ እና ጦጣ ለዳኝነት ተመረጡና ጉዳዩን ማየት ጀመሩ::

በመጀመሪያ ዝንጀሮ ቀረበና «ይኸማ ክምር እንዳልዘረጥጥ በውሾች የሚያስባርረኝ ምቀኛ ስለሆነ ሊበላ ይገባል::» ሲል ፍርዱን ሰጠ:: ሚዳቋም በበኩሏ «ሰው የሚባለው ተንኮለኛ ፍጡር እኔን

በወጥመድ እየያዘ ዘሬን ለማጥፋት ሁልጊዜ ሳይታክት የሚሰራ ክፉ ስለሆነ እንዲበላ ፈርጀበታለሁ፡፡» ስትል ፍርዷን አሰማች፡፡

በመጨረሻም ተራው የጦጣ ሆነና ፍርድ ለመስጠት ተዘጋጀች፡፡ «እኔ ፍርድ የምሰጠው ተደላድዬ ዛፍ ላይ ተቀምጬ እንጂ እዚህ መሬት ሆኜ አይደለም፡፡» ስትል ሀሳብ ተናገረች፡፡ ሁሉም ይሁን ብለው ተስማሙና ጦጣ ዛፍ ላይ ወጥታ ተቀመጠች፡፡ ቀጥላም «ፍርድ ከመስጠቴ በፊት ድርጊቱን አንድ ባንድ ማየት ስለምፈልግ ከሳሽና ተከሳሽ ይህን ለማድረግ ይስማሙ እንደሆነ ጠየቀች» እነርሱም ተስማሙ፡፡

በመጀመሪያ ነብር ክሱን እንዲህ ሲል አቀረበ «ይህ ሰው ሊገድሉኝ ከሚያሳድዱኝ ሰዎች ህይወቴን አድንልኝ ብለው ስልቻው ውስጥ አስገብቶ ጦሜን አዋለኝ» ሲል ክሱን አሰማ፡፡ ቀጥሎ ተራው የተከሳሽ ነበርና «እስቲ እንዴት አድርገህ እንዳዳንከው አሳየኝ» ስትል ጦጣ ጠየቀች እሱም «አያ ነብሮን እዚህ ስልቻ ውስጥ አስገብቼና የስልቻውን አፍ አስሬ ነው» በማለት መልስ ሲሰጥ ወዲያው ቀጠል አድርጋ፣ «እስቲ አያ ነብሮ ስልቻ ውስጥ ግባና ልይ» አለችውና ገባ፡፡ «እስቲ አንተ ደግሞ አፉን እንዴት እንዳሰርክ አሳየኝ» ስትል ገበሬውን ጠየቀችው እርሱም ግጥም አድርጎ የስልቻውን አፍ አስሮ «እንዲህ ነው» ሲል አሳያት፡፡

እርሷም በመቀጠል
«እንግዲህ ገበሬ ምኑን ልንገርህ
ጠላትህ ከእግርህ ስር በትሩም በእጅህ» አለችና ወደዛፉ አናት ላይ ርቃ ወጣች፡፡ ምስጢሩ የገባው ገበሬም ነብሩን በያዘው ዱላ ቀጥቅጦ ገደለው ይባላል፡፡

**X12. የእንስሳት ኑዛዜ**

አንድ ጊዜ በምድር ላይ የሚገኙ እንስሳት በሙሉ ባንድነት ተሰብስበው ተመካከሩና የሚበላ ምግብ ፍለጋ ተሰማሩ፡፡ በሄዱበት ቦታ ሁሉ ግን ምንም የሚበላ ነገር ሊያገኙ አልቻሉም፡፡

ታዲያ አንድ ቀን ከመካከላቸው አንዱ ተነሳና «እኛ በነዚህ ሁሉ ቀናት ባደረግነው የምግብ ፍለጋ ዘመቻ እስከዛሬ ምንም ያገኘነው የለም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ከመካከላችን ኃጢያት የሰራ ቢኖር ነው እንጂ ከቶ ምን ሊሆን ይችላል?» ሲል ጠየቀና ካሁን ጀምሮ እያንዳንዳችን ከዚህ በፊት ስለሰራናቸው ነገሮች በግልፅ መናዘዝ አለብን ሲል ሀሳብ አቀረበ፡፡ ሌሎችም በተሰጠው



ADDIS ABABA UNIV. ILS LIBRARY

አስተያየት ላይ በሙሉ ድምጽ ተስማሙ ። እያንዳንዳቸው ስለፈፀሟቸው ተግባራት አንድ በአንድ መናዘዝ ጀመሩ::

በቅድሚያ አንበሳ የሰራውን እንዲህ ሲል ተናዘዘ:: «አንድ ቀን አጥር ዘላ የወጣች አንዲት ጊደር አግኝቼ በልቼኣለሁ:: ይህ ኃጢያት ከሆነ ፍረዱኝ» ብሎ ተቀመጠ::

ቀጥሎ አያ ጅቦ ተነስቶ ቆመና እንዲህ አለ:: አንድ ቀን ጭነቱ ያልተራገፈለት አንድ ፈረስ አግኝቼ በልቼዋለሁ::» ይህ ኃጢያት ከሆነ ፍረዱብኝ አለ::

ነብርም ተነሳና «አንዲት ቁብ ፍየል ከእረኛዋ አምልጣ ቅጠል ስትለቃቅም አግኝቼ በልቻታለሁ:: ይህ ኃጢያት እንደሆን የምትሉኝን ልቀጣ ዝግጁ ነኝ» ብሎ ተቀመጠ::

የቀሩት እንስሳት በየተራ እየተነሱ የሰሩትን ኃጢያት እየተናዘዙ ተቀመጡ:: የአህያ ተራ ደረሰና ተነስታ እንዲህ አለች::

«አንድ ቀን ጌታዬ ከባድ ጭነት ጭኖብኝ ስሄድ በመንገድ ላይ ከሚያውቀው ሰው ጋር በድንገት ይገናኝና ሠላምታ ከተለዋወጠ በኋላ እየተጨዋወቱ ጥቂት ቆየ:: በዚህ መካከል እኔ ስለራበኝ ትንሽ ወደፊት እልፍ ብዬ ከመንገድ ዳር ሳር ነጭቼ፣ በልቼኣለሁ። ይህ ኃጢያት ከሆነ ፍረዱብኝ» አለችና ተቀመጠች::

ኑዛዜው ካበቃ በኂላ ሽማግሌዎቹ ርስ በርስ ተመካከሩና ፍርዳቸውን ማሰማት ጀመሩ «አንበሳን ብንመለከት ጊደሯ አጥር ዘላ የወጣች ስለሆነ ጥፋተኛ ነች:: ፈረስን የወሰድን እንደሆነ ከባድ ጭነት ጭኖ ፈረሱን ያደከመው ሰው እንጂ ጅብ አይደለም:: ነብርም ቢሆን ከእረኛዋ ጠፍታ የሄደችው ፍየሏ እንጂ እርሱ አይደለም:: ነገር ግን እስካሁን ከቀረቡት ሁሉ ለየት ያለ ሆኖ ያገኘነው ያህያን ጀብዱ ስለሆነ በጥንቃቄ ሊመረመር የሚገባው ጉዳይ ነው» ሲሉ ተናገሩ:: ከብዙ ውይይት በኂላ ያህያ ድፍረት ከሁሉም በላይ ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ፍርድ ተላለፈባት::

«አህዩት ጌታዋን ቆማ መጠበቅ ሲገባት በራሷ ፈቃድ ሳር ነጭታ መብላቷ ከሁሉም እጅግ የከፋ ኃጢያት ነው። ስለዚህ የሞት ቅጣት ይገባታል:: ፍርዱም ያለይግባኝ እንዲፈፀም ወስነናል::» ሲሉ አሰሙ::

በቦታው ተገኝተው የፍርድ ውሳኔውን ይጠባበቁ የነበሩ ሁሉ ይህን ውሳኔ እንደሰሙ ወዲያውኑ አህይትን ተቀራመቷት ይባላል::

X13 **የዝንጀሮና ጅብ ውርርድ**

በዱሮ ጊዜ ዝንጀሮና ጅብ ስለ ቁንጅና አንስተው ሲወያዩ፣ «እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ» ተባብለው ይወራረዳሉ:: ዳኝነት የሚሰጣቸው «ሰው» እንዲሆን ተስማሙና ያካባቢያቸውን አንድ ገበሬ አግኝተው አንተ "ዳኝነት ስጠን" አሉት:: እርሱም እኔ በምሰጣችሁ ፍርድ የምትስማሙ ከሆነ እሺ ይላቸውና ተስማምተው ይለያያሉ:: ትንሽ ቆየት ብሎ ጅብ ወደ ገበሬው ይሄድና እኔን ቆንጆ ነህ ብለህ ባትፈርድልኝ ጥጆችህን እበላብሃለሁ::» አለውና ሄደ:: ቀጥሎም ዝንጀሮ መጣና ለኔ ባትፈርድልኝ ሰብልህን በሙሉ አበላሸዋለሁ::» አለውና ተመልሶ ሄደ::

ገበሬውም የሁለቱንም ዛቻ በሚገባ ካጤነ በኋላ፣ ምን ማድረግ እንዳለበት እያሰለሰለ እስከ ቀጠሮው ጊዜ ቆየ:: ጅብና ዝንጀሮም ውሳኔያቸውን ለመስማት መጡ:: ገበሬው አንድ ባንድ ለብቻ ጠራቸውና እኔ የምሰጠው ትክክለኛ ፍርድ ነው:: አሸናፊው ወገን የሚለየው በቁንጥጫ ነው እንጂ በሌላ አይደለም::» ሲል ነገራቸው::

እሱ ፍርድ ሲሰጥ ተከራካሪዎች ጀርባቸውን ወደ እሱ መልሰው እንዲቆሙ በጋራ ተስማሙ አዘዛቸውና ተስማሙ:: ጊዜው ሲደርስ በታዘዙት መሠረት ፊታቸውን አዙረው ቆሙ :: ዳኛው በመሀላቸው ሆነና በሁለት እጆቹ ሁለቱንም ድብን አድርጎ ቆነጥጣቸው :: በዚህ ጊዜ « ያሸነፍኩት እኔ ነኝ ያሸነፍኩት እኔ ነኝ » እያሉ በየፊናቸው እየፈነጠዙ ሄዱ:: ገበሬውም ከብቱንና ሰብሉን በዘዴ አተረፈ ይባላል::

**X14. ያንድ ሀብታም ኑዛዜ**

በዱሮ ጊዜ አንድ ባለጸጋ ሰው በአንድ አገር ይኖር ነበር:: ይሁን እንጂ ይህ ሰው ሲሞት ሀብትና ንብረቱን የሚያወርሰው ምንም ልጅ አልነበረውም:: ልጅ ማግኘት የዘወትር ፀሎቱ ነበር፣ ሆኖም ምኞቱ ሲሳካለት ባለመቻሉ ሥራው ሁሉ እያገባ መፍታት ብቻ ሆኖ ቀረ::

ይሁን እንጂ እያገባ ከሚፈታቸው ሴቶች መካከል ከአንዷም እንኳን መውለድ ሳይችል እስከሽምግልና እድሜው ዘለቀ:: የኋላ ኋላ ግን በሽምግልና ዕድሜ ደረጃው ላይ እያለ አንዲት ልጃገረድ አግብቶ ጥቂት ጊዜያት አብረው እንደኖሩ በጠና ታመመ:: እርሱም የሰውነቱን ሁኔታ

ገምቶ በተኛበት ቦታ አዲሷን ሚስቱን ጠርቶ አጠገቡ ካስቀመጣት በኋላ እንዲህ አላት «ይኸውልሽ እኔ ህመሜ የበረታ ነው፤ የምድንም አይመስለኝም፤ አሁን አንቺ ፀንሰሻል፤ የምትወልጂውም ወንድ ልጅ ነው፤ እዚህ በግቢያችን ባለው ትልቅ ዛፍ ስር ብዙ ወርቅና ብር አኑሬአለሁ፤ የተፀነሰው ልጅ ተወልዶ ካደገ በኋላ፣ ይህን ምስጢር ንገሪው፤ ከዚያ በፊት አንቺም ሆንሽ ሌላ ሰው ይህን ነገር መንካት የለበትም::» ብሎ ያደራ ቃል ተናገረ::

ሰውዬው ይህን በነገራት በሶስተኛው ቀን ይሞታል:: እንደኑዛዜው ጥቂት ወራት ቆይታ ወንድ ልጅ ወለደች:: ልጁን በማሳደግ ሂደት ውስጥ እያለች በቸገራት ጊዜ የወርቅና የብሩ ጉዳይ ትዝ እያላት ለተወሰነ ጊዜያት ብትቆይም ግን ልጁ እስከሚያድግ ድረስ አላስቻላትም:: ልጁስ ለምን ይሰቃያል? አለችና ከውጭ ሰው ቀጥራ የዛን ትልቅ ዛፍ ስሩን ብታስቆፍር፣ ብታስቆፍር፣ የተባለውን ወርቅና ብር ልታገኝ አልቻለችም:: ስሩ ሳትቆርጥ በተከታታይ፣ በስፋትም፣ በጥልቀትም፣ አስቆፍራ ዛፉን ጭምር ብታስነቅለው እንኳን ለማግኘት ሳትችል ቀረች:: እሷም «ባሌ ዋሽቶኝ ነው እንጂ ማግኘት ነበረብኝ::» ትልና ተስፋ ቆርጣ አርፋ ልጇን ማሳደግ ቀጠለች::

ልጁ አባትየው በነገራት ዕድሜ ደረጃ ላይ በደረሰ ጊዜ ለማንኛውም ኑዛዜውን መንገር አለብኝ አለችና አንድ ቀን ይህንኑ ሚስጢር ለልጁ ትነግረዋለች:: ልጁም «እናቴ ሆይ አባቴ ይህን በነገረሽ ጊዜ የት ሆኖ ነበር?» ሲል ጠየቃት:: እርሷም አስታወሰችና «እዚህ ቦታ ላይ ነበር» ብላ ታሞ ተኝቶ የነበረበትን ሥፍራ አመለከተቺው:: ልጁም ያንን ቦታ ቆፈር ቆፈር ቢያደርገው በርካታ ወርቅና ብር ተገኘ:: እሷም ከቶ ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ደጋግማ ብታሰላስል ሚስጢሩን ማግኘት አልቻለችም:: ልጁ ግን «ይኸውልሽ እናቴ፣ አባቴ ሲናዘዝ ትልቁ ዛፍ ያለው ሌላ ሳይሆን ራሱን ነው:: ከስሩ ያለውም ታሞ ተኝቶበት የነበረበትን ቦታ ነው::» ብሎ ተናገረ:: ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ያገኙትን ወርቅና ብር እየተጠቀሙ በደስታ መኖር ጀመሩ ይባላል::

### X15. የሰውና የጅብ ጓደኝነት

በአንድ ሀገር ውስጥ አንድ ልጅ ብቻ የነበረው አንድ ሰው ነበር:: ይህ ሰው ሀብቱ የበዛ ስለነበር ብዙ ልጆች የመውለድ ምኞት ቢኖረውም ሊሳካለት ባለመቻሉ በአንድ ወንድ ልጅ ብቻ በመቅረቱ ሁሌ ያዝን ነበር::

ለልጁ ወንድም ፈልጎ ለማግኘት ባለመቻሉ ከእንስሳት መካከል አንድ የጅብ ልጅ አገኘና ከልጁ ጋር እንዲያድግ ወደ ቤቱ ወሰደው:: እዚያም በጥሩ እንክብካቤ ተይዞ ከልጁ ጋር አብረው መኖር



ADDIS ABABA UNIV ILS LIBRARY

ጀመረ፡፡ ዕድሜው ከፍ እያለ በመጣ ቁጥር አንዳንድ የባህርይ ለውጦች እየታየበት ቢመጣም አሳዳጊው ምንም አላለውም፡፡

በመጀመሪያ ቀን ላሞች የታሰሩበትን ገመድ በሙሉ በልቶ አደረ፡፡ የቤቱ ባለቤትም «ጅብ ይህን ያደረገው ተርቦ ነው» በማለት ተጨማሪ ምግብ እንዲሰጠው አዘዘ፡፡

እንደገና፣ ለሁለተኛ ጊዜ በቆዳ የተለጎሙ የወተት ማለቢያዎች ኦኮሌ (Okkolie) (ጮጮ) በሙሉ እንክት አድርጎ በመብላቱ ማለቢያ ለጊዜው ቢታጣም አሁንም ባለቤትየው ምንም የወሰደው እርምጃ የለም፡፡ ነገር ግን ተጨማሪ ምግብ እንዲበላ አሁንም ተፈቀደለት፡፡

ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ለሦስተኛ ጊዜ አንዲት ጥጃ በላ፡፡ ባለቤትየው ብዙ ባይደሰትም ጅብን ላለማስከፋት አሁንም ምንም የወሰደው ርምጃ የለም፡፡

«የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ» እንደሚባለው በጥፋት ላይ ጥፋት እየጨመረ መሄዱ የተወደደለት የመሰለው ጅብ አንድ ቀን እንደልማዱ ያን እንደ አይኑ ብሌን የሚሳሳለትን የሰውዬውን ልጅና ጓደኛውን በተኛበት በልቶት አደረ፡፡ በዚህን ጊዜ ሰውዬው እንደ እብደት አደረገው፡፡ ጦሩን ይዞ ጎራዴውን መዝዞ ጅቡን ለመግደል ያሳድደው ገባ፡፡ ጅቡም ጉልበቱን ተማምኖ ከመሞት ማምለጥ ይሻላልና ሽሽቱን ተያያዘው፡፡ ሰውዬው ሲያባርር ጅቡ ሲሸሽ ከአባገዳ 'Abba Gada' ግቢ ደረሱና ጅቡ ዘሎ ከግቢ ውስጥ ገባ፡፡ በባህሉ መሠረት ማንም አስጥሉኝ እያለ አባገዳ ዘንድ የደረሰ አይነካም፡፡ ነገሩ ከተረጋጋ በኋላ ለሁለቱም በየተራ ጥያቄ ቀርቦላቸው አስረዱ፡፡

በመጀመሪያ ሰውዬው ሲገልጽ የነበረውን አንድ ልጁን ይህ ጅብ የበላበት መሆኑን አሳዝኖ ተናገረ፡፡

በመቀጠልም ጅብ «እርግጥ ነው ይህ ሰው እኔን ከልጁ እኩል በድሎት ያሳደገኝ መሆኑን አልክድም፡፡ መጀመሪያ ላሞች የታሰሩበትን ጠፍር በሙሉ በላሁ፡፡ ጌታዬም እርቦት ይሆናል ብሎ ምግብ ጨመረልኝ እንጂ ምንም አላለኝም ቀጥሎም የጮጮውን ጠፍር በላሁ ምንም አላለኝም፡፡ ቀጥሎም ከከብቶቹ መካከል አንድ ጥጃ በላሁ እነዚህን ሁሉ ሳደርግ ምንም አልተባልኩም፡፡



ADDIS ABABA UNIV. GS LIBRARY

ሁልጊዜ የማደርገው ሁሉ ለእኔ ትክክል ስለሚመስለኝ ልጁን የበላሁትም ከዚህ የተነሳ ነው፡፡ ነገር ግን አባትዬው በጣም ተናድዶ ይኸው ነገር በጦር ሊገድለኝ ሠሥቼ እዚህ መጣሁ » አለ፡፡

አባገዳም ግራና ቀኙን ካዳመጠ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጠ፡፡ "እርግጥ ነው የመጨረሻው የጅብ ድርጊት የሚያሳዝን ቢሆንም ነገሩ ከስረ-መሠረቱ የተበላሸ ነው፡፡ ጅብ በተደጋጋሚ ለፈፀማቸው ጥፋቶች፣ በአንዳቸውም ጊዜ ቢሆን ማድረግ ያቀበትንና የሌለበትን ነገሮች ተለይተው አልተነገሩትም ስለዚህ ጥፋቱ ያሳዳጊውም እንጂ የጅቡ ብቻ ሊሆን አይችልም ይ ነገር ሁለተኛ እዳይደገም» ብሎ አስጠነቀቃቸውና ይቅር አባብሎ ዳግም ላይፈላለጉ ታርቀው ተለያዩ፡፡ ጅብም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰውን ስለሚፈራ ቀን ቀን በዋሻው ውስጥ ተደብቆ መዋል ጀመረ ይባላል ፡፡

**X16. ድመትና ሰው**

በድሮ ጊዜ አንድ ሀብታም ሰው ታማኝ ሆኖ የሚሰራ የሰው አገልጋይ በማጣቱ የተነሳ ከእንስሳት መካከል ለቤት ውስጥ የመላላክ ሥራ ድመትን ለመቅጠር አሰበና ካንዲት ድመት ጋር ውል ገቡ፡፡ ድመት በቤት ውስጥ ማናቸውንም የመላላክ ተግባር በቅንነትና በታማኝነት ልታከናውን ከቤትም ውስጥ የምትፈልገውን ማንኛውንም ምግብ አሰሪዋ ሊሰጣት፣ እርሷ ግን በምንም ዓይነት ሌላ ላትፈልግ፣ አይጥም እንኳ ቢሆን በራሷ ፈቃድ አድና ላትይዝ፣ ግዴታ ገባች፡፡

ሰውዬው በስምምነቱ መሠረት ለድመት የሚያስፈልጋትን ወተት፣ ስጋ፣ ሌላም የምትፈልገውን ሁሉ እየሰጠ ሊያሰራት ይህንን ስምምነት ያፈረሰ/ያጓደለ ወገን ለዘላለም እንዲረገም ተስማሙ ፡፡ ድመት ከተቀጠረችበት ቀን ጀምሮ ስራዋን በትጋት ማከናወን ያዘች ፡፡ በዚህ ዓይነት ሲኖሩ ከዕለታት አንድ ቀን ሰውዬው የሚያከብራቸው እንግዶች ወደ ቤቱ ሊጠይቁት መጡ ፡፡ እርሱም ከሰው ይልቅ ድመት ታማኝ አገልጋይና ቃሏን አክባሪ እንደሆነች እየገለፀላቸው ሲጫወቱ እነሱም እየተገረሙ ቆዩ፡፡

በመሐሉ፣ የምሳ ሰዓት ደረሰና፡፡ ድመት ተፍ ተፍ እያለች ስትሰራ እንግዶቹ እየተመለከቱ እውነትም እንዴት ያለ ብልሃት ነው እየተባባሉ ይገረሙ ነበር፡፡ እንግዶቹ ምሳቸውን በልተው እንዳበቁ ቡና ተፈላላቸው፡፡ ድመትም የተቀዳውን ቡና ለእንግዶች በማደል ላይ እንዳለች አንዲት አይጥ ከየት መጣች ሳትባል በግድግዳው ላይ ሽረር ብላ ስታልፍ ቀና ብላ አየቻትና ወዲያው



ADDIS ABABA UNIV. ILS LIBRARY

የያዘችውን ስኒ ለቃ አይጧን ለመያዝ ወደ ግድግዳው ስትዘል አምልጣት ከጉድጓዷ ጥልቅ አለችባት፡፡

ሲነውም ተሰበረ፡፡ ቡናውም ፈሰሰ፡፡ ቀድሞ ለአሰሪዋ የገባችውን ቃል በመርሳቷ ደነገጠች፡፡ ባለቤቱም በሆነው ሁሉ በእንግዶች ፊት በጣም አፈረ፡፡ እነሱ ከሄዱ በኋላ ጠራትና «እኔን እንዳሳፈርሽኝ አንቺም ዕድሜ ልክሽን እፈሪ» ብሎ ረገማት፡፡ ድመት ቅልስልስና ዓይነ አፋር ሆና የቀረችው በዚህ ምክንያት ነው እየተባለ ይነገራል፡፡

**X17. ልጅነት በትዳር ዓለም**

ትዳር መስርተው የሚኖሩ ባልና ሚስት በአንድ ሀገር ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ እነዚህ ተጋቢዎች ዕድሜያቸው ለአካለ መጠን ይድረስ እንጂ ምንም የህይወት ልምድ የሌላቸው የትዳርን ምንነት የማያውቁ ነበሩ፡፡ በተለይ ደግሞ ልጅ እንዴት እንደሚያድግ ምንም ዕውቀት አልነበራቸውም፡፡

በዚህ ሁኔታ አብረው ሲኖሩ ልጅ ይወልዳሉ፡፡ ባካባቢያቸው ያሉ ሰዎች «እነዚህ ሁለቱም ራሳቸው ልጆች ልጅ መውለዳቸው እንዴት አድርገው ሊያሳድጉ ነው» እያሉ ይገረሙ ነበር፡፡ የወለደችውን አራስ ጎረቤቶች በባህላቸው መሰረት «(Yuuya) /እንኳን የልጅ ክብር አገኘሽ/» እያሉ ይመርቃሉ (እንኳን ማርያም ማረችሽ እንደማለት ነው፡፡) ጥቂት አጫውተዋት ለመሄድ ሲወጡ ደግሞ«ልጅሽ የከብት ጭራ ይያዝ፣ የከብት ጭራ ተከትሎ የሚያድግ ይሁን፡፡» እያሉ መሰናበት የተለመደ ነው፡፡ ይህንን ምርቃት የሰሙ ባልና ሚስት እጅግ ተደሰቱ፡፡ ለማንም ሳያማክሩ ለብቻቸው ሆነው «እንግዲህ ልጃችን አድጎልን የእገሌ አባት እንድንባል፣ የባለ ወተቷን ላም ጭራ አስይዘን እንልቀቀው፣ ይህን ባናደርግ ምርቃቱን እንዳልተቀበልን ተቆጥሮ ይሞትብናል፡፡» ብለው ተማከሩ፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ «ምርቃቱ እዲሰምር የልጃቸውን እጅና ላሚቷን ጭራ በገመድ አቆራኝተው ለቀቁት፡፡ ላሟ ጭራዋን ወዲያና ወዲህ ባወዘወዘች ቁጥር ህፃኑ ግራና ቀኝ ተላግቶ ሞተባቸው ፡፡ እነሱም በሆነው ሁሉ በጣም አዘኑ፡፡ ልምድ የህይወት መግሪያ/ ማስተካከያ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡

**X18.** ይቅር ባይነት

ባንድ ሀገር ውስጥ ሁለት ጓደኛሞች ክፉኛ በመጣላታቸው የተነሳ ለገላጋይም አስቸግረው ለየብቻ ይኖሩ ነበር፡፡ የእነዚህ ሰዎች ጠብ በጣም ስላስቸገረ ወደ ሶንጎ ይቀረብ ተባለና ቀረበ፡፡ ነገሩ ከዚህ ደረጃ ደርሶ ሲጠየቁ አንደኛው ተስማምቶ «እሺ እታረቃለሁ» አለ፡፡ ሁለተኛው ግን አሻፈረኝ እንዳለ ቆየ፡፡ በዚህ መካከል ለሰይጣን ስለት አድርጋ ልጅ የወለደች አንዲት ሴት ድንገት መጣችና «አባካችሁ ልጅ መውለድ አቅቶኝ ብቸገር ለሰይጣን ተሳልኩ፡፡ እንዳጋጣሚም ሰምሮልኝ ወለድኩ ታዲያ አሁን ይህን ልጅ ለማን ክርስትና ልስጥ ሁሉም ሰው ጉዳዩን ስለሚያውቅ እምቢ አለኝ» እያለች መፍትሔ እንዲሰጧት ትለምናቸው ጀመር፡፡

በዚህ መካከል ለእርቅ ሲለመን የነበረው ሰውዬ በእምቢታ አቋሙ ፀንቶ እርቁን ረግጦ ወጥቶ ይሄዳል፡፡ ለአስታራቂነት የተቀመጡት ሽማግሌዎች ሁኔታውን ተመካከሩና ሴትየዋን እንዲህ አሏት፡፡ «ይህን ያንቺን ልጅ ወስደሽ ለዚያ አሁን ከዚህ ወጥቶ ለሄደው ሰውዬ ስጪው ሲጠይቅሽም እነርሱ አዘውኝ ነው በይው፡፡» ብለው ወደርሱ ላኳት፡፡ እርሷም ፈጥና ሰውዬው የሄደበትን አቅጣጫ ተከትላ እደደረሰችበትና እንደተባለችው 'የእኔ ልጅ ክርስትና አባት አንተ ነህ' አለችው፡፡ እሱም ተመልሶ ወደ ሽማግሌዎቹ መጣና ለምን እንደሆነ ቢጠይቃቸው «በእኛ ባህል በተደጋጋሚ ሲለመን እርቅን እምቢ የሚል ሰይጣን ብቻ ስለሆነ ነው፡፡» አሉት፡፡ በዚህ ጊዜ ክፉኛ ይደነግጥና ይቅርታ ጠይቆ ከጓደኛው ጋር እርቁን ፈጽሞ ወደ ቤቱ በሰላም ተመለሰ ይባላል፡፡

**X19.** አመል ያፋታው ትዳር

ዘወትር በትዳራቸው ተደስተው የሚኖሩ ሁለት ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ እነዚህ ሰዎች በኑሮኣቸው ምንም ያልተጓደለባቸው ናቸው፡፡ እሷ በቤት ውስጥ በምታከናውናቸው ሥራዎች ሁሉ እርሱ ከአጠገቧ አይለይም፡፡ በስለው የሚቀርቡ ነገሮች ስታዘጋጅ፣ "ካላዘጋጀሁ" እንጀራም ስትጋግር፣ "ካልጋገርኩ"፣ ወጥ ስትሰራ "ማማሰያ ካልያዝኩ"፣ ስታቦካ "ዱቄት ካላቀረብኩ"፣ እያለ በእያንዳንዱ ስራዋ ውስጥ ጣልቃ መግባቱን ግን አጥብቃ ትጠላበት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ «ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም» እንደሚባለው የዚህ ሰው ድርጊት በባህሉ የማይወደድ ቁራንጆ (qurranjo) "ሴት አውል" እንደሚያሰኝ፣ ደጋግማ ብትነግረው "ተው" እያለች ብትመክረውም ምንም ሊያሻሽል አልቻለም፡፡ እሷ በምትሰራቸው ስራዎች ሁሉ ጥልቅ ስለሚልባት ብቻ ሳይሆን ባለመተዉ ትበሳጭ ነበር፡፡ አንድ ቀን በዚህ ዓመሉ የተነሳ ታኮርፍና ወደ ወላጆቿ ዘንድ ጥላው



ADDIS ABABA U... ILS LIBRARY

ሄደች። እርሱም በማግስቱ ተከትሏት አማቾቹ ቤት መጣ። እንደደረሰም ሚስቱ መኖሯን አረጋገጠ። ልጅቷ ወላጆችም አማታቸውን ወደ ቤት አስገቡት። ተረጋግተው ጥቂት ከቆዩ በኋላ ምንም እንዳላደረጋት ልቦናው ስለሚያውቅ «ኧረ ለመሆኑ አኩርፋ የመጣችበት ምክያንት ምን በደል ተፈጽሞባት ነው?» ሲል አባት ጥያቄ አቀረበ። እርሷም በወላጆቿ ስትጠየቅ «ባለቤቴ ሌላ ምንም በደል ያደረሰብኝ የለም። ነገር ግን፣ ሁልጊዜ በምሰራው የሴት ስራዎች ሁሉ ጣልቃ ስለሚገባ ያስጨንቀኛል፣ ሁኔታው በባህላችንም ቢሆን ቁራንጆ ስለሚያሰኝ፣ የእገሊት ባል እኮ «እንደዚህ ነው» እየተባለ ስም እንዲሰጠኝ አልፈልግም።» በማለት ተናገረች። ስባሏ አመል በአማቾቹ ፊት ሲነገር እጅግ አፈረ። ቀስ ብሎ ብድግ አለና ሾልኮ ከአካባቢው ጠፋ። ነገሩ ከአማቾቹ አልፎ በአካባቢው ህዝብ መዘባበቻ እንዳይሆን ስለሰጋ ዳግመኛ አልተመለሰም። ዓመል ያወጣል ከመሐል የሚባለውም ይህን መሳይ ሁኔታ የሚያስከት ነው።

X20 **ህብረት**

አሥር ልጆች የነበሯቸው አንድ ሽማግሌ ነበሩ። እሳቸውም ምንም የሚበሉትና የሚለብሱት ስለሌላቸው ልጆቻቸውን ሁሉ በየመንደሩ አስቀጥረው ይኖሩ ነበር። አንድ ቀን ሽማግሌው ታመው ሊሞቱ ሲሉ ልጆቼን ጥሩ ልናዘዝላቸው ብለው ሰው ይልካሉ። ልጆቹም መልዕክቱ ሲነገራቸው «አባታችን ምንም የሌለው ደሃ ነው ምን ይናዘዝልናል? እንዲያው ብቻ ሄደን ቀብረነው እንመለስ።» ብለው ይሄዳሉ። አባትየውም ሁሉም ልጆቻቸው እንደመጡ ካረጋገጡ በኋላ “ኑ! ወደ እኔ” አሏቸውና አንድነት ተሰብስበው ቀረቡ። «በሉ አሁን እያንዳንዳችሁ አንዳንድ ብትር አምጡ።» ብለው አዘዟቸው። ልጆቹም እንደታዘዙት አንዳንድ ብትር ፈልገው ይዘው መጡ። እያንዳንዱ የያዙትን ብትር ሁለት ሁለት ቦታ እንዲሰብሩ ነገሯቸውና እንደታዘዙት አደረጉ። ሽማግሌው “አሁንም አንዳንድ በትር ፈልጋችሁ አምጡ” አሏቸውና አመጡ። “ለሁለተኛ ጊዜ ስበሩ” አሏቸውና ሰበሩ። “የተሰበሩትን በሙሉ አንድ ላይ ሰብስቡና እሰሩ” አሏቸው እነሱም አንድ ላይ ሰብስበው አሰሩ። ከዚያ በኋላ ከታላቁ ልጅ ጀምረው ተራ በተራ ይህን እስር እንደገና እንዲሰብሩ አዘዙ። ሁሉም ቢሞክሩ አቃታቸው። ሽማግሌውም በዚህ ጊዜ «ልጆቼ አሁን እንግዲህ እያንዳንዳችሁ ለየብቻችሁ የሆናችሁ እንደሆነ እንደመጀመሪያዎቹ አንዳንድ ብትሮች በቀላሉ ትጠቃላችሁ አንድነትና ህብረት ካላችሁ ግን እንደዚህ ስብስብ ማንም አይነካችሁም ስለዚህ አንድነትና ህብረት ምንጊዜም ከመካከላችሁ እንዳይጠፋ ብለው መርቀዋቸው ሞቱ ይባላል።

X21. የአባት ምርቃት

ሁለት ወንዶች ልጆች ብቻ የነበሩት አንድ ሰው በአንድ አገር ይኖር ነበር። ከነዚህ ልጆች መካከል ታላቅየው ያባቱን ትዕዛዝ የሚያከብር አልነበረም። ከብቶችንአያሰማራም፣ አይጠብቅም። ስራ አይሰራም። እንዲያውም ይባስ ብሎአንድ ቀን ከቤቱ ጠፍቶ ወደ አንድ ሩቅ አገር ሄዶ ለብቻው መኖር ጀመረ። ታናሽዬው ልጅ ግ አባቱን በሁሉም ነገር ያገለግለዋል። ከብቶቹን ያሰማራል፣ ማንኛውንም የጉልበት ስራ ይሰራል፣ ሁሉንም የቤት ውስጥ ሆነ የውጭውን ስራ ሁሉ ይሰራል። በዚህ ሁኔታ ሲኖሩ ቆይተው አባትየው ዕድሜው ገፍቶ/አርጅቶ ሲሞት በተቃረበ ጊዜ ለታናሽ ልጁ። «ያለኝን ሀብት በሙሉ ላንተ ብቻ አውርሼሃለሁና ተጠቀምበት።» በማለት ተናዘዘለት ታናሹ ልጅ ግን መልሶ "አባቴ ሆይ ታላቅ ወንድሜ ያንተም የበኩር ልጅህ ነው። ምንም እንኳን ጉልበቱን ቢነፍግህና አልታዘዝም ቢልህ ለእርሱ የሚገባውን ድርሻ እባክህ አትከልክለው" ብሎ አጥብቆ ለመነው።

"አባትየውም ከእኔ ሀብት አንድም ነገር ለእርሱ አይገባውም" ሲል ተናገረ። ታናሹ ልጅ የለም አባቴ ለእኔ ሁሉንም ከምትሰጠኝ ለእርሱ እንደ ትልቅነቱ ከፍ ያለውን ለኔም እንደታናሽነቴ አነስተኛውን ድርሻዬን መርቀህ ስጠኝ።» ሲል ደጋግሞ ቢለምነውም አይሆንም ብሎ ታናሹን "በል እንዳልከው ይሁንልህ የሰጠሁህ በሙሉ በእጥፍ ይብዛልህ። የያዝከው ሁሉ ይለምልም። ምንግዜም ከእጅህ አትጣ። ታላቅ ወንድምህ ይታዘዝህ!" ብሎ መርቆት ሞተ።

ያባቱን ሞት ሲሰማ፣ ታላቁ ልጅ ከሄደበት አገር ተመልሶ መጣ። እንደደረሰም እርሙን አውጥቶ ድርሻው እንዲሰጠው ታናሽ ወንድሙን ጠየቀ። እርሱም ምንም ሳያስቀር በኑዛዜው መሰረት ድርሻውን ለታላቅየው ሰጠውና ይዞ ወደነበረበት ተመለሰ።

ሁለቱም በየፊናቸው ሲኖሩ የታናሽየው የራሱ  ሀብት እየበዛለት፣ ከብቶቹም እያደር በረት እየሞሉ ፣ እርሱም በህዝቡ ዘንድ ታዋቂነትንና ክብርን እያገኘ መጣ። ባንፃሩ የታላቅየው ሀብት እየቀነሰና እየጠፋ፣ ከብቶቹም እየተመናመኑ ሄዱና በመጨረሻእጅግ ደኸየ። በደረሰበት ሁኔታ እጅግ ቢያዝንም፣ በምቀኝነት መንፈስ ተነሳስቶ የገዛ ወንድሙን ገድሎ ንብረቱን ለመውሰድ አሰበ። የአባቱን ኑዛዜ ምን እንደሆነ ባለመስማቱ «ወንድሜ አስቀርቶብኝ ይሆን?» ብሎ ወደ ወንድሙ ሄዶ «ለመሆኑ አባታችን ሲሞት ምን ብሎ ተናዝዞ ነበር?» ብሎ ጠየቀው። እርሱም አባቱ እንቢ ብሎት የነበረውን ውርስ እንዴት አግባብቶ ማግኘት እንደቻለ ነገረው። ሆኖም ታላቅየው በታናሹ ንብረት በመቅናቱ  «የለም ይህን ለማረጋገጥ ሁለታችንም ለአደን እንሰማራና



ADDIS ABABA UNIV. IES LIBRARY

ማንኛችን በቅድሚያ እንደቀናን እውነቱን ማረጋገጥ ይቻላል» ሲል ታላቅየው ሀሳብ አቀረበ ታናሽየውም ባለመታመኑ እጅግ ቢያዝንም እውነቱን ህሊናው ስለሚያውቅ ተስማማ።

ከመሄዳቸው ጥቂት ቀደም ብሎ ታላቅየው ወደ ቤቱ ሄደና ረጅም ገመድ አዘጋጅቶ መጣ። ታናሹም የበኩሉን ዝግጅት አድርጎ ጊዜው ሲደርስ ሁለቱም ወደ አደናቸው ሄዱ። ብዙ ከተጓዙ በኋላ ካንድ ትልቅ ገደል ውስጥ ውሃ አገኙ። «እዚህ አረፍ ብለን ስንቃችንን በልተን የምንጠጣው ውሃ ያስፈልገናልና እኔ የገመዱን አንድ ጫፍ በወገቤ ላይ ጠምጥሜ ገደል ውስጥ ገብቼ ውሃውን ቀድቼ እስከምወጣ ድረስ አንተ የገመዱን ሌላ ጫፍ ይዘህ በመቆም ትጠባበቃለህ ከጉድጓድ ውስጥ መውጣት በምፈልግበት ጊዜም ገመዱን አጥብቀህ በመያዝ ትጎትተኛለህ። እኔ ደርሼ ከተመለስኩ በኋላ ደግሞ አንተ በተራህ ወርደህ ታመጣለህ» ሰል ታላቁ ተናገረ። ታናሹም «እሺ» ብሎ የተባለውን ይፈጽማል። ውሃውን አምጥቶ ስንቃቸውን ከበሉና ከጠጡ በኋላ፣ በል «ተራው ያንተ ነውና ለሌላ ጊዜ የሚሆነን ውሃ ከገደሉ ውስጥ ወርደህ አምጣ» ይለውና ወገቡን እርሱ እንዳደረገው አስሮለት ሌላውን ጫፍ ይዞ ይቆማል። ታናሽየው ገደሉ ውስጥ ገብቶ ውሃው ዘንድ መድረሱን ሲያረጋግጥ የሚያወጣው አጥቶ እዚያው እንዲቀር ገመዱን ወደ ውስጥ ለቅቆ እርሱ ወደ ቤት ተመለሰ። እንደደረሰም «ታናሽ ወንድሜን ጫካ ውስጥ ዝሆን ገደለብኝ» ሲል በአካባቢው በሙሉ አስወራ።

ሆኖም ታናሽዬው በአባቱ የተመረቀ ስለነበር ሌሎች ሰዎች ውሃ ሊቀዱ ሲመጡ ድንገት አይተውት ባደረጉለት ዕርዳታ ሳይሞት ከነህይወቱ ከገደሉ ውስጥ ወጣ። ሰዎች ይህን ደባ ያደረገው ማን እንደሆነ ሲጠይቁትም ታላቅ ወንድሙ እንደሆነ ተናገረ። አብረውት እቤቱ ድረስ ወሰዱትና «ይህ ሰው ከሙታን መንደር የተመለሰ በመሆኑ የፈጣሪ ታላቅ ምህረት የተገለፀበት ነው» ብለው ወደ መጡበት ተመልሰው ሄዱ። ታላቅ ወንድሙም ይህን ተዓምር ባየ ጊዜ እጅግ ፈራ። በድርጊቱም ከማፈሩ የተነሳ ከአካባቢው ተሰድዶ በሄደበት አገር በችግር ማቅቆ ሞተ ይባላል። ቅንነትም ለራስ ክፋትም ለራስ ነው የሚለው የጌዴኦ ምሳሌያዊ አነጋገር የሚያመለክተው ይህንን ነው።

**X22. ያልጠረጠረ ተመነጠረ**

ትዳር መስርተው በፍቅር ይኖሩ የነበሩ ሁለት ባልና ሚስት በአንድ አገር ይኖር ነበር። በቤታቸው ውስጥ የበቃ ንብረት ባይኖርም ትልቁ ነገር "ፍቅር" ነበራቸው። ይሁን እንጂ ሰው ሆኖ ያለአንዳች ባህርይ አይፈጠርምና ሴትዬዋ ሲበዛ ዝንጉ ነበረች። ውሎ አድሮ ይህ ጉዳይ ችግር እያስከተለ ሄዶ ለጠብና ጭቅጭቅ መንስኤ ሆነ። ባልዬው በሚስቱ ቀልብ ማጣት ተቸግሮ

«እንዲያው ባለቤቴን ልብ የሚሰጣት ማነው?» እያለ ሰዎችን ሲያማክር አንድ ብልህ ሰምቶ ኖሮ «ልብ እኮ ይሸጣል አሁን ወደ ቤት ስትመለስ ሄዳ ፈልጋ እንድትገዛ ንገራት።» ሲል መከረው። እርሱም እንደተባለው ሄዶ በነገራት ጊዜ ደስ ብሏት አንድ ቀን ቢያጋጥማት እንደምትገዛ በልቧ ወሰነች። አንድ ቀን ያ ብልህ ሰውዬ ሚስቲሩን ስለሚያውቅ «ልብ የሚገዛ» እያለ በእነሱ አጥር አካባቢ ሲያልፍ፣ ሰማችና «ፍለጋ ከምሄድ እዚሁ ድረስ መጣልኝ አይደለም» ትልና ዋጋ ትጠይቃለች። ሰውዬውም «ልብ በጣም ውድ ነገር እንደሆነና በገንዘብ ሳይሆን፣ አለ በምትለው የቤት ውስጥ ዕቃ ብቻ፣ የሚለውጣት መሆኑን ነገራት። እሷም እቤት ውስጥ ካሉ ዋጋ ሊያወጡ ከሚችሉ ንብረቶች መካከል በቅርብ የተገዛ አዲስ ብርድልብስ ብቻ እንዳለ ነገረችው። እርሱም በዚህ እንደሚለውጣት ይስማሙና ልብ የሚያስቀምጥበት አንድ አነስተኛ ቆሬ (ገበቴ) እንድታመጣ አደረገ። በመቀጠልም በቆሬው ውስጥ እስከ ግማሽ ድረስ ውሃ እንድትሞላ ይነግራታል። እርሷም የተባለችውን ሁሉ ታደርጋለች። «እርሱም በይ እንግዲህ ይህንን ነገር ጠዋት ጠዋት ስትነሺ፣ ውስጥ ውስጡን እያየሽ «ልብ ለኔ» «ልብ ለኔ» እያልሽ መልሰሽ በጥንቃቄ አስቀምጪው። ብሎ ነገራትና ብርድ ልብሱን ይዞ ሄደ። ባልየው ከሥራ ሲመጣ በሆነው ነገር በጣም ተናደደ። ፈረሱን ጭኖ አታላዩ ሰውዬ የሄደበትን አቅጣጫ ተከትሎ ፍለጋ ቀጠለ።

አታላዩም የሚመጣውን ሰው ከሩቅ መሆኑን ተገንዝቦ ብርድ ልብሱን ወደ ጫካ ሸሽጎ ጠበቀው። እንደደረሰም ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ፈላጊው ሁኔታውን ገልጾለትና ምናልባት በዚህ በኩል አልፎ እንደሆን ጠየቀው አታላዩም አቅጣጫ ቀይሮ ወደ ገደላማ ስፍራ ሄዷል ነገረው። ሰውዬው ፈረሱን ለአታላዩ ሰጥቶ ገደሉን ቁልቁል ወርዶ ቢፈልግ አጣው። ፈረሱን ትቶለት ወደሄደበት ሰው ሲመለስ እሱንም አጣው። ከሚስቱ ይበልጥ የእርሱ የባሰ ሆነ። ፈረሱን ጭምር አስረክቦ ንዴቱንና ብስጭቱን ዋጥ አድርጎ እያዘነ ወደ ቤቱ ተመለሰ ይባላል። ምስጢርን ባለቤቱ ለራሱ ጠብቆ መያዝ ሲገባ ለዚህም ለዚያም ማባከን አስፈላጊ አለመሆኑን ተረኩ ያስተምራል።

### X23. የቅል ልጆች

ሁለት ሚስቶች አግብቶ የሚኖር አንድ ሰው ነበረ። ይህ ሰው የሚተዳደረው በግብርና ሙያ ነው። የመጀመሪያ ሚስቱ እርጉዝ እያለች ሰውዬው ድንገት ይታዘዝና ወደ ዘመቻ ይሄዳል። የመውለጃዋ ጊዜ በደረሰ ጊዜም መንታ ወንዶች ልጆች ወለደች። ሁለተኛዋ ሚስት ደግሞ በዚህ ትቀናና ህጻናቱን ሰርቃ በአንድ ትልቅ ቅል ውስጥ ደብቃ አፉን ውሃ እንዳያስገባ አድርጋ ዘግታ



ADDIS ABABA UNIV. IES LIBRARY

ወንዝ ውስጥ ትጥላቸዋለች። ቅሉን እያንሳፈፈ ወስዶ ራቅ ወዳለ አንድ ዳርቻ ላይ ውሃው ተፋው።

ውሃ ልትቀዳ የመጣች አንድ ሴት ቅሉን አውጥታ ስትከፍተው በውስጡ ሁለት የሚያማምሩ ወንዶች ልጆች ታገኝና ወደ ቤቷ ወስዳ ታሳድጋቸዋለች። ስማቸውንም «የቅል ልጆች» ብላ አወጣችላቸው። እነርሱም ከፍ እያሉ ሲሄዱ መጠሪያቸው ለየት ያለ በመሆኑ ይገረሙ ነበር። ሁኔታውን ለማወቅ ሁልጊዜ አሳዳጊያቸውን ይጠይቁ ነበር።

አባወራው ዘመቻ ቆይቶ በተመለሰ ጊዜ ያልወለደችው ሚስቱ በቀድሞው ድርጊቷ እንኳን ሳትፀፀት ተሽቀዳድማ «ሚስትህ የወለደቻቸውን ልጆች ገድላ በልታቸዋለች» ስትል ነገረችው። እሱም በጣም ተናደደ። ከከብቶቹ መካከል አንዱን በሬ አርዶ ቆዳውን ከገፈፈ በኋላ በርጥብ ቆዳ የልጆቹን እናት እግሮቿን ጠፍሮ አስሮ እቤት ውስጥ እንድትቀመጥ አደረገ። «የቅል ልጆች» እየተባሉ የሚጠሩት ሁለቱ መንትዮች የስማቸውን ሚስጥር ለማጣራት የአካባቢያቸውን ሰዎች መጠየቅ ጀመሩ። ሰዎቹም «በቅል ውስጥ ሆናችሁ ወንዝ ስለተጣላችሁ ነው እንደዚህ የተባላችሁት።» ይሏቸዋል። «እንግዲያውስ የዚህን ምስጢር መጨረሻ ማወቅ አለብን።» ብለው የወንዙን አቅጣጫ ተከትለው እየጠየቁ መጓዝ ጀመሩ። በአቅራቢያ የሚያገኙትን ሁሉ «ከመቼ ወዲህ ቅል አባት ሆነ?» እያሉ ሲጠይቁ «ከመቼ ወዲህ እናት ልጇቿን ገድላ ትበላለች?» የሚል ምላሽ ይሰጣቸው ነበር። «ይህን እንቆቅልሽ ፍቺውን ሳናገኝ አናቆምም።» ብለው እያጠያየቁ ጉዟቸውን ቀጠሉ። "ከመቼ ወዲህ ቅል አባት ይሆናል?" እያሉ እየጠየቁ ሲጓዙ በመጨረሻ የደረሱበት አካባቢ ያሉ ሰዎች ግን «ልጆቿን የበላች እናት እዚያ መንደር አለችላችሁ ሄዳችሁ ጠይቋት» ብለው ነገሯቸው።

እነርሱም «የእንቆቅልሹ መጨረሻ ሊሆን ይሆን?» ብለው ተገረሙና ፈጥነው ወደተባሉበት ሄዱ። እንደደረሱም በከብት ቆዳ ተጠፍራ የታሰረች ሴት አገኙ። ቀስ ብለው ቢጠይቋት የሆነውን ሁሉ አንድ ባንድ ነገረቻቸው። «ያልወለደች ሴት የኔን ልጆች ሰርቃ ወስዳ በቅል ውስጥ ከትታ ወንዝ ውስጥ ጣለቻቸው። ቀጥላም የወለድኳቸውን ልጆች መልሼ እንደበላኋቸው አድርጋ ከዘመቻ ሲመለስ ነገረችው፡ እርሱም በዚህ ጉዳይ ተናዶ ከዚያ ቀን ጀምሮ በከብት ቆዳ ጠፍሮ አስሮኝ ይኸው እስካሁን አለሁ።» በማለት ገለፀችላቸው።

ልጆቹም እናታቸው እርሷ መሆኗን በሆነውና በተናገረቸው እጅግ አዘኑ:: ከዚያም አንድ ትልቅ ጉድጓድ በሚስጢር ቆፍረው አዘጋጁና ሰወዬው በማይኖርበት ሰዓት ሄደው ያቺን ሴት አምጥተው ካንገቷ በታች ጉድጓዱ ውስጥ ቀበሯትና በጭንቅላቷ ላይ ከብት ነዱባትና ሞተች:: እናታቸውንም ከታሰረችበት ፈቷት:: የታሰረችበትን ጠባሳ በቅቤ እያሻሹ አድነዋት ሁሉም በሰላም አብረው ኖሩ ይባላል::

**X24. ወይኢ /woyyi/**

በዱሮ ጊዜ በአንድ ሀገር ውስጥ ህዝብን የሚያስተዳደር ወይኢ የሚባል አውሬ ነበር። ይህ አውሬ ከሚያስተዳድረው ህዝብ መካከል የሚበላው አንድ ሰው እየተመረጠ በየጊዜው ግብር ይደረግለታል:: በዚህ ዓይነት ያካባቢው ህዝብ ሰውን ከነነፍሱ ለ 'woyyi' በመገበር ረጅም ዓመታት ኖረ:: ግብሩን ያስተባብር የነበረው ቦራ በዕድሜው ገፋ ያለ የአካባቢው ሰው ነበር::

እያደር ግን ህዝቡ ሰውን ለእንስሳ ከነህይወቱ መገበር ትክክል እንዳልሆነ እየተገነዘበ መጥቶ ውስጥ ውስጡን ማጉረምረም ጀመረ:: «ካሁን ጀምሮ ሰውን የሚያህል ፍጡር ለአውሬ አንገብርም::» እያለ ህዝቡ አመፁን ቀጠለበት:: ይህንኑ የህዝብ ውሳኔ ለቦራ ነገሩት:: ውሳኔውን ቦራ ወስዶ ለወይኢ እንዲነግረው ነገር ግን እርሱ ተበሳጭቶ «ለምን ይሆናል? የሚል ከሆነ ከዋሻው ወጥቶ እኛን እንዲያነጋግር ይሁን» በማለት ቁርጡን አሳወቁት::

ቦራም የህዝቡን ውሳኔ ለወይኢ በነገረው ጊዜ ከመጠን በላይ ተቆጣ:: «ይኼ ከቶ ሊሆን አይችልም ሲል ጮኸ:: በል አሁኑኑ! እንደማልቀበለው ሄደህ ንገራቸው::» ሲል ድምጹን ከፍ አድርጎ ተናገረ:: ቦራም መልሶ ኸረ ጌታዬ! አንተ ራስህ ካልነገርካቸው በስተቀር እኔን አይቀበሉኝም የሚታዘዙልኝም አይመስለኝም:: እንዲያውም እዚሁ በቅርቡ ተሰብስበው ውሳኔውን እየተጠባበቁ ናቸው:: ስለዚህ አብረን ሄደን እንንግለጽላቸው የአመፁ መሪ ማን መሆኑን እግረመንገድህን ታውቀዋለህ ሲል አግባባው:: «ህዝቡ ከተሰበሰበስ እንግዲያው እሺ» አለና ለማነጋገር አብረው ከእርሱ ዋሻ ወጡ:: ህዝቡም ገና ሲያየው አስቀድሞ የመከረበትና የተስማማበት ጉዳይ ነበርና ከዋሻው ወጥቶ ወደ ህዝቡ መሃል ገና እንደገባላቸው ይዘዋቸው በወጡ ጦር፣ መጥረቢያ፣ ዱላ በመሳሰሉ መሣሪያዎች ጨፍጭፈው ገድለው ጣሉት:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አውሬ ተፈርቶ የሰዎች አስተዳዳሪ መሆኑ ቀርቶ ሰው ራሱን በራሱ ማስተዳደር ጀመረ ይባላል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

**X25.** ምስኪን ባልና ሚስት

በአንድ አገር ሁለት ምስኪን ባልና ሚስት ነበሩ:: በትዳር አብረው ሲኖሩ ምንም ልጅ አልወለዱም ። በየፊናቸው ጥረው ግረው ለጉሮሮሯቸው ከሚያውሉት በስተቀር፣ ተቀማጭ የሚሆን አንድ የክንድ አምባር (Nakelece) ብቻ እንጂ ሌላ ጥሪት የላቸውም:: ሆኖም ሀብት አይኑራቸው እንጂ በመካከላቸው ከፍተኛ መተሳሰብና ፍቅር አለ::

ሴትየዋ ተፈጥሮ ያደላት እዚህ ቀረሽ የማትባል ውብ ነበረች:: በተለይም ዞማ ፀጉሯ ከሽንጧ አልፎ ዳሌዋ ይደርስ ነበር። ሆኖም ችግረኞች ስለሆኑ ፀጉሯን በእንክብካቤ ለመያዝ የምታበጥርበት ሚዶ አልነበራትም:: መግዛት ባለመቻሏ በየጊዜው ትበሳጭ ነበር:: «አንድ ማበጠሪያ ቢኖረኝ ምንኛ በታደልኩ» እያለች ዘወትር ትመኛለች:: የሚስቱን ችግር የተገነዘበው ባል ችግሩን ለመፍታት ሲያሰላስል አንድ ዘዴ መጣለት ። ያለችውን አንድ የክንድ አምባር ገበያ ወስዶ በመሸጥ ለሚስቱ ማበጠሪያ መግዛት ፈለገ:: ሁኔታውን ለሚስቱ ሳያማክር በድብቅ ሄዶ ገዝቶ ድንገት ሊያስገርማት አሰበና አንድ ቀን አምባሩን ይዞ ወደ ገበያ ወስዶ ሸጠው:: ከዚያም ለሚስቱ ፀጉር ተስማሚ የሆነ ሚዶ ፈልጎ ገዛና ወደ ቤቱ ሲመለስ፣ እርሷ ሚዶ መቸገሯን የነገረቻት ጓደኛዋ በሰጠቻት ምክር ፀጉሯን ሙልጭ አድርጋ ተላጭታ ጠበቀችው:: የነበራቸው አንድ ቅርስ ተሸጦ ሚዶ ቢገዛም ለታለመለት ዓላማ ባለመዋሉ ሁለቱም ክፉኛ አዘኑ:: ምክር ከፀፀት ያድን የሚባለውም ከእንደዚህ ዓይነቱ ስህተት ለመዳን ስለሚያገለግል ነው::

ምክር

**X26.** ሞኝና ብልጥ ጓደኛሞች

ባንድ አገር ውስጥ አንድ ብልህና አንድ ሞኝ ጓዳኛሞች አብረው ይኖሩ ነበር:: አብዛኛውን ጊዜ ሥራቸውን የሚያከናውኑት ተመካክረው ነው:: እነዚህ ሁለት ጓደኛሞች በውጪ የግብርና ስራዎቻቸውን ሲያከናውኑ የሚስቶቻቸው በቤት ያለስራ መዋል ዘወትር ያናድዳቸው ነበር:: ስለዚህ እነርሱም ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ማድረግ እንዳለባቸው ተመካከሩ:: «ሚስቶቻችን እኛ ሰርተን ደክመን ለፍተን ያፈራነውን ገበያ እያወጡ ይሸጣሉ፣ የፈለጉትን ለዘመዶቻቸው ይሰጣሉ፣ ሌላውንም የፈለጉትን ነገር በመግዛት ያባክናሉ፣ ስለዚህ ለምን እንደኛ ወጥተው በስራ እንኳን አይረዱንም» ሲል ብልሁ ሰው ሀሳብ አቀረበ:: በዚህ ጊዜ ሞኙ «እምቢ ያሉን እንደሆን ምን ሌላ መንገድ ይኖረናል» ሲል ብልሁን ጓደኛ ጠየቀው:: እርሱም መልሶ «እንዴ ትዳርን በጋራ መምራት የወንዶችም የሴቶችም እኩል አላፊነት እንጂ ወንዶች ብቻቸውን ለፍተው በሚያመጡት ሴቶች ተቀምጠው በላተኛ ሊሆኑ አይገባም::» ሲል መለሰለት:: ሞኙም «አዎን

ትክክል ብለሃል፡፡ ታዲያ በምን ዘዴ ከእኛ ጋር እንዲስማሩ ማድረግ ይቻላል?» በማለት መልሶ ጠየቀው፡፡

ብልሁም «ነገሩ ቀላል ነው ሴቶቹ እምቢ ማለት ቀርቶ ያንገራገሩ እንኳ እንደሆን ያለው ምርጫ ዱላ ብቻ ነው፡፡ ወደው እስኪጠሉ ድረስ በዱላ መቀጥቀጥ ብቻ ነው፡፡ ዛሬ ማታ ወደ ቤት እንደገባን ይህንኑ እንጀምራለን፡፡» ብለው ተማከሩ፡፡ ሞኙም የተነገረውን ሁሉ በሆዱ ያዘ፡፡ ስራቸውን አጠናቀው ወደ ቤታቸው ሲሄዱ፣ በል እንግዲህ እንደ ተመካከርነው» ይሁን ተባብለው ተለያዩ፡፡

ወንዶቹ ወደቤት ሲገቡ ሚስቶቻቸው የተለመደውን አቀባበል ቢያደርጉላቸውም በተለይ ሞኙ ከወትሮ የተለየ ለውጥ በፊቱ ላይ ይታይበት ነበር፡፡ ቀጠል አድርጎ «እኔ ከውጪ በጭቃ፣ በእሾህና በዝናብ ስለፋ አንቺ ተጎልተሽ ከመቀለብ አልፈሽ ታባክኛለሽ? ስለዚህ ከነገ ጠዋት ጀምሮ ሁለታችንም ወደ እርሻ መሰማራት አለብን፡፡» ይላታል፡፡ እሷም እንዴት ሆኖ ጭራሽ አይደረግም?» ብላ አንገራገረች፡፡ ጥቂት ቆይቶ ወደ ውጭ ለዕዳሪ ሲወጣ 'ዢው'፣ 'ዢው' የሚል የዱላ ድምፅ ይሰማል፡፡ «ለካ እኔ ወደ ኋላ ዘግይቻለሁ ይልና ወዲያው እንደተመለሰ እህል ውሃ የማያሰኝ ዱላ አንስቶ ሚስቱን ሲቀጠቅጣት ድንገት ትሞትበታለች፡፡ በነጋታው የምክራቸው ውጤት ምን እንደደረሰ ሲጠያየቁ ብልሁ ሞኙን «እንዴት ነው ደበደብካት ወይ ›› ቢለው «ኧረ ይሽውልህ አኩርፋም ይሁን እንጃ ተዘርራለች፡፡» አለው፡፡ ብልሁ ግን ሚስቱ የተኛችበትን ቁርበት ቸብ፣ ቸብ፣ እያደረገ በማስፈራራት እንዳሳመናት ነገረው፡፡ ሞኙም ይህ ዘዴ ስላልመጣለት በገዛ እጁ ሚስቱን አጣ፡፡ ተረቱም «ሞኝ ሚስቱን ብልህ ቁርበቱን» እየተባለ የሚነገረው በዚህ ምክንያት ነው እየተባለ ይነገራል፡፡

**X27. ምክር የማይሰማ መከራን ያጭዳል**

አንድ ምክር የማይሰማ ሰው በአንድ አገር ውስጥ ይኖር ነበር፡፡ ይህ ሰው የጎረቤቶቹንና የወዳጆቹን ምክር ብቻ ሳይሆን የስጋ ዘመዶቹንም ጭምር አሻፈረኝ ያለ ነበር፡፡ እንዲያውም ከሰዎች ጋር ከሚሆን ይልቅ ብቻውን መሆንን ብዙ ጊዜ ይመርጣል፡፡ ታዲያ አንድ ቀን ዘመዶቹን ጨምሮ ባጠቃላይ ሰዎች የተባሉትን ሁሉ ከመጥላቱ የተነሳ አገሩን ጥሎ ወደ ማይታወቅበት አገር ተሰደደ፡፡ እዚያም እንደደረሰ ከዚህ በፊት አይቶት ከማያውቀው ፍጡር ጋር ድንገት ተገናኘ፡፡ የተገናኘው ፍጡር በጣም ደስ ብሎት «ለመሆኑ ወዴት ትሄዳለህ?» ሲል ጠየቀው ሰውዬውም «የሰውን፣ ምክር ጠልቼ የዘመዶቼን ምክር ጠልቼ፣ የጎረቤቶቼን ምክር



ADDIS ABABA ... LIB...

ጠልቼ ባጠቃላይ ሰው ከሚባል ፍጡር ጋር መኖርን ሸሽቼ እግሬ ወደ መራኝ ቦታ እየሄድኩ ነው፡፡» ሲል መለሰለት፡፡

ያም ፍጡር «ይህማ ቀላል ነው ዘመዶቹን፣ ጎረቤቶቹን፣ ባጠቃላይ ሰዎችን የጠላ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት ምክር የሚሰጡ ስላሉ ተነስ እንሂድ አገናኝሃለሁ» አለውና፡፡ ተያይዘው ሄዱ ሲሄዱ፣ ሲሄዱ ሲመሽ አንድ ትልቅ ዋሻ ወዳለበት አካባቢ ይደርሳሉ፡፡

ቀጥሎም ሰውየው ጦሩን ከውጪ አስቀምጦ ወደ ውስጥ እንዲገባ ይጋብዘዋል፡፡ እርሱም እንደተነገረው ጦሩን አስቀምጦ ወደ ዋሻው ገባ፡፡ ወዳያው ተከትሎት "ስማችሁ ወገኖቼ የዘመዶቹን፣ የጎረቤቶቹንና ባጠቃላይ የሰውን ምክር ጠልቶ ወደ እኛ የመጣ አንድ ሰው አለ፡፡ ይህ ሰው ምን ማድረግ እንደሚገባው ስለማስረዳው የልቡን የጆሮዎቹንና የዓይኖቹን ጉዳይ ለኔ ተውልኝ፡፡» አለና ወደ ኋላው ተመለሰ፡፡ ከዚያም ሰውዬው ወደ ዋሻው የውስጥ ክፍል ሲዘልቅ፣ አስቀድሞ በተነገራቸው መሰረት ዓይኑን ፣ እጅና ልቡን ብቻ አስቀርተው ከመቅፅበት ተቀራመቱት፡፡ ነገር ግን ምግብ ፍለጋ ሄዶ ሲዞር ደክሞት ወደ ዋሻ የተመለሰ ሌላ ጅብ ምንም የሚበላ ሳያገኝ ድንገት መጣ ፡፡ እነዚህ ምንድናቸው ብሎ ቢጠይቅ አንድ ሰው ወደ እኛ ሲገባ ምን ማድረግ እንዳለብን የገለፀልን የባልደረባችን ፋንታ ነው ብለው ነገሩት፡፡» የተራበው ጅብ ግን "ቃልን ማክበር ባህላችን ቢሆንም በልቼ ለፍርድ እቀርባለሁ" ሲል የተቀመጠውን አንስቶ በላ፡፡ ጥቂት ቆይቶ የመጀመሪያው ጅብ መጣና ‹‹ይቀመጥልኝ ያልኳችሁ የታለ?» ብሎ ቢጠይቃቸው፣ የተቀመጠለትን ድርሻውን የበላበት ጅብ ፈጥኖ ተነሳና «ሰውዬው ዓይንም ፣ ጆሮም ፣ ልብም ፣ የለውም» ሲል ምላሽ ሰጠ ፡፡ ከዚያ ሌሎቹም ተጨምረው ‹‹ እንዴ ምን ማለትህ ነው?›› ብለው ቢጠይቁት፣ እርሱም ቀጠል አድርጎ፣ «እያችሁ ወገኖቼ ሰውዬው ጆሮ ቢኖረው ኖሮ የዘመዶቹንና የጎረቤቶቹን ምክር በሰማ ነበር፤ ዓይን ቢኖረው ኖሮ ወደኛ ዋሻ ውስጥ ባልገባ ነበር፤ ልብ ቢኖረው ይዞት የመጣውን ጦር ውጪ አስቀምጦ ባዶ እጁን ባልገባ ነበር፡፡» ብሎ መለሰላቸው ይባላል፡፡ ምከረው ምከረው እንቢ ካለ መከራ ይምከረው የሚባለው ምሳሌያዊ አነጋገር የሚያስታውሰው ይህን መሳይ ሁኔታ ነው፡፡

## X28. የነብርና የፍየል ግልገል

በአንድ ወቅት የፍየልና የነብር ግልገሎች ጓደኝነት ለመመሥረት ፈልገው ነበር ይባላል:: ይህ ሃሳብ የመነጨው፣ በግጦሽ ሥፍራዎች ስለተገናኙ አብረው ውሃ በመጠጣት፣ ሰላምታ ከመለዋወጥ፣ የተነሳ ውሎ አድሮ ከዳበረ የርስ በርስ መተዋወቅ ሳ ነበር::

በዚህ ምክንያት ሁለቱ ግልገሎች «ከእንግዲህ እኛ አብረን ሳር እየበላን፣ አብረን ውሃ እየጠጣን፣ አብረን እየተወያየን እንኖራለን ጠላት ሲመጣብንም በጋራ እንከላከላለን::» ተባባሉ:: እነዚህ ግልገሎች በዚህ ሁኔታ ስለወደፊቱ ጓደኝነታቸው ሲመካከሩ አብረው ሲበሉ ዋሉ:: ማታ ሁሉም ወደቤታቸው ሲመለሱ እያንዳንዳቸው ለእናቶቻቸው ውሎአቸውን አስረዱ:: የነብር ግልገል «ይኸውልሽ እማዬ ዛሬ ያገኟት ጓደኛዬ እንደኔው ያለች ሆና ነገር ግን ጭራዋ ወደ ላይ የተቀለበሰ ነው:: ነገም ተነገ ወዲያ ሁልጊዜም አብረን በጓደኝነት እንደምንቀይ ተስማምተን ነው የተለያየነው ብላ ትነግራታለች:: ምንነቷን አስቀድማ ያወቀች የነብር እናት «ጥሩ ነው ልጄ ብቻ ነገ ጠዋት ስትገናኙ በደንብ ጠጋ ብለሽ አጫውቻት እኔም ቀስ ብዬ ከኋላ ከኋላችሁ ተከትዬ አያችኋለሁ ጨዋታችሁን ስትጨርሱም ወደቤታችን አምጥተን ልንጋብዛት እንችላለን::» አለቻት:: እሷም «እሺ» ብላ የሌሊቱን መንጋት ስትናፍቅ አደረች::

የፍየል ግልገልም በበኩሏ «ይኸውልሽ እናቴ ዛሬ በመስክ ያገኘሁት አዲስ ጓደኛ ገላው ልስልስ፣ ፀጉሩ ዝንጉርጉር ጭራው ወደ ታች የሆነ ደስ የሚል ነው ቀኑን ሙሉ ሲያጫውተኝ፣ አብረን ስንበላ ስንጠጣ ዋልን:: ለወደፊቱም በየቀኑ እየተገናኘን ጓደኝነታችንን እንደምናጠነክር ተስማምተናል::» አለቻት:: ምንነቱን የተረዳች እናትም «አሃ! አለችና በይ ከዛሬ ጀምረሽ ከዚህ ካልሽው ቡራቡሬ ግልገል ጋር እንዳትገናኚ እርሱ የኛን ዘር የሚበላ ጠላታችን ነው::» ስትል አስጠነቀቀቻት:: የሰጠቻትን ምክር ረስታ ትሄዳለች ብላ በዓይነ ቁራኛ ትጠብቃት ጀመር:: በቀጠሮዋ መሠረት የነብር ግልገል ቀድማ ደርሳ ብትጠብቅ የፍየል ግልገል በሩቅ ከእናቷ ጋር ሆና አየቻት «ወዲያው ጓደኛዬ ነይ! እንደተናንቱ እዚህ እንጫወት፣ እያለች ብትጠራት» «አንቺ ለእናትሽ እንደነገርሽ ሁሉ እኔም በመንገሬ ስለምንነትሽ አውቄአለሁና ከዛሬ ጀምሮ ጓደኝነታችን ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ፈርሷል::» ብላ መልስ ሰጥታ ከእናቷ ጋር መንገዷን ቀጠለች:: ‹‹የነብር ዓይን ከፍየል፣ የፍየል ዓይን ከቅጠል የሚባለው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነው ይባላል::

## X30 አንድ አንበሳና ዘጠኝ ጅቦች

ዘጠኝ ጅቦችና አንድ አንበሳ ሆነው ለአደን ወጡ:: በጫካ ውስጥ ሲዘዋወሩ አስር ላሞች ሳር ሲበሉ አገኙና እየነዱ ሲሄዱ በመንገድ ላይ እያሉ ጅቦች ለመካፈል ፈልገው ለአንበሳ ሀሳቡን አቀረቡለት:: አንበሳም «እናንተ ዘጠኝ ስለሆናችሁ አንድ ላም ስትወስዱ አስር ትሞላላችሁ::



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

እኔም ዘጠኝ ላሞች ስወስድ አንድ ላይ አስር እንሆናለን አላቸው:: ጅቦችም ‹‹ አንበሳ ምን ይበላ ተበድሮ ምን ሊከፍል ማን ጠይቆ ›› ሆነባቸውና በፍርሀት ተውጠው እንኳንስ ባዶ እጃችንን ያልወጣን ብለው እሺ አሉ::

ሁለቱም ወገኖች በዚህ ሁኔታ ተከፋፍለው ድርሻ ድርሻቸውን ይዘው ወደ ቤታቸው ሄዱ:: እቤት እንደደረሱ የጅቦቹ አባት ሁኔታውን ጠየቃቸውና የሆነውን ሁሉ አስረዱት:: በዚህ ጊዜ «እንዴት ዘጠኝ ሆናችሁ አንድ ላም ብቻ ሲሰጣችሁ ዝም ብላችሁ ተቀበላችሁ ትመጣላችሁ? ብሎ በጣም ተናደደ:: እነሱም ኸረ አባዬ ከግዙፍነቱ ሌላ ዓይኑ ራሱ የሚያስፈራ ነበር በጣም ስለፈራንና ስለሰጋን እርሱ ያለንን ተቀብለን መጥተናል::» አሉት::

እሱም አይሆንም እኔ ራሴ ሄጄ እጠይቀዋሁ::» ብሎ ተካፍለው ያመጡትን ላም እየነዳ ይዞ ሄደ:: በአካባቢው እንደደረሰም ገና በሩቅ ሲያየው እሱም ራሱ ብርክ ይዞት ተንቀጠቀጠ :: ዘሎ የሚከመርበት መሰለውና ጌታዬ ይቺ ላም የምታስፈልገው እንደርስዎ ላለ ነው ብዬ ከልጆቼ ተቀብዬ አምጥቻለሁና ይቀበሉኝ ብሎ ያቺኑ የተገቺውንም ላም አስረክቦ ባዶ እጁን ተመለሰ ይባላል::

X31 የድመት ሚዜ

ዓይጦች ሲጋቡ ድመት ሚዜ ሆኖ ነበር ይባላል:: ያገባቺው አይጥ ጥቂት ጊዜ ቆይታ ታረግዝና፣ ልጆች ወልዳ አራስ ቤት ትተኛለች:: አንድ ቀን ባልየው እህል ለመሸመት ወደ ገበያ ሄደ:: እርሱ ከቤት እንደወጣ፣ ሚዜዋ የነበረው ድመት አራሷን ሊጠይቅ መጣ:: እንደደረሰም «እንኳን ማርያም ማረችሽ» አላት «ማርያም ታኑርህ አያ ድመት» አለችው «ለመሆኑ በደህና ተገላገልሽ? ባለቤትሽ የለም እንዴ?» አለ «ደህና ነኝ አያ ድመት አሁን ወደ ገበያ ሄደ» አለችው «የወለድሻቸው ልጆችህ ለመሆኑ እንዳንቺ ቆንጆ ናቸው?» ሳቅ እያለ ጠየቃት «ምንም አይሉ እንግዲህ ደህና ናቸው አያ ድመት?» ብላ እሷም ፈገግ ብላ «እንዳታያቸው እንኳን ተኝተዋል» አለችው ወዲያውኑ መልሳ «አይ! እዚህ ድረስ መጥቼ እንዴት ሳላያቸው ልሂድ!» እያለ ብስጭት ሲል አየችና «አያ ድመት እኔን ለመጠየቅ እዚህ ድረስ መጥተህ ሳታያቸው እንዳትሄድ፣ እንካ» ብላ በእቅፉ ላይ አደረገችለት:: እርሱም እንዴት ያምራሉ፣ እንትፍ ትፍ እደጉ፣ እደጉ፣ እያለ አንድ ባንድ ውጦ ጨረሳቸው:: እናቲቷ አይጥ ድርጊቱን ስታይ በጣም ደነገጠችና ወደ እርሷ እንዳይመጣ ሮጣ ወደ ጉድጓድ ገብታ ተደበቀች:: ድመትም ወደ አንድ ጥግ አድፍጦ አፉን ሲጠራርግ ባልየው ከገበያ ተመልሶ ወደ ቤቱ ሲገባ ድመትን አላየውም ነበር::

እንደገባም ሚስቱ እየተንሰቀሰቀች ስታለቅስ አገኛት ። ምነው ምን ሆነሻል? ሁሉንም ነገር አምጥቼልሻለሁ እባክሽ ዝም በይ? እያለ ቢያባብላት ፣ እባክህ ተወኝ ያኔ እኔና አንተ ስንጋባ ሚዜያችን የነበረው ድመት ዛሬ ሲጠይቀኝ መጥቶ ልጆቼን ልያቸው ብሎኝ ስሰጠው ሁሉንም በልቶብኝ ሄደ ።» ብላ እያለቀሰች ነገረችው።

እርሱም በጣም ተናደደና ‹‹ይኼ ወራዳ አፈር ይብላ እኔ አለመኖሬን አይቶ ነው መጥቶ ልጆቼን የበላብኝ! ቆይ ግዴለም» እያለ ሲፎክር አያ ድመት ከውጭ ሚያው! ሚያው! እያለ ሲጮህ የሰማው መሰለውና ደንግጦ ወደ ሚስቱ ዞር አለና አያ ድመት ከጠየቀሽ ጠዋት እንደወጣ ነው ገበያ እንደሄደ አልተመለሰም፣ በይልኝ አደራሽን! አደራሽን! እያለ ተሽቀዳድሞ ወደ ጉድጓዱ ሮጦ ገባ ይባላል። የማያደርጉትን እንደሚያደርጉ ማስመሰል የኋላ ኋላ ትርፉ ውርደት ነው።

**X32 በግና ፍየል**

በአንድ ገበሬ ቤት የሚኖሩ አንድ በግና አንድ ፍየል ነበሩ። እነዚህ ሁለት እንስሳት ጓደኝነት መሰረቱና ከጌታቸው ቤት ወጥተው ሩቅ አገር ሄደው ለመኖር ተስማሙ። የሚሄዱበት ቦታ ከሚኖሩበት እጅግ የሚርቅ ስለነበር ሲሄዱ ውለው በጣም ደከማቸው። ሲመሽም ከአንድ ትልቅ ግራር ስር አርፈው በማንግስቱ ጉዞአቸውን ለመቀጠል በግ በቅድሚያ ሃሳቡን አቀረበች። ፍየል በበኩሏ በማደሩ ብትስማማም ከዛፍ ስር መሆኑን ግን አልወደደችም። ስለዚህ መሬት ላይ ከምንሆን ከዛፉ ላይ ወጥተን ሌሊቱን ብናሳልፍ ይሻላል ተስማሙና ሁለቱም ከዛፉ ላይ ወጡ። እኩለ ሌሊት ሲሆን ምድረ አራዊት ከያሉበት ተሰባስበው በዚያ ትልቅ ዛፍ ስር ጉባኤ ማድረግ ጀመሩ። አገር ደህና ብለው በዛፉ ላይ የነበሩት በግና ፍየል ሁኔታውን ሲመለከቱ ዋነኛ ጠላቶቻቸው የሆኑ አራዊቶች በሙሉ በዚያ ትልቅ ዛፍ ስር ተሰባስበው ምክር ሲያደርጉ ተመለከቱ። በጣም ደነገጡና በዚህ ውድቅት ምድረ አራዊት እዚህ ምን ይመካከራሉ? ከዚህ በፊት እንደዚህ ያለ ሁኔታ አይተንም ሰምተንም አናውቅም በማለት ሁለቱም ልባቸው ትር ትር ይልባቸው ጀምር። በዚህ መካከል ድንጋጤዋን መቋቋም የተሳናት ፍየል ወደ በግ እጠጋለሁ ብላ ከቦታዋ ስትንቀሳቀስ የቆመችበት ቅርንጫፍ ከዳትና ወርዳ ከአንበሳ ጀርባ ላይ እረብ ስትልበት ክፉኛ ድንጋጤ የዋጣት በግ እዚያው ላይ እንዳለች ጓደኛዋ ስትወድቅ ደመነፍሷን «ትልቅ ትልቁን ያዥ፣ ትልቅ ትልቁን ያዥ» እያለች የነፍሷን ስትለፈልፍ፣ ምድረ አራዊት ከዚህ በፊት ይህን መሰል ነገር በዚህ ቦታ አጋጥሟቸው አያውቅምና ምን መጣብን ብለው ሁሉም በየአቅጣጫው ሽሽታቸውን ቀጠሉ። ጠላቶቻቸው ከቦታው መጥፋታቸውን አረጋግጣ በግ ቀስ ብላ ወርዳ ከጓደኛዋ ጋር ሆነው በሰላም ወደ አሰቡት ሄዱ። በግና ፍየል ጥብቅ ጓደኛሞች መሆን የጀመሩት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው ይባላል ።



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## X33. አንበሳና ቆቅ

ሁለት ቆቆች የጠበቀ ጓደኝነት መስርተው በአንድ ትልቅ ድልድይ ስር አብረው ይኖሩ ነበር:: ከጊዜ በኋላ ዓመል ላመል በደንብ ሲግባቡ «ለምን አንበሳን አሞኝተን ወንዝ እዲገባና እንዲሞት አናደርገውም » ብለው በሚሥጢር ተማከሩ:: ከዕለታት አንድ ቀን አንበሳ ወደሚኖርበት ሥፍራ ተነስተው ሄዱ:: እንደደረሱም «ታላቁ ያራዊት ንጉሥ ሆይ! » በማለት ይጠሩት ጀመር:: እርሱም ምን ትፈልጋላችሁ ? ጠየቃቸው:: «አንተ አንበሳ ንጉሠ አራዊት ሁሉን የምታሸንፍ የምታስፈራ ነህ ነገር ግን በዚህ ባቅራቢያህ ባለ ወንዝ ላይ የተሰራውን ድልድይ አንተ ማቋረጥ እንደማትችልና ፈሪ እንደሆንክ ላገር ሁሉ እየተነገረ ነው:: እኛ ግን ‹‹የለም፣ ሐሰት ነው፣ አያደርገውም ነው እያልን እተከራከርን ነውና ይህንኑ ልናረጋግጥ ነው የመጣነው ለምን ሄደህ ድፍረትህንና ኃያልነትህን አታሳይም::» ሲሉ ጠየቁት::

እርሱም «እሺ መጥቼ እንደማልፈራና ማቋረጥ እንደምችል አሳያቸዋለሁ እናንተ ግን ስለነገራችሁኝ አመሰግናችኋለሁ::» ብሎ በመጀመሪያ ቀን አሰናበታቸው:: እነርሱም ሁለት ሶስት ጊዜ ደጋግመው በመምጣት ቢጎተጉቱትም «እሺ እመጣለሁ» እያለ ቀረባቸው:: በመጨረሻም ተስፋ ቆርጠው እንግዲውስ «የምናደንቅህና የምናጀግንህ በስህተት ነበር ለካ የመጨረሻው ፈሪ ነህ» ሲሉት ተናድዶ ድልድዩን ሁለት ሶስት ጊዜ ተመላልሶ ያለፍርሃት እንደሚሻገር አረጋገጠላቸው :: በአካባቢውም ከእነርሱ ሌላ ምንም ድምፅ ምንም የሚናገር ፍጡር ማግኘት ስላልቻለ ተመልሶ ወደ ሥፍራው ሄዶ ተቀመጠ:: የነርሱም እቅድ አንበሳ ተናድዶ ወደ ድልድዩ ሲመጣ ከስር ሆነው በሚጮህ ያን ለማረጋገጥ ሲመጣ ምስሉን ቁልቁል ያይና በውሃ ውስጥ ዘሎ ይገባና ይሞታል ብለን ነበር :: ነገር ግን ብልህ ስለሆነ አልተሳካልንም ብለው ተስፋ ቆረጡ :: ያጠመዱት የተንኮል ወጥመድም ሳይዝላቸው ቀረ::

## X34 «እየሰማ የሞተን እያየ ቅበረው»

በዱሮ ጊዜ አንድ ሆዱን በጣም የሚወድ ሰው ነበር ይባላል:: ዘወትር ሲበላ ውሎ ሲበላ ቢያድር ይደሰታል :: ይህን ሀሳቡን ለማሟላት ሚስቱን «አሞኛል» እያለ እቤት ይውላል:: እቤት በዋለ ቁጥርም ጥሬ እህል እየፈጨ ገንፎ እያገነፋ ይበላል:: በባሏ ታሞ አለመዳን ክፉኛ የሰጋችው ሚስቱ ምን እንደሚሻል ብትጠይቀው «እዚያ ማዶ አንድ ባህታዊ ባዶ ቤት ውስጥ አሉና ሄደሽ መድኃኒቱን ጠይቂልኝና ነይ ስትሄጂ ግን ድንጋይ ድንጋዩን እየረገጥሽ እንጂ አፈሩን እንዳትረግጪ አደራ» ይላታል:: እርሷም የባሏን መዳን ብቻ እያሰበች ድንጋይ እየፈለገች ቀስ

እያለች ስትንዝ፣ እርሱ በሌላ አቋራጭ ቀድሞ ባህታዊው ይኖሩበታል በተባለው ቤት ውስጥ ሽፍንፍን ብሎ ተኝቶ ጠበቃት።

እርሷም እንደደረሰች ባህታዊ መስሏት የመጣችበትን ጉዳይ አስረዳችና ለመሆኑ መድኃኒቱ «ምን ይሆን ጌታዬ» ብላ ጠየቀች። የተሸፈነው ሰውዬም እንዲህ ሰል ተናገረ። ለዚህ በሽተኛ በሬ ይታረድለትና ማንም ሰው ሳይጋራው ብቻውን ይብላ ሰው ከነካበት ጭራሹን ይሞታልና አሁን በመጣሽበት አኳኋን ተመቂሰሽ ሄደሽ ስሪለት» ብሎ መለሳት። አሁንም ከርሷ ቀድሞ ሄዶ ተኝቶ ጠበቃት እርሷም ባህታዊው እነደነገሯት አዘጋጅታ ሰጠችው። በአንድ ቤት ለብቻው ሆኖ የበሬውን ሥጋ ሲበላ ሰነበተና ሲሰለቸው የተለመደውን ገንፎ ማገንፋት ጀመረ። አንድ ቀን ገና ሠርቶ ሊበላ ሲል ሚስቱ ድንገት ብትደርስ ድስቱን ጋቢው ስር ቢከተው እዚያ ሆኖ መንተክተኩን ቀጠለ ። ሚስቱም ምንድነው? ብትለው ሆዴን አሞኝ ነው ሲል መለሰላት። እርሷ ሳትኖር ሁልጊዜ የወፍጮ ድምፅ እንደሚሰሙ ጎረቶቿ ለነገሯት ነገር ይበልጥ ማረጋገጫ ስለሆናት በጣም ተናደደች ። ልፋቷ ሁሉ ባሏን ከስስታምነቱ ሊያላቅቀው አልቻለም። እርሷም በንዴት ልጆቿን ሰብስባ የተረፈውን ስጋ ለርሱ ሳያቀምሱ ሙልጭ አድርገው በሉት። ውስጥ ውስጡን የተናደደው ባልም የሚታዘንለትና ሌላ የሚሰጠው መስሎት «መድኃኒቱ ተቋረጠ፣ በጣም አመመኝ፣ ሞቻለሁ፣ ነይ ገንገርኝ እያለ ወተወተ» ንደቱ ያበገናት ሚስቱ፣ ግጥም አድርጋ ትገንዘውና ወደ ቀብር ይወስዳል። ወደ መቃብሩ ሥፍራ እየተቃረቡ ሲመጡ፣ በቁርጥ እንዳልቀረለት ተረድቶ ከሳጥኑ ውስጥ መንቀሳቀስ ጀመረ። ሰዎቹም ይህን ያህል ስንደክምና ስንለፋ ዝም ያለንን እዚህ አድርሰን አንመልሰውም፣ ብለው ቀብረው አፈር አልብሰውት ተመለሱ። « ስስታም አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው» የሚባለው ምሳሌያዊ ንግግርም ይህንን የሚያመለክት ነው።

X35 ሰውና ዘንዶ

የክረምት ዝናብና ጎርፍ መኖሪያ ያሳጣው አንድ ትልቅ ዘንዶ፣ ከመንደሩ ነዋሪዎች መካከል ወደ አንድ ሰው ዘንድ ጠጋ አለና «እባክህ ይህን ክረምት እስከምወጣ ድረስ አስጠጋኝ» ብሎ ይጠይቀዋል። ሰውዬውም እንዴት ሊሆን ይችላል እያለ ሲያቅማማ ተመልክቶ እምቢ ይለኛል ብሎ ሰግቶ ደጋግሞ ተማጸነው። ሰውዬም ከተቸገርክ ምን አደርጋለሁ ብሎ ፈቀደለትና አብረው ክረምቱን አሳለፉ።



ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

ክረምቱ ካለፈ በኋላ ዘንዶ ወደነበረበት ቦታ ተመልሶ መኖር ጀመረ። አንድ ቀን ሰውዬው ለጉዳዩ በዚያ አካባቢ ሲያልፍ ያ ዘንዶ ያገኘውና ካልበላሁህ ይለዋል። እሱም ደንግጦ «እንደዚያ በቸገረህ ጊዜ ውለታ የዋኩልህን ረስተኸው ነው እበላሃለሁ የምትለኝ እባክህ ያለፈውን ጊዜ አስታውስ ቢሎ ቢለምነው አሻፈረኝ አለ፡ እረ ባክህ ተወኝ ብሎ አጥብቆ ቢማፀነው «በል እንግዲህ እኔ የምበላህ ሚስትህ፣ በሬህ ልጅህ ከፈረዱብህ ብቻ ነው» አለውና ተያይዘው ወደ ቤት ይሄዳሉ። ሰውዬውም ቀደም ብሎ ይገባና «ያ ክረምቱን እኛ ቤት ያሳለፈው ዘንዶ ካልበላሁህ ብሎ ዛሬ በስንት ልመና ሚስትህ፣ ልጅህ ፣ በሬህ ፣ ከፈረዱብህ እበላሃለሁ ብሎኛልና ምን ትሉኛላችሁ » ብሎ አንድ ባንድ ጠየቃቸው።

ከዚያም ሚስት፣ «ስትወጣ ስትገባ የምትጨቀጭቀኝ ስለሆንክ ይብላህ» ብዬ እፈርድብሀላሁ አለችው። ልጁንም ሲጠይቀው « አንተ ሁልጊዜ ስለምትደበድበኝ፣ ይብላህ» ብዬ እፈርድብሃለሁ። አለው። በሬውንም ቢጠይቀው « ሁልጊዜ በጅራፍ ስትገርፈኝና ከተቀለለው ገለባ እንዳልበላ ስለምትከለክለኝ እኔም ይብላህ ብዬ እፈርድብሀለሁ » አለው። ሰውዬው በቤተሰቦቹና በበሬው ተስፋ ቆርጦ ወደ ዘንዶው ተመልሰና ምስክሮቹን እስከሚያሰማ ድረስ በድኑ ብቻ እየተንቀጠቀጠ ቁጭ አለ። ከዚያም የመጀመሪያ ምስክር ሆና የቀረበችው ሚስትዬው ነበረች። እርሷም እንደተጠራች በቅድሚያ ሄዳ ለዘንዶው «ጌታዬ እርሶስ እንዲህ ብለዋል ሰውዬውን ግን እዚያ እቤት ውስጥ ያለ ሌላ ሀይለኛ ዘንዶ ካልበላሁህ ብሎታልና ሰውዬው የእርስዎ ብቻ እንዲሆን ምን ማድረግ ይሻላል?» አለችው ከወዲሁም አንድ መላ መፈጠር አለበት ስትልም አጥብቃ ጠየቀችው። ዘንዶውም « እንግዲያውስ ሰውዬው የኔ ብቻ እንዲሆን ከመስከርሽ ለዚያኛው ዘንዶ መግደያ መድሀኒት እሰጥሻለሁ» አላት። «እንዴት ነው የማደርገው ?» ብላ ስትጠይቀው እሱም «ይኸውልሽ ይህንን ሶስት ጊዜ በራሱ ላይ አዙረሽ ወደ መሬት ስትጥይው ወዲያውኑ ይሞታል።» ብሎ ሰጣት። እሷም እሺ ብላ ተቀበለችና« እንዲህ ነው የማደርገው?» እያለች በእሱው ላይ እያዞረች ስታሳየው «ተይ ከእጅሽ ድንገት አምልጦ መሬት እንዳይወድቅ» እያለ ሲያስጠነቅቃት ፍርሃቱን አወቀችበትና ያንን መድኃኒት በራሱ ላይ አዞረችና መሬት ስትጥለው ያ ሰወዬውን ለመብላት አሰፍስፎ የነበረ ዘንዶ፣ ወዲያውኑ እዚያው እፊታቸው ድብን አለ። ሴትዬዋም በዚህ ዘዴ የባሏን ህይወት አተረፈችና በሰላም አብረው ኖሩ ይባላል። ተረኩ «ዶሮ ጭራ ጭራ አወጣች ማረጃዋን ካራ» የሚባለውን ምሳሌያዊ ንግግር የሚያስታውስ ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY



"በጌዴኦ ህብረተሰብ ማህበረ-ባህላዊ ህይወት ውስጥ ገዳ የማይገባበትና የማይዳስሰው አንድም ሥፍራ የለም ፡፡ በደርግ ታግዶ የነበረው የገዳ እንቅስቃሴ ከ1994 ዓ.ም.ጀምሮ እንደገና እንዲያንሰራራ የበኩሌን ጥረት አድርጌአለሁ ተሳክቷልም፡፡"

አቶ ጥላሁን ኢቢዶ በጌዴኦ ዞን ት/መምሪያ የሲቢክ ጉዳዮች ኤክስፐርት ዲላ 18/12/98 ዓ.ም.




"ተረትን የድሮ ሰዎች እንደ ዕውቀት አድርገው ይወስዱታል ፡፡ያኔ መፅሐፍ የለም ባንደበታቸው ብቻ ይኼ ነገር የመጣው ከዚህ ነው...፡፡ ያ ደግሞ የተፈጠረው እንደዚህ ነው... እያሉ" ጨዋታ አዋቂዎች የሚያቀርቡት ነው፡፡

ዎቻማ ቀበሌ ገ/ማህበር ከተረት አዋቂዎች ጋር (ጌዴኦ ዞን)

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

በኢት/ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል የሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

በሥነ-ቃል ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ

ማሳሰቢያ፡- ከዚህ በታች የሚገኙትን ጥያቄዎች በተገቢው መንገድ ምላሽ በመስጠት ስለተባበሩኝ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

**ክፍል አንድ፡ ክዋኔና መቼት**

1. ዱሮ በልጅነትዎ ተረት ተተርቶሎታል? የሚተርትሎት ምን ነበር?

2. ተራቹ ተረቱን ከየት አገኙት? ከማን ሰሙት?

3. ምን ምን ጊዜ ነበር የሚተረተው ቀን ፡ማታ ፡በጨረቃ... ወዘተ?

4. ስፍራውስ የት ነው?

5. ተረት ከመጀመሩ አስቀድሞ የሚደረግ ሥርዓት አለ?

6. ካለ ምን ምን ይደረጋል? ከሌለ ምክንያቱ ምንድ ነው?

7. ተረት እንዴት ተብሎ ነው የሚጀመረው?

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

8. የተረቱ አቅራቢ ምን የተለየ ልብስ ይለብሳል?

9. ታዳሚዎች /አድማጭ/ ምን ያደርጋሉ? /በምን በምን ይሳተፋሉ/?

10. ተራች ተረቱን የሚያቀርበው በእንዴት ያለ ሁኔታ ነው? በአካላዊ እንቅስቃሴዎች /እጅ በማወናጨፍ፣ ዓይን ማጉረጥረጥ፣ ድምጽ መለዋወጥ፣ ዝምታ፣ ወይስ ሌላ/ (ካለ ይገለጽ)

11. ተረቱ በሚነገርበት ወቅት ሥርዓቱ ምን ይመስላል? /መጠጥ፣ ቆሎ፣ ዳቦ፣ ንፍሮ፣ ዕጣን፣ ጉዝጓዝ ወይም ከተጠቀሱት ሌላ ከሆነ ይገለጽ)

12. ተረቱ ምን ተብሎ ይቋጫል? ታዳሚዎችስ ምን ይላሉ?

13. ተረት በመተረት ሥርዓት ላይ ቦታ ያለው ማነ ምንድነው? ዕድሜስ?

## ክፍል ሁለት፡ አገልግሎት

14. ለእርስዎ ተረት የሚነገርዎት ምን ሊያደርግሎት ወይም ምን እንዲሆኑ ነበር?

15. ተረት ለምን ያገለግላል? ወይም ለምን ይጠቅማል ይባላል?

16. በዛሬ ዘመን ተረቶችን የሚተርቱ ወላጆች /ሰዎች/ አሉ? ካሉ እነማን እንደሆኑ ይዘርዝር

17. እርስዎ የሚያውቋቸው ተራቾች ከሌሉ ምክንያቱ ምንድነው ነው ብለው ያስባሉ?

18. ተረቶች ቢተረቱ ለምን ይጠቅማሉ?

19. ባይተረቱስ ምን ያጎድላሉ፧ ብለው ይገምታሉ?

20. ቀደም ሲል ተረቶች በህብረተ-ሰቡ ውስጥ ምን ቦታ ነበራቸው?

21. ተረቶች በህብረተ-ሰቡ ውስጥ ምን ሚና ነበራቸው?

22. በእርስዎ አመለካከት ተረቶች በምን ደረጃና በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?


23. በዚህ መጠይቅ ውስጥ ያልተካተቱ ነገር ግን ለጥናቱ ጠቃሚ ናቸው የሚሏቸው አስተያየቶች ካሉ ይግለፁ?

24. ከሰሟቸው /ከሚያውቋቸው/ ተረቶች መካከል ምንም ሳይጨምሩ ወይም ሳይቀንሱ አንድ ወይም ሁለት ጽፈው ከመጠይቁ ጋር ያያይዙ።

አመሰግናለሁ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# GEDEO ZONE ADMINISTRATIVE MAP




CAUTION: The delination of the bounderies on thise map are not authoritative

K E Y

REGIONAL BOUNDARY
ZONE BOUNDARY
WOREDA BOUNDARY
ZONE CAPITAL
WOREDA CAPITAL
OTHER TOWNS

.E 1:400000
APRIL1998

ILS LIBRARY